በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

በደቡብ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛ እና 8ኛ) ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት

በ

ዳዊት ፍሬሕይወት

ሰኔ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በደቡብ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛ እና 8ኛ) ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት


*በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ*

*ድጎረ ምረቃ መርሐ ግብር*

*የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል*


አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ
በከፊል ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት


በ

ዳዊት ፍሬሕይወት



ሰኔ 2000 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

በደቡብ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛ እና 8ኛ) ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት

በ

ዳዊት ፍሬሕይወት

በቋንቋ ጥናት ተቋም

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል

የፈተና ቦርድ አባላት

አማካሪ

የውስጥ ፈታኝ

የውጭ ፈታኝ

ፊርማ

ፊርማ

ፊርማ

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የአሠራር አቅጣጫን በማመላከት፣ የጥናቱን ረቂቅ በማረም ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠትና በማበረታታት ጥናቴን የአሁኑን ቅርጽ እንዲይዝ ለረዱኝና በተጨማሪም የዕረፍት ጊዜያቸውን ጭምር መስዋዕት በማድረግ፣ በዚህ ወቅት አይደርስ የነበረውን ሥራዬን ለፍፃሜ እንዲደርስ ከፍተኛ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶክተር አረጋ ኃይለሚካኤል ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለጥናቱን ማካሄጃ የገንዘብ ድጋፍ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለጥናቱ ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ በደቡብ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልሎች ውስጥ ለሚገኙ የትምህርት ቢሮ የስራ ኃላፊዎችን እና የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ትምህርት ቤቶች ርዕሳነ-መምህራን እንዲሁም ጊዜያቸውን ሰውተው በቃለመጠይቁና በጽሑፋዊ መጠይቁ መረጃ በመስጠት የተባበሩኝ መምህራን በሙሉ ምስጋናዬ ወደር የለውም።

ትምህርቴን ጀምሬ እስካጠናቅቅ ድረስ ትዕግስታችሁ ያልራቀኝና የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ በማድረግ ዘወትር ከአጠገቤ ያልተለያችሁኝ ወላጆቼን መቶአለቃ ፍሬሕይወት አዲሱን እና ወ/ሮ ሻሼ መንግስቱን ሳላመሰግን አላልፍም።

የጥናቱን ረቂቅ ያለመሰልቸት በኮምፒውተር በመጻፍ ከፍተኛ ድጋፍ ላደረጉልኝ ወ/ት ትዕግስት በየነ እና ወ/ት ተናኜ ገብረእግዚአብሔር ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ።

# ማውጫ


አርዕስት ገጽ

ምስጋና ..... I

የሠንጠረገሮች ማውጫ ..... II

የአባሪዎች ማውጫ ..... III

አህፅሮተ ጥናት ..... IV

**ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ**

1.1 የጥናቱ ዳራ ..... 1

1.2 የጥናቱ ዓላማ ..... 4

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 5

1.4 የጥናቱ ወሰን ..... 6

1.5 የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት መፍቻ ..... 6

**ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት**

2.1. የሥነጽሑፍ ምንነት ..... 8

2.2. ሥነጽሑፍ እና ቋንቋን ማስተማር ..... 11

2.2.1. ሥነጽሑፍን እንደ አንድ የትምህርት ወይም የሙያ ዘርፍ ማጥናት 11

2.2.2. ሥነጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር መሣሪያነት መጠቀም---------- 12

2.2.3. በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር ያሉት ፋይዳዎች ..... 13

2.2.3.1. የቋንቋ ኪሂሎችን ለማዳበር ..... 13

2.2.3.2. የቋንቋ ትምህርቱን ማራኪና ተወዳጅ ለማድረግ ..... 16

2.2.3.3. ሥነልሳናዊ እና ሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን ለማጎልበት..... 17

2.2.3.4. ባህልን ለመማር (ለማወቅ)..... 19

2.3 ቋንቋን ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ..... 21

2.3.1 የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ የሚያሳኩ ..... 22

2.3.2 ከመርሐትምህርቱ ትልም ጋር የሚጣጣሙ ..... 24

2.3.3 ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ተገቢነት ያላቸው ..... 24

2.3.4 የተማሪዎቹን ሥነልሳናዊ ተክህኖ ዳራ ያገናዘቡ..... 26

2.3.5 የተማሪዎቹን የሥነጽሑፍ ዳራዊ ዕውቀት ያገናዘቡ..... 29

2.3.6 የተማሪዎቹን ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ዳራ ያገናዘቡ..... 31

2.3.7 የሥነጽሑፋዊ ሥራውን ርዝማኔ መመጠን..... 33

2.3.8 የሥነጽሑፋዊ ሥራው ተተግባሪነት..... 34

2.3.9 የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተገቢነት መፈተሻ ስልት ..... 36

2.4 ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ..... 36
2.4.1 የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በፋይዳቸው ሚዛን ደራኒት ማደራጀት .....37
2.4.2 የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራወችን ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ ማደራጀት ..... 38
2.4.3 የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ከተከታትይነትና ተለጣጣቂነት መርሆዎች አንፃር ማደራጀት ..... 39
2.4.4 የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው ማደራጀት ..... 39
2.5 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ..... 40
ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ዘዴና መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች
3.1 የአጠናን ዘዴ ..... 44
3.2 የተጠኚዎች አመራረጥ ..... 44
3.2.1 የተጠኚ የክፍል ደረጃዎች አመራረጥ ..... 44
3.2.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ..... 45
3.2.3 የመምህራን ናሙና አመራረጥ ..... 46
3.3 የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች..... 46
3.3.1 የሠነድ ምርመራ..... 47
3.3.2 በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ..... 47
3.3.3 ለመማሪያ መጻሕፍቱ አዘጋጆችና አርታኢ የቀረበ ቃለመጠይቅ ..... 48
3.4 የመረጃ አተናተን ዘዴዎች ..... 48
ምዕራፍ አራት፡- የመረጃ ውጤት ትንተና
4.1 ከሰነድ ምርመራ የተገኙ ውጤቶች ትንተና ..... 50
4.1.1 የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ..... 50
4.1.1.1 የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ከማሳካት አንፃር..... 51
4.1.1.2 የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከመርሐትምህርቱ ትልም ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ ..... 60
4.1.1.3 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ያላቸው ተገቢነት..... 65
4.1.1.4 ከተማሪዎቹ ሥነልሳናዊ ተክህኖ ዳራአንፃር..... 70
4.1.1.5 የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት

ከተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዳራ አንፃር ..... -77
4.1.1.6 በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዳራ አንፃር ..... 80
4.1.1.7 በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከርዝማኔ ምጠና አንፃር ..... 82
4.1.1.8 በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተተግባሪነት..... 84
4.1.2 በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ..... 85
4.1.2.1 የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከፋይዳቸው ሚዛን ደፊነት አንፃር .....86
4.1.2.2 የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከክብደት-ቅለታቸው አንፃር .....88
4.1.2.3 ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ሁኔታ .....-91
4.1.2.4 በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው የመደራጀታቸው ሁኔታ.....104
4.2 ለመምህራን ከቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ እና ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና ----------108
ምዕራፍ አምስት፡- ማጠቃለያ እና የመፍትሔ ሐሳቦች
5.1 ማጠቃለያ ----------142
5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች----------144
ዋቢ ጽሑፎች ----------147
አባሪዎች ----------152

# የሠንጠረዥ ማውጫ


ሠንጠረዥ 1፡- በሦስቱ ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍሎች በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ዳራዊ መግለጫ .....--50

ሠንጠረዥ 2፡- የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉ መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ .....--109

ሠንጠረዥ 3፡- የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ ፅድሜ፣ ዝንባሌ፣ ፍላጎትና ግንዛቤ አንፃር ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ፣ .....--111

ሠንጠረዥ 4፡- የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዳራ አንፃር ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ .....--114

ሠንጠረዥ 5፡- የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ አጠቃላይ ዳራ አንፃር ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ .....--118

ሠንጠረዥ 6፡- የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ሂደት የትምህርቱን ዓላማ ከማሳካትና ከመርሐትምህርቱ ጋር ከመጣጣም አንፃር ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 121

ሠንጠረዥ 7፡- የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተተግባሪነታቸው አንፃር ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 124

ሠንጠረዥ 8፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነት በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 127

ሠንጠረዥ 9፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተሰጣጣቂነት በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 129

ሠንጠረዥ 10፡- የሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎቹ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ክሂሎችን ማጎልበት በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 132

ሠንጠረዥ 11፡- ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ማጎልበት በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 134

ሠንጠረዥ 12፡- ሥነልሳንን ማስተማር በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 137

ሠንጠረዥ 13፡- ሥነጽሑፍን ማስተማር በተመለከተ ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ..... 139

# የአባሪዎች ማውጫ


አባሪ 1፡- ለመምህራን የቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ ..... 152

አባሪ 2፡- ለመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችና ለአርታኢ የቀረበ ቃለመጠይቅ ..... 161

አባሪ 3፡- በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ናሙና ..... 162

3 (ሀ)፡- ከደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ጋር የተካሄደ ቃለምልልስ..... 162

3 (ለ)፡- ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ጋር የተካሄደ ቃለምልልስ ..... 166

3 (ሐ)፡- ከደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አርታኢ ጋር የተካሄደ ቃለምልልስ..... 172

አባሪ 4፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ናሙና. -177

4 (ሀ)፡- ከጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ የተወሰዱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ናሙና..... 177

4 (ለ)፡- ከጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ላይ የተወሰዱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ናሙና..... 198

4 (ሐ)፡- ከደቡብ እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ላይ የተወሰዱ ናሙናዎች ..... 208

4 (መ)፡- ከደቡብ እና ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ላይ የተወሰዱ ናሙናዎች ..... 220

# አህፅሮተ ጥናት


የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛ እና 8ኛ) ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አመራረጥና አደረጃጀት በመመርመር ጠንካራና ደካማ ጐናቸውን መለየትና የመፍትሔ ሐሳቦች መጠቆም ነው። ይህን ጥናት ለማካሄድም መረጃዎች በሶስት መንገዶች ተሰብስበዋል። ዋነኛው የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልት የሰነድ ምርመራ ሲሆን በአጋዥነት ደግሞ በጽሑፋዊ መጠይቅና በቃለመጠይቅ መረጃዎች ለማሰባሰብ ተችሏል። በነዚህ መሣሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ለመተንተን ገላጭ የትንተና ዘዴ በዋነኛነት ስራ ላይ ውሏል።

ይህን ጥናት ለማካሄድ አጥኚው ያነሳሱት፣ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መሣሪያነት ቋንቋን ማስተማር (መማር) በተለይ ለኢአፈ-ፈት ተማሪዎች ከሚኖረው ከፍተኛ ጠቀሜታ አንፃር በነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ሶስት ክልሎች (ለኢአፈ-ፈት ተማሪዎች) በሚዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ምን ያህል ትኩረት ተሰጥቷቸዋል? በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችስ በቋንቋ ምሁራን የተጠቆሙ የአመራረጥና የአደረጃጀት መርሆዎችን የተከተሉ ናቸውን? የሚሉት ዓበይት ጥያቄዎች ናቸው። እነዚህን መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስም ከፍ ሲል የተዘረዘሩትን የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያዎች በመጠቀም በተካሄደው ፍተሻ የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል፤

ለጋምቤላ ክልል ለ7ኛ ክፍል ከተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ በስተቀር በጋምቤላ ክልል 8ኛ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ እና 8ኛ እንዲሁም በደቡብ ክልል 7ኛ እና 8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተሰጠው ሽፋን እጅግ አነስተኛ መሆኑን በጥናቱ ተደርሶበታል፤ በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል መጽሐፍ ውስጥ 57% ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ትኩረት ሲሰጥ በቀሪዎቹ መጻሕፍት ውስጥ ግን ከ13.8% እስከ 40% ሽፋን ተሰጥቷቸዋል። ባጠቃላይም ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ በአማካይ 34% ትኩረት ሲሰጥ በአንፃሩ ሥነጽሑፋዊ ላልሆኑት ሥራዎች 66% ትኩረት መሠጠቱን በጥናቱ ውጤት ለማረጋገጥ ተችሏል።

የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አመራረጥ ተገቢነት በተመለከተም አንዳንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ከማሳካትና ከመርሐትምህርቱ ጋር ከመጣጣም አንፃር ተገቢነት ያላቸው ሆነው ቢገኙም በአብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ሂደት ላይ ግን ችግሮች ተስተውለዋል። ከነዚህም የአመራረጥ ችግሮች ውስጥ፣ በመርሐትምህርቱ ላይ የተተለመውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ አለማሳካት፤ ከመርሐትምህርቱ ትልም ጋር አለመጣጣም፣ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የርዝማኔ ምጠና ችግር፣ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸውን ጉዳዮች ማካተትና፣ የተማሪዎቹን ዕድሜ (የአዕምሮ ብስለት) ያላገናዘቡ ርዕሰጉዳዮችን ማቅረብ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አደረጃጀት ሂደት በተመለከተም፣ ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ በሚጓዝ መልኩ አለመደራጀታቸውንና በፋይዳቸው ሚዛን ደራኒት የማደራጀቱ ሂደትም ተግባራዊ አለመደረጉን ለመገንዘብ ተችሏል። በሌለ በኩል ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አደረጃጀት የተከታታይነትና ተለጣጣቂነት መርሆዎችን እንዲከተሉ ከመሆኑም በላይ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር አሰባጥሮ የማደራጀቱ ስልት አለመተግበሩ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል።

በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥር የተደራጁት በክሂል እና በእውቀት ዘርፎች ላይ የተመሠረቱት ልዩ ልዩ መልመጃዎችም ሚዛናዊነትን ጠብቀው ያልቀረቡ ሲሆን፣ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ በተደጋጋሚ የዋሉት አንብቦ መረዳትን ለመተግበር እና ለቃላት ትምህርት ብቻ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ከሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አደረጃጀት ጋር በተያያዘም አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በሥራቸው ለሚገኙት መልመጃዎች በምንጭነት (በሞዴልነት) እንዳላገለገሉ በተካሄደው ጥናት ለማረጋገጥ ተችሏል።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ችግሮች ሊከሰቱ የቻሉትም የመርሐትምህርቱ አዘገጃጀት ባሕሪ፣ የመማሪያ መጻሕፍቱ አዘጋጆች የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀትን በተመለተ ያላቸው የግንዛቤ ማነስ፣ ለመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ሂደት አስፈላጊ ግብአቶች አለመሟላት እና የዝግጅት ሂደቱ እጅግ በጣም አጭር (አንድ ወር) በሆነ የግዜ ገደብ ውስጥ እንዲከናወን በመደረጉ መሆኑ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል።

በመጨረሻም በጥናቱ ውጤት በተስተዋሉት ፈርጀ-ብዙ ችግሮች መነሻነት የዚህ ጥናት አቅራቢ የመፍትሔ ሐሳቦችን ሰንዝሯል። ከነዚህ የመፍትሔ ሐሳቦች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ፤

- በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መሣሪያነት ቋንቋን የማስተማሩ ተግባር በተለይ ለኢአፈ-ፊት ተማሪዎች የሚኖራቸውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ልዩ ትኩረት በመስጠት በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲካተቱ ቢደግ፤
- ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት በተቻለ መጠን አብዛኞቹ የቋንቋ ምሁራን የተስማሙባቸው የአመራረጥና የአደረጃጀት መርሆዎች (መስፈርቶች) ተለይተው ተገቢው ትኩረት እንዲሰጣቸው ጥረት ቢደረግ እና፤
- በመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጅነት፣ አርታኢነት ወይም አሻሻይነት የሚመደቡ (የሚመረጡ) ባለሙያዎች በመምህርነት ሙያ ላይ ለረዥም ዓመታት ያገለገሉ፣ በመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ወይም አርትኦት ላይ ስልጠና የወሰዱ እንዲሁም መጻሕፍቱ የሚዘጋጅላቸውን ተማሪዎች የሚገኙበትን አካባቢ ማኅበረሰብ ባሕል፣ ሃይማኖት፣ የአኗኗር ዘይቤና መልክዓምድራዊ አቀማመጥ ጠንቅቀው የተረዱ መሆናቸው ቢረጋገጥ የሚሉት ይገኙበታል።

# መግቢያ

## ምዕራፍ አንድ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

በሥነጽሑፍ ቋንቋን የማስተማር ተግባር እ.ኤ.አ. በ1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ልዩ ትኩረት አልተሰጠውም ነበር። በዚህ ምክንያት ሥነጽሑፍ ሁለተኛ ቋንቋን ወይም የውጭ ቋንቋን ለማስተማር ባለው ጠቀሜታ ዙሪያ የሚካሄዱት ውይይቶች በጣም አናሳ ነበሩ። በ1980ዎቹ ውስጥ ግን ሁኔታዎች ሁሉ ተለዋውጠው ሥነጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ሙያ ውስጥ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት ዳግም ትንሣኤ አግኝቷል። ከዚህም ባሻገር በተለያዩ ርዕሶች፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ መጻሕፍት፣ አውደጥናቶች ላይ እና በሥርዓተትምህርት ክለሳ (curricular reviews) ላይ የመነጋገሪያ ጉዳይ ለመሆን በቃ። የነዚህ ጽሑፎች መውጣት ሠፊ ክርክሮችና ውይይቶች እንዲካሄዱ በር ከፍቷል (Cartet and Michael 1999፣ 1)።

ሥነጽሑፍ የቋንቋ አጠቃቀም ዕውቀትን ለማዳበር ይረዳል። ቋንቋ በመማር-ማስተማር ተግባር ላይም የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ያነቃቃል። አንድ መምህር መልመጃዎችን ከአንድ ሥነጽሑፋዊ ምንባብ ላይ ተመስርቶ በሚያዘጋጅበት ጊዜ ሥነልሳናዊ ክሂል ተኮር የሆኑ መልመጃዎችን ሊያካትትበት ይችላል። በጽሑፉ ውስጥ ከሚገኙት ገፀባሕርያት፣ መቼቶች፣ ጭብጦች፣ ወዘተ. በመነሳት የገላጭ፣ የትረካና የሌሎች የድርሰት ዓይነት መልመጃዎችን ሊያዘጋጅም ይችላል። በዚህ ምክንያት ነው ሥነጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር ጠቃሚ መሳሪያ ነው የሚባለው (Hill 1986፣ 7)። ከዚህም በተጨማሪ ፈቃደ (1995፣ 112) የሚከተለውን ብለዋል፤

> *ሰነጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር ይጠቅማል የምንለው የቃላትን፣ የሐረጎችን እና የዐረፍተ ነገሮችን አሰካክ እና ባሕርያቸውን ለማሳወቅ ስለሚጠቅም ብቻ አይደለም። አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ የሥነጽሑፍ ጥናትና ትችት ማኅበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ፖለቲካዊና ምጣባራዊ ዳራን እና ዐውድንም እያስገባ መተንተን ስላለበት እና ተማሪው ከነዚህ የዕውቀት መስኮች በኢርቱዕ መንገድ የሚያገኘው ትምህርት ስላለም ነው።*

ከላይ ከቀረበው ገለጻ የምንረዳው በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች በተለይ የሰዋሰው ሕግጋትን ጠንቅቀው እንዲገነዘቡ ለማስቻል እና በሚካሄዱት ውይይቶችና ክርክሮችም እግረ መንገዳቸውን የንግግር ክሂልን ማጐልበት መቻላቸውን-

ነው። ስለዚህም እንደ በድሉ (1996፣ 6-7) ገለጻ፣ «የሥነጽሑፍ ትምህርት በሥርዓተትምህርት ውስጥ መካተት ተማሪዎች በከፍተኛ ደረጃ የማንበብን፣ በመካከለኛ ደረጃ ደግሞ የማዳመጥን፣ የመናገርንና የመጻፍን ክሂሎች እንዲያዳብሩ ያግዛል»።

ይሁን እንጂ የሥነጽሑፍ ሥራዎች ሁሉ ቋንቋን ለማስተማር አመቺ ናቸው ማለት አይደለም። ካሉት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት አመቺ የሆኑትን ብቻ በጥንቃቄ መርጦና አደራጅቶ ማቅረብ ይገባል። ተማሪዎች በሥነጽሑፍ አማካይነት የቀረበውን የቋንቋ አጠቃቀም በመከተል የሥነልሳንና የክሂል ችሎታቸውን ማጎልበት ይችላሉ። ዘይቤአዊ አገላለጾችን፣ ውይይቶችን፣ ክርክሮችን፣ ሐተታዎችን፣ ወዘተ. እንዴት መጠቀምና ማቅረብ እንደሚቻል የተሻለ ግንዛቤ ያገኛሉ (Collie and Slater 1987፣ 3-4)።

በአንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ አማካይነት ሊተላለፍ የሚፈለግ መልእክትና በኢልቦለድ ጽሁፍ አማካይነት የሚቀርብ መልዕክት ለቋንቋ ማስተማሪያነት እኩል አያገለግሉም። በአንፃራዊነት ሲታይ በሥነጽሑፋዊ ሥራ ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት እንደ ኢልቦለዳዊ ጽሑፍ ቀጥተኛ ባለመሆኑ ምክንያት ተማሪዎች እና መምህራን መልዕክቱን (ጭብጡን) ለማግኘት በአንድምታ ብዙ ውይይት፣ ክርክር፣ ጥያቄና መልስ እንዲሁም ሂስ እንዲያቀርቡ ይጋብዛል። ይህንን የሥነጽሑፋዊ ሥራ ባሕርይ በውል በመገንዘብ ቋንቋ ለማስተማር ልንገለገልበት እንችላለን (ፈቃደ 1991፡112)። ስለዚህም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በቋንቋ መማር-ማስተማር ተግባር ላይ ማዋል ተማሪዎቹን በታላሚው ቋንቋ ብቁ ተናጋሪዎች ለማድረግ የላቀ አስተዋጽኦ አላቸው።

Carter እና Mcre (1996፣24) እንደገለጹት፣ አንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ስንመርጥ በዋናነት መታወቅ ያለበት ጽሑፉን በመጠቀም ተማሪዎችን ምን ማስተማር እንዳለብን ነው። ለትምህርቱ ያለው ጠቀሜታ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ጽሑፉን ስለወደድነው ብቻ ወደ መማሪያ ክፍል የምናመጣበት ጉዳይ አይኖርም። ስለዚህ ከተመረጠው ሥነጽሑፍ ተማሪዎች ምን ይማራሉ? የሚለውን መሠረታዊ ጥያቄ ማንሳት አስፈላጊ ነው። ይህንን በተመለከተ ወንድወሰን (1995፣ 25-26) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፣

> *ሥነጽሑፍ የተማሪዎችን ትኩረት የመሰብሰብ፣ ስሜታቸውን የመሳብና ለትምህርት የማነሳሳት አቅም አለው። . . . ሥነጽሑፍ ተማሪውን በማዋዛት በፍላጎት ወደ ትምህርቱ ገበታ ያቀርበዋል። ተፈላጊውን የባሕሪ ለውጥ ማምጣት የሚቻለው ደግሞ በመሉ ፍላጎት ወደገበታው የቀረበ ሰው (ተማሪ) ላይ ነው። በተግባራዊ ፍላጐት የተወጠነ ማንኛውም ሰብአዊ እንቅስቃሴ ገና ሲጀመር በግማሽ እንደተፈጸመ ይቆጠራል የሚባለውም ለዚህ ነው።*

የሚመረጡት ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ለክፍል ደረጃው የሚመጥኑ መሆን አለባቸው። የተማሪዎቹን ዕድሜ፣ የአእምሮ ብስለት፣ ዝንባሌና ፍላጎት ባጠቃላይ በደረጃው የሚጠበቀውን የቋንቋ ችሎታ ታሳቢ ያደረገና ሁሉንም ተማሪዎች ሊያሰሩ የሚችሉ ውህድ አሀዶችን ለመምረጥ ጥረት ማድረግ ይገባል (ወንድወሰን 1995፣ 52)።

በከፍተኛ ጥንቃቄ የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራችዎን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መጠቀም አያሌ ፋይዳች አሉት። ከዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የመማር ፍላጎት ያነሳሳሉ፤ አእምሮን በማስላት መልእክት በቀላሉ እንዲሰርጽ ያግዛሉ። ቋንቋ የመማር ፍላጎትን በመቀስቀስ ትምህርቱ ውስጣዊ እንዲሆን ይረዳሉ፤ የተግባቦት አቅምን ይገነባሉ፤ የአስተሳሰብ አድማስን ያሰፋሉ፤ እንዲሁም ተንትኖ የመረዳት አቅምን ያጎለብታሉ (Collee and Slater 1987፣ 6)።

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የተለያዩ ምሁራን አመለካከቶች የምንገነዘበው በጥንቃቄ የተመረጠ ሥነጹሑፋዊ ሥራን በቋንቋ መማር-ማስተማር ተግባር ላይ መገልገል ለአፈ-ፈትም ሆነ ለኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ሊሰጥ እንደሚችል ነው። ነገር ግን ከሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ባሻገር የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አደረጃጀትም የላቀ ትኩረት ይሻል።

በመጨረሻም ሥነጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ያለውን ፋይዳ አስመልክተው ወንድወሰን (1995፣ 25-32) በዝርዝር ከጠቀሱት ውስጥ የሚከተሉትን አንኳር ነጥቦች በማጠቃለያነት እንመልከት፤

1. *ሥነጽሑፍ የተማሪዎችን ትኩረት የመሰብሰብ ሰሜታቸውን የመሳብና ለትምህርት የማነሳሳት አቅም አለው።*
2. *ሥነጽሑፍ የቋንቋን ልዩ ልዩ ክሂሎች ለማዳበርና የሥነልሳን እንዲሁም የሥነጽሑፍ ዕውቀትን ለማሰጨበጥ የሚያስችል እምቅ ይዘት አለው።*
3. *ሁለተኛ ቋንቋን የመማር ተግባር በመሠረታዊ ባሕሪው የተናጋሪውን ማኅበረሰብ ባህል ማጥናት ማለት መሆኑ ከታመነ ባህሉን ሕይወታዊ በሆነ መልኩ በማስተማር የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል ሁነኛ መሣሪያ ሥነጽሑፍ ነው።*

በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የቀረበው ዐቢይ ነጥብ የሚያስረዳን ሥነጽሑፍ በተለይ ሁለተኛ ቋንቋን በመማር-ማስተማር ተግባር ላይ ሁነኛ መሣሪያ በመሆን እንደሚያገለግል ነው። ከዚህ አንፃር የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረትም የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ሦስት ክልሎች አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር ታቅደው በ2000 ዓ.ም. በሥራ ላይ በሚገኙት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አመራረጥና አደረጃጀት ማጥናት ይሆናል።

ይህንን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱ ምክንያቶችም ሁለት ናቸው። አንደኛው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለረዥም ዓመታት ይሠራበት የነበረው አካሄድ ተለውጦ ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ የመማሪያ መጻሕፍት በማዕከል ደረጃ መዘጋጀታቸው ቀርቶ ከ1ኛ እስከ 8ኛ ክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች አንዳንድ ክልሎች ኃላፊነቱን ወስደው እንዲያዘጋጁ ተደርጓል። ከዚህ አንፃር በተለይ ታዳጊ በሚባሉት ክልሎች አማካይነት በሚዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የመማሪያ መጻሕፍቱ አዘጋጆች ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ሥራዎች ምን ያህል ኢአፈ-ፈት ተማሪዎችን በቋንቋው ተጠቃሚ ለማድረግ ያላቸው ከፍተኛ ፋይዳ ተገንዝበው በተግባር ላይ አውለዋቸዋል? አመራረጣቸው እና አደረጃጀታቸው የመስኩ ምሁራን የጠቆሟቸውን መርሆዎች መሠረት ያደረገ ነውን? ለሚሉት ጥያቄች መልስ ለመፈለግ ሲሆን፤ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢ በሥነጽሑፍ ቋንቋ ማስተማር (Literature as Applied to Amharic Teaching (TeAm 644)) ለሚለው ኮርስ ከፊል ማሟያነት ባካሄደው የሙከራ ጥናት የዚህ ጥናት ተተኳሪ ከሆኑት ክልሎች ውስጥ በሁለቱ ክልሎች (ቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልሎች ለአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት) ላይ ችግሮች መኖራቸውን ፍንጭ በማየቱ የችግሮቹ ስፋት፣ መንስኤና መፍትሄቻቸው በስፋት መፈተሽ ይኖርበታል ብሎ በማሰቡ ነው። በዚህ ጥናት ከነዚህ ከተጠቀሱት ሁለቱ ክልሎች በተጨማሪ ደቡብ ክልል እንዲካተት የተደረገበት ምክንያትም ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች የተዘጋጁት መጻሕፍት መሠረት ያደረጉት ለደበቡ ክልል 7ኛ እና 8ኛ ክፍል የተዘጋጁትን መጻሕፍት በመሆናቸው ነው።

### 1.2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በደቡብ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛው እርከን (7ኛ እና 8ኛ) ተማሪች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አመራረጥና አደረጃጀት በማጥናት ጠንካራና ደካማ ጐኖቻቸውን መለየትና የመፍትሔ ሐሳቦችን መጠቆም ነው። ይህን ዐቢይ ዓላማ ከግብ ለማድረስም ጥናቱ ለሚከተሉት ቁልፍ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፤

- ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ሥራዎች አንጻር ሲቃኙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ምን ያህል ሽፋን ተሰጥቷቸዋል?

- በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ በመስኩ ምሁራን የተጠቆሙትን የአመራረጥ መርሆዎች መሠረት ያደረጉ ነበሩ?
- ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ እንዴት ተደራጅተዋል? በምሁራን የቀረቡትን የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት መርሆዎች ባገናዘበ መልኩ ነውን?
- በመርሐ ትምህርቱ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አማካይነት እንዴት ተተግብረዋል?

የሚሉት ጥያቄዎች በዚህ ጥናት መልስ ከሚሰጥባቸው መካከል ቀዳሚዎቹ ናቸው። ከዚሁ ጋር በተያያዘም በጥናቱ ውጤት ላይ በመመሥረት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ሥራዎች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ በማካተቱ ተግባር ላይ የተሻሉ (ተመራጭ የሆኑ) የአመራረጥና የአደረጃጀት ሥልቶችን በመፍትሔ ሐሳብነት መጠቆም በዚህ ጥናት ዓላማዎች ውስጥ የሚካተት ይሆናል።

## 1.3. የጥናቱ አስፈላጊነት

ጥናቱ በደቡብ፣ በቤንሻንጉል ጉምዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁ የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አመራረጥና አደረጃጀት በመመርመር ጥንካሬና ጉድለቶቹን ያሳውቃል። በመሆኑም የጥናቱ ውጤት በቀዳሚነት ለየክልሎቹ የመጻሕፍቱ ተጠቃሚዎች የአማርኛ ቋንቋ መማር-ማስተማር ሂደት ውጤታማ እንዲሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል ተብሎ ይገመታል። ከዚህም በተጨማሪ፦

- የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ክልሎች የሚገኙ መምህራን የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቋንቋን ለማስተማር ያላቸውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ተገንዝበው ልዩ ትኩረት እንዲሰጧቸው ያደርጋል፤
- የየክልሉ ትምህርት ቢሮዎች የሥርዓተ ትምህርት ክፍል ባለሞያዎች ወደፊት በሚያካሂዷቸው የመርሐትምህርት ማሻሻል ተግባር ላይ ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተሻለ ትኩረት እንዲሰጧቸው ያሳስባል፤
- የመማሪያ መጻሕፍቱ አዘጋጆችና አሻሻዮችም ከጥናቱ ውጤት በመነሳት በወደፊቱ የመጻሕፍቱ የማዘጋጀት ወይም የማሻሻል ተግባር ላይ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በተሻለ የአመራረጥና የአደረጃጀት ሥልት እንዲያቀርቡ ጥቆማ ይሰጣል፤

- በሌሎች መሰል ክልሎች በተለይ የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን የመርሐትምህርትም ሆነ የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችና አሻሻዮች በሥነጽሑፍ ቋንቋን የማስማተር ተግባር ትኩረት እንዲሰጡ ያሳስባል፤
- በተለይ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ትምህርቱን ከቀድሞው በተሻለ መልኩ ማራኪና ሳቢ በሆነ የአቀራረብ ስልት እንዲማሩት ጠቋሚ በመሆን ሊያገለግል ይችላል፤

ተብሎ ይታመናል::

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደቡብ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልላዊ መንግሥታት የትምህርት ቢሮች በተዘጋጁት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዘትን ሲመረምር በተለይ ትኩረት ሰጥቶ የሚያጠናው ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የተሰጠውን ሽፋን፣ የአመራረጥና የአደረጃጀታቸውን ተገቢነት ብቻ ነው::

በመጻሕፍቱ የቀረቡ ሌሎች ኢልቦለዳዊ ሥራዎች፣ የክሂል ዘርፎች እንዲሁም በሥነልሳን ላይ ያተኮሩ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን አመራረጥና አደረጃጀት አይመለከትም:: በሌላም በኩል ለተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች በ2000 ዓ.ም. በሥራ ላይ የሚገኙትም መጻሕፍት ቀድመው ከነበሩት መጻሕፍት ጋር የሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አቀራረብ በተመለከተ አያነጻጽርም:: በተጨማሪም በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር የመምህር- ተማሪ መስተጋብር እና የመምህራን የሥነጽሑፋዊ ይዘቶች የክፍል ውስጥ ትምህርት አተገባበር ከዚህ ጥናት መጠነ - ርዕይ ውጭ ናቸው::

## 1.5. የቁልፍ ቃላትና ሐረጋት ፍች

ሥነጽሑፍ:- (Literature) ሥነጽሑፍ ሰዎች ስለራሳቸው፣ ስለህይወት የሚሰማቸውን፣ የሚያስቡትንና የሚመኙትን በአጠቃላይ ግንዛቤአቸውን በቋንቋ አማካኝነት የሚያንጸባርቁበት ኪነጥበብ ሲሆን በተለያዩ ቅርጾች የሚከሰትና ህልውናው በቃል ወይም በጽሑፍ የሆነ የፈጠራ ሥራ ነው::

**ሥነጽሑፋዊ ሥራ፡-** (Literary work) በዚህ ጥናት ውስጥ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ተብሎ የሚጠራው አጭር ልቦለድ፣ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ፣ ተውኔት ወይም ድራማ፣ ግጥም እና ተረትን ያጠቃልላል።

**ቅንጫቢ፡-** (Extract) በዚህ ጥናት ውስጥ የቃሉ ፍቺ የሚያመለክተው ከአጭር ልቦለድ፣ ከረጅም ልቦለድ ከተውኔት ወይም ከግጥም ላይ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታስቦ የተወሰነው ክፍል ብቻ ተመርጦ (ተቀንጭቦ) የቀረበን ጽሑፍ ነው።

**ተለጣጣቂነት፡-** ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በአንድ የክፍል ደረጃም ሆነ (ጎናዊ) በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች (ተዋረዳዊ) በተደጋጋሚ ሲቀርቡ ስፋትና ጥልቀት-በሚያሳይ መልኩ አንዱ ወደ ሌላው የሚያሸጋግር መሆን እንደሚገባው የሚያሳይ ነው።

**ተከታታይነት፡-** ተከታታይነት ሲባል በሥነጽሑፍ ሥራዎች አማካይነት የሚቀርብ አንድ የትምህርት ይዘት በአንድ የክፍል ደረጃም ሆነ በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች ላይ ከትምህርቱ መጀመሪያ እስከ መጨረሻ ድረስ ሳይቋረጥ፣ ሥልታዊ የሆነ ድግግሞሽ በማሳየተ መቅረብ (መደራጀት) እንዳለበት ያመለክታል።

**አፈ-ፈት፡-** በዚህ ጥናት ውስጥ የቃሉ ፍቺ የመጀመሪያ ቋንቋቸው ወይም የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የአማርኛ ቋንቋ የሆኑ ተማሪዎችን ያመለክታል።

**ኢአፈ-ፈት /ሁለተኛ ቋንቋ/፡-** በዚህ ጥናት ውስጥ ኢአፈ-ፈት እና ሁለተኛ ቋንቋ የሚሉትን ቃላት/ሐረጋት አጥኚው እያፈራረቀ የተጠቀመባቸው ሲሆን ፍችያቸው የሚያመለክተውም የመጀመሪያ ቋንቋቸው አማርኛ ቋንቋ ያልሆኑ ተማሪዎችን ወይም በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎችን ለመጠቆም ነው።

ባጠቃላይ በምዕራፍ አንድ በጥናቱ ዳራ ሥር በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር አጀማመር፣ ፋይዳ፣ አመራረጥ እና አደረጃጀት በመጠኑ በመጠቆም የጥናቱን አነሳሽ ምክንያቶች ለመግለጽ ጥረት ተደርጓል። በተጨማሪም የጥናቱን ዓላማ፣ አስፈላጊነትና ወሰን ለማመልከት ተሟክሯል። በተከታዩ ምዕራፍም ክለሳ ድርሳናት ይቀርባሉ።

# ምዕራፍ ሁለት፡- ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የሥነጽሑፍ ምንነት

የሥነጽሑፍን ምንነት በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን የተሰጡት አስተያየቶች ፈርጀ-ብዙ ገጽታዎችን የያዙ ናቸው። ይህም የሥነጽሑፍን ምንነት በተወሰኑ ዐረፍተ-ነገሮች ለመጠቆም አዳጋች ያደርገዋል። ለዚህም እንደምክንያት የሚጠቆመው በሥነጽሑፍ የማይደፈር (የማይዳሰስ) ርዕሰጉዳይ ባለመኖሩና የተለያዩ ምሁራን ከየራሳቸው የሙያ ዘርፎች (ሥነትምህርት፣ ፍልስፍና፣ ሥነሰብዕ፣ ሥነአእምሮ፣ ወዘተ.) ጋር በማያያዝ የተለያየ ብያኔ በመስጠታቸው እንደሆነ ዘሪሁን (1992፣ 1)፣ እንዲሁም በድሉ (1996፣7) ያስረዳሉ።

ስለሥነጽሑፍ ምንነት ከተሰጡት ብያኔዎች መካከል በሀገራችንና በውጭ ሀገራት ምሁራን ከቀረቡት ሐሳቦች ውስጥ የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፤

> *ሥነጽሑፍ እጅግ አጠቃላይ በሆነ አነጋገር፣ የአውናዊውን ዓለም ማኅበረሰባዊ ሕይወት መሠረት አድርጎ፣ እሱን ግን እንዳለ ሳይቀዳ የመፍጠር ችሎታ በተሰጠው ሰንካኝ (የሥነጽሁፍና የኪነት ባለሙያ) የምናብ ኃይል መሣሪያነት የሚበጅ፣ የሰው ልጆች ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ምግባራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እሴቶች የሚገለጹበት፣ የሰንካኙም ሐሳብና ስሜት ለዛ ባለው ስልትና ቋንቋ የሚገለጹበት የዘራሰብ ሥንክናዊ ሀብት ነው (ወንድወሰን 1995፣ 17)።*

ከቀረበው ማብራሪያ የምንረዳው ሥነጽሑፍ የሰዎችን የዕለት ተዕለት ሕይወት የሚዳሰስና በዚህ ጭብጥ ላይ ብቻ ያተኩራል ተብሎ የማይገደብ ፈርጀ ብዙ ኪነጥበባዊ እሴት መሆኑ ነው። ለዚህም ነው ዘሪሁን (1992፣ 1) «የሥነጽሑፍ ዋነኛ ጉዳይ ሰው ነው ምንጨም፣ ፈጣሪውም፣ ተቀባዩም ሰው ነው። ከሰው ሕይወት ተቀድቶ፣ በሰው ተፈጥሮ፣ ስለሰው ተነግሮ የሰውን ጉዳይ ይዞ መልሶ ለሰው የሚቀርብ በመሆኑ ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው» በማለት የሚያብራሩት።

በሌላ በኩል Lazar (1993፣ 2)፣ የሥነጽሑፍን ምንነት በተመለከተ የተለያዩ ዕውቅ ጸሐፍት ያቀረቧቸው ብያኔዎች ናቸው ካሏቸው ውስጥ የሚከተሉትን ለአብነት ጠቁመዋል፤

- *ሥነጽሑፍ የሰዎችን ስሜት ሥርዓታዊ በሆነ ጥበብ የሚያሳውቅ የሞያ ዘርፍ ነው፤*
- *ሥነጽሑፍ ያፈነገጠ የቋንቋ አጠቃቀም የሚከተል በሌላ አገላለጽ ከዘወትራዊው የቋንቋ አጠቃቀም በአንድ እርከን ከፍ ያለ የፈጠራ ሥራ ነው፤*
- *ሥነጽሑፍ ማለት መልስ የሌለው ጥያቄ እንደማለት ነው፤*
- *ሥነጽሑፍ (ልቦለድ፣ ግጥም ወዘተ.) በአመዛኙ ከደካሞች ወይም ከተሸናፊዎች ጐራ በመቆም በዓለም ላይ ፍትህና እኩልነትን የሚያሰፍን መሣሪያ ነው፤*

እነዚህ በተለያዩ ምሁራን የቀረቡት ብያኔዎች የሥነጽሑፍን ምንነት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመመልከት የሞከሩ ናቸው። በተናጠል ሲታዩም ምንነቱን በምልዐት ይገልጹታል ለማለት ባያስደፍርም አንዳች የሚጠቁሙት ሐቅ ያዘሉ ናቸው። በአጠቃላይ ስንመለከታቸው ግን ዘሪሁን (1992፣ 1-2) በሦስት እንዲሁም ወንድወሰን (1995፣ 13-19) መድበው ካቀረቧቸው የተለያዩ ምሁራን ብያኔዎች (ትርጓሜዎች) ውስጥ በአንዱ ሊፈረጁ የሚችሉ ናቸው ለማለት ይቻላል። እነዚህም፡-

1. *ሥነጽሑፍ የሚባለው የተጻፈ ነገር ሁሉ ነው።*
2. *ሥነጽሑፍ የሚባሉት ታላላቅ መጻሕፍት ብቻ ናቸው።*
3. *ሥነጽሑፍ የፈጠራ ሥራ ብቻ ነው።*

ከነዚህ እምቅ የሆነ ሐሳብ ከያዙት ብያኔዎች ውስጥ አንዱን ብቻ መርጦ ይህ ትክክለኛና ተገቢ ነው፤ ያ ግን ስሕተት ነው ብሎ ለመናገር አዳጋች ነው። ምክንያቱም ሦስቱም የሥነጽሑፍን ምንነት የሚገልጹበት የተለያየ መንገድ አላቸው። ስለዚህም ብያኔዎቹን ይዞ እንደተነሳው ተመራማሪ ዓላማና አመለካከት የየራሳቸው ተግባራዊ ፋይዳ ሊኖራቸው እንደሚችል ወንድወሰን (1995፣ 17) ያስረዳሉ።

በመሆኑም ይህ ጥናት ከተነሣበት ዓላማ እና ከርዕሰጉዳዩ መጠነ-ርዕይ አኳያ በተራ ቁጥር ሦስት ላይ የተጠቆመውን ገለጻ ማለትም «ሥነጽሑፍ የፈጠራ ሥራ ብቻ ነው» የሚለውን መሠረት ያደረገ ነው። ለዚህም ዐቢይ ምክንያት የመጀመሪያው ማለትም «ሥነ ጽሑፍ የሚባለው የተጻፈ ነገር ሁሉ ነው» የሚለው ትርጓሜ እጅግ ሰፊ ጽንሐሳብን የሚያካትት ሲሆን በተመሳሳይ «ሥነጽሑፍ የሚባለው ታላላቅ መጻሕፍት ብቻ ናቸው» የሚለው ብያኔም የተረጋገጠላቸውና «ዘመን ተሻጋሪ» ሊባሉ የሚችሉት

ዕውቅ ልቦለዳዊም ሆነ ኢልቦለዳዊ ይዘት ያላቸውን ጽሑፋዊ የኪነጥበብ ሥራዎች ብቻ- ነው። በአንባሩ ይህ ጥናት ለ7ኛና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን (ኢልቦለድን ሳይጨምር) ምንባቦች ብቻ አመራረጥና አደረጃጀታቸውን የሚመረምር በመሆኑ እነዚህን ሁለት ብያኔዎች መሠረት አያደርግም።

የሥነጽሑፍን የፈጠራ ሥራነት የሚያረጋግጡ በርካታ ምሁራን (ፈቃደ (1991)፣ ዘሪሁን (1992)፣ ወንድወሰን (1995)፣ Lazar (1993)፣ Trace (1997))፣ በሥነጽሑፍ ዘርፍነት ሊፈረጁ የሚችሉትን የፈጠራ ሥራዎች እንደሚከተለው ጠቁመዋል፤

- *. . . በግጥም፣ በቅኔ፣ በአጭር እና በረዥም ልቦለዶች (እንዲያውም ሰፋ አድርገን በተረታተረት፣ በምሳሌዎች፣ በእንቆቅልሽ፣ በሥነቃላዊ ግጥሞች፣ ወዘተ) አማካይነት የቋንቋን ትምህርት አስደሳች እና አእምሮ አሰይ ማድረግ ይቻላል (ፈቃደ 1991፣ 111)።*
- *ሥነጽሑፍ በተለያዩ ቅርጸች፣ በቋንቋ አማካይነት የሚከሰት፣ ህልውናው በቃል ወይም በጽሑፍ የሆነ የፈጠራ ሥራ ሲሆን በዋናነት ሥነግጥምን፣ ተውኔትን፣ ረዥምና አጭር ልቦለድን እንዲሁም ከዚህ ጋር ኪነጥበባዊ ተቀራራቢነት ያላቸውን ጽሑፎችና የሥነቃል ሀብቶች ያጠቃልላል (ዘሪሁን 1992፣ 3)።*
- *ሥነጽሑፍ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር ያለውን ፋይዳ ለመመርመር በፈጠራ የሥነጽሑፍ ዘርፍነት የሚካተቱት ሥነግጥም፣ ተውኔትና ልቦለድ (አጭርና ረጅም) ናቸው (ወንድወሰን 1995፣ 17)።*
- *በሥነጽሑፍ ሥር የሚፈረጁት መጠናቸው ትልቅም ይሁን ትንሽ አእምሮን ለማነቃቃትና መንፈስን ለማበረታታት በደራሲው (ገጣሚው) ጥበብ የተጻፉ (የተነገሩ) ናቸው። በዚህ ሥር የሚታቀፉትም ሥነግጥም፣ ተውኔት፣ ልቦለድና አፋዊ ኪነ-ቃሎች (ሥነቃሎች) ናቸው (ጌትነት 1998፣ 8)።*
- *በሥነጽሑፍ ዘርፍነት በዋነኛነት የሚመደቡት በረዥም ልቦለድ፣ በአጭር ልቦለድ፣ በተውኔት እና በግጥም መልክ መልእክት-አዘል በሆነ ቋንቋ ተከሽነው ድርበርብ በሆነ ፈጠራዊ ውበት በልጽገው የሚቀርቡትን ኪነጥበባዊ የፈጠራ ውጤቶች ነው (Lazar 1993, 5)።*
- *ሥነጽሑፍ ስንል በቀዳሚነት የምንጠቅሳቸው ድራማ፣ ግጥም እና ልቦለድ ናቸው (Trace 1997፣ 1)።*

ባጠቃላይ ይህ ጥናት ከላይ በተለያዩ የሀገራችንና የውጭ ሀገራት ምሁራን የቀረቡትን ውሣኔዎች መሠረት በማድረግ በሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራነት የሚቃኙቸው በዋነኛነት አጭር ልቦለድን፣ ረጅም ልቦለድን፣ ግጥምን እና ተውኔትን ሲሆን እንዲሁም በጽሑፍ መልክ የሰፈሩትን ሥነቃላዊ የፈጠራ ሥራዎች (ለምሳሌ ተረቶችን) ያጠቃልላል።

## 2.2 ሥነጽሑፍ እና ቋንቋን ማስተማር

ሥነጽሑፍ እና ቋንቋን ማስተማር ሁለት የተለያዩ የሞያ ዘርፎች ናቸው። ነገር ግን የአንዱ ሕልውና በሌላው ላይ የተመረኮዘ ነው። ማንኛውም ሕብረተሰብ ለትውልዱ የሚያስተላልፈው ሁለንተናዊ እሴት አለው። ይህ ተስተላልፎም በረኻም ዘመን የተገኘ የሕይወት ልምድ በትምህርት አማካኝነት ከማቀበል ጋር የተቆራኘ ነው። ዘመናዊ ትምህርት ሲታሰብም የሥርዓተ ትምህርት መኖር አይቀሬ ነው። በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ከሚካተቱት ጉዳዩች አንዱ ደግሞ ሥነጽሑፍ ነው። ነገር ግን ሥነጽሑፍ በአንድ ሥርዓተ ትምህርት ውስጥ ሁለት እጅግ የተለያዩ ዓላማዎችን ይዞ ሊቀርብ ይችላል። ይኸውም ሥነጽሑፍን እንደ አንድ የትምህርት ወይም የሞያ ዘርፍ (Literature as a subject or discipline) ማጥናትና ቋንቋን ለማስተማር ሥነጽሑፍን በመሣሪያነት መጠቀም (literature as an instrument) ነው (Widdowson 1975, 71፣ እንዲሁም Lazar 1993, 13)።

### 2.2.1 ሥነጽሑፍን እንደ አንድ የትምህርት ወይም የሞያ ዘርፍ ማጥናት

ሥነጽሑፍን እንደ ሌሎቹ የትምህርት ዓይነቶች (ሒሳብ፣ ኬሚስትሪ፣ ጂኦግራፊ፣ ወዘተ.) ማስተማርም ሆነ ሥነጽሑፍን እንደ አንድ የጥናት መስክ ማጥናት ዐቢይ ግቡ ተማሪዎች የሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ምንነትና እንዴትነት በመገንዘብ ሂሳዊ ማብራሪያ መስጠት እንዲችሉና የሱ ደቀመዝሙር እንዲሆኑ (የሥነጽሑፍ ባለሙያ እንዲሆኑ) ማስቻል ነው። ስለዚህም ከሥነጽሑፋዊ ሥራው የሚወጡት መልመጃዎችና ልዩ ልዩ ተግባራት ይህን ግዕከል ያደረጉ ናቸው። ከትምህርቱ በኋላም ከተማሪዎቹ የሚጠበቀው ጥሩ ሥነጽሑፋዊ ዕውቀት እንዲኖራቸው ብሎም በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ ሂሳዊ ትንታኔ እንዲያቀርቡ ማስቻል ነው።

### 2.2.2 ሥነጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር መሣሪያነት መጠቀም

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ በመገኘታቸው ብቻ የተማሪዎቹን የቋንቋ ክሂሎች ወይም የሥነልሳን ዕውቀት ለማዳበር አግዘዋል ለማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ሥነጽሑፍን እንደ አንድ የጥናት መስክ በማጥናትና ቋንቋን ለማስተማር በመሣሪያነት መገልገል የተለያዩ አካሄዶችን የሚከተሉ በመሆናቸው ነው (Lazar 1993, 13)። ቋንቋን በሥነጽሑፍ መሣሪያነት የማስተማር ዋና ዓላማን በተመለከተም ፊቃደ (1991፣ 111) የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተዋል፤

> *የቋንቋ ትምህርት በሥነጽሑፍ ሥራዎች አማካይነት ማከናወን የራሱ አላማዎች፣ ጠቀሜታዎች፣ ብርታቶችና ድክመቶች አሉት። ዓላማዎቹን በተግባር ለማዋል የሚደረግ ጥረት ተማሪዎች ሥነጽሑፍ እንዲወዱና እራሳቸውም እንዲጽፉ ቢያነቃቃቸው መልካም ነው። ቋንቋን በሥነጽሑፍ የማስተማር ዋና ትኩረት ግን በተመረጠ የፈጠራ ጽሑፎች አማካይነት ልዩ ልዩ የቋንቋ ክሂሎችን ማስተማር ነው።*

ከላይ እንደተገለጸው በርግጥ ሥነጽሑፍን በቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያነት የምንገለገልበት ዓቢይ ዓላማ አራቱን የክሂል ዘርፎች ማለትም ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን ለማጎልበት ቢሆንም ከዚሁ ጎን ለጎን ተማሪዎቹ የሥነልሳንና የሥነጽሑፍ ግንዛቤአቸው በአንባራዊነት ሊሻሻል እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

ይህ በሥነጽሑፍ መሣሪያነት ቋንቋን የማስተማር ስልት በተለይ በመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ እና በሁለተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። ነገር ግን እንደምንመርጣቸው ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ክብደትና ቅለት እንዲሁም ከሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ እንደሚዘጋጁት ልዩ ልዩ መልመጃዎች ባሕሪ በማንኛውም የዕድሜ እርከን ወይም የክፍል ደረጃ ላይ ለሚገኙ የቋንቋ ተማሪዎች ልንገለገልባቸው እንደምንችል Collie እና Slater (1989፣ 2)፣ እንዲሁም Ghosn. J (2002፣ 172-179) ጠቁመዋል።

ይህ ጥናት ሁለኛውን ዘርፍ ማለትም ሥነጽሑፍ ቋንቋን ለማስተማር መሣሪያነት መጠቀም ተከትሎ የተዘጋጀ ነው።

### 2.2.3. በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር ያሉት ፋይዳዎች

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቋንቋን በማስተማር ተግባር ላይ በመሣሪያነት መጠቀም በርካታ ጠቀሜታዎች እንዳሉት የቋንቋ ትምህርት አቀራረብን በተመለከተ በሚቀርቡ የተለያዩ አስተያየቶችና በጥናታዊ ሥራዎች ላይ በስፋት ተጠቁመዋል። በርግጥም ሥነጽሑፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መገልገል የተማሪዎቹን አጠቃላይ ግንዛቤና ንቃተ ሕሊና (intellectual maturity)ለማጎልበት፣ ማኅበራዊና ሥነምግባራዊ እድገት ለማምጣት እንዲሁም ግብታዊነትን ለማስወገድ ይጠቅማል (Hill 1986፣ 7)። ከዚህም በተጨማሪ የሚከተሉት ሥነልሳናዊና ሥነአእምሮአዊ ፋይዳዎች ሊኖሩት እንደሚችሉ እኚሁ ምሁር ጠቅሰዋል፤

- *አውዳዊነት፡- የቋንቋ ትምህርቱን በእውነተኛ አውድ (ከዕለት ተዕለት ህይወታቸው ጋር በተያያዘ መልኩ) በማቅረብ ተማሪዎች ቀደም ብለው የሚያውቁትን እንዲያጠናክሩትና ቋንቋውን የግላቸው እንዲያደርጉት መንገድ ያመቻቻል፤*
- *ተግባቦት ይፈጥራል፡- ተማሪዎች በግል ጥረታቸው ቋንቋውን በአውድ በመገልገል እርስ በርሳቸው ተግባቦትን እንዲፈጥሩ እንዲሁም ከክፍል ውጭ በተግባር ላይ እንዲያውሉት ያስችላቸዋል።*
- *ተነሳሶትን ይፈጥራል፡- ልዩ ልዩ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ማቅረብ ስለሚቻል ከተለያዩ ሰዎች ባሕልና የሕይወት ልምዶች ጋር እንዲተዋወቁ በማድረግ በተማሪዎች ዘንድ የሐሴትና የመደነቅ ስሜትን ይፈጥራል።*

በሥነጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን ማስተማር ያሉት ጠቀሜታዎች በተወሰኑ አንቀጾች ዘርዝሮ ማሳየት አዳጋች ቢሆንም የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት ወደሆነው የአመራረጥና የአደረጃጀት ሂደት ከመሸጋገራችን በፊት «በመጀመሪያ በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር ምን ፋይዳ አለው?» የሚለውን መመልከት ወሳኝ ጉዳይ በመሆኑ የሚከተሉትን ዐበይት ሊባሉ የሚችሉትን ጠቀሜታዎች ብቻ ነቅሰን ለአብነት እንመልከት፤

#### 2.2.3.1. የቋንቋን ክሂሎች ለማዳበር

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ቋንቋን ለማስተማሪያነት ማዋል አራቱን የክሂል ዘርፎች ማለትም ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን ያጎለብታል። የተለያዩ ምሁራን ፈቃደ (1991፣ 11)፣ ወንድወሰን (1995፣ 28)፣ በድሉ (1996፣ 6)፣ Hill (1986, 7-8)፣ Collie and Slater (1987, 3-4)፣ Lazar (1993, 8)፣ እና

Mckay (1996, 191)) በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር ክሂሎችን እንደሚያጐለብት በዝርዝር አስረድተዋል።

ሥነጽሑፍን በቋንቋ መማር-ማስተማር ተግባር ላይ መጠቀም ከአንድ ምንባብ መልመጃዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ ሥነልሳናዊ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎችን ለማቅረብ ያግዛል። ከዚህም ባሻገር በምንባቡ ውስጥ ከሚገኙት ጭብጦች፣ መቼቶች፣ ግጭቶች፣ ገጸባሕርያት፣ ወዘተ. ጋር በተያያዘ አያሌ መልመጃዎችን እና የተለያዩ የድርሰት ዓይነቶችን ማሰናዳት ይቻላል (Hill 1986, 7-8)። በተጨማሪም በድሉ (1996፣ 6) ይህን በተመለከተ እንደሚከተለው ያብራራሉ፤

> *የሥነጽሑፍ ሥራን አስመልክቶ በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ውይይት ተማሪዎችን ስለሚሰብ የተሳታፊነታቸውን ደረጃ ከፍ ያደርገዋል። ተማሪዎች ድራማዎችን ሲሠሩ ግጥሞችንና አጫጭር ታሪኮችን ሲያነቡ የመናገርና የማንበብ ክሂላቸው ይዳብራል። ከሁሉም በላይ ደግሞ ሥነጽሑፍ በባሕሪው ሳቢ ስለሆነ ተማሪው የሥነጽሑፍ ሥራ ላይ ተመስርቶ ክሂሎችን ለማዳበር በሚከናወኑ ልምምዶች ላይ ለመሳተፍ በአብዛኛው ውጫዊ ግፊት አይፈልግም፤ ስለሥነጽሑፍ መናገር ይፈልጋል፤ ሥነጽሑፍ መጻፍ ይፈልጋል፤ ሥነጽሑፍን ማዳመጥ ይፈልጋል።*

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ጠቀሜታዎች ልናገኝ የምንችለው Lazar (1993፣ 10) Selden (1989፣ 79) የተባሉ ፀሐፌን ዋቢ በማድረግ እንደገለጹት፣ ተገቢነት ያለው ሥነጽሑፋዊ ሥራን መርጠን በመጀመሪያም ተማሪዎቹ ግልጽ ሆነው ሥራውን በመረጡት አቅጣጫ እንዲወያዩበት ማድረግ ስንችል ነው። ነገር ግን በተማሪዎቹ የአተረጓጎምና የአረዳድ ሂደት ላይ ተጽእኖ ሊያስከትሉ የሚችሉ ጉዳዮች ሊኖሩ እንደሚችሉ መዘንጋት የለብንም። እነዚህም፦

- *ተማሪው በሕይወት ዘመኑ ያሳለፋቸው ልዩ ልዩ አጋጣሚዎችና የሕይወት ተሞክሮዎች፣*
- *ተማሪው በማኅበራዊ ደረጃው ያለው ተቀባይነት፣*
- *የተማሪው ሃይማኖታዊ ዳራ*

ናቸው።

ከዚህ አንፃር በጥንቃቄ ተመርጦ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚውል ስነጽሑፋዊ ሥራ የታሰበውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግቡ ሊያደርሱ ይችላል። ተማሪዎችም

በክፍል ውስጥ ከሚያደርጉት የርስበርስ መስተጋብር በተጨማሪ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸውም ውስጥ በስፋት ሊገለገሉበት ይችላሉ። ይህን በተመለከተ Lazar (1998, 8) የሚከተለውን ጠቁመዋል፤

> *የሥነጽሑፍ ቋንቋ ከሌሎች ቋንቋዎች ማለትም ከዕለት ተዕለት የመግባቢያ ቋንቋ ብዙም የተፈታ ባለመሆኑ ሥነጽሑፋዊ ውሀድ አሀዶችን (literary text) በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ መጠቀም ተማሪዎች የቋንቋ ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ ያግዛል። በሌላም በኩል ተማሪዎች ከአያሌ ዘይቤዎች፣ ከቃላት አውዳዊ ትርጉም፣ ከሆሄያት ሥነድምጻዊ ሂደትና ቅደም ተከተላዊ ስደራ ጋር እንዲተዋወቁ ወይም ልምምድ እንዲያካሂዱ በርካታ የተለያዩ ውሀድ አሀዶችን በማቅረብ ለመተግበር እድል ይሰጣል።*

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መገልገሉ ለመጀመሪያ ቋንቋም ሆነ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ጠቀሜታ ቢኖረውም በተለይ ግን ሁለተኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ላይ የምንገለገልበት መሠረታዊ ዓላማ ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ በከፍተኛ ደረጃ ለማጎልበት ስለሚያስችል ነው። ለዚህም ዋናው ምክንያት ሥነጽሑፍ ትክክለኛና እውነተኛ አውድን በመፍጠር፣ የቃላትን አውዳዊ አጠቃቀም በማሳየት፣ ወዘተ. ሥነልሳናዊ ብቃትን ከፍ ስለሚያደርግልን መሆኑን Mckay (1996፣ 191) የተባሉ ምሁር Povey (1997፣ 187) «ን» ጠቅሰው ገልጸዋል።

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ክሂሎችን የሚያጎለብቱ ዘላቂነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ ነው። ምክንያቱም ሥነጽሑፍ የሰዎችን መሠረታዊ ጉዳዮች በመያዝ የየዘመናቸውን ማኅበራዊ የኑሮ ውጣ ውረዶች ከማንሳታቸውም ባሻገር በአንድ አካባቢ የነበሩ ታሪካዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ድንበርና ዘመን ተሻግሮ ለሚኖር ማኅበረሰብ ውበትና ማራኪነት ባለው አቀራረብ ግንዛቤን ያስጨብጣሉ (Collie and Slater 1987, 3-4)። በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ (በልቦለድም ሆነ በስነቃላዊ ትረካዎች) ታሪካቸው የሚነገርላቸው ገጸባሕርያት ሕይወት የገሀዱን ዓለም ወክለው የቀረቡ በመሆናቸው በተመሳሳይ መልኩ ለመሰሎቻቸው እንዲተርኩ ያበረታታል። በዚህ ጊዜም ገጸባሕርያቱ የተጠቀሙባቸው ቃላትና የአተራረክ ስልት በመከተል የንግግር እና የቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓትን እንዲለምዱ ያስችላቸዋል (Toolan 1996፣ 105)።

### 2.2.3.2. የቋንቋ ትምህርቱን ማራኪና ተወዳጅ ማድረግ

ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራ ከአእምሮአችን ቀድሞ ለልባችን ይደመጣል፤ የሰዎችን ውስጣዊ ስሜት ይነካል። ስለዚህም ከተማሪው ዳራ አንፃር የተቃኙ፣ ተመጣጣኝ የሆኑና ልዩ ልዩ የሕይወት ገጽታዎችን ያነገቡ በርካታ ውህድ አሀዶችን በጥንቃቄ በመምረጥ ተማሪዎች ትምህርቱን ሳይሰላቹ በንቃትና በጉጉት ስሜት እንዲከታተሉ ማድረግ ይቻላል (Collie እና Slater 1996፣ 2)።

ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች የአስደሳችነትና የማራኪነት ባሕርያት እንዲኖራቸው ያስቻሏቸውን ጉዳዮች በተመለከተ Lazar (1993፣ 1) የሚከተሉትን ጠቁመዋል፤

- *ሥነጽሑፍ የስሜት እና የሐሳብ መግለጫ መሆኑ፣*
- *ሥነጽሑፍ አንባቢያንን ወይም አድማጮች ግላዊ መልስ እንዲሰጡ የሚጎነትል ወይም የሚያነሳሳ (evoke) የቋንቋ አጠቃቀም ስልት መሆኑ፣*
- *ሥነጽሑፍ የዓለምን ድንቃይ (fantasy)፣ ስሜት፣ አስፈሪነት (horror)፣ ርዕይ (vision) ገጽታ በቃላት የሚቀርጽ በመሆኑ፣*
- *ሥነጽሑፍ አያሌ ሰዎችን በአንድ በማገናኘት፣ የሌሎችን አተያይ፣ ሐሳብ፣ እና ግንዛቤ፣ ወዘተ. የሚያሳውቅ እንዲሁም ራሳችንን አጥብቀን እንድንረዳ የሚያስችለን መሳሪያ በመሆኑ፣*

ነው።

ስለዚህም ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራ የተማሪዎችን አእምሮአዊ ብቃትና ማኅበራዊ ግንዛቤ እንዲሁም ጠቅላላ ዕውቀት በማጎልበት ዕውቀትን፣ ብልሀትና ጥበብን ከማስገኘቱም በላይ በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ ሐሴትን ሊፈጥር እንደሚችል Hill (1986, 7) ጠቁመዋል። Widdowson (1975, 81) በተጨማሪ እንደገለጹት፣ ሥነጽሑፋዊ ሥራ በተማሪዎቹ ዘንድ ተወዳጅነት ሊቀናጅ የቻለው አንድን በቀጥተኛ መንገድ ሊገለጽ የሚችልን ሰዋዊ ጉዳይ ባልተለመደና አስደናቂ በሆነ አገላለጽ ስልት በማቅረብ በተማሪዎቹ አእምሮ ውስጥ ምስል የመከሰትና የመደመም ስሜት ስለሚያጭር እንደሆነ በአፅእኖት ያስረዳሉ።

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የምንመርጣቸው ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች አስደሳችነት የሆነ አቀራረብ መከተላቸው በተለይ ለኢአፈ-ፈት (ለሁለተኛ ቋንቋ) ተማሪዎች ልዩ የሆነ ጠቀሜታ እንዳላቸው ወንድወሰን (1995፣ 27) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፤

*በተለይ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን እንግዳና ከባድ አድርጎ በመቁጠር በትምህርቱ ሂደት ይገጥመናል ብለው የሚያስቡትን የአዋኪነት ፍራቻና ሥጋት አስወግደው ሀሴት እያገኙና ፍላጎት እያደረባቸው ይማሩ ዘንድ ስሜታቸውን ከጅምሩ ለማጥመድ ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች የሚኖራቸውን ጉልህ ፋይዳ አሌ ልንለው እንደማይገባ በአጽንኦት ለማስገንዘብ እንወዳለን።*

ባጠቃላይ ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ስራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ማዋል የቋንቋ ትምህርቱ አቀራረብ ማራኪና ተወዳጅ እንዲሆን ያደርጋል (Lazar 1993፣ 14) በተመሳሳይ የቋንቋውን የክሂልና የዕውቀት ዘርፎች (ሥነልሳንና ሥነጽሑፉን) ማሳካት ወይም ማከናወን የምንችለው ከመነሻ ላይ ተማሪዎቹ በሙሉ ተነሳሽነት፣ ያለማንም ጎትጓች ወደ ትምህርቱ መቅረብ ሲችሉ ነው። «ፍላጎትና ተነሳሽነት ከሌለ አንድ የትምህርት ሂደት ፍሬያማ ይሆናል ብሎ ማሰብ ዘበት ነው» (ወንድወሰን 1995፤25)። ስለዚህም የተነደፈውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሥነጽሑፋዊ ሥራ ማራኪነት ወይም አስደሳችነት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው።

## 2.2..3.3. ሥነልሳናዊ እና ሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን ለማጎልበት

*ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን* በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የምንገለገልበት ዓቢይ ዓላማ የክሂል ዘርፎችን ለማጎልበት መሆን እንዳለበት ከላይ እንደተገለጸው በርካታ ምሁራን የሚስማሙበት ነጥብ ቢሆንም ከዚሁ ጎን ለጎን ግን ተማሪዎች የዘይቤዎችን፣ የፊሊጦችን፣ የቃላትንና የሐረጋትን፣ አገባብ በአውድ እንዲረዱ በማስቻል፣ የሥነልሳን ዕውቀታቸውንም ሊያጎለብት እንደሚችል Chapman (1973)፣ Widdowson (1975)፣ ፣ Hill (1986)፣ Collie እና Slater (1987)፣ Meek (1995)፣ Mckay (1996)፣ ፈቃደ (1991)፣ ወንድወሰን (1995) እና በድሉ (1996) በዝርዝር ጽፈዋል። ከነዚህ ውስጥ ፈቃደ (1995፣112፣113) በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሥነጽሑፉን ሥነልሳናዊ ፋይዳ እንደሚከተለው ገልጸዋል፣

> *ተማሪዎች ሥነጽሑፋዊ ሥራን አንብበው የተፈለገውን ትርጉም ለማግኘት ሲጠያየቁና ሲወያዩ ስለቋንቋ ልዩ ልዩ ባሕርያት በራሳቸው ጥረት ይማራሉ፤ የቃላት ሀብታቸውን እንዴት ማዳበር እንደሚችሉ በጥረታቸው ይገነዘባሉ። ምን ዓይነት የዐረፍተነገርና የሐረጎች አመጣጠንና አሰዳደር (አወቃቀር) አንድ ሊተላለፍ የተፈለገን ትርጉም ይበልጥ አሳምሮ ሊያቀርብ እንደሚችልም በዚሁ ጥረታቸው መገንዘባቸው አይቀርም። የሥነጽሑፍ ሥራ ይህንን የሚያስረዳና የሚያስተምራቸው በቀጥታ አይደለም።*

ይህ የሥነጽሑፋዊ ሥራ ሥነልሳናዊ ፋይዳ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለአፈ-ፈት የቋንቋ ተናጋሪዎችም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው። አፈ-ፈት የሆኑ የቋንቋ ተናጋሪዎች ከሚያውቋቸው ቃላት ውስጥ 90 ከመቶ ያህሉን ያገኟቸው ከመዝገበ ቃላት ወይም በተናጥል ሳይሆን ከአውዳዊ አገባባቸው ነው። አንዳንድ እንግዳ ቃላት

ሲያጋጥማቸውም ትርጓሜያቸውን የሚገነዘቡት አውዳቸውን በመመልከት ነው። በመሆኑም ይህን የቃላትና የሐረጋትን ትክክለኛ አውድ የሚያገኙበት ማራኪነት ያለው፣ እውነተኛ የፈጠራ ስራ ያስፈልጋቸዋል። በዚህ ምክንያት የሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራን ለቋንቋ ማስተማሪያነት መገልገሉ ታላቅ ፋይዳ እንዳለው Hill (1986፣ 7-8) Fowler (1971) የተባሉ ጸሐፊን ጠቅሰው ያስረዳሉ።

የቃላትን እና ሐረጋትን ትርጓሜና አውዳዊ አገባብ ከኢልቦለዳዊ ጽሑፍም ማግኘት ይቻላል የሚል ሐሳብ ሊነሳ ይችላል። ነገር ግን «በአንድ የሥነጽሑፍ ስራ አማካኝነት ሊተላለፍ የተፈለገ መልዕክትና በአንድ ኢልቦለዳዊ (ተርታ) ጽሑፍ ሊተላለፍ የተፈለገ መልዕክት ለቋንቋ ማስተማሪያነት እኩል አያገለግሉም» (ፈቃደ 1991፣ 112)። ስለዚህም ሥነጽሑፋዊ ሥራ የሰዎችን ንግግር ቀጥተኛ በሆነ (በምልልስ) መንገድ ከማቅረቡም በተጨማሪ የተፈለገውን መልዕክት ለማግኘት ልዩ ልዩ ውይይትና ጥይይቅን የሚጠይቅ በመሆኑ ለቋንቋ ማስተማሪያነት ተመራጭ ያደርገዋል። እንደ Meek (1995፣6) ገለፃ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተማሪዎች የቃላትንና የሐረጋትን ተናጥላዊ ትርጓሜ እንዲረዱ ከማስቻላቸውም ባሻገር ሐሳባቸውን በሀላፊና በወደፊት ጊዜ አመልካች ዓረፍተነገሮችን ተጠቅመው እንዲገልጹ ያስችላቸዋል።

## ❖ በሥነጽሑፍ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ላይ የሚነሱ የተቃውሞ ሐሳቦች

በሥነጽሑፍ አማካኝነት ቋንቋን የማስተማር ሂደትን የሚቃወሙ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን የመከራከሪያ ነጥቦች በተመለከተ Mckay (1996፣ 191) የሚከተሉትን ለአብነት ጠቁመዋል፣

1. *ሁለተኛ ቋንቋን ስናስተምር ዋነኛው ዓላማችን ሰዋሰዋዊ ሕጎችን ማስተማር ነው። በአንዳንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከዕለት ተዕለት የመግባቢያ ቋንቋ ያፈነገጠ አጠቃቀም ስለሚከተሉና ሰዋሰዋዊ የመዋቅር ውስብስብነት ስለሚታይባቸው የሰዋሰው ሕጎችን ለማስተማር አያስችሉም።*
2. *ሥነጽሑፋዊ ጥናት ራሱን ችሎ ሊካሄድ የሚችል ተግባር በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የትምህርቱን ዓላማና ተግባር ለማሳካት ምንም ዓይነት አስተዋጽኦ የለውም።*
3. *ሥነጽሑፍ የታላሚው ቋንቋ ተናጋሪ ማኅበረሰብን (የአፈ-ፈት ተናጋሪዎችን) ባህላዊ ጉዳዮች (Cultural perspective) የሚያሳውቅ ነው። ይህም ለተማሪዎቹ ፍጹም አባድ ሊሆንባቸው ይችላል።*

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን የተቃውሞ ሐሳቦች ተጨባጭ ማስረጃ በማቅረብ የተሳሳቱ መሆናቸውን የሚያስረዱ ምሁራን አሉ። Hill (1986፣ 7) እነ Cairns (1976፣ 216 - 220) ያቀረቡትን ዋቢ አድርገው እንደገለጹት ተማሪዎች አፍመፍቻ ቋንቋቸውን በሚማሩበት (በሚለምዱበት) ጊዜ የሚያጠኑት የቋንቋውን ሕጎች ወይም የቃላትን ተናጥላዊ ትርጓሜ ሳይሆን የሚያዳምጡት ቋንቋ ከሚናገሩት ጋር ያለውን ዝምድና በመመርመር ነው። በመጨረሻም ስለቋንቋው ያላቸውን ግንዛቤ በአእምሮአቸው ይቀርጹታል ወይም ከራሳቸው ጋር ያዋህዱታል። Widdowson (1975፣ 83) በተመሳሳይ «በመጀመሪያ ደረጃ ሥነጽሑፋዊ ጥናት ማለት የቋንቋ አጠቃቀምን ማጥናት (Language use) ማለት ሲሆን ይህም ተግባር ቋንቋ ከመማር ሂደት ተለይቶ የሚታይ ሳይሆን የራሱ የቋንቋ ትምህርት ሂደት አንዱ አካል ነው» በማለት አስረድተዋል።

እንደ Chapman (1973፣ 49) ገለጻ፣ ሥነጽሑፍን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መገልገል ተማሪዎች የቃላትን አገባብ (syntax) ሆን ብለው (consciously) ካለገደብ እንዲማሩ ከፍተኛ እድል ይሰጣል። ይህ ነው ተማሪው አንድ ታላሚ ቋንቋን እንደ አፈ-ፈት ተናጋሪ ወይም አካባቢያዊ (Colloquial) ቋንቋ እንዲማር የሚያስችሉት። ስለዚህም Celce - Murcia (1993፣ 14-15) እንዳብራሩት ሥነጽሑፍ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ተጨባጭነት ያለው እውነተኛ የቋንቋ ማስተማሪያ መሣሪያ ነው የሚለው ሐሳብ በበርካታ የቋንቋ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ሀቅ ነው።

ባጠቃላይ ከላይ ለመጠቀም እንደተሞከረው በሥነጽሑፍ መሣሪያነት ቋንቋን የማስተማር ተግባርን የሚቃወሙ ወገኖች ቢኖሩም በሐገራችን የተካሄዱ ጥናቶች እና በርካታ ምሁራን በተጨባጭ ማስረጃ እንዳረጋገጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በማካተት ቋንቋን ለመማር-ማስተማር ተግባር መገልገል እጅግ አያሌ ፋይዳዎች አሉት።

### 2.2.3.4 ባህልን ለመማር (ለማወቅ)

በሥነፅሑፍ ቋንቋን ማስተማር ተማሪዎች የራሳቸውንም ሆነ የሌሎችን ባሕል እንዲገነዘቡ ያስችላል (Bretz 1990፣ 335-338)። በአንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ የቀረቡትን ባህላዊ ጉዳዮች መነሻ በማድረግም ተማሪዎቹ እርስ በርስ ውይይት፣ ክርክርና ጭውውት እንዲያካሂዱ በማድረግ ወይም ሐሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ በማበረታታት የቋንቋ ክሂሎችን እንዲያጎለብቱ ማድረግ ይቻላል። ይህን በተመለከተ-

Collie (1987:3) ሲያብራሩ፣ ሥነጽሑፍ የአንድ ማኅበረሰብ ነባራዊ ሐቅ አሻራ ነው። ስለዚህም ሥነጽሑፍ የማኅበረሰቡን ባህል፣ ወግና ሥርዓት ያስተዋውቃል፣ አጠቃላይ የቋንቋን ባሕርይ ያስረዳል፣ በሌላም በኩል ታላሚውን ቋንቋ የሚማሩትን ወገኖች የክሂል ዘርፎች ያጎለብታል።

ተማሪዎች ባህላዊ ጉዳዮችን በተለያዩ አጋጣሚዎች ሊማሯቸው ቢችሉም በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ግን በስፋት ሊገለገሉባቸው እንደሚችሉ በድሉ (1996፣ 8-9) የሚከተለውን ጠቁመዋል፤

> *ባህልን ከቤተሰብ መማር ይቻላል ከቤተሰብ የማይገኙት ባህላዊ እሴቶች ደግሞ በማኅበራዊ ተራክቦና በመደበኛ ትምህርት ይገኛሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ከሦስቱ (ቤተሰብ፣ሕብረተሰብ፣ ትምህርት) በአንዱ ቦታ ክፍተት ይፈጠራል። በዚህ ጊዜ ተማሪዎች ባህላቸውን ጠንቅቀው የማወቅ ዕድል ላይኖራቸው ይችላል። ሥነጽሑፍ ይህን ክፍተት ለመሙላት አይነተኛ መሣሪያ ነው። ተማሪዎች ከኅብረተሰብ ወይም ከመደበኛው የትምህርት ፕሮግራም የሚያጡትን ባህላዊ ዕሴት ከሥነጽሑፍ ያገኙታል።*

ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች ባህልን የማሳወቅ ጠቀሜታ አላቸው ሲባል የመጀመሪያው ዓላማቸው ባህላዊ ጉዳዮችን በማቅረብ የተማሪዎችን ስሜት ካጠመዱ በኋላ ተፈላጊውን የክህሎት እና የዕውቀት ዘርፎች ለማስተማር መሆን እንደሚገባው (Schulz 1981፣ 43-53) ጠቁመዋል።

ባጠቃላይ Lazar (1993፣ 14-15) ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ለቋንቋ ማስተማሪያነት የምንገለገልባቸውን ዓበይት ምክንያቶች ባጫጭሩ እንደሚከተለው ጠቁመዋል፤

- በመርሐትምህርቶች ውስጥ ከሚካተቱ ይዘቶች መካከል አንዱ ስለሆነ፣
- ተማሪዎች የራሳቸውንና የሌሎችን ባህሎች እንዲያውቁ ስለሚያደርግ፣
- የተማሪዎችን የአተረጓጎም ብቃት ስለሚያጎለብት፣
- በተማሪዎች ዘንድ የደስታና የሳቅ ሥሜትን ስለሚፈጥር፣
- ታላቅ ጠቀሜታ ያለውና ላቅ ያለ ደረጃ ላይ የሚገኝ የፈጠራ ሥራ ውጤት በመሆኑ፣
- የተማሪዎች ቋንቋን የመማር ተነሳሶት ስሜትን ስለሚጨምር፣

- ተማሪዎች የራሳቸውን ሐሳብና ሥሜት (Opinions and feelings) እንዲናገሩ ስለሚያበረታታ ነው፤

የሚሉት ይገኙበታል።

ስለዚህም ሥነጽሑፋዊ ሥራ ቋንቋን ለማስተማር ከፍተኛ ፋይዳ አለው። ይጠቅማል የሚባለው የቃላትን፣ ሐረጎችን እና የዓረፍተነገሮችን አሰካክ እና ባሕሪያቸውን ለማስተማር (ለመማር) ስለሚረዳ እንዲሁም ዘይቤአዊ፣ ምሳሌአዊና ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በአውዳቸው ስለሚያቀርብ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ሥነጽሑፋዊ ሥራ የክሂል ዘርፎችን ከማጎልበቱም በላይ አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ የሥነጽሑፍ ጥናትና ትችት ማነበራዊ፣ ታሪካዊ፣ ሥነልቦናዊ፣ ፖለቲካዊና ምግባራዊ ዳራን በዐውድ እያስገባ ስለሚተነትን ኢርቱዐ በሆነ መንገድ ለተማሪዎቹ ተጨማሪ ዕውቀትን ሊሰጥ እንደሚችል ፈቃደ (1991፤112) እና Bearne (1996፤318) ገልፀዋል።

## 2.3. ቋንቋን ለማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ

በክፍል ውስጥ የሚከናወነውን የቋንቋ ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ጉዳዮች አሉ። እነዚህን መሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ያስፈሯቸውን ከዚህ ቀጥሎ ለመመልከት እንሞክራለን፤

Lazar (1993፣ 52)፣ ሥነጽሑፋዊ ሥራን ቋንቋን ለማስተማር ተግባር ለማዋል ከመምረጣችን በፊት የሚከተሉትን ሦስት ዓበይት ነጥቦች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንዳለብን ጠቁመዋል፤

- *የተማሪዎችን ባህላዊ ዳራ ፣*
- *የተማሪዎች ሥነልሳናዊ ተክህኖ እና*
- *የተማሪዎች ሥነጽሑፋዊ ዳራ ናቸው።*

ከነዚህ ከተጠቀሱት በተጨማሪ ተከታዮቹ ነጥቦች በተጓዳኝነት መታየት እንዳለባቸው ከላይ የተገለጹት ምሁር አክለው ገልፀዋል።

- *ሥነጽሑፋዊ ሥራው በበቂ መጠን መገኘቱ፣*
- *የሥነጽሑፋዊ ሥራው ርዝማኔ ፣*
- *ተተግባሪነት*
- *ከመርሐትምህርት ጋር መጣጣም*

በሌላ በኩል Brumfit እና Carter (1986፣ 189) ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የሚከተሉትን ስድስት መሠረታዊ መሥፈርቶች ማሟላት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፤

- ሥነልሳናዊ ደረጃ
- ባሕላዊ ዳራ
- ርዝማኔ
- ሥነትምህርታዊ ጠቀሜታ
- ላቅ ያለ ደረጃ

እነዚህ መስፈርቶች በሥነጽሑፍ እንግሊዝኛን ለማስተማር የቀረቡ ቢሆኑም ለማንኛውም ቋንቋ ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ከላይ የተገለጹት ምሁራን ገልጸዋል። እነዚህን በተናጠል የቀረቡትን የሥነጽሁፍ ሥራ መምረጫ መስፈርቶች ምንነት በተመለከተ በተከታዩ ክፍል ለመመልከት እንሞክራለን።

### 2.3.1. የቋንቋ ትምህርቱን ዓላማ የሚያሳኩ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከሁሉም በፊት የትምህርቱን ዓላማ የሚያስቀድሙ መሆን ይኖርባቸዋል። Brumfit እና Carter (1996፣ 190) እንደገለጹት፣ አንዳንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውበትና ማራኪነት ያላቸው እንዲሁም በተማሪዎቹ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኙ ሆነው በአንባሩ ከትምህርቱ መጨረሻ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ የማያሳኩ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህን በተመለከተ ወንድወሰን (1995፣ 27) የሚከተለውን ብለዋል፤

> *ቋንቋን ለማስተማር የሚቀርቡ (የሚመረጡ) ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች አመለኛ ፈረስን አታሎ ለመያዝ፣ ለልሶሽ (ለምግብነት) እንደሚቀርብ ጨው አይደለም- ፈረሱ ከተያዘ በኋላ የሚወረወር ጨው ዓይነት። ተማሪውን አባብለው ካቀረቡ በኋላም የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚበጅ የቋንቋ ትምህርት ጥሬ ነገር የሚይዙ መሆናቸው መዘንጋት የለበትም። ተማሪው የቋንቋውን ክሂሎች ለማዳበርም ሆነ የሥነልሳንና የሥነጽሑፍ ዕውቀት ለማግኘት የሚችልባቸው ሁነኛ ይዘቶች ናቸው።*

ስለዚህም ለየክፍል ደረጃው የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተቀዳሚ ዓላማ ተማሪዎቹ በይዘቶቻቸው እንዲማረኩ ወይም ሥነጽሑፋዊ ይዘቶቹን ተረድተው ከክፍል ውጭ በተግባር እንዲያውሏቸው ሳይሆን፣ በመርሐትምህርቱ ውስጥ የተጠቆሙትን ዓላማዎች እውን የሚያደረጉ ሊሆን ይገባል። Brumtit እና Carter (1996፣ 190) እንዳስረዱት፣ ለምሳሌ የቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ የሚያተኩረው የንባብ ክሂልን

ለማሳልበት ከሆነ ምርጫችን የግድ በአጭር ልቦለድና በግጥም ላይ ብቻ መገደብ የለበትም። ስለዚህም ማንኛውንም ዓይነት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን መምረጥ እንችላለን። በአንዳሩ የቋንቋ ትምህርቱ ዓላማዎች የንግግር፣ የማዳመጥና የመጻፍን ክሂሎች ለማጐልበት ከሆነ የሚመረጡት ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ መሆን ይኖርባቸዋል።

በሌላ በኩል ተማሪዎቹ ከትምህርቱ መጨረሻ እንዲያዳብሩት የተፈለገው ችሎታ ፈሊጣዊ ወይም ምሳሌያዊ ንግግሮችን በአውዳቸው ተረድተው በዕለት ተዕለት የቋንቋ አጠቃቀማቸው ላይ በተግባር እንዲያውሉ ቢሆንና በአንዳሩ የመረጥነው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከተማሪዎቹ ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ሆኖ፣ ነገር ግን ፈሊጦችን ወይም ምሳሌያዊ ንግግሮችን ያላካተተ ከሆነ፣ የተነደፈውን ዓቢይ የትምህርት ዓላማ ለማሳካት አይችልም። ስለዚህም የምንመርጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን ለማዘጋጀት የሚያስችለን መሆንና አለመሆኑን አስቀድመን መጠየቅ አለብን። ይህን በተመለከተ በድሉ (1996፣ 16) የሚከተለውን ጠቁመዋል፤

> *ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚቀርብ የሥነጽሑፍ ሥራ ይዘትን ያገናዘበ መሆን አለበት። እዚህ ላይ ይዘት ብለን የምናተኩርበት የተመረጠውን የሥነጽሑፍ ሥራ ጭብጥ አይደለም። በዚህ አውድ ይዘት ስንል ሥራው የቀረበበትን ቋንቋ ማለታችን ነው። ለተወሰነ ደረጃ የሚቀርብ የሥነጽሑፍ ሥራን ከቀረበበት ቋንቋ ይዘት አንፃር በምንመርጥበት ጊዜ ማነፃፀሪያ የሚሆነን ለደረጃው የተዘጋጀው ማስተማሪያ መሣሪያ ይዘትና የተነደፈው የትምህርት ዓላማ ነው። ስለዚህ ወደምርጫ ከመግባት አስቀድመን ከትምህርቱ መጨረሻ «ተማሪዎች እንዲያዳብሩት የተፈለገው ችሎታ ምንድነው?» የሚለውን አጠቃላይ ጥያቄ መጠየቅ ያሻል።*

ባጠቃላይ ከላይ በምሁራኑ ከቀረቡት ዝርዝር ሐሳቦች የምንገነዘበው፣ አንድን ሥነጽሑፋዊ ሥራ በአንድ የተወሰነ የክፍል ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ከመምረጣችን በፊት የትምህርቱን ዓላማ በጥልቀት በመመርመር ይህን ዓላማ ሊያሳኩልን የሚችሉትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በጥንቃቄ መምረጥ እንደሚኖርብን ነው።

### 2.3.2. ከመርሐትምህርቱ ትልም ጋር የሚጣጣሙ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከመርሐትምህርቱ ትልም ጋር የሚጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል (በድሉ 1996፣ 16)። ይህ ሃሳብ በንዑስ ክፍል 2.3.1 ላይ ከቀረበው ሐሳብ ጋር የሚመሳሰል ጉዳይ ቢመስልም ልዩነት ግን አላቸው። ምክንያቱም በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የምናካትታቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን የሚያሳኩ ሆነው በአንጻሩ በመርሐትምህርቱ ላይ ያልሰፈሩ ወይም የተለየ አካሄድን የተከተሉ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። ከዚህ አንባር Lazar (1993፣ 55) የምንመርጣቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከመርሐትምህርቱ ጋር መጣጣማቸውን ለማረጋገጥ የሚከተሉትን ሁለት መሠረታዊ ጥያቄዎችን መመለስ እንዳለብን ገልጸዋል፤

1. *የምንመርጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከመርሐትምህርቱ ጋር በምን መልኩ ይገናኛል? በጭብጡ? በቃላት ትምህርት? በሰዋሰዋዊ ትምህርት? በፈሊጣዊ አነጋገር? በምሳሌያዊ አነጋገር? ወዘተ.*
2. *በመርሐትምህርቱ ላይ የተጠቆመውን የማስተማር ሥነዘዴ ተከትሎ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን ማውጣት ይቻላልን?*

የሚሉት ናቸው።

ስለዚህም Hill (1986፣ 15) እንዳስረዱት፣ መምህራን ወይም የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች የሚመርጧቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መርሐትምህርቱን (syllabus) ማዕከል በማድረግ ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ችሎታ፣ ከሥነጽሑፋዊ ሥራው ሥነልሳናዊ ክብደትና ቅለት እንዲሁም ተማሪዎቹ ምንባቡን አንብበው ለመረዳት ካላቸው ዳራዊ ዕውቀት አንባር ተገቢነታቸው በጥንቃቄ ተፈትሾ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል።

### 2.3.3. ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ተገቢነት ያላቸው

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሚዛናዊነታቸውን በጠበቀ መልኩ ከተማሪዎቹ እድሜ፣ ፍላጎት ዓላማ እና የአእምሮ ብስለት ጋር የሚጣጣሙ መሆን ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ የተወሰኑት ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች ለህፃናት የሚሆኑ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በተመሳሳይ ለታዳጊ ወጣቶች እና ለጎልማሶች የሚሆኑ ተመጣጣኝ ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች ይኖራቸዋል። በመሆኑም-

በየደረጃው የሚገኙትን ተማሪዎች ማንነት ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርብናል። ለምሳሌ ርዕሰ-ጉዳዩ ለጎልማሶች የሚመጥን ነገር ግን ቋንቋው በጣም ቀላል የሆነ ሥነጽሑፋዊ ሥራን ለሕፃናት ወይም ለወጣቶች ብናቀርበው ተገቢነት የለውም (Hill 1986, 18)። ተማሪዎቹም የቀረበውን ሥራ በገጉትና በመሉ ፍላጎት የሚከታተሉት በሚቀርበው ሥራ ውስጥ የራሳቸውን ማንነት ሲመለከቱ ወይም ገጸባሕርያቱ በእነሱ የእድሜ ደረጀ ላይ የሚገኙ ሲሆኑ ነው። ባጠቃላይም ከራሳቸው (ከተማሪዎቹ) ሕይወት ጋር የተሳሰረና ማራኪ አቀራረብን የተከተለ ሊሆን ይገባል። ይህን በተመለከተ ወንድወሰን (1995፣ 26) የሚከተለውን ብለዋል፤

> *ቋንቋን ለማስተማር የሚመረጠ ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ተማሪውን ገና ከጅምሩ ያጠምዳታል። የሚያጠምዱት በግድ አይደለም በማባባል ነው በባሕሪያቸው ባላቸው የኩሸት ኃይል። የሚኒሸው የተማሪውን ስሜት የሚያባብለውና የሚማርከው ከሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ምልዐት ማስገኛ ልዩ ልዩ አካላት (ingredient elements) የሠመረ ቅንጅት የሚሰርፀው ውበታቸው (ለዛቸው) ነው። የምናባዊ ሥነጽሑፍ መለያዎች ካልናቸው ዓበይት ባሕርያት መካከል አንዱና ቀዳሚው ይኸው ውበቱ ነው።*

ይህ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ማራኪነት፣ ለዛና ውበት ጎልቶ ሊወጣ የሚችለው ከተማሪዎቹ ፍላጎት፣ የእድሜ ደረጃ፣ ዝንባሌ እና የአእምሮ ብስለት ጋር የሰመረ ግንኙነት ሲኖረው ነው። ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጀ የሚመጥኑ ከሆኑ የምንመርጣቸው ሥራዎች የግዴታ ታላላቅ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች (Greet literature) የሚባሉ መሆን አይጠበቅባቸውም። ነገር ግን ተመሳሳይ አቀራረብን ተከትለው ተማሪዎቹን እንዳያሰለቹ ወቅታዊ ታሪኮችንና ፈርጀ-ብዙ ገፀባሕርያትን የያዙ ልዩ ልዩ ሥራዎችን ማካተት እንዳለብን Hill (1986፣ 18) በመግለጽ፣ የሚከተሉትን መጠቀም እንደሚቻል በምሳሌነት (በአማራጭነት) ጠቁመዋል፤

1. *ግጥም*
2. *አጫጭር ልቦለዶች*
3. *ድራማዎች/ ተውኔቶች*
4. *ሳይንሳዊ ልቦለዶች*
5. *የጀብድ ታሪኮች*
6. *ሰብዓዊ ስሜት ያዘሉ ታሪኮች*

እነዚህን እና ሌሎች ቃላዊም ሆኑ ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያነት አፈራርቆ መጠቀሙ ተማሪዎቹ እንዳይሰለቹ ይረዳል። ባጠቃላይ ከነዚህ ማብራሪያዎች እንደምንረዳው ቋንቋን ለማስተማር የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተማሪዎቹን የክፍል ደረጃ ማለትም ፍላጎት፣ ዝንባሌና የአእምሮ ብስለት ወይም ዕድሜ ያገናዘቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

### 2.3.4. የተማሪዎቹን ሥነልሳናዊ ተክህኖ ዳራ ያገናዘቡ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጥ ሥነጽሑፋዊ ሥራ የቃላትና የዘይቤ ምርጫው እንዲሁም የሰዋሰዋዊ መዋቅሩ ከተማሪዎቹ ሥነልሳናዊ ግንባቤ ጋር የተገናዘበ ሊሆን ይገባል። Hill (1986, 19) እንደገለጹት፣ ተማሪዎች አስቸጋሪ የሆኑ ቃላትና የዐረፍተነገር መዋቅሮችን ለመረዳት እንቅፋት የሚገጥማቸው ከሆነ በቀረበላቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ሊደሰቱና ሊረኩ ካለመቻላቸውም በተጨማሪ የምንባቡን አጠቃላይ ጭብጥ ወይም ታሪክ ለመረዳት ይቸገራሉ። ስለዚህም ሥነጽሑፋዊ ሥራውን ስንመርጥ የሚከተሉትን ነጥቦች በአእምሮአችን ልናስተውላቸው ይገባል፤

1. *የቃላቱ ክብደት እና የሥነጽሑፋዊ ሥራው ሰዋሰዋዊ መዋቅር ከተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት ጋር የተጣጣመ መሆን እንዳለበት፣ እንዲሁም፣*
2. *በተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ የሚገኙት የአራዳ ቋንቋ ቃላት (slangs)፣ ዘዬዎች (dialect)፣ ፈሊጣዊ አነጋገሮች፣ ዘይቤአዊ አገላለጾች፣ ወዘተ. በብዛት አለመገኘታቸውን፣*

ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

በርግጥ ዘዬያዊ ቃላት፣ የአራዳ ቋንቋ ቃላት እና ዘይቤዎች መኖራቸው መቼቱንና የታሪኩን ዳራዊ ገጽታ ለማሳየት ቢረዱም የሚከተሉት ሁለት መሠረታዊ ጉዳቶችን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ Hill (1986፣ 20) ያስረዳሉ። እነዚህም፡- አንደኛ ታላሚውን ቋንቋ የሚማሩት ተማሪዎች የሚገኙበት አካባቢ የቋንቋው አፈ-ፈት ተናጋሪዎች ከሚገኙበት ሥፍራ እጅግ የራቀ ከሆነ፣ ተማሪዎች ቃላቱንም ሆነ ሰዋሰዋዊ መዋቅሩን ለመረዳት ይቸገራሉ። ሁለተኛ የተሳሳቱ ሥነልሳናዊ ሞዴሎችን (linguistic models) ሊያቀርብላቸው ይችላል። በዚህ ምክንያት ተማሪዎቹ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ውስጥ የሚያገኟቸውን አካባቢያዊ ዘዬዎችና የአራዳ ቋንቋ ቃላት እንደ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም ወስደው ሊገለገሉባቸው ይችላሉ። በእርግጥ በምንባቡ ውስጥ የሚገኙት ዘዬዎች፣ የአራዳ ቋንቋ ቃላትና ዘይቤአዊ አገላለጾች ጥቂት ከሆኑ ተማሪዎቹ ከመምህራናቸው እገዛ ሊደረግላቸው ይችላል። በጣም በርካታ ከሆኑ-

ግን የንባብ ፍላጎታቸው ሊቀንስ ወይም ለነሱ ወደማይጠቅም አላስፈላጊ ምርምር ሊመሯቸው ይችላሉ። ከዚህም ባሻገር ዘይቤአዊ አገላለጾች ከቃላቱ ተናጠላዊ ፍች የተለየ ትርጓሜ ሊኖራቸው ስለሚችል ተማሪዎች በተሳሳተ መንገድ ሊተረጉሟቸው ወይም ፍጹም ላይገነዘቧቸው ይችላል።

Lazar (1993፣ 53) እንዳስረዱት፣ ተማሪዎቹ በአንድ ቋንቋ (በታላሚው ቋንቋ) የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኙና ከቋንቋው አፈ-ፈት ተናጋሪዎች ጋር በቀላሉ ተግባቦትን የሚፈጥሩ ሊሆኑ ይችላሉ። በአንዛሩ የቀረበላቸውን ሥነጽሑፋዊ ሥራ አንብበው ለመረዳት ሊሳናቸው ይችላል። ለዚህም ምክንያቱ ተማሪዎቹ የቋንቋው አፈ-ፈት ተናጋሪዎች ከሚገኙበት ሥፍራ እጅግ ርቀው የሚገኙ ሊሆኑ ስለሚችሉ ነው። በዚህም ምክንያት በታላሚው ቋንቋ ውስጥ የሚገኙትን ዘይቤአዊ፣ ቅኔያዊ፣ ፊሊጣዊ እና ምሳሌያዊ የአነጋገር ስልቶችን እንዲሁም ሞያዊ የሆኑ ቃላት (ለምሳሌ የህግ ቃላት) እና ዘዬአዊ (dialect) አገላለጾች የሚገኙበትን አንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ አንብበው መረዳት ሊያዳግታቸው ይችላሉ።

እነዚህ ከላይ የተገለጹትን ችግሮች ለመቅረፍ የሚከተሉትን ሁለት ነጥቦች ትኩረት ልንሰጣቸው እንደሚገባ Hill (1986፣ 19) ያስገነዝባሉ፤

*ሀ. ዘዬያዊ እና የአራዳ ቋንቋ ቃላትን የመሳሰሉ አስቸጋሪ ቃላትና ሐረጋት በአንድ ምንባብ በመቶ ቃላት ውስጥ ከአንድ ወይም ከሁለት እንዲበልጡ በማድረግ፣ የአብዛኞቹን እንግዳ ቃላት ትርጓሜ ተማሪዎች በቀላሉ ከአውዳቸው እንዲረዷቸው ማስቻል፣ ውስብስብ የሆነ ሰዋሰዋዊ መዋቅር አለመኖሩን ማረጋገጥ፣*

*ለ. ፍሰቱን የጠበቀ ምንባብ ወይም ውህድ አሀድ ማቅረብ። ተማሪዎቹ እያንዳንዱ የምንባቡ ዓረፍተ ነገርም ሆነ አንቀጽ የተያያዘና ተከታታይነት ያለው መሆኑን እንዲረዱ ማስቻል። ይህን የታሪኩን ፍሰት የሚጠብቁልን አያያዥ ቃላትና ሐረጋት ለምሳሌ፦ ቢሆንም፣ ስለዚህ፣ በዚህም ምክንያት፣ ወዘተ. በተገቢው ቦታ መኖራቸው ማረጋገጥ ያሻል። ይህ ተግባራዊ ከሆነም ተማሪዎቹ በተናጥላዊ የቃላት ትርጓሜ ላይ ከማተኮር ይልቅ፣ በአጠቃላይ የታሪኩ መዋቅር ላይ እንዲያረተኩሩ በማድረግ በስተመጨረሻ ላይ ለሚካሄደው ውይይት፣ ክርክር፣ ሐሳብን በጽሑፍ መግለጽና ልዩ ልዩ ተግባራት ዝግጁ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል።*

ባጠቃላይ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የምንመርጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከተማሪዎቹ ሥነልሳናዊ ተክህኖ አንፃር ተገቢነት ያለው መሆንና አለመሆኑን ለማረጋገጥ-

የሚከተሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት መልስ መሻት እንዳለብን Lazar (1993፣ 53-54) ጠቁመዋል፤

- *በዚህ በተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ የተካተተውን የቋንቋ አጠቃቀም ተማሪዎቹ በአውድ ውስጥ በበቂ ሁኔታ ተለማምደውታል? ወይም ይጠቀሙበታል?*
- *በተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ ከሚገኙት ቋንቋ (ቃላት) ውስጥ ምን ያህሉን በቀላሉ ሊገነዘቡት ይችላሉ?*
- *ተማሪዎቹ ይህን የሚቀርበውን ሥነጽሑፋዊ ሥራ ማንበብ አስደሳች ወይም ጠቃሚ ነው ብለው ሊቀበሉት ይችላሉን? ወይስ በቋንቋው አስቸጋሪነት ምክንያት የንባብ ተነሳሽነታቸው ሊቀንስ ይችላል?*
- *ምንም እንኳ የተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ወይም ውህድ አሀድ (text) ቋንቋውን ለመረዳት እጅግ አስቸጋሪ (extremely difficult) ቢሆንም ተማሪዎቹ በሌሎች ውጫዊ ምክንያቶች የንባብ ጉጉታቸውን ሊጨምር ይችላል፣ ለምሳሌ በአንድ በሚወዱት ወይም በሚያውቁት ታሪክ (ፊልም) ላይ ተመስርቶ የቀረበን አጭር ልቦለድ ቋንቋው አስቸጋሪ ቢሆንም ለማንበብ ይጓጓሉ።*
- *በመጨረሻም በሥነጽሑፋዊ ሥራው የቀረበው የቋንቋ አጠቃቀም ተማሪው ቋንቋው መማር ከሚፈልግበት ዓላማ ጋር የተገናዘበ ነውን? ሊጠቀመውስ ይችላልን?*

የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው።

ባጠቃላይ ከላይ በተለያዩ ምሁራን ከተሰጡት ማብራሪያዎች የምንገዘበው ለቋንቋ ማስተማሪያነት በምንመርጣቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ የተማሪዎቹን የንባብ ሂደት የሚያደናቅፉ እንደ ዘዬያዊ ቃላት፣ መደያዊ ቃላት፣ የአራዳ ቋንቋ ቃላት፣ ያልተለመዱ ፊሊጣዊ፣ ምሳሌያዊ፣ ቅኔያዊና ዘይቤአዊ የአገላለጽ ስልቶችን በብዛት የያዙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን መምረጡ አላስፈላጊ እንደሆነ ነው። ይህ ማለት ግን ፍጹም መገኘት የለባቸውም ማለት እንዳልሆነ Hill (1986፣ 20) ገልጸዋል። ስለዚህም በመጠኑ ብንጠቀምባቸው ከመምህራናቸው በሚደረግላቸው ድጋፍ መሠረት ለተማሪዎቹ አካባቢያዊ መቼቱን በመፍጠር ምስል የመከሰት ኪነጥበባዊ ፋይዳ ሊኖራቸው ይችላል።

### 2.3.5 የተማሪዎቹን የሥነጽሑፍ ዳራዊ ዕውቀት ያገናዘቡ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጥ ሥነጽሑፋዊ ሥራ የተማሪዎቹን የሥነ-ጽሑፍ ዳራዊ ግንዛቤ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል። እንደ Hill (1986፣ 23) ገለጻ በሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች መዋቅራዊ የአጻጻፍ ስልት ውስጥ በደራሲያን የሚዘወተረው ከተለምዷዊው የቃላት ቅደምተከተላዊ ስደራ ማፈንገጥ ነው። ይህ የቃላትን ቅደምተከተላዊ ስደራ ማቀያየር ስልት በአብዛኛው በግጥም ውስጥ ዜማና ምጣኔን ለመጠበቅ ሲባል ተዘውትሮ የሚታይ ቢሆንም በአጭርና ረዥም ልቦለዶችም ውስጥ ለአንድ ለተወሰነ ሥነጽሑፋዊ ዓላማ ሊያገለግል ይችላል። ለምሳሌ በአንድ አጭር ልቦለድ ውስጥ «ልጅቷ መጽሐፍ እያነበበች ነበር- አባቷ የቤታቸውን በር ሲያንኳኩ» የሚል ዓረፍተ ነገር ቢኖር ምናልባት ተማሪዎች ይህን የአጻጻፍ ስልት አስቀድመው የማያውቁት ከሆነ፣ ምን ማለት እንደሆነ ላይረዱት ወይም በተሳሳተ መንገድ ሊተረጉሙት ይችላሉ። ስለዚህም እነዚህን መሰል ያፈነገጡ መዋቅራዊ ስደራዎች የተከተሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ለቋንቋ ማስተማሪያት ከመምረጣችን በፊት የተማሪዎቹን ሥነጽሑፋዊ የቀደመ እውቀት ልንፈትሽ ይገባል።

Lazar (1993፣ 54) እንዳስረዱት በተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዳራ እና በሥነልሳናዊ ተክህኖአቸው መካከል አስገራሚ የሆነ ግንኙነት አለ። ሁለቱም አንድ ላይ የማይሄዱ ሊሆኑ ይችላሉ። ለምሳሌ ተማሪዎቹ አስቀድመው የተለያዩ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ያነበቡ ከሆኑ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የቀረበው ምንባብ እንግዳ ቃላት ቢበዙበትም (ለምሳሌ፡- የፍቅር ቋንቋ Romantic language) ሊረዱት ይችላሉ። ለዚህም የሚረዳቸው ሥነጽሑፋዊ ግንዛቤአቸው ነው። በአንጻሩ ስነጽሑፋዊ እውቀታቸው አነስተኛ ሆኖ ነገር ግን ሥነልሳናዊ ብቃታቸው ከፍ ያለ ተማሪዎች እያንዳንዱን በሥነጽሑፋዊ ሥራው ውስጥ ያሉትን ቃላት በተናጥል ሊያውቋቸው ቢችሉም አጠቃላይ ታሪኩን ግን ላይገነዘቡት ይችላሉ። ስለዚህም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የምንመርጠውን ሥነጽሑፋዊ ሥራ የቋንቋ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ሥነጽሑፋዊ ባሕሪውን ከተማሪዎቹ ግንዛቤ አንፃር ልንመረምረው ይገባል። ምክንያቱም የአንዳንድ ደራሲያን ሥራዎች በቋንቋ አጠቃቀማቸው በጣም ቀላል ሆነው ሥነጽሑፋዊ አንደምታቸውን ለመረዳት ግን ጥልቅ እውቀትን የሚሹ ሊሆኑ ይችላሉ።

በሌላ በኩል እንደ Hill (1986፣ 16) ገለጻ የተማሪዎቹ የሥነጽሑፍ ዳራዊ ግንዛቤ ከንባብ ፍጥነታቸው ጋር የተያያዘ ነው። ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ውህድ አሀዶች (texts) ተማሪዎቹ ለመረዳት የሚችሉት ተጠየቃዊ በሆነ ፍጥነት፣ ካለድካምና-

የመሰላቸት ስሜት በፍጥነት ማንበብ ሲችሉ ነው። ይህ የንባብ ፍጥነታቸው በደቂቃ ውስጥ ከ200-250 ቃላት ወይም ከዚያ በላይ በሆነ ፍጥነት ማንበብ ሲችሉ ነው አጠቃላይ የውህድ አሀዱን ትርጉም በቀላሉ ሊገነዘቡት የሚችሉት። ምክንያቱም ተማሪዎቹ በፍጥነት ማንበብ መቻላቸው በቃላቱ ተናጥላዊ ፍች ላይ ሳይሆን በአጠቃላዩ የምንባቡ ይዘት ላይ እንዲያተኩሩ ይረዳቸዋል። በአንባሩ የተማሪዎቹ የንባብ ፍጥነት በዝግታ ከሆነ፣ አጠቃላይ ታሪኩን ለመረዳት ስለሚቸገሩ፣ ተከታዮቹን ተግባራት ለማከናወን ይሳናቸዋል።

ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን በፍጥነት ማንበብ የሚችሉ ከሆነ የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ሊያገኙ እንደሚችሉ Hill (1986፣ 17) ገልጸዋል፤

- በቃላት የተገለጸው ሐሳብ በአእምሮአቸው ውስጥ ምስል ይከስትላቸዋል፤
- በቀረበው ውህድ አሀድ የተሰማቸውን ስሜት በቃላት መግለጽ ወይም በቀረበው ታሪክ ውስጥ ባሉት ገፀባህርያት ማዘን- መደሰታቸውን፣ ድጋፍ- ተቃውሟቸውን፣ ንዴት- ብስጭታቸውን፣ ወዘተ. ሊገልጹ ይችላሉ።
- የገፀባህርያቱን ማንነትና ተነሳሱት ስሜት ለመረዳት ይችላሉ፤
- በአነበቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራ ላይ ሂሳዊ አስተያየት መስጠት ይችላሉ፤
- በውህድ አሀዱ (ሥነጽሑፋዊ ሥራው) እና በፀሐፊው መካከል ያለውን መስተጋብር መመርመር፣ የፀሐፊውን አመለካከት እና ዓላማ ማወቅ፣ እንዲሁም ምንባቡ ቁምነገር አዘል መሆን-አለመሆኑን መረዳት ይችላሉ።

ነገር ግን የሚመረጡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በፍጥነት እንዲያነቧቸው ተማሪዎቹ በአእምሮአቸው ውስጥ ካለው ፍላጎት ጋር የሰመረ መሆን ይኖርባቸዋል። የምንመርጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከተማሪዎቹ ዳራዊ ግንዛቤ ጋር ተመጣጣኝ መሆን-አለመሆኑን ለመለየትም ብርቱ ጥንቃቄ የሚፈልግ ጉዳይ መሆኑን Brumfit እና Carter (1986፣ 189) ይገልጻሉ። የሥነጽሑፋዊ ቃላትን ክብደትና ቅለት ሊመዝንልን (ሊለካልን) የሚችል ግልጽ መስፈርት አናገኝም። ስለዚህም የአንዳንድ እውቅ ደራስያን ወይም ገጣምያን ሥራዎች ሥነልሳናዊ አቀራረባቸው ቀላል ሆኖ በአንባሩ አንዳንድ ሥነጽሑፋዊ ቃላትን ለመረዳትና መልእክቱን ወይም አጠቃላይ ታሪኩን ለመገንዘብ እጅግ አስቸጋሪ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዳራ ልዩ ትኩረት ልንሰጥ ይገባል።

ሌላው ከተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዳራ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ የሥነጽሑፋዊ ሥራው ሥልታዊነት ደረጃ (Stylistic Level) እንደሆነ Hill (1986፣ 22-23) በመጠቆም የሥልትን ምንነት ሲያስረዱ ሥልት ማለት «ተገቢውን ቃል-

በተገቢው ሥፍራ መጠቀም ነው::» የሚለው ብያኔ በተለያዩ ጸሀፍት ዘንድ የተለመደ ቢሆንም ዘመናዊው ንድፈሐሳብ እንደሚጠቁመን ግን የደራስያን የአፃፃፍ ሥልት የሰዋሰው ስርዓትን ሊከተል ወይም ሊጥስ እንደሚችል በመግለጽ ተማሪዎቹ እነዚህን የደራሲያን የአፃፃፍ ሥልት ያስገኙትን ሥነልሳናዊ መዋቅሮች ማወቅ እንደሚኖርባቸው ያሳስባሉ::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ Hill (1986፣2) ፣ Rodger (1983፣ 53) የተባሉ ፀሐፊን ጠቅሰው ሲገልጹ፣ ተማሪዎቹ አንድን ሥነጽሑፋዊ ሥራ አንብበው ለመረዳት የአፃፃፍ ስልቱን ካልተረዱ የማይሞከር ጉዳይ መሆኑን በመጠቆም፣ አንድን ግጥምም ሆነ ልቦለዳዊ ሥራ ለመረዳት የአፃፃፍ ሥልቱን በተመለከተ ዳራዊ ግንዛቤ እንደሚያስፈልጋቸው ያስረዳሉ:: ይህ ዳራዊ ግንዛቤ ሊኖራቸው የሚችሉ ተማሪዎች የተለያዩ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን የማንበብ ልምድ ያላቸውና አጠቃላይ የሆነ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን የአፃፃፍ ስልት እንዲሁም የተለያዩ የቃላትና የመዋቅር አጠቃቀም ሥልቶችን የተረዱ ተማሪዎች መሆናቸውን አስረድተዋል::

ባጠቃላይ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የምንመርጣቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ የሥነልሳን ዳራዊ ግንዛቤ ጋር የሚጣጣሙ ሲሆኑ ነው የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ማድረስ የምንችለው:: ስለዚህም አንድን ሥነጽሑፋዊ ሥራ ስንመርጥ ተማሪዎቹ ከአሁኑ በፊት የሥነጽሑፋዊ ዕውቀት ያላቸው መሆንና አለመሆኑን በቀደሙት የክፍል ደረጃ ላይ የተማሩባቸውን የመማሪያ መጻሕፍት በመመርመር ወይም ጽሑፋዊ መጠይቅና ቃለመጠይቅ በማቅረብ ማረጋገጥ ብንችል የተሻለ ይሆናል::

## 2.3.6. የተማሪዎችን ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ዳራ ያገናዘቡ

በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎች የተለያዩ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራ ካሏቸው ማኅበረሰቦች የተውጣጡ ሊሆኑ ይችላሉ:: በአንባሩ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይህን ማኅበረሰባዊ ልዩነቶች የሚያበላልጡ ሳይሆን ልዩነትን በማስወገድ ሁሉንም በእኩል ዓይን የሚመለከቱ ቢሆኑ ይመረጣል:: እንደ Lazar (1993፣53) ገለፃ፣ የምንመርጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከተማሪዎቹ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ዳራ ጋር ምን ያህል የራቀ ወይም የቀረበ እንደሆነ መመርመር ይኖርብናል:: ለተማሪዎቹ ባህላዊ ዳራ በጣም የቀረበ ወይም የራቀ ከሆነ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ ሊኖረው ይችላል:: ለምሳሌ በተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ ከተማሪዎቹ ባሕልና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር-

የሚቃረኑ ጉዳዮች ቢስተዋሉ በትምህርቱ ሂደት ላይ ከባድ መሠናክል ሊፈጥሩ ይችላሉ። በአንባሩ በተማሪዎቹ ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ ተመርኩዞ አዎንታዊ በሆነ መንገድ የተዘጋጀ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ማቅረብ ተማሪዎቹ በፍላጎትና በጉጉት እንዲከታተሉትና በቀላሉ እንዲገነዘቡት ያግዛቸዋል።

በሌላ በኩል ከተማሪዎች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ማኅበረሰባዊና ባህላዊ ዳራ አንፃር በዘመንና በቦታ እጅግ የተራራቁ ጉዳዮችን ያነገቡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ስንመርጥ ጥንቃቄ ካልተደረገ በትምህርቱ ሂደት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያስከትላሉ። ለምሳሌ ከደራሲ ሀዲስ አለማየሁ «ፍቅር እስከመቃብር» ረጅም ልቦለድ ታሪክ ላይ ቀንጭበን ባለንበት ዘመን በሚገኙ የአንደኛ ደረጃ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ቢካተት ቋንቋው ቀላል ቢሆንም ተማሪዎቹ አንዳንድ የማዕረግ ስሞችን ምንነት ወይም የገጸባሕርያቱን መገልገያ ቁሳቁስ፣ አልባሳት፣ ወዘተ. መጠሪያ ቃላት ብያኔን በተመለከተ ከመዝገበ ቃላት ላይ ወይም ከመምህራናቸው ካልተነገራቸው በቀላሉ ለመረዳት ሊቸገሩ ይችላሉ።

በርግጥ እንደ Lazar (1993 ፣53) ገለፃ፣ አሁን ላለንበት ዘመንና ቦታ እጅግ የራቁ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በዘመናችን ለሚገኙ ተማሪዎች ግልጽነትና ማራኪነት ያላቸው ሆነው ልናገኛቸው እንችላለን። ለነዚህም ምክንያቱ የጭብጥ መመሳሰል (የከተሞች ህይወት፣ ኢንዱስትሪ መስፋፋት፣ ወዘተ)፣ በሰዎች መሠረታዊ ግንኙነቶች ላይ በማተኮራቸው (ለምሳሌ፡ በወላጆችና በልጆች መካከል ሥለሚፈጠሩ አለመግባባቶች) ወይም የተማሪዎቹን የግል ህይወት የሚዳስሱ ጭብጦችን የያዙ ሲሆኑ ነው። ከነዚህ በተጨማሪ ተማሪዎቹ የሌሎችን ማሕበረሰቦች ባሕልና ወግ የማወቅ ጠንካራ ጉጉት ካደረባቸው ወይም የሌሎችን ሥነጽሑፍ ማጥናት የማኅበረሰቡን ማንነትና አመለካከቶች (insights) ለማጥናት ያግዛል ደስታንም ይሰጣል የሚል አመለካከት ካላቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራው የቀረበበት ዘመንና ሥፍራ ርቀት ላይገድባቸው ይችል ይሆናል።

Brumfit እና Carter (1986፣189) እንደገለጹት፣ በኢኮኖሚያዊ የእድገት ደረጃ ልዩነቶች ምክንያት የዘመን ልዩነቶች ቢኖሩም የጥበብ መመሳሰል ሊያጋጥም እንደሚችል ያስረዳሉ። ለምሳሌ የ19ኛው ክፍለ ዘመን ሥነጽሑፋዊ ሥራ የአኗኗር ዘይቤው ብዙም ላልተለወጠ አንባቢ ከወቅታዊው (ዘመናዊ) ሥነጽሑፋዊ ሥራ የበለጠ ለባህሉ (ለኑሮው) ሊቀርበው ይችላል። በመሆኑም በአንዳንድ የሦስተኛው ዓለም ሀገራት ለሚገኙ ሕዝቦች በ18ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፉ ሥራዎች ከፍ ባለ ደረጃ ስሜታቸውን-

ሊነኩ ይችላሉ። ምክንያቱም የአካባቢው ማኅበረሰብ ገና በቅደመ ኢንዱስትሪ (ግብርና) የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ሊሆን ስለሚችል ነው።

ባጠቃላይ ከላይ በተለያዩ ምሁራን ከቀረቡት ዝርዝር ማብራሪያዎች መረዳት የምንችለው ቋንቋ ለማስተማሪያነት የምንመርጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ታላሚውን ቋንቋ ከሚማሩ ተማሪዎች ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማሕበረሰባዊ የአኗኗር ዘይቤ ጋር ምን ያህል ቅርበት ወይም ርቀት እንዳለው መመርመር የሚገባ መሆኑን ነው። በተጨማሪም ለባሕላቸው መቅረቡ ወይም መራቁ ሊያስከትል የሚችለውን ተጽዕኖ (አሉታዊም ሆነ አዎንታዊ) በመፈተሽ ለተማሪዎቹ ዳራዊ ግንዛቤ ማስጨበጥ ይኖርብናል።

## 2.3.7 የሥነጽሑፋዊ ሥራውን ርዝማኔ መመጠን

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎች የንባብ ፍጥነት እና ለትምህርቱ ከተመደበው የክፍለ ጊዜ መጠን አንፃር የተመጠኑ መሆን ይኖርባቸዋል። በጣም ረዥም፣ አመራማሪ፣ አላስፈላጊ ምልልሶችና ገለጻዎችን የያዙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ለተማሪዎቹ አሰልቺ ከመሆናቸውም በላይ በተመደበው የክፍለጊዜ መጠን ለመተግበር አዳጋች ሊሆኑ እንደሚችሉ Hill (1986፣16) ይገልፃሉ።

አንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ለታቀደው የትምህርት ዓላማ እና ለተማሪዎቹ ዳራዊ ዕውቀት ተስማሚ ሆኖ ነገር ግን በክፍል ውስጥ ለመተግበር ርዝማኔ ካለው ተገቢ ማስተካከያ አድርገን በቅንጫቢ መልክ በመውሰድ ልንገለገልበት እንደምንችል Brumfit እና Carter (1986 ፣189) ሐሳብ ያቀርባሉ።

ባጠቃላይ Lazar (1993 ፣55) ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ስንመርጥ ርዝማኔያቸውን በተመለከተ ተገቢነታቸውን ለመወሰን ለሚከተሉት ሦስት ጥያቄዎች አስቀድሞ መልስ መሻት እንደሚገባ ያስረዳሉ፣

1. *ሥነጽሑፋዊ ሥራውን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎቹን ልዩ ልዩ መልመጃዎች ለማሰራት የሚያስችል በቂ ጊዜ ሊኖር ይችላልን?*
2. *ተማሪዎቹ ከሥነጽሑፋዊ ሥራው የወጡ መልመጃዎችን በቤት ስራ መልክ ለመሥራት ምን ያህል ጊዜ ይኖራቸዋል? እና*
3. *ከሥነጽሑፋዊ ሥራው ውስጥ ምን ያህሉን ክፍል ነው የምንወስደው? ግማሹን ብቻ? ወይስ ተሻሽሎና ተስተካክሎ የተመጠነውን? ይህ ከሆነስ ተማሪዎቹ ሙሉ ታሪኩን በተገቢው ሁኔታ እንዲገነዘቡት ምን ያህል ዳራዊ ግንዛቤ ማቅረብ ይኖርብናል? የሚሉት ናቸው።*

## 2.3.8. የሥነጽሑፋዊ ሥራው ተተግባሪነት

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መመረጥ ያለባቸው በቋንቋ ለዛቸው ወይም በታሪካቸው አስደሳችና ማራኪነት ብቻ ሳይሆን ፈቃደ (1995 ፣ 189 - 190) እንደገለፀት፣ «ተፈላጊውን ክሂል ለማስተማር ያላቸው ተገቢነት ተጠንቶ መሆን አለበት። ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ምንባቡቹ ለቋንቋ ትምህርት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ እንጂ ለምንባቡቹ ይዘት መሆን የለበትም።» ከዚህም ባሻገር Lazar (1993 ፣ 55) እንዳስረዱት ተተግባሪነቱን ለማረጋገጥ ከመምረጣችን በፊት የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች በጽሞና መመለስ ይኖርብናል፤

- *በመርሐትምህርቱ ላይ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ ምን ያህል መልመጃዎችን ማዘጋጀት ይቻላል?*
- *ለሚመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ አጋዥ የሆኑ መርጃ መሳሪያዎች (ለምሳሌ ስለቀረበው ልቦለድ ሚተርክ ፊልም፣ በካሴት የተቀረጹ ተውኔቶች፣ ግጥሞች ፣ ሥለደራሲው የህይወት ታሪክ የሚገልጹ በቤተመጻሕፍት የሚገኙ ማቴሪያሎች፣ ወዘተ.) በምን ያህል መጠን ሊገኙ ይችላሉ? የሚሉት ናቸው።*

Carter እና Mcre (1996፣17) እንዳስረዱት፣ ከአጋዥ መረጃ መሣሪያዎች (መጻሕፍት) በተጨማሪ ሆነ ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁ መጻሕፍት ሊኖሩ ይገባል። አጋዥ መሣሪያዎች የምንላቸው መዝገበ ቃላትና ልዩ ልዩ ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎችን ሲሆን፣ ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚዘጋጁት ግን ትክክለኛውን የሰዋሰው ህግ የሚጠቁሙ ናቸው። እንደ ምሁራኑ ገለጻም ከጠቀሜታቸው አንፃር ሆን ተብለው የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግ ለማስተማር ከተዘጋጁት መርጃ መጻሕፍት ይልቅ አጋዥ ለሆኑት መርጃ መሣሪያዎች ትኩረት መስጠት አለብን። ይህ ማለት ግን ሆን ተብለው የሚጋጁትን ማቴሪያሎች ጠቀሜታቸው ዝቅተኛ ነው ማለት ሳይሆን ማንኛውም ተማሪ የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ህግና ስርዓት በሂደት ሊማረው ይችላል። በአንፃሩ አጋዥ መረጃ መሣሪያዎች (መጻሕፍት) ተማሪው በህጎቹ እየተጫወተ፣ እየጠየቀ፣ እየተወያየ፣ ወዘተ. እንደ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ቋንቋውን እንዲማረው ያደርጉታል ለማለት ነው።

ስለዚህም ለቋንቋ ማስተማሪያነት የምንመርጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ የተወሰደበት መጽሐፍም ሆነ ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ልዩ ልዩ አጋዥ መረጃ መሣሪያዎች (መዝገበቃላት፣ቻርቶች፣ የተቀረጹ ድምጾችና ምስሎች፣ ወዘተ.) እንዲሁም ሆን ተብለው

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተመደቡ መጻሕፍት በምን ያህል መጠን ተማሪዎቹ በቅርብ ሊያገኟቸው እንደሚችሉ አስቀድሞ ማረጋገጥ ይኖርብናል።

ባጠቃላይ ከላይ የተጠቀሙትን እነዚህን ዘጠኝ የመምረጫ መስፈርቶች Lazar (1993 ፣55) በሦስት ርእሰ-ጉዳዮች ስር እንደሚከተለው ባጭሩ አጠቃለው አቅርበዋቸዋል፤

1. *የሚቀርበው የቋንቋ ትምህርትን በተመለከተ (Type of course)*
   - *የተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣*
   - *ተማሪዎቹ ቋንቋውን የሚማሩበት አብይ ዓላማ፣*
   - *ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር (ለመማር) የሚፈጀው ጊዜ፣*
   - *ማስተማር የተፈለገው የቋንቋ ክፍል።*
2. *የተማሪዎች ዳራ*
   - *የንቃተ አእምሮ ደረጃ (Intellectual Maturity)*
   - *የሥሜታዊነት ወይም የግንዛቤ ደረጃ (Emotional or understanding)*
   - *ዝንባሌ ወይም መዝናኛዎች (Interest or hobbies)*
   - *ባህላዊ ዳራ (Cultural background)*
   - *ሥነጽሑፋዊ ዳራ (Literary background)*
3. *ከሥነጽሑፋዊ ሥራው ጋር ተዛምዶነት ያላቸው ጉዳዮች*
   - *የሥነጽሑፋዊ ሥራው በበቂ መጠን መገኘት*
   - *የሥነጽሑፋዊ ሥራው ርዝማኔ*
   - *የሥነጽሑፋዊ ሥራው ተተግባሪነት*
   - *ሥነጽሑፋዊ ስራው ከመርሐትምህርቱ ጋር መጣጣሙ*

### 2.3.9. የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተገቢነት የመፈተሻ ስልት

### ( A Checklist for choosing literary texts)

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተመረጠ አንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከላይ በተናጠል በተለያዩ ምሁራን የተጠቆሙትን ዝርዝር የመምረጫ መስፈርቶችን በጥቅሉ ማሟላት አለማሟላቱን ለማረጋገጥ የሚያስችለንን የተጠቃለለ አጭር ቀመራዊ ስልት Lazar (1993፣ 60) እንደሚከተለው ገልጸዋል፤

| | በጣም ጥሩ | ጥሩ | በቂ | ደካማ |
|---|---|---|---|---|
| 1. አቀራረቡ ለተማሪዎች ያለው ተሰማሚነት | | | | |
| 2. ለተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ያለው ተገቢነት | | | | |
| 3. ሥነጽሑፋዊ ሥራው የተማሪዎቹን ፍላጎትና ዝንባሌ የማሟላት ብቃቱና ያለው ጠቀሜታ | | | | |
| 4. የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስና ልዩ ልዩ መልመጃዎች ለማዘጋጀት የማስቻል ብቃት | | | | |
| 5. ተማሪዎች በተናጥል እና በቡድን እንዲሳተፉ የማስቻል ብቃት | | | | |
| 6. ሥነልሳናዊ መምሪያ (Lingustic guidance) ይገኙበታል | | | | |
| 7. ለተማሪዎቹ ባሕላዊ፣ ሥነጽሑፋዊ ወይም ታሪካዊ ዳራ አቅርቧል | | | | |
| 8. ግልጽ የሆኑ ትእዛዞች አሉት (Clarity of instruction) | | | | |

ከላይ በዝርዝር የተጠቆሙት ጥያቄዎችን ድምር ውጤት መሠረት በማድረግ ልንመርጥ ያሰብነውን ሥነጽሑፋዊ ስራ ተገቢ መሆን ወይም አለመሆኑን ልናረጋግጥ እንችላለን፡፡

### 2.4. ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ስራዎች የታቀደውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ከግብ ያደርሱ ዘንድ በመምህርነት መሥያ ለረኸቦም አመት ልምድ ባላቸውና ተገቢውን ሥልጠና በወሰዱ ባለሙያዎች ጠቃሚነታቸው በተለያዩ ምሁራን የተረጋገጠላቸው መርሆዎችን በመከተል በጥንቃቄ በሚገባ መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡የሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች አደረጃጀት መርሆዎችን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ተመሳሳይ የሆኑ ሀሳቦችን ሰንዝረዋል፡፡ ከነዚህ የምሁራኑ ሐሳቦች ውስጥ ተስፋዬ (1982)፣ ወንድወሰን (1995) እና Hill(1986) የጠቆሟቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፤

### 2.4.1 የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ይዘቶችን በፋይዳቸው ሚዛን ደፊነት መሠረት ማደራጀት

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲደራጁ በፋይዳቸው ቅደምተከተል መሠረት መሆን ይኖርባቸዋል ሲባል ሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎችን ያመለክታል። ይኸውም ጐናዊ (በአንድ መማሪያ መጽሐፍ) እና ተዋራዳዊ (በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች) ግንኙነት ውስጥ ያለውን የይዘት አደረጃጀት ነው።

ጎናዊ አደረጃጀታቸውን በተመለከተ የተማሪዎችን ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ ዳራዊ ግንዛቤ፣ ወዘተ. ባገናዘበ መልኩ፣ የሚመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ ካላቸው ዝቅተኛ ጠቀሜታ ወዳላቸው በሚንዝ መልኩ መደራጀት ይኖርባቸዋል። ወንድወሰን (1995፣44) ይህን ጉዳይ በተመለከተ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፤

> *በአንድ የክፍል ደረጃ አማርኛ በሁለተኛ ቋንቋነት (በኢአፈ-ፈተነት) ለማስተማር በሚዘጋጅ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ይካተቱ ዘንድ የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ጉልህ ፋይዳ ካለው ይዘት ቀለል ያለ ፋይዳ ወዳለው ይዘት በሚንዝ መልኩ መደራጀት ይኖርባቸዋል። ይህ የሚሆነው ተማሪዎች አማርኛን የሚማሩት በሁለተኛ ቋንቋነት እንደመሆኑ መጠን ጉልህ ፋይዳ ያላቸው ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች አስቀድሞ ሲያጋጥማቸው ቋንቋውን መማራቸው በሕይወታቸው ውስጥ ወደፊት እንደዚሁ ትርጉም ያለው አገልግሎት እንደሚሰጣቸው በማሰብ እንዲማሩ ያደርጋቸዋል የሚል እምነት ስላለ ነው። ገና ከጅምሩ አንባራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ ፋይዳው የቀለለ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካጋጠማቸው ግን ለቋንቋው ትምህርትም የሚሰጡት ትኩረት የቀለለ ይሆናል።*

በአንባሩ ከፋይዳቸው አንባር የማደራጀቱ ሥልት በተከታታይ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች ከሆነ ግን የተማሪዎቹ የግንዛቤና የአእምሮ ብስለት ደረጃ ቀስ በቀስ እያደገ የሚሄድ በመሆኑ አደረጃጀቱም ይህን መንገድ መከተል አለበት። ስለዚህ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከዝቅተኛ የክፍለ ደረጃ ወደከፍተኛ የክፍለ ደረጃ ሲደራጁ ዝቅተኛ ፋይዳ ካላቸው ከፍተኛ ፋይዳ ወዳላቸው መደራጀት ይኖርባቸዋል፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ በተከታዩ የክፍል ደረጃ ላይ የተሻለ አነቃቂና ከህይወታቸው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ይዘት ካላጋጠማቸው፣ ድግግሞሽ ወይም ከግንዛቤአቸው በታች ስለሚሆንባቸው በመሰላቸት ስሜት ቁብ ሊሰጡት አይችሉም። ሥነጽሑፋዊ ሥራውን ማንበብም እርባናቢስ መስሎ ሊታያቸው ይችላል። በዚህም ምክንያት የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግቡን ሳይመታ ይቀራል።

### 2.4.2. የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ ማደራጀት

ለአንድ የክፍል ደረጃ በሚዘጋጁም ሆኑ ተከታተይ ለሆኑ የክፍል ደረጃዎች የሚቀርቡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲደራጁ ቀለል ካለው ይዘት ከበድ ወደሚለው ሊሆኑ ይገባል። ይህ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ክብደትና ቅለት ከሁለት የተለያዩ አቅጣጫዎች የሚታይ ነው። ይኸውም በአንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ (ለምሳሌ ግጥም) ክብደትና ቅለት ወይም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አንዱ ከሌላው አንጻር ከሚኖራቸው ክብደትና ቅለት አኳያ ሊኖራቸው የሚችለውን ስፍራ መወሰንን ይመለከታል።

ከአንድ ሥነጽሑፋዊ ዘር አንጻር ሲባል ለምሳሌ ግጥምን ብንወስድ ሁሉም ግጥሞች በቃላት፣ በሰዋስው፣ በዘይቤ አጠቃቀማቸው፣ በአተራረካቸው፣ ወዘተ. እኩል ቅለት ወይም ክብደት (ንረት) የላቸውም። አንዱ ከሌላው በጣም ቀላል ወይም ከባድ ሊሆን ይችላል። ስለዚህም ይህን የክብደትና የቅለት ባህሪያቸውን ከተለያዩ መስፈርቶች አኳያ በመመርመር በጐኖዊም ሆነ ተዋረዳዊ አደረጃጀታቸው ላይ ከቀላል ወደ ከባድ መደራጀት አለባቸው። በሥነጽሑፍ ዘሮች መካከል ያለውን ክብደትና ቅለት ደረጃ በተመለከተ ወንድወሰን (1995፣45) የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ የሚከተለውን ብለዋል፤

> *ንጣይ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች (Specific literally works) በማየት ሳይሆን በጥቅሉ ሥነጽሑፋዊ ዘሮችን (literally genres) በማሰብ ሲደመድሙም ከግጥምና ከተውኔት ልቦለድ እንደሚጋራ፣ ከተውኔትም ግጥም እንደሚጠን ብዙዎች ይመሰክራሉ። ስለዚህ ከልቦለድ የምንወስዳቸውን ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ብናስከትል፣ ግጥማዊ ይዘቶችን በመጨረሻ ብናመጣ ቋንቋውን ለማስተማር ዓላማ የተመረጡበት ፋይዳ ጉልህ ይሆነል፣ የቋንቋው ትምህርት ሊያሳካ ያሰባቸው ዓላማዎችም የተማሪዎች የመቀበል አቅም ሳይፈታተኑ ግብ ይመታሉ።*

ከቀረበው ገለፃ የምንረዳው የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተለያዩ ዘርፎች ተመሳሳይ የክብደት ቅለት ደረጃ የሌላቸው በመሆኑ ሲደራጁ አጭር ልቦለድን ወይም ተራከ. ተረትን በማስቀደም ረዥም ልቦለድን ማስከተልና ተውኔትና ግጥምን ወደ መጨረሻ ማምጣት አስፈላጊ መሆኑን ነው።

### 2.4.3 የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በተከታታይነትና ተለጣጣቂነት መርሆዎች ማደራጀት

ተከታታይነት ሲባል አንድ የትምህርት ይዘት በትምህርት ሂደት በተከታታይ የሚከሰትበትን ሁኔታ ያመለክታል (ተስፋዬ፣1982፣40፣ Richards 2001፣150)። በትምህርቱ መጀመሪያ የቀረበ ይዘት ሳይቋረጥ እስከ ትምህርቱ መጨረሻ በተከታታይ መቀጠል አለበት፤ በየምዕራፉ፣ በየክፍል ደረጃው በተከታታይነት መቅረብ ይጠበቅባታል። አንድ ትምህርት ቀድሞ ከቀረበው ይዘት የሚያያዝበት ሥር በተጨማሪ ቀጥሎ ከሚመጣው የሚሰናሰልበት ቅርንጫፍ አለው (Billows 1961፣67)።

በተለይ አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን በሚመረጡት ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች አማካይነት ከቋንቋ ትምህርት ሊገኝ የሚችለውን የቋንቋ ችሎታ ማዳበርም ሆነ የተሟላ ሰብዕና መፍጠር የሚቻለው የሚቀርቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች እዚያው መጽሐፉ ውስጥም ሆነ ለተቀዳሚና ተከታይ ክፍሎቹ በሚዘጋጁት ውስጥ እርስበርስ ተያያዥነት ሲኖራቸው መሆኑን ወንድወሰን (1995፣46) ገልፀዋል።

ይዘቶቹ ተለጣጣቂነት ይኑራቸው ሲባልም አንድ ይዘት በሚከታተልበት ጊዜ ጥልቀትና ስፋት እያሳየ መምጣት እንዳለበት ያሳያል። ጥልቀት ሲባል ክብደቱ፣ - ውስብስብነቱ፣ ረቂቅነቱ፣ ወዘተ. በአንጻራዊነት እያደገ መሄድ አለበት ለማለት ነው። ስለዚህም የሚመረጡት ይዘቶች ንዑሳን ክፍሎች፣ ምዕራፎች፣ ወዘተ. አንዱ ወደሌላው የሚሸጋገር ባሕሪ ያላቸው መሆን ይገባቸዋል። ትምህርቱ እድገት እንዲያሳይ ይዘቶቹ ሲደራጁ አንዱ ክፍል ወደሚቀጥለው እያሸጋገረ በተማሪው ላይ የባህሪ እመርታ እያመጡ የሚሄዱ መሆን አለባቸው (ተስፋዬ፣ 1982፣ 40-41)።

### 2.4.4.የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው መደራጀት

ሥነጽሑፋዊ ይዘት የሌላቸው ሥራዎች የራሳቸው ጠቀሜታ ስለሚኖራቸው መካተታቸው ተገቢነት አለው። ነገር ግን ሲደራጁ ከሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ጋር ተሰባጥረው መሆን ይኖርበታል። ተማሪዎቹ በሥነጽሑፋዊ ስራዎቹ ሲማረኩ ወይም ሊደሰቱ የሚችሉት ሁለቱንም ገና ለገና በንጽጽር ማቅረብ ስንችል ነው። ይህን ሐሳብ በተመለከተ ወንድወሰን (1995፣47) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፤

*በመፅሐፍ ውስጥ ይካተቱ ዘንድ ሥነጽሑፋዊ የሆኑም ያልሆኑም ይዘቶች በተለያየ መጠን ከመረጥን በኋላም አንዱን አይነት (ለምሳሌ ሥነጽሑፋዊዎቹን) አንድ ላይ አከታትለን ከምናጣ ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ጉራማይሌ ሆነው እንዲደራጁ ብናደርግ አዋጪ ነው። ይህን ጉዳይ ጀሮ ዳባ ልበስ ብለን የሚዘጋጀውን የመማሪያ መጽሐፍ በሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ብቻ ብንሞላው... ለቋንቋው ትምህርት ስኬት የሚኖረው ፋይዳ እንዳሰብነው ሆኖ እንደማናገኘው መረዳት ይበጃል።*

ስለዚህ ባጠቃላይ ሁለቱም ይዘቶች የየራሳቸው ፋይዳ እንዳላቸው በመገንዘብ እያፈራረቅን ማደራጀት አማራጭ የማይገኝለት ዘዴ መሆኑን ከቀረበው ማብራሪያ መረዳት ይችላል።

## 2.5. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

እስካሁን በተደረገው ፍለጋ ከዚህ ጥናታዊ ሥራ ጋር በቀጥታ የሚዛመዱ ጥናቶች ባያጋጥሙም ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ ቅርበት ያላቸውን ግን ለማግኘት ተችሏል። እነዚህም ሁለት በትምህርታዊ ጉባዔ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች፣ ሦስት ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡና ሁለት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች ናቸው።

በትምህርታዊ ጉባዔ ላይ ከቀረቡት ሁለት ጥናታዊ ጽሑፎች ውስጥ ቀዳሚው ፈቃደ አዘዘ (1991) «የሥነ ጽሑፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት» በሚል ርዕስ ያቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፍ ሲሆን አጥኚው በሥነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው በመጠቆም በሀገራችን ሥርዓተትምህርት ውስጥ እስካሁን የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ገልጸዋል። ስለዚህም ወደፊት ትልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን በአፅንኦት አሳስበዋል። ሁለተኛው በትምህርታዊ ጉባዔ ላይ የቀረበው ጥናት በወንድወሰን አዳነ (1995) «አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ፋይዳ፣ አመራረጥና አደረጃጀት» በሚል ርዕስ ነው። በዚህ ጥናታዊ ሥራ ውስጥ በክፍል አንድ ሌሎች ጽንሰሐሳባዊ ማብራሪያዎች የቀረቡ ሲሆን በክፍል ሁለት «አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የሥነጽሑፍ ፋይዳ» በሚል ርዕስ ሥነጽሑፍ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ስላለው ፋይዳ፣ ስለሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ሂደት ሰፊ ጽንሰሀሳባዊ ማብራሪያዎች ቀርበዋል።

የእኔን ጥናት ከላይ ከቀረቡት ሁለት ጥናቶች ጋር የሚያመሳስለው በምዕራፍ ሁለት በሚቀርቡት አንዳንድ ጽንሰሐሳባዊ ማብራሪያዎች ሲሆን ልዩነቱም በዋነኛነት በጽንሰሐሳባዊ ማብራሪያዎች መሣሪያነት የመማሪያ መጻሕፍትን በናሙናነት ወስዶ ጥናት በማካሄዱ ነው።

ዘመንፈስ ባራኪ (1991) «በሥነጽሑፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልቦለድ ሚና በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት» በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል። የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ዓላማ በናሙናነት የተመረጡትን ተማሪዎች በሁለት ምድብ ማለትም አንዱን መከራዊ (experimental) ሌላውን ቁጥጥር (controlled) ብሎ በመመደብ በመከራዊ ሁኔታ የተመደቡት ተማሪዎች በአጭሩ አማካይነት በሥነጽሑፍ መማሪያነት የአማርኛ ቋንቋን ከተማሩ በኋላ ሐሳባቸውን በጽሑፍ በመግለጽ ደረጃ በመደበኛዋ መምህር በነባሩ (traditional) ዘዴ ከተማሩት መከራዊ ቡድን ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆኑ ማረጋገጥ ነው። ጥናቱ መጠናዊ (quantiative) የምርምር ዘዴ የተከተለ ሲሆን መረጃ ማሳሰቢያ ስልቱም ቅድመ ትምህርት እና ድኅረ ትምህርት ፈተና በመፈተንና ጽሑፋዊ መጠይቅ ናቸው። በመጨረሻም የጥናቱ ውጤት በአዲሱ ዘዴ እንዲማሩ የተደረጉት ተማሪዎች በነባሩ ዘዴ ከተማሩት የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን አረጋግጧል።

የእኔን ጥናት በዘመንፈስ ከተካሄደው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በሥነጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን የማስተማር ፋይዳን በተመለከተ በምዕራፍ ሁለት ሥር በቀረበው ጽንሰሐሳባዊ ማብራሪያ ሲሆን ልዩነቱ ሁሉንም የሥነጽሑፍ ፈርጆች (አጭር ልቦለድ፣ ረዥም ልቦለድ፣ ግጥም፣ ተውኔት፣ ወዘተ. ) ስለሚመረምርና በዋነኛነት የሚያተኩረው በመማሪያ መጽሐፍ ላይ በመሆኑ ነው።

ተከታዩ ጥናት ክንፈሚካኤል ሱጋ (1995) «ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂልና የሥነጽሑፍ አውቀት ለማሳደግ ያላቸው እገዛ በ1993 እና በ1994 ዓ.ም. ለ10ኛና ለ11ኛ ክፍል መማሪያነት በተግባር ላይ በዋሉት መጻሕፍት።» በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ያቀረቡት ሲሆን የጥናቱ ዓላማ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂል ለማዳበርና የክፍል ደረጃውን የሚመጥን የሥነጽሑፍ ዕውቀት ለማሳደግ ያላቸውን እገዛ መመርመር ነው። ከመማሪያ መጽሐፉ፣ ከመምህራንና ከተማሪዎች ከተሰባሰቡ መረጃዎች ትንታኔ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው በ10ኛና በ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች በምንባብ፣ በመመሪያና በማብራሪያ እንዲሁም በመልመጃ መልክ የቀረቡ መሆናቸውን፣ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹም ከተለያዩ የሥነጽሑፍ ዘሮች የተወሰዱ በመሆናቸው አራቱን የክሂል ዘርፎችና የሥነጽሑፍ እውቀት ለማሳደግ ትልቅ እገዛ እንዳላቸው ጠቁመዋል። በአንባሩ ግን በ11ኛ ክፍል-

መጽሐፍ ውስጥ ባሉ ሥነጽሑፋዊ ይዘቶች ውስጥ አንዳንድ ለደረጃው የማይመጥኑ መኖራቸውን በመግለጽ የመፍትሔ ሐሳብ አቅርበዋል::

የእኔን ጥናት በክንፈሚካኤል ከተካሄደው ጋር የሚያመሳስለው በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሁሉንም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን የማመለከት በመሆኑ ሲሆን፣ ልዩነቱም በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ፋይዳ ላይ ሳይሆን በአመራረጥና አደረጃጀታቸው ተገቢነት ላይ ስለሚያተኩር፣ የመማሪያ መጻሕፍቱ አዘጋጆች በቃለመጠይቅ መረጃ ስለሚያሰባስብ፣ መርሐትምህርቱን በማካተቱ እንዲሁም የጥናቱ ተተኳሪ በሆነው የትምህርት እርከን ነው::

ፈሰሴ ገብረሀና (1991) «ከዘጠነኛ ክፍል እስከ 11ኛ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ግጥሞች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ሚና» በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ጥናታዊ ጽሑፋቸውን አቅርበዋል:: የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የቀረቡት ግጥሞች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸውን አስተዋጽኦ መመርመር ነው:: በመሆኑም ለምንባቦቹ መመዘኛ መስፈርቶችን በማውጣት አቀራረባቸውን ፈትሸዋል:: የተሰበሰቡትን መረጃዎች በመተንተንም የተገኘውን ውጤት ሲገልጹ ግጥሞች ለቋንቋ ትምህርት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ቢያበረክቱም፣ እሳቸው የተመለከቷቸው ግጥሞች ግን የሚጠበቅባቸውን ያህል የሚሰሩ እንዳልሆኑ ገልፀዋል:: ስለዚህም ግጥሞች በአደረጃጀታቸው ረገድ የተስተካከለ ሊሆኑ እንደሚገባ በመፍትሔ ሐሳብነት ጠቁመዋል:: ከዚህም ባሻገር ግጥሞቹ ወቅታዊና የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የሚያነሱ ሊሆኑ እንደሚገባ ገልጸዋል::

የእኔን ጥናት በፈሰሴ ከተካሄደው ጋር የሚያመሳስለው ከሥነጽሑፍ ዘርፎች ውስጥ አንዱ በሆነው በግጥም ቋንቋን ማስተማር ሂደትን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ አደረጃጀቱን የሚመለከት በመሆኑ ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ በዋነኛነት ይህ ጥናት ከግጥም በተጨማሪ ሌሎቹን የሥነጽሑፍ ዘርፎችን በማካተቱ፣ መረጃዎችን ከአዘጋጆቹ በቃለመጠይቅ በማሰባሰቡ እና በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ሂደት በተመለከተ ከመርሀትምህርቱ ጋር መጣጣም-አለመጣጣቸውን የሚፈትሽ በመሆኑ ነው::

ይልቃል ተስፋው (1997) ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ‹‹ከ9ኛ-12ኛ ባሉት ክፍሎች በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ግጥሞች ቋንቋን ለማስተማር ያላቸው ፋይዳ» በሚል ርዕሰ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል:: የጥናቱ ዓላማ ለተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት የግጥም ምንባቦች ለቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ፋይዳ መመርመር ነው::

ከመማሪያ መጻሕፍቱ እና በጽሑፋዊ መጠይቅ ከመምህራንና ከተማሪዎቹ የተሰባሰበ መረጃዎች ተተንትነው በተገኘው ውጤት መሠረት፣ የግጥም ምንባቦች በስድስት የቋንቋ ትምህርት መመዘኛ ማለትም የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን እንዲሁም ሥነልሳንና ሥነጽሑፍን በማስተማር ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን አጥኚው ጠቁመዋል። በተጨማሪም በግጥም ምንባቦቹ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች ለቋንቋ ትምህርቱ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳላቸውና ለክፍል ደረጃዎቻቸው የተመጠኑ መሆናቸውን በመግለጽ በአንባሩ የግጥም ምንባቦች በይዘት ደረጃ ጥሩ ቢሆኑም በቁጥር ደረጃና የተለያዩ ርዕሰጉዳዮችን ከማንሣት አንጻር ቢስተካከሉ መጻሕፍቱን ከአሰልችነት ሊያድናቸው እንደሚችልና ተማሪዎቹም በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ሊጨብጡ እንደሚችሉ ጠቁመዋል።

የእኔን ጥናት በይልቃል ከተካሄደው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ከሥነጽሑፍ ዘርፎች ውስጥ አንዱ የሆነው ግጥም በተመለከተ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ እንዲኑ እንደቀረበ የሚፈትሽ በመሆኑ ሲሆን ልዩነቱም ይህ ጥናት ሌሎቹንም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በማካተት፣ በአመራረጥና አደረጃጀታቸው ላይ ስለሚያተኩር ነው። ከዚህ በተጨማሪም ቃለመጠይቅን በመረጃ ማሰባሰቢያነት በመጠቀሙና፣ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከመርሐትምህርቱ አንፃር ስለሚቃኝ ከተጠቀሰው ጥናት የተለየ ያደርገዋል።

ጌትነት ታፈረ (1998) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ «ልቦለድን በመጠቀም በክፍል ውስጥ አንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብ ፍተሻ» በሚል ርዕስ ጥናታዊ ጽሑፍ አቅርበዋል። የጥናቱ ዓላማም በክፍል ውስጥ ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳት ትምህርት አቀራረብን መፈተሽ ነበር። የጥናቱ መረጃ ማሰባሰቢያ ሥልቶችም በዋነኛነት በቪዲዮ ካሜራ የታገዘ የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲሆን በአጋዥነት የጽሑፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅን ተጠቅመዋል። የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው የተገኙትን ውጤቶች እንደሚያመለክቱትም መምህራኑ ልቦለድን በመጠቀም የአንብቦ መረዳትን ትምህርት የአቀራረብ ደረጃዎችን ዓላማ በአግባቡ ለይተው ተግባራዊ እንደማያደርጉና የአንብቦ መረዳትን ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያገለግሉትን የማስተማሪያ ስልቶች ተጠቅመው ተማሪዎቹን እንደማያለማምዷቸው መስተዋሉን አጥኚው ገልፀዋል።

የእኔን ጥናት በጌትነት ከተካሄደው ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በሥነጽሑፍ ቋንቋ ማስተማርን በተመለከተ ልቦለድን የሚያካትት በመሆኑ ሲሆን ልዩነቱም፣ የጌትነት ጥናት በክፍል ውስጥ ባለው የአተገባበር ሂደት ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ያተኩራል። በተጨማሪም ሁሉንም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመመልከቱ በጌትነት ከተካሄደው ጥናት የተለየ ያደርገዋል።

ባጠቃላይ እነዚህ ከላይ የተጠቆሙት ጥናታዊ ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰሉበትና የሚለያዩበት ጉዳዮች የተገለጹ ቢሆንም አንዳንዶቹ ለጥናቱ በመነሻነትም ሆነ በማጣቀሻ ምንጭነት አስተዋጽኦ ማበርከታቸው መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው።

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 የጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያያዎች

ይህ ጥናት በዋናነት የተጠቀመበት ዘዴ የገላጭ (Descriptive) ጥናትና ምርምር ስልት ነው። ስለዚህም የተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍቱን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ይመረምራል። በዚህ ምዕራፍም የጥናቱ ናሙና አመራረጥ፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያያዎችና የጥናቱ አተናተን ዘዴዎች ቀርበዋል።

## 3.2 የተጠኚዎች አመራረጥ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ለጥናቱ የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለገሉት ናሙናዎች የተመረጡበት መንገድ ይቀርባል። በዚህም መሠረት የተጠኚ የክፍል ደረጃ፣ ትምህርት ቤቶች እና የመምህራን ናሙና አወሳሰድ ሥልት ይገለፃል።

### 3.2.1 የተጠኚ የክፍል ደረጃ አመራረጥ

በሀገራችን በአሁኑ ጊዜ በአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ሥር የሚመደቡት የክፍል ደረጃዎች ከ5ኛ እስከ 8ኛ ክፍሎች ናቸው። ከነዚህ የክፍል ደረጃዎች ውስጥ 7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች በታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴ (purposive sampling) የጥናቱ ተተኳሪ ሆነው ተመርጠዋል። እነዚህ የክፍል ደረጃዎች የተመረጡበት ዓቢይ ምክንያት ከዚህ በፊት በተካሄደው የአሰሳ ጥናት ከገበቱኛ የክፍል ደረጃዎች (5ኛ እና 6ኛ) መማሪያ መጻሕፍት ይልቅ፣ በነዚህ በናሙናነት በተመረጡት የክፍል ደረጃዎች የተዘጋጁት መጻሕፍት ላይ በቁጥር በዛ ያሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመገኘታቸው ነው። ይህም ለጥናቱ በቂ ናሙና በመሆን ስለሚያገለግሉ መረጃውን አስተማማኝ ሊያደርገት ይችላሉ የሚል ሐሳብ በመኖሩ ነው። ሁለተኛው ምክንያት በእነዚህ የክፍል ደረጃዎች በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን ከዚህ ቀደም በገበቱኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን ሊያስተምሩ ስለሚችሉ ለጥናቱ እጅግ ጠቃሚ መረጃዎችን ሊሰጡ ይችላሉ ተብሎ በመታመኑ ነው።

### 3.2.2 የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና በጋምቤላ ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ላይ ነው። ስለዚህም በነዚህ ሶስት ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ማዕከላዊ ዞኖች በታላሚ የናሙና አወሳሰድ ሥልት ተመርጠዋል። በጥናቱ መነሻ ላይ ከየክልሎቹ ሁለት ትምህርት ቤቶችን በመውሰድ በድምሩ 6 ትምህርት ቤቶች ለማካተት የታቀደ ቢሆንም የመምህራኑን ቁጥር ለመጨመር ሲባል በነዚህ ማዕከላዊ ዞኖች ውስጥ የሚገኙ 10 ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ተካተዋል። በዚህም መሠረት በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልል ማዕከላዊ ዞን ውስጥ የሚገኙት 7ኛ እና 8ኛ ክፍልን የሚያስተምሩት አንደኛና መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሙሉ በጥናቱ ሲካተቱ በደቡብ ክልል ማዕከላዊ ዞን ውስጥ ከሚገኙት አምስት ትምህርት ቤቶች መካከል ግን ሦስቱ ብቻ በነሲብ የናሙና አወሳሰድ ሥልት (Random sampling) ተመርጠዋል። ከሦስቱ ክልሎች የተመረጡት ትምህርት ቤቶችም የሚከተሉት ናቸው፤

#### ➢ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት

1. አዋሳ ሐይቅ አንደኛ ደረጃ አንደኛና ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤት
2. ታቦር አንደኛ ደረጃ አንደኛና ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤት
3. ቤተክህነት አንደኛ ደረጃ አንደኛና ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤት

#### ➢ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግሥት

1. አሶሳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
2. ሠላም በር አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
3. ጎህ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

#### ➢ ጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

1. ራስ ጎበና አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት ቤት
2. ዊቡር አንደኛ ደረጃ አንደኛና ሁለኛ ሳይክል ትምህርት ቤት
3. ኢለይ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
4. ዳልኮች አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

ማዕከላዊ ዞኖቹና ትምህርት ቤቶቹ በሚከተሉት ምክንያቶች ተመርጠዋል፤

- ከየክልሎቹ ትምህርት ቢሮ ኃላፊዎች በተገኘው መረጃ መሠረት በማዕከላዊ ዞኖቹ ውስጥ የሚገኙት መምህራን የረዥም ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው በመሆኑ ለጥናቱ አስተማማኝ መረጃዎችን በጽሑፋዊ መጠይቅ ማሰባሰብ ይቻላል ተብሎ በመታመኑ፤
- በተለያዩ ቋንቋዎች አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ተሰባጥረው የሚገኙት በማዕከላዊ ዞኖች ውስጥ መሆኑን ከየክልሎቹ የሥርዓተ-ትምህርት ክፍል ባለሙያዎች ጋር በተካሄደው ቃለመጠይቅ ማወቅ በመቻሉ፤ የተማሪዎችን ዳራ በተመለከተ መምህራናቸው የተለያዩ ልምዶች ሊኖሯቸው ይችላል ተብሎ በመገመቱ፤
- ትምህርት ቤቶች የሚገኙባቸው ቦታዎች ለአጥኚው ለትራንስፖርት አመቺ በመሆናቸውና ጥናቱን በታቀደው ጊዜ ለማጠናቀቅ ስለሚያግዝ፤

የሚሉት ናቸው።

### 3.2.3. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎችን የሚያስተምሩ መምህራን በጥናቱ ተካተዋል። በዚህም መሠረት ከየክልሉ በ7ኛና በ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ያሉ አምስት የ7ኛ እና አምስት የ8ኛ ክፍል መምህራን መረጃ በመስጠት ተባብረዋል። በ7ኛና በ8ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ላይ ያሉ መምህራን ብቻ የተወሰዱበት ዋነኛ ምክንያት ጥናቱ የሚካሄደው በተጠቀሱት የክፍል ደረጃዎች፤ የአማርኛ መማሪያ የተማሪው መጽሐፍ ላይ በመሆኑ በሌሎች የክፍል ደረጃዎች ከሚያስተምሩ መምህራን ይልቅ እነዚህ መምህራን አስተማማኝ መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ በመታመኑ ነው።

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች

ለጥናቱ በቂና አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት እንዲቻል ሦስት ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች በጥቅም ላይ ውለዋል። እነሱም፤ የሰነድ ምርመራ (ዋነኛው የመረጃ ማሰባሰቢያ መሣሪያ)፤ የጽሑፍ መጠይቅና ቃለመጠይቅ ናቸው።

### 3.3.1. የሰነድ ምርመራ

በጥናቱ ተተኳሪ ክልሎች፣ በ2000 ዓ.ም በአገልግሎት ላይ የሚገኙ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት እና ለየክፍል ደረጃዎቹ የተዘጋጁት መርሐትምህርቶች ለዚህ ጥናት ዋነኛ የመረጃ ምንጮች ናቸው። በተጨማሪም በተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገራት ምሁራን የተዘረዘሩትን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ሂደት (የመገምገሚያ መስፈርቶችም) ተቃኝተዋል። በነዚህ (በክለሳ ድርሳናት ውስጥ በተካተቱት) የመገምገሚያ መስፈርቶች (ንድፈሀሳቦች) መነሻነትም የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥና አደረጃጀት በተመለከተ መረጃዎች በዝርዝር ተተንትነዋል።

### 3.3.2. በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

ለ7ኛ እና 8ኛ የክፍል ደረጃዎች አማርኛ ቋንቋ መምሕራን የተዘጋጁት የጽሑፍ መጠይቆች እያንዳንዳቸው ሦስት ሦስት ክፍሎች አሏቸው (አባሪ አንድን ይመለከቷል)። በመጠይቆቹ የመጀመሪያ ክፍል የመምህራኑ ዳራ የተጠየቀ ሲሆን በሁለኛው ክፍል የተተኳሪ መጻሕፍቱን የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዞታ የተመለከቱ ዘርዝር ያሉ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው። በዚህ ክፍል የቀረቡት ጥያቄዎች በሊከርት የደረጃ ስኬል- (Likert rating scale) የጥያቄ አቀራረብ ስልት መሠረት፤ በአምስት ደረጃዎች (በጣም እስማማለሁ፣ እስማማለሁ፣ ለመወሰን ያስቸግረኛል እና ፍጹም አልስማማም በሚል) የቀረቡ ናቸው። በክፍል ሦስትም አስተያየታቸውን እንዲሰጡ የሚጋብዙ ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል።

የጽሑፍ መጠይቆቹ በሙሉ በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ላይ የቀረቡትን ንድፈሐሳቦች መሠረት በማድረግ በአጥኚው የተዘጋጁ ናቸው። መጠይቆቹ ሲዘጋጁ በመካሪ ጥናቱ ላይ በተስተዋሉ የሐሳብ መደጋገምና ግልጽ አለመሆን ችግሮች ምክንያት አንዳንድ ጥያቄዎች ሊቀነሱና ቅርፃቸውን ሊለውጡ ችለዋል። የጥያቄዎቹን ይዘትና አቀራረብ በተመለከተ በአንድ ከመጀመሪያ ዲግሪ በላይ ባላቸው የሥነልቦና ባለሙያና በሶስት የ2ኛ ዓመት የድኅረምረቃ (TeAm) ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጥባቸው ተደርገው በማሻሻያ ሐሳብ መሠረት ተስተካክለው ለጥናቱ አማካሪ ከቀረቡ በኋላ በተሰጡ አስተያየቶች መሰረት በድጋሚ ተስተካክለው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል።

### 3.3.3. ቃለመጠይቅ

ቃለመጠይቁ የቀረበው የጥናቱ ተተኳሪ መጻሕፍቱን ላዘጋጁና በአርታኢነት ላገለገሉ የትምህርት ባለሞያዎች ነው። ዋና ትኩረቱም በመጻሕፍቱ ዝግጅት ወቅት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን ለመምረጥና ለማደራጀት በሥራ ላይ የዋሉ መስፈርቶችንና ስልቶችን በመለየት ላይ ያረፈ ነው። ቃለመጠይቁ የመጀመሪያው ረቂቅ በዩኒቨርስቲውለሚገኙ ሦስት የTeAm 2ኛ ዓመት የድኅረ ምረቃ ተማሪዎች ታይቶ ተገቢው ማስተካከያ- ከተደረገበት በኋላ፣ ለጥናቱ አማካሪ ቀርቦ በተሰጠው አስተያየት መሠረት አስፈላጊው ማሻሻያም ተደርጎበታል።

ለቃለመጠይቁ 3 የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆችና አንድ አርታኢ ምላሽ ሰጥተዋል። በቃለመጠይቁ ሁሉንም አዘጋጆችና አርታኢያን ለማካተት ጥረት የተደረገ ቢሆንም ከአዘጋጆቹ ውስጥ አንዳንዶቹ በትምህርትና በሥራ ምክንያት ክልላቸውን በመልቀቃቸው ሊገኙ ስላልቻሉና አድራሻቸውንም ለማወቅ ስላልተቻለ በወቅቱ የተገኙት ብቻ እንዲካተቱ ተደርጓል። ከመጻሕፍቱ አርታኢያን መካከልም አንዳንዶቹ በአማርኛ ቋንቋ ያልሰለጠኑ በመሆናቸው፣ ለጥያቄዎቹ መ.ያዊ መልስ ለመስጠት እንደሚቸገሩ በመጠቆማቸውና ፈቃደኛ ሆነው ባለመገኘታቸው ምክንያት ከሞያው ጋር ቀረቤታ ያላቸውና ለቃለመጠይቁ ፈቃደኛ የሆኑት ብቻ ተካተዋል።

ቃለመጠይቁ በሚካሄድበት ወቅት ባለሞያቹ የሚሰጡትን አስተያየት እንዳለ በጽሑፍ ለማስፈር አስቸጋሪ በመሆኑ፣ ምልልሱ በመቅረጸ ድምጽ (በካሴት) እንዲቀረጽ ከተደረገ በኋላ በጽሑፍ ተለውጦ ቀርቧል (አባሪ '3'ን ይመልከቷል)።

## *3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴዎች*

በዚህ ጥናት ከሰነድ ምርመራ፣ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅና ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል። ከሰነድ ምርመራ የተገኙ መረጃዎች በአስረጂነት እየተመሰዱ የተተነተኑ ሲሆን፣ በአስረጅነት ከተወሰዱት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው መረጃዎችም በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚገኙባቸው ገጾች (የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን ርዕሶችና ምንጮቻቸው በማከል) በዝርዝር ተጠቁሟል።

ከዚህ በተጨማሪም ከመምህራን በጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበውን መረጃ (በየክልሎቹ እና በየክፍል ደረጃዎቹ) በመለየት ለእያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጠውን መልስ በጥራት በመልቀም ተቆጥሮ፣ በሰንጠረዥ ተጠቃሎ እንዲቀርብ ተደርጓል። በሰንጠረዡ ውስጥ የሚታዩት አህዞች የየራሳቸው አማራጭ መልሶች ውክልና አላቸው በዚሁ መሠረት 5 በጣም እስማማለሁ፣ 4 እስማማለሁ፣ 3 መወሰን ያስቸግረኛል፣ 2 አልስማማምና 1 ፍጹም አልስማማም የሚሉ መልሶችን ይወክላሉ። እነዚህ ምላሾች ሲተነተኑም ሁለቱ አዎንታዊ መልሶች (5፣4) ባንድ ላይ ሲሰሉ፣ ሁለቱ አሉታዊ መልሶችም (2፣1) በተመሳሳይ ባንድ ላይ ተሰልተዋል። 3(ለመወሰን ያስቸግረኛል) ግን በመጠይቆቹ የቀረበውን ሃሳብ በአዎንታም ሆነ በአሉታ ያልተመለከተ በመሆኑ ለብቻው ተሰልቷል።

በቃለመጠይቅ አማካይነት ከአራት የመጻሕፍት አዘጋጆችና አርታኢ የተሰበሰቡ መረጃዎችም ከሰነድ ምርመራና ከመምህራን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ጋር እየተጣቀሱ ተብራርተዋል። በተጨማሪም የተለያዩ መረጃዎችን በግልጽ ለማሳየት እንዲቻል አስፈላጊ ሆኖ በተገኘበት ቦታ ሁሉ ሰንጠረገሮችንና ስሌቶችን በቁጥር (በመቶኛ) በማስላት በጥንቃቄ ለመተንተን ጥረት ተደርጓል።

# ምዕራፍ አራት

# የመረጃ ውጤት ትንተና

## 4.1. ከሰነድ ምርመራ የተገኙ ውጤቶች ትንተና

በዚህ ክፍል ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍሎች በተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች አመራረጥና አደረጃጀት ሂደትን በተመለከተ ከየመጻሕፍቱ የተሰባሰቡትን መረጃዎች መሠረት በማድረግ ሰፊ ትንታኔ ይቀርባል። ከዚህ ጐን ለጐን መርሐትምህርቶቹም (በተለይ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ሂደት ሲፈተሽ) ከመማሪያ መጻሕፍቱ ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ ይቃኛል።

### *4.1.1. የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት*

በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተመረጡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ሂደት ከመመርመራችን በፊት ቀዳሚው ጥያቄ፣ ምን ያህል ሥነ-ጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ይዘቶች ተካተዋል? ሥነጽሑፋዊ ይዘት ከሌላቸው አንባር ሲቃኙስ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ሥራዎች ምን ያህል ትኩረት አግኝተዋል? በየክልሎቹ ብሎም በየክፍል ደረጃቸውስ ተለይተው በንጽጽር ሲታዩ ምን ልዩነቶች ይስተዋላሉ? ወዘተ. የሚሉትን ጥያቄዎች አጠቃላይ ዳራዊ ግንዛቤ ከተከታዩ ሠንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል፤

**ሠንጠረዥ 1፡- በሦስቱ ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍሎች በተዘጋጁት የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ዳራዊ መግለጫ**

| የክፍል ደረጃ | ክልል | የታተመበት ዓ.ም. | የገጾች መጠን | የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች | ከአጠቃላይ ምንባቦቹ በመቶኛ ስሌት /%/ | ሥነጽሑፋዊ ይዘት የሌላቸው ሥራዎች | ከአጠቃላይ ምንባቦቹ በመቶኛ ስሌት /%/ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7ኛ | ጋምቤላ | 1997 | 189 | 20 | 57 | 15 | 43 | 35 |
| | ደቡብ | 1997 | 125 | 13 | 40.6 | 19 | 59.4 | 32 |
| | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 1998 | 114 | 12 | 37.5 | 20 | 62.5 | 32 |
| 8ኛ | ጋምቤላ | 1997 | 104 | 10 | 35.7 | 18 | 64.3 | 28 |
| | ደቡብ | 1998 | 238 | 6 | 17.14 | 29 | 82.86 | 35 |
| | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | 1998 | 162 | 4 | 13.8 | 25 | 86.2 | 29 |
| | | ድምር | | 65 | 34 | 126 | 66 | 191 |

በሠንጠረዥ አንድ ላይ ከቀረበው ዝርዝር መረጃ መረዳት እንደሚቻለው፣ ለጋምቤላ ክልል በተዘጋጀው የ7ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በቁጥር በአንፃራዊነት ከቀሪዎቹ የተሻሉ ሆነው ተገኝተዋል፤ ከ35 ምንባቦች ውስጥ 20ዎቹ (57 በመቶ) ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ሲሆኑ 15 (43 በመቶ) ያህሉ ግን ሥነጽሑፋዊ ይዘት የሌላቸው ናቸው። ስለዚህም በአንፃራዊነት ሲታይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከፍተኛ ትኩረት አግኝተዋል ማለት ይቻላል። በሌላ በኩል የደቡብ ክልል 7ኛ 40.6 በመቶ፣ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ 37.5 በመቶ በተጨማሪም የጋምቤላ 8ኛ ክፍል 35.7 በመቶ ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ትኩረት ተሰጥቷል። ስለዚህም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በአማካይ ከአጠቃላይ ምንባቦቹ ቁጥር ውስጥ አንድ ሦስተኛ (ሲሶ) ያህሉን ይሸፍናሉ። በመሆኑም በነዚህ ሶስት መጻሕፍት ውስጥ ሥነጽሑፋዊ ይዘት የሌላቸው ምንባቦች ከፍተኛ ትኩረት አግኝተዋል። በአንፃሩ ለደቡብ ክልል 8ኛ ክፍል እና ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ 8ኛ ክፍል በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተገቢ ትኩረት አልተሰጣቸውም ለማለት ያስደፍራል።

ይህ በአንድ ክልል ውስጥ በተዘጋጁ ሁለት (በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች) መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መጠን ከፍተኛ ልዩነቶች ማሳየት የሚጠቁመን ነገር ቢኖር በክልሉ ውስጥ የሚገኙት የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች መሠረታዊ የሆነና የተጠና መርህ እንዲከተሉ ባለመደረጉ የየራሳቸውን ግላዊ ግንዛቤ መጠቀማቸውን፣ በየክልሉ የሚገኙት የሥርዓተትምህርት ባለሞያዎችና ሌሎቹም ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ሰፊ ውይይት አለማካሄዳቸውን፣ ወይም መጽሐፉን እንዲያዘጋጁ የተመረጡት ባለሙያዎች የልምድ ልውውጥ አለማድረጋቸውን ይጠቁማል የሚል ግንዛቤ እንድንይዝ ያደርገናል።

### *4.1.1.1. የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት አንፃር*

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ስንመርጥ ቀዳሚውን ትኩረት መስጠት ያለብን የትምህርቱን ዓላማዎች ስኬታማ ለማድረግ ያላቸውን ብቃት መመርመር ነው። የቋንቋ ትምህርት መሠረታዊ ዓላማዎች አራቱን የክሂል ዘርፎች እና ሁለቱን ንዑሳን የዕውቀት ዘርፎች (የሥነጽሑፍና የሥነልሳን

ዕውቀትን ማጎልበት) ከግብ ማድረስ እንደሆነ በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ላይ በሰፊው ተገልጿል። ከዚህ አንፃር በዚህ ንዑስ ክፍል ሥር ለሦስቱ ክልሎች የተዘጋጁት የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋውን ትምህርት ዓላማዎች ለማሳካት ያላቸው አመቺነት ወይም እርባና ይተነተናል።

## ሀ. *በጋምቤላ ክልል ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ትምህርት አላማዎችን ለማሳካት ያላቸው አመቺነት*

በጋምቤላ ክልል ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቁጥራቸው 20 ሲሆን ይህ ቁጥር ከቀሪዎቹ መጻሕፍት አንፃር ሲታይ እጅግ ከፍተኛ መሆኑን ከሠንጠረዥ አንድ ላይ መገንዘብ እንችላለን። ነገር ግን ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ በትክክል የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ያሳካሉ ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት 8ቱ ብቻ ናቸው። ቀሪዎቹ 12 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግን በሥራቸው ለቀረቡት መልመጃዎች በምንጭነት የማያገለግሉ ወይም የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ግልጽ በሆነ ሁኔታ ከግብ ለማድረስ የማያስችሉ ናቸው። የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ከሚያሳኩ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ የሚከተሉትን በምሳሌነት እንመልከት፤

"እንባ እፈልጋለሁ" በሚል ርዕስ፣ ከገጽ 103 እስከ ገጽ 108 ድረስ የቀረበው፣ ምንጩ ያልተገለጸ፣ ባለሦስት ትዕይንት ተውኔት የትምህርቱን ዓላማ በትክክል የማሳካት ብቃት አለው። ይህ ተውኔት ተመርጦ የቀረበው ተማሪዎቹ በምንጭነት (በሞዴልነት) ተጠቅመው እነሱም በክፍል ውስጥ ድራማ እንዲያዘጋጁ ታቅዶ ነው። በተጨማሪም የቀረበው ተውኔታ ውስብስብነት የሌለው ቋንቋ፣ የታሪክ መዋቅር፣ ገፀባህርያት፣ ጭብጥ፣ መቼት፣ ወዘተ. የተጠቀመ በመሆኑ ለተማሪዎቹ በመነሻነት ሊያገለግል ይችላል። በዚህ ተውኔት ውስጥ የሚገኙት ገፀባህርያት የዕድሜ ደረጃ ከተማሪዎቹ ጋር የማይመጣጠኑ ቢሆኑም ታሪኩ ግን የአገናኝነት ባህሪ ያለው በመሆኑ የተማሪዎቹን ሥሜት የመግዛት አቅም አለው። በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ ወቅታዊ በሆኑ ርዕሰጉዳዮች ላይ ተዘጋጅተው ተውኔት እንዲያቀርቡ አቅጣጫ ያመላክታቸዋል።

"ሰላም ይስፈን" ገጽ 122 እስከ 123፣ በሚል ርዕስ የቀረበው ምንጩ ያልተጠቀሰ ግጥም ዜማዊነቱን የጠበቀና ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ግልጽ የሆነ መልዕክት ያዘለ ነው። በዚህ ግጥም ሥር የቀረቡት መልመጃዎችም የትምህርቱን ዓላማ ያልዘነጉ ናቸው። ለተማሪዎቹ የግጥም ቅርጽ ከዝርው (ከስድ) ጽሑፍ የተለየ እንደሆነ የሚያስገነዝቡ ቅድመ ንባብ ተግባራት የሚገኙበት፣ በአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችም ስለስንኝ እና የሐረግ ምንነት የሚያወያዩ፣ በተጨማሪም ተማሪዎቹ ቤት መምቻን እና ቤት መድፊያን እንዲለዩ የሚያደርጉ ልዩ ልዩ መልመጃዎች በግጥሙ ላይ ተመስርተው ቀርበዋል። ባጠቃላይም ይህ ምንባብ የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃት አለው። በተመሳሳይ በተከታዮች ርዕሶች ሥር የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት አቅም ያላቸው ሆነው ተገኝተዋል፤

- "የአማላጁ መልዕክት" ገጽ 27-29፣ ከይልማ ሀብተየስ "ደላላው" ረኻርም ልቦለድ መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ፤
- "ሞልቶት" ገጽ 111-112 በሚል ርዕስ የቀረበ ተረት፤
- "ነፃነት" ገጽ 125 በሚል ርዕስ፣ ከአሰፋ ገብረማርያም "ፅጌረዳ ብዕር" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ግጥም፤
- "ንብና ትንኝ" ገጽ 126-127 በሚል ርዕስ የቀረበ፣ ምንጩ ያልተጠቀሰ ግጥም፤
- "ደብዳቤ አንድ" ገጽ 132-137 በሚል ርዕስ፣ በአጭር ልቦለድ መልክ የቀረበ ምንጩ ያልተጠቀሰ ምንባብ፤
- "ምንባብ ሶስት" ገጽ 171-175፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ" ረጅም ልቦለድ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ ምንባብ።

በሌላ በኩል "ስርቅታ" በሚል ርዕስ፣ በገጽ 62-64 ላይ የቀረበው፣ ከደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" ረጅም ልቦለድ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደው ምንባብ፣ የትምህርቱን ዓላማ ከማያሳኩት ሥነሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ አንዱ ነው። ይህ ምንባብ የቀረበው ሥርዓተነጥቦችን በተለይም የድርብ ሠረዝ አገልግሎትን እና ከአራት ነጥብ የሚለይበትን ባሕሪ ተማሪዎቹ በዓውድ (ከምንባቡ) ተረድተው በጽሑፋቸው ውስጥ እንዲገለገሉበት ለማድረግ ነው። በአንዳሩ በምንባቡ ውስጥ በጥቅም ላይ ውለው የምናገኛቸው ሁለት ድርብ ሠረዞችን ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንደኛው ብቻ በትክክለኛ ዓውድ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን አንዱ ግን ድርብ ሠረዝ በማያስፈልግበት ቦታ የገባ በመሆኑ በምላሌነት ሊያገለግል አይችልም። በአንዳሩ በዚህ ምንባብ ውስጥ

የትምህርተ ጥቅስ ሥርዓተነጥብ በሰፊው በአውድ ለማግኘት ይቻላል። በመሆኑም ይህ ምንባብ የድርብ ሰረዝን አውዳዊ አገባብ ሳይሆን የትምህርተ ጥቅስን ጠቀሜታዎች ለማሳየት ቢቀርብ የሻለ የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃት ይኖረው ነበር። ምንባቡ የተወሰደው ከእውቁ ደራሲ ሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር" ረጅም ልቦለድ ሥራ ላይ በመሆኑ በሥነጽሑፋዊ ሥራነቱ ላቅ ባለ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን ለታቀደው የትምህርት ዓላማ ግን ፋይዳ የለውም። ስለዚህ ከዚህ ዕውቅ የፈጠራዊ ሥራ ይልቅ የድርብ ሠረዝን ዓውዳዊ አገባብ በስፋት በያዘ ሥነጽሑፋዊ ሥራ መገልገል ይቻል ነበር።

### ለ. ለደቡብና ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት ያላቸው አመቺነት

በመጀመሪያ በደቡብ ክልል ከዚያም ይኸው መጽሐፍ በመጠነ ተሻሽሎ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ቀርቧል። በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች 13 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን መሉ በሙሉ ለያደርስ የሚችለው አንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ብቻ ነው። የሚከተሉት ማብራሪያዎች ለሁለቱም (ዓላማውን ለሚያሳኩት እና ለማያሳኩት) በምሳሌነት ቀርበዋል፤

"ተከሰተና ወይዘሮ ጽጌ" በሚል ርዕስ በገጽ 42-43 ላይ የቀረበው፤ ከሀዲስ አለማየሁ "የልምጥ" ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ ምንባብ የትምህርቱን ዓላማ በትክክል ያሳካል። ለዚህም ማጠየቂያው፤ አንደኛ የምንባቡ አቀራረብ መሉ በሙሉ በምልልስ ቴክኒክ (ጭውውት) መልክ የቀረበ ሲሆን በመርሐትምህርቱ ላይ የተቀረጸውም ዓላማ ተማሪዎች ምንባቡን በምንጭነት (በሞዴልነት) ተጠቅመው በተመረጡ ርዕሶችን ላይ ጭውውት እንዲያካሂዱ ለማስቻል በመሆኑ፤ ሁለተኛ በምንባቡ ስር የቀረቡት መልመጃዎች በሙሉ በምንባቡ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸው፤ ሦስተኛ የምንባቡ ይዘትና አቀራረብም የትምህርቱ እምብርት ወደሆነው ርዕሰጉዳይ ተማሪውን ሊያቀርብ የሚችል ነው። ለዚህ አስተዋጽኦ የሚያደርገውም የታሪክ ጭብጥ በአንድ ቤተሰብ ላይ የተመሠረተ በመሆኑና ከተማሪዎቹ የሕይወት ልምድ ብዙም ያልተራራቀ ነው። በተጨማሪ ገጸባሕርያቱ ሁለት ሲሆኑ አንደኛው ገፀባሕሪ በተማሪዎቹ የዕድሜ ክልል የሚገኝ ልጅ በመሆኑ

የሚናነገራቸው ቃላት (የቋንቋ አጠቃቀም) ግልፅና የማያደናግሩ ናቸው። ባጠቃላይም ይህ ምንባብ የተማሪዎቹን ቀልብ (ትኩረት) በመሳብ የትምህርቱን ዓላማም በተንዳኝነት የማሳካት ብቃት አለው ለማለት ይቻላል።

በአንፃሩ "ዳፋሩ አሸብር" ገጽ - 35፣ ከሲሳይ ንጉሱ "ረቂቅ አሻራ"፣ ረጅም ልቦለድ ላይ "መጠነኛ ማሻሻል ተደርጎ የተወሰደ" ቅንጫቢ ታሪክ የትምህርቱን ዓላማ ለማያሳኩት በምሳሌነት ሊጠቀስ ይችላል። ይህ ምንባብ የተመረጠው በመርሐትምህርቱ ላይ የተተለመውን የድርብ ቃል ዓውዳዊ አገባብ ለማሳየት (ለማለማመድ) እንዲውል ነው። በዚህም መሠረት ከምንባቡ ቀጥሎ የቀረበው መልመጃ ተማሪዎቹ ከምንባቡ ውስጥ ድርብ ቃላትን እያወጡ (እንዲያመለክቱ) የሚያዝ ጥያቄ ቀርቧል። ነገር ግን በምንባቡ ውስጥ በተጨባጭ የቀረበው ድርብ ቃል "ህገ-ወጥ" የሚለው ብቻ ነው፤ ከዚህ ውጭ በምሳሌነት የሚጠቀስ የትምህርቱን ዓላማ የሚያጠናክር ማሳያ ፍጹም ማግኘት አይቻልም። የመጽሐፉ አዘጋጆች ይህን ዓላማ የሚያሳካና በርካታ ጥምር ቃላትን የያዘ ምንባብ ቢመርጡ፣ ይህም ካልተቻለ ያካሄዱትን ማሻሻያ ገፋ አድርገው፤ ድርብ ቃላትን በማከል ቢያቀርቡት የተሻለ ይሆን ነበር።

በተመሳሳይ "ከባሌ መልስ" ገጽ 105 በሚል ርዕስ፣ ከሙሉጌታ ገደታ "የእንባ ጠብታዎች" ረዥም ልቦለድ መጽሐፍ ላይ የተወሰደ ቅንጫቢ ታሪክ የትምህርቱን ዓላማ አያሳካም። ይህ ምንባብ "ለዛ ካላቸው ንግግሮች" ውስጥ በፊሊጣዊ አነጋገሮችና በዘይቤአዊ አነጋገሮች መካከል ያለውን ልዩነት ምን እንደሆነ ተማሪዎቹ በንጽጽር እንዲረዱ የተመረጠ ነው። ይህ በመርሐትምህርቱ ላይ በግልጽ የሰፈረው ትልም በመማሪያ መጽሐፉም ውስጥ ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ መግቢያ ላይ (በቅድመ ምንባብ መወያያ ጥያቄነት) ቀርቧል። የምንባቡን ይዘት ስንፈትሽ የምናገኛቸው ከሰባት ያላነሱ ዘይቤአዊ አነጋገሮችን እንጂ ፊሊጣዊ አነጋገሮችን አይደለም። ስለዚህም ይህ የተመረጠው ምንባብ በመርሐትምህርቱ ላይ የተነደፈውን ዓላማ ከግቡ ሊያደርስ አይችልም።

ሐ. ለጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት ያላቸው አመቺነት

በጋምቤላ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የምናገኛቸው ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች 10 ሲሆኑ ከነዚህ መካከል 5ቱ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ የሚያሳኩ ናቸው። እነሱም፡-

- "ማነው ተጠያቂው" ገጽ 26 በሚል ርዕስ፣ በአለልኝ መኳንንት የቀረበ ግጥም፤
- "ትንሿ መንደር" ገጽ 54-56 በሚል ርዕስ፣ ከሸ.በሸ. ለማ "ሰብሉ አንድ ማሳ በላተኛው ሀምሳ" ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ ምንባብ፤
- "ደብዳቤው" ገጽ 69-70፣ ምንጩ ያልተገለጸ አጭር ልቦለድ (ትረካ)፤
- "ነገ ጥሩ ቀን ነች" ገጽ 79 በሚል ርዕስ፣ ሀይሉ ፀጋዬ በተባለ ገጣሚ የቀረበ ግጥም፤
- ርዕስ ያልተሰጠው ተውኔት ገጽ 83-84 ከመንግስቱ ለማ "ያላቻ ጋብቻ" ከተውኔት መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ፣

የሚሉት ይዘቶች ናቸው።

ከነዚህ ውስጥ ለአብነት ያህል ተከታዩን እንመልከት፤

## ማነው ተጠያቂው

*ወላጅ አዝናኙን ላነሆለለ፣*
*የቀለም አባቱን ላታለለ፣*
*በአንድ ምክንያት ለኮበለለ፣*
*ነገር አምታቶ ላባበለ፣*
*የእውቀት ማዕዱን ላቃለለ፣*
*የክፍሉን በር ለነቀለ፣*
*መስተዋቱንም ላጣጣለ።*
*መፀዳጃን በፀያፍ ቃላት ላረከሰ፣*
*ደረቱን ነፍቶ በቡድን ለተቧቀሰ፣*
*ወሬውን በማመለላለስ እብሪት ለፀነሰ።*
*በሰዎች አፉን ላሾከከ፣*
*የትምህርት ቤት አጥር ቀዳ ላሾለከ።*
*ከቁም ነገር ይልቅ ለአርቲ ቡርቲ ለተካነ፣*
*የትምህርት ቤቱን ስርዓት ለአመከነ።*
*ወጪ ወራጁን ለዘለፈ፣*
*የሰውን ክብር ላጎደፈ።*
*አዛውንትን በቅፅል ስም ላሳፈረ፣*
*ከመስራት ይልቅ ማውደልደል የለመደ፣*
*ኮረዶችን ለለከፋ ላስገደደ።*

*በነዲያን ምላሱን ላሰላ፣*
*ስልጡን መስሎ ላጥላላ።*
*ባህል ወጉን ለዘነጋ፣*
*ንሁህ ልምድ ላናጋ።*
*በደባል ሀባይ ለተምላ፣*
*መጤ ባህልን ላሰላ።*
*በዚህ አውቆ አጥፊ፣*
*ማን ይሆን ኃላፊ፣*
*ቀድሞ ተሰላፊ።*

*/ከአለልኝ መኳንንት/*

"ማነው ተያቂው" በሚል ርዕስ የቀረበው ይህ ግጥም በመርሐትምህርቱ ላይ የተተለመውን፤ ተማሪዎች "ለቃላት ቀጥተኛ እና ዓውዳዊ ፍች ይሰጣሉ።" በሚል ርዕስ የቀረበውን ዓላማ ለመተግበር የቀረበ ነው። በርግጥም ግጥሙ ውስብስብነት የማይታይበት እና ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ከባድ የሆኑ ቃላትን ያልያዘ ነው። በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ የግጥሙን አጠቃላይ መልዕክት ተረድተው፣ በተለይ የቃላትን ቀጥተኛ ትርጓሜያቸውን ወይም በዓውዱ ሲገቡ የያዙትን ፍች ለማስረዳት እንቅፋት አይገጥማቸውም። ከዚህም በተጨማሪ ግጥሙን ተከትሎ የቀረቡትና በቃላት ዓውዳዊና ቀጥተኛ ትርጓሜ ላይ ያተኮሩት መልመጃዎች ምንባቡን በምንጭነት ተጠቅመውበታል። ስለዚህ ባጭሩ ይህ ምንባብ የመርሐትምህርቱን ፈር ከመከተሉም በላይ የቀረበውን ዓላማ ለማሳካት ያስችላል።

በሌላ በኩል በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት ተከታዮቹ 5 ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከቋንቋ ትምህርቱ ዓላማ ጋር የማይዛመዱ ናቸው፤

- "ጽጌሬዳና ደመና" ገጽ 4፣ ምንጩ ያልተገለጸ ግጥም፤
- "ሁለቱ ጓደኛሞች" ገጽ 90-20፣ ምንጩ ያልተገለጸ ተውኔት፤
- "ከበሮ ሲያዩት ያምር" ገጽ 44-75 ተረት፤
- "አሜ ቴዎድሮስ" ገጽ 88፣ ምንጩ ያልተገለጸ ግጥም፤
- "ሽልንጌን" ገጽ 93-97፣ ምንጩ ያልተገለጸ አጭር ልቦለድ፤

ለምሳሌ "ሁለቱ ጓደኛሞች" በሚል ርዕስ የቀረበው ሥነጽሑፋዊ ሥራ በተዳሚነት ተማሪዎቹ "በአጣማሪ የተመሠረቱ ጥምር ቃላትን በዓውዳቸው በማሳየት ጥምር ቃላቱን የመሠረቱትን ሁለት ቃላት እየለዩ ፍችዎቻቸውን እንዲያመለክቱ (ከዓውዳዊ ፍችዎቻቸው ጋር እንዲያነፃጽሩ) እና ምሕንፃረቃላትን በመለየትና በመመሥረት እንዲገለገሉ" የሚለውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ነው። ነገር ግን ምንባቡን ተከትሎ የተዘጋጁት መልመጃዎች (ከምንባቡ ውስጥ በምሕፃረ ቃል ሊፃፍ የሚችል ሐረግ ወይም ዓረፍተነገር ነቅሶ ማውጣት

ስለማይችል) ምንባቡን በምንጭነት አልተጠቀመበትም። ስለዚህም ከምንባቡ ያፈነገጡ መልመጃዎች የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት በተግባር ላይ ውለዋል። በተመሳሳይ ያለ አጣማሪ የተመሠረቱ ጥምር ቃላትም በምንባቡ ውስጥ ስለሌሉ ይህ (ጥምር ቃላትን ያለአጣማሪው መመስረት) በመርሐትምህርቱ ላይ የተተለመውን ዓላማ ለመተግበር አልተቻለም። ስለዚህ በአጠቃላይ ይህ ምንባብ የታቀደውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ የማያሳካ ነው። ከላይ የተጠቀሱት ቀሪዎቹ አራት ይዘቶችም መሰል ችግሮች የታዩባቸው ናቸው።

### መ. ለደቡብና ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ለማሳካት ያላቸው አመቺነት

ለደቡብ ክልልና ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት 6 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ 4 ያህሉ ይዘቶች ተመሳሳይ ናቸው። ልዩነታቸው ለደቡብ ክልል በተዘጋጀው 8ኛ ክፍል መጽሐፍ ላይ ሁለት ተጨማሪ ሥራዎች "ሱጴ" እና "የአንድ ቀን ውሎ" በሚል ርዕስ የቀረቡ በመኖራቸው ነው። ስለዚህም በእነዚህ ሁለት ይዘቶች (ምንባቦች) ላይ የሚቀርበው ገለጻ ለደቡብ ክልል የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሐፍ ሲመለከት በቀሪዎቹ አራት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ የቀረበው ትንታኔ ግን ሁለቱንም ይመለከታል።

በተጠቀሱት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት 6 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ በመርሐትምህርቱ ላይ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ በትክክል የማሳካት ብቃት ያለው፣ "ሥነግጥም" በሚለው ምዕራፍ ሥር ርዕስ ሳይሰጠው ለደቡብ ክልል በተዘጋጀው መጽሐፍ ላይ በገጽ 175፣ በተመሳሳይ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በተዘጋጀው በገጽ 122 ላይ የምናገኘው ግጥም ብቻ ነው። የግጥም ይዘት እንደሚከተለው ቀርቧል፤

*ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት*

*ሁለት በራ ሰዎች ሲያልፉ በጎዳና፣*
*ዕቃ መሬት ወድቆ ብልጭ ሲል አዩና።*
*ተሸቀዳደመው ሄደው ከቦታው ሲደርሱ፣*
*ተፎካከሩበት ሁለቱም ሊያነሱ።*
*በሁዋላም ተማተው በጥፊ በጡጫ፣*
*አንደኛው ነጠቀ በጉልበቱ ብልጫ፣*
*አገላበጠና ቢመለከት ፈጥኖ፣*
*ዕቃውን አገኘው ማበጠሪያ ሆኖ።*
*እስቲ ሁላችሁም በሱ ፍረዱት፣*
*እሱ ራሱ በራ ጠጉር የለበት።*
*ሮጦ ተማቶ ቀምቶ ቢያመጣ፣*
*ምን ያደርግለታል ሚዶ ለመላጣ።*

( ምንጭ ዘሪሁን አስፋው ምንጭ ጠቅሶ ከከበደ ሚካኤል የወሰደው፣ የሥነጽሑፍ መሠረታውያን፣ አዲስ አበባ፣ 1992፣ ገጽ 76።)

ይህ ግጥም የተመረጠው በመርሐትምህርቱ ላይ "ግጥም ያነባሉ፣ ይጽፋሉ፣ የግጥምን ፍሬ ነገር ተረድተው ይገልጻሉ፣ የግጥምን ባሕርያት በሥርአት ማጣጣም ይችላሉ" የሚሉትን ዓላማዎች ለማሳካት ነው። በዚህም መሠረት ግጥሙን ስንመረምረው ዜማዊነቱን የጠበቀ፣ ምትና ምጣኔው የተስተካከለ፣ ግልጽ የሆነ አዝናኝ ታሪክ ያዘለ ነው (የግጥሙን መሉ ይዘት ከአባሪው ይመለከቷል)። የግጥምን ባሕርያት የሚያሟላ በመሆኑም የታቀደውን የትምህርት ዓላማ የማሳካት ብቃት አለው። በተጨማሪም የቀረቡት የተለያዩ መልመጃዎች ምንባቡን በምንጭነት ከመጠቀማቸው ባሻገር ከትምህርቱ ዓላማ ጋር የሚጣጣሙ ናቸው። በሌላ በኩል፣

- "የፊውስ ሐዋርያቶች" ባለአንድ ትዕይንት ተውኔት፣ ምንጩ ያልተገለጸ፣
- "ሥነቃል" ቃላዊ ግጥሞች፣
- "ሱጴ" ከበአሉ ግርማ "የህሊና ደውል" ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የቀረበ፣
- "የአንድ ቀን ውሎ" አጭር ልቦለድ፣ ምንጩ ያልተገለጸ፣
- "መሉ ልብስ" አጭር ልቦለድ፣ ከወጋየሁ ተበጀ "መሉ ልብስ" የአጭር ልቦለዶች ስብስብ መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፣

እነዚህ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመርሐትምህርቱ ላይ የታቀደውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የዘነጉ ናቸው። ለአብነት የሚከተለው ማብራሪያ ቀርቧል፤

"ሱጴ" በሚል ርዕስ የቀረበው ልቦለድ፣ በመርሐትምህርቱ ላይ የገለጸውን ተማሪዎች "የአማርኛ ፊሊጦችና ዘይቤአዊ ንግግሮችን ይተዋወቃሉ፣ ፊሊጣዊ ንግግሮችን የቋንቋው ተጠቃሚዎች እንዴት እንደሚጠቀሙበት በምሳሌ ማሳየት" የሚሉትን ዝርዝር ዓላማዎች ለመተግበር የቀረበ ነው። በመማሪያ መጽሐፉም ውስጥ በዚህ ምንባብ ሥር የቀረቡት ልዩ ልዩ መልመጃዎች ሙሉ በሙሉ ይህን የታቀደውን ዓላማ መሠረት ያደረጉ ናቸው። (ተማሪዎቹ በፊሊጣዊ እና በምሳሌያዊ ንግግሮች ልምምድ እንዲያካሂዱ የሚያደርጉ ናቸው።) ነገር ግን ምንባቡ ዘይቤአዊ አነጋገሮችን እንጂ ፊሊጣዊ አነጋገሮችን በአውዳቸው ለማስተማር ስለማያስችል (በምንባቡ ውስጥ ስለማይገኙ)፣ በመልመጃዎቹ ውስጥ የቀረቡት ፊሊጣዊ አነጋገሮች በምንባቡ ውስጥ በአውድ አናገኛቸውም። በተጨማሪም በምንባቡ ውስጥ የሚገኙት ዘይቤአዊ አነጋገሮች ውስን በመሆናቸው በመልመጃዎቹ ውስጥ የቀረቡት የተለያዩ ዓይነት ዘይቤዎች ከምንባቡ የወጡ አይሉም። ባጠቃላይ ይህ ምንባብ ለታቀደው የትምህርት ዓላማ የሚመጥን ባለመሆኑ ለመልመጃዎቹ በምንጭነት (በሞያሌነት) ሲያገለግል አልተስተዋለም። ቀሪዎቹ ከላይ የተጠቀሱት አራት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም ተመሳሳይ ጉድለት ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋል።

### *4.1.1.2. የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከመርሐትምህርቱ ትልም ጋር ያላቸው ተጣጥሞሽ*

ቋንቋን ለማስተማር የሚውሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ ከመርሐትምህርቱ ትልም ያፈነገጡና ለደረጃው የተመረጡትን ይዘቶች ያገናዘቡ መሆን እንደሚጠበቅባቸው በምራፍ ሁለት (ንዑስ ክፍል 2.3.2) ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቶበታል። ከዚህ መርህ አንፃር በደቡብ፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝና በጋምቤላ ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍሎች የተዘጋጁት መጻሕፍት፣ ለየደረጃው በተዘጋጁት መርሐትምህርቶች ላይ ተመሥርተው የተነደፉትን ዝርዝር ዓላማዎች ለመተግበር የሚያስችሉ፣ በክሂሎችና በዕውቀት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ልዩ ልዩ መልመጃዎች መቅረብ - አለመቅረባቸውን በተመለከተ በዚህ ንዑስ ክፍል ገለፃዎች (ትንታኔዎች) ይቀርባሉ።

## ሀ. ለጋምቤላ ክልል የተዘጋጀው 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍና የመርሐትምህርቱ ተጣጥምሽ

በጋምቤላ ክልል ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መመሪያ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት 20 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው መርሐትምህርት ውስጥ የተተለሙትን ዓላማዎች ሊያሳኩ የሚችሉት 10፣ ያህሉ ብቻ ናቸው። ቀሪዎቹ ግን ምንባቦቹን በምንጭነት ያልተጠቀሙ፣ ያፈነገጡ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን ያካተቱ ወይም ከመርሐትምህርቱ ጋር የማይገናኙ ናቸው።

በመርሐትምህርቱ ላይ ከተጠቆሙት ዓላማዎች ጋር የሠመረ ግንኙት ያላቸው ሥነጽሑፋዊ ምንባቦችም የሚከተሉት ናቸው፤

- "የአማላጁ መልዕክት" ገጽ 27-29፣ ከይልማ ሀብተየስ "ደላላው" መጽሐፍ የተወሰደ፣ የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ፤
- "እንባ እፈልጋለሁ" ገጽ 103-108፣ ምንጩ ያልተገለጸ፣ ባለ ሶስት ትዕይንት ተውኔት፤
- "ሞልቶት" ገጽ 111-112፣ ምንጩ ያልተገለጸ፣ ተረት፤
- "ጉዱ ካሳ" ገጽ 113-115፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ፤
- "ሰላም ይስፈን" ገጽ 112-123፣ ምንጩ ያልተገለጸ ግጥም፤
- "ነፃነት" ገጽ 125፣ ከአሰፋ ገብረማርያም "ዕጌረዳ ብዕር" ግጥም፤
- "ንብና ትንኝ" ገጽ 126-127፣ ምንጩ ያልተገለጸ ግጥም፤
- "ደብዳቤ አንድ" ገጽ 132-137፣" "ብዕር" ከተሰኘ ደብዳቤ መድብል ተቀንጭቦ የተወሰደ (ያልታተመ)፣ በአጭር ትረካና ግጥም መልክ የቀረበ፤
- "ምንባብ ሶስት" ገጽ 171-175፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ"፣ ከረጅም ልቦለድ ተቀንጭቦ የተወሰደ፤
- "ጅብ ነች" ገጽ 175-185፣ ከታደሰ ሊበን "መስከረም"፣ አጭር ልብወለድ የተወሰደ።

ለምሳሌ "የአማላጁ መልዕክተኛ" በሚል ርዕስ የቀረበው ሥነጽሑፋዊ ሥራ የተመረጠው በመርሐትምህርቱ ላይ "ቃላትን ያውቃሉ፤ የቃላትን ትርጉም (ፍች) ይሰጣሉ፤ የቃላትን ቀጥተኛና ዓውዳዊ ፍች ይሰጣሉ፤ የቃላትን ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ ይገልፃሉ" በሚል የቀረቡትን ዝርዝር ዓላማዎች ለማሳካት ነው። በመሆኑም ከዚህ ምንባብ የወጡ ቃላት ለዚህ ዓላማ ትግበራነት አገልግለዋል። በመልመጃነት የቀረቡት ሁሉም ተግባራትም ከቃላት ትምህርት ጋር የቀጥታ ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ስለዚህም ይህ ምንባብ ከመርሐትምህርቱ ጋር በምልዐት ይጣጣማል።

### ሐ. ለጋምቤላ ክልል የተዘጋጀው የፀኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ እና የመርሐትምህርቱ ተጣጥምሽ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች 10 ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ ከመርሐትምህርቱ ጋር የሚጣጣሙት 5 ያህሉ ብቻ ናቸው። እነዚህ 5 ይዘቶች ሁሉም የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ የማሳካት ብቃት አላቸው ማለት ሳይሆን በመርሐትምህርቱ ላይ የተጠቆመውን ይዘትና የትምህርት ዓላማ መሠረት ያደረጉ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። የሚከተሉት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በምሳሌነት ቀርበዋል፤

በገጽ 26 ላይ "ማን ነው ተጠያቂው" በሚል ርዕስ የቀረበው፣ በአለልኝ መኳንንት የተጻፈ ግጥም ከመርሐትምህርቱ ጋር የሰመረ ቁርኝት አለው፤ ምንባቡ በመርሐትምሕርቱ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ነው። "ለቃላት ፍች ይሰጣሉ" በሚለው አቢይ የትምህርቱ ዓላማ ሥር "ቀጥተኛ እና አውዳዊ ፍች መስጠት" የሚሉ ንዑሳን ዓላማዎች ቀርበዋል። በዚህም መሠረት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ምንባቡን ተከትሎ ከቀረበው የአንብቦ መረዳት መልመጃ በተጨማሪ የቀረቡት ሁለት መልመጃዎች በቃላት አውዳዊና ቀጥተኛ ፍችዎች ላይ ያተኩሩ በመሆናቸው ከመርሐትምህርቱ ጋር ለሚጣጣሙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በምሳሌነት ቀርቧል። በተመሳሳይ በተከታዮቹ ርዕሶች ሥር የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም በመርሐትምህርቱ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፤

- "ትንሿ መንደር" ገጽ 54-56፣ ከሺበሽ ለማ "ሰብሉ አንድ ማሳ በሰቲኛው ሀምሳ" መጽሐፍ ላይ "ለማስተማሪያ ተሻሽሎ የቀረበ"፤
- "ደብዳቤው" ገጽ 69-70 ምንጩ ያልተገለፀ፣ አጭር ልቦለድ፤
- "ነገ ጥሩ ቀን ነች" ገጽ 79፣ ከሀይሉ ፀጋዬ የቀረበ ግጥም፤
- ርዕስ ያልተሰጠው የተውኔት ቅንጫቢ፣ ገጽ 83-84፣ ከመንግሰቱ ለማ "ያላቻ ጋብቻ" የተውኔት መጽሀፉ ላይ የተቀነጨበ፤

በአንባሩ "ጽጌሬዳና ደመና" በሚል ርዕሰ የቀረበው ምንጩ ያልተገለጸ ግጥም፣ በመርሐትምህርቱ ላይ "ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን አዳብረው በተለያዩ

አጋጣሚዎች ሐሳባቸውን በአግባቡ ይገልጻሉ፤ ለክፍል ደረጃው በሚመጥኑ ርዕሶች ተዘጋጀተውና ማስታወሻ በመያዝ ንግግር ያደርጋሉ" የሚሉትን ዓላማዎች ለማሳካት ታቅዶ የተመረጠ ምንባብ ቢሆንም፣ በመልመጃነት የቀረቡት ተግባራት ግን በስንኞች ውስጥ የሚገኙ ፆታ-አመልካች ቃላት በተቃራኒያቸው እንዲተኩ፣ ግጥምን ወደ ስድ (ዝርው) ንባብ እንዲለውጡ፣ በግጥሙ ውስጥ በሚገኙ ዘይቤዎች ላይ እንዲወያዩና በቃላቸው ግጥም እንዲያቀርቡ የሚጠይቁ ናቸው። እነዚህ መልመጃዎች የተማሪዎችን የንግግር ችሎታ የማጎልበት አቅማቸው የደበዘዘ ነው። በመርሐትምህርቱ ላይ ያልሰፈረ ይዘት (የጽሀፈት ክሂልን ማጎልበት) ከንግግር ክሂል ተግባራት ጋር በጣምራነት መቅረቡ የተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ የንግግር ክሂልን ለማጎልበት የሚያስችሉ መልመጃዎችን ለማውጣት አመቺ አለመሆኑን ነው። ለዚህ ለታቀደው ዓላማ ከግጥም ይልቅ አንድ አጭር ልቦለድ ታሪክ ወይም ከረጅም ልቦለድ ላይ የተወሰደ ቅንጫቢ ታሪክ ቢቀርብ ተማሪዎቹን የሚያወያዩ ልዩ ልዩ ተግባራትን ማካተት ይቻል ነበር። ባጠቃላይ ይህ ግጥም በመርሐትምህርቱ ላይ የታቀደውን ዓላማ የማያሳካና ዓላማውን የሳተ ነው ለማለት ይቻላል። በተከታዮቹ ርዕሶች ሥር የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም ይህን መሠል ችግር ተስተውሎባቸዋል፤

- "ሁለቱ ጓደኞሞች" ገጽ 19-20 ምንጩ ያልተገለጸ፣ ተውኔት፤
- "ከበሮ ሲያዩት ያምር" ገጽ 74-75 ተረት፤
- ርዕስ ያልተሰጠው ግጥም፣ ገጽ 88 ምንጩ አልተገለጸም፤
- "ሽልንጌን" /ልብወለድ/ ገጽ 93-97 ምንጩ ያልተገለጸ፤

### መ. *ለደቡብ እና ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የተዘጋጁት የ8ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጻሕፍትና ለደረጃው የተዘጋጀው መርሐትምህርት ተጣጥመሽ*

ለደቡብ ክልል እና ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ ከሚገኙት 6 ሥነጽሑፋዊ የፊጠራ ሥራዎች ውስጥ ከመርሐትምህርቱ ትልም ጋር የሚጣጣሙት 4 ብቻ ናቸው። ቀሪዎች ምንባቦች ግን ከመርሐትምህርቱ ጋር የሠመረ ግንኙነት የላቸውም ማለት ይቻላል። ተከታዮቹ በምሳሌነት ቀርበዋል፤

"የፊውስ ሐዋርያዎች" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንጩ ያልተገለፀ "ባለአንድ ትዕይንት ተውኔት" ተማሪዎች "ጭውውት በስርዓት ያካሄዳሉ፤ የጭውውትን ሂደት ተከትለው የራሳቸውን አስተያየት ይሰጣሉ፤ ካሰባሰቧቸው ጭውውቶች፣ ምልልስች ውስጥ ጠቃሚ ናቸው ብለው የመረጧቸውን ያቀርባሉ።" በማለት በመርሐትምህርቱ ላይ የሠፈረውን የትምህርት ዓለማ ለመተግበር የተመረጠ ነው። የዚህ ተውኔት ታሪክ የሚያጠነጥነው 4ቱ ገፀባህርያት፤ (ሙሉነሽ፣ አክሊሉ፣ ሚስጥረና አዳነች) በትምህርታቸው ሂደት ላይ የሚያካሂዱትን ጭውውት በምልልስ ቴክኒክ የሚያቀርብ ነው። መልመጃዎቹም በቀረበው ተውኔት ላይ የተመሠረቱ ሲሆኑ በክፍል ሶስት የቀረበው መልመጃም ተማሪዎቹ ተውኔቱን አጥንተው በክፍል ውስጥ እንዲተውኑ የሚጠይቅ ነው። በነዚህ በተጠቀሱት ምክንያቶች ሳቢያ ይህ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከመርሐትምህርቱ ጋር ይጣጣማል ማለት ይቻላል። የምንባቡ ይዘት፣ የቀረበበት ቋንቋ፣ የገጸባሕርያቱ ማንነት፣ የሚወያዩበት ርዕሰጉዳይ፣ ወዘተ. ተማሪዎቹ በመርሐትምህርቱ ላይ የተነደፈውን ዓላማ እንዲተገብሩ የሚያበረታታ ነው።

በአንባሩ "የአንድ ቀን ውሎ" በሚል ርዕስ የቀረበ ምንጩ ያልተገለጸ አጭር ልቦለድ፣ ከመርሐትምህርቱ ጋር የሚሄድ አይደለም። ይህ ምንባብ የተመረጠው በመርሐትምህርቱ ላይ ጽሑፍን ማሳጠርና ማስፋፋት በተመለከተ ተማሪዎች "አንድን ጽሑፍ በሁለት ሦስተኛ (2/3) አሳጥረው ይጽፋሉ፤ አንድን ጽሑፍ ሐሳቡን አሳጥረው ፍሬነገሮችን ብቻ ተጠቅመው ይጽፋሉ" ተብሎ የቀረበውን ዓላማ ለማሳካት ቢሆንም ምንባቡን ተከትለው የቀረቡት መልመጃዎች ግን ይህን ዓላማ የዘነጉ ናቸው። "ጽሑፍን ማሳጠር" ለሚለው "ቃላትን፣ ሐረጋትን ወይም ዓረፍተነገሮችን በምሕላፊቃል አሳጥሮ መጻፍ" በሚል ያልተዛመደ ተግባር በመልመጃነት ተተክቶ ቀርቧል። ለዚህም ዓላማ ቢሆን ምንባቡ በምንጭነት ሲያገለግል አይታይም። ቀሪዎቹ ተግባራትም ተማሪዎቹ፤

- ከተሰጡት አማራጭ ርዕሶች አንዱን ምረጡና ተራኪ ድርሰት ጻፉ፤
- ዓረፍተነገሮቹን አስፋፍታችሁ ከሰባት አረፍተነገሮች ባላነሰ አንቀጽ ጻፉ፤

በሚሉ ትዕዛዛት ከመርሐትምህርቱ ያፈነገጡ ይዘቶች የተካተቱበት ነው። ስለዚህ ይህ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከመርሐትምህርቱ ጋር አይጣጣም፤

### 4.1.1.3 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ያላቸው ተገቢነት

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ያሳኩ ዘንድ ከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ፍላጎት (interests) ወይም ዝንባሌ ጋር የሠመረ ግንኙነት ሊኖራቸው ይገባል። ተማሪዎቹ ከሕይወት ልምዳቸው የራቁ ጉዳዮችን ለያዙ ታሪኮችና ለዛ፣ ውበትና ማራኪነት ለጎደላቸው ምንባቦች ትኩረት ሊሰጧቸውና በጉጉት ሊያነቧቸው አይችሉም። ስለዚህም አንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከመመረጡ በፊት የተማሪዎቹን ማንነት (ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ ዝንባሌ፣ ዓላማ፣ የአዕምሮ ብስለት) በጥንቃቄ መመርመር ይኖርበታል። ከዚህ ርዕሰጉዳይ አንፃር በሦስቱ ክልሎች በተዘጋጁት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጻሕፍት ላይ ከቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ በተለይ በአጭር ልቦለዶች እና በረዥም ልቦለዶች ቅንጫቢ ታሪኮች ላይ ችግሩ ጎልቶ የተስተዋለ ሲሆን በአንፃራዊነት ሲታዩ በግጥሞቹ፣ በተውኔቶቹና በተረቶቹ ላይ ጎልቶ የወጣ ችግር አልተስተዋለም ለማለት ይቻላል።

በዚህ ጥናት ውስጥ ከተገቢነት አንፃር ችግሮች ያሉባቸውን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በጠቅላላ አቅርቦ ትንታኔ ለማቅረብ ጊዜና ቦታ ስለሚገድብ መታለፍ የሌለባቸውና ጎላ ጎላ ያሉ ችግሮች የተስተዋለባቸውን በተመሳሰሉነታቸው (በየዓይነታቸው) በመለየትና ለየአንዳንዱ ምድብ ማሳያ የሚሆኑትን በማቅረብ ትንታኔ ይሰጥባቸዋል፤

*ሀ. ከተማሪዎቹ የአእምሮ ብስለት (እድሜ) ጋር የሚጋጩ*

የተማሪዎቹ የአእምሮ ብስለት (ዕድሜ) ከግምት ሳያስገቡ የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ስራዎች 4 ያህል ሲሆኑ በእነዚህ ሥራዎች ውስጥ የቀረበው ታሪክ በገፀባሕርያቱ መካከል ገደብ የለሽ የሆኑ የተቃራኒ ጾታ ግንኙነቶችን ምስል ካሳች በሆኑ ቃላትና ዘይቤአዊ አገላለጾች የሚያሳዩ ናቸው። ለአብነት የሚከተሉትን ከየምንባቦቹ ተቀንጭበው የተወሰዱትን እንመልከት (የምንባቦቹን መሉ ይዘት ከአባሪው ይመለከታል)፤

ምሳሌ 1፡- ለጋምቤላ ክልል በተዘጋጀው የ7ኛ ክፍል መጽሐፍ "ምንባብ ሁለት" በሚል ርዕስ በገጽ 80-84 ላይ የቀረበ፤ ከበአሉ ግርማ፣ "ከአድማስ ባሻገር" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤

ረጅም አንገቷን በትኩስ ከንፈሮቹ መዳሰስ ቢያሰኘውም ቅሉ ወኔው እንደገና ከዳው ግን ጊዜውን አላጠፋም ወደቤቱ ይዟት ከነፈ። ወደቤቱ ይዟት ሲበር በሐሳቡ አልጋ ውስጥ ገብተው ሲጫወቱ፣ ሲስማት ስትስመው፣ ሲያቅፋት ስታቅፈው ገላው የሷን ገላ ጠረን ወስዶ በደስታ ሲረካ ታየው። ...

በቁምሳጥኑ መስታወት ጠይም ፊቷን የብር እንክብል የመሳሰሉትን አይኖቿን እያየች የጣኦት ሥሜቷ በመምጣት ላይ ሳለ ራስ ምትሃት እንደያዘው ሰው በጭፍኑ እየተሳበ፣ እየተንተተ፣ እያደባ መጥቶ እንደ እሳት በሚነድ ከንፈር ማጅራቷን በሰመመን ይስም ጀመር። . . . አልጋው ጫፍ ላይ ቁጭ ብሎ እንደ አገዳ ቀጥ ብለው የወጡትን እግሮቿንና ሳይወዱ የሚያናግሩትን ዳሌዋን እያየ ልሂድ ልቅር እያለ ከራሱ ጋር ብዙ ተሟግቷል። መመለሻ አልነበረውም ፊት ለፊት ዙራ ጡቶቿ እንደሌባ ጣት እየጠቆሙት ከንፈሯን አላቃ ሰጠችው የዕፄሬዳ እምቡጥ የሚመስለውን ከንፈሯን ፊልቅቆ የትንፋሿ መዓዛ የከንፈሯን ማር እንደንብ ቀሰመ።

እንደረመጥ የሚፋጁትን ከንፈሮቿ ላይ ሳያነሳ የጋለውን ሰውነቷን ከሰውነቱ ሳይርቅ እቅፉን ሳያላላ በመካከላቸው የተፈጠረውን የምትሀት ሀይል ሳይቀንስ የትንፋሿን ሽቶ እየጠጣ "ከሰላም ሰገነት" ላይ አብሯት ወደቀ።

ምሳሌ 2፦ ለጋምቤላ ክልል በተዘጋጀው የ7ኛ ክፍል መጽሐፍ "ካርለት" በሚል ርዕስ በገጽ 35-37 ላይ የተወሰደ፤ የቀረበ፤ ከፍቅረማርቆስ ደስታ፣ "ድንግል ውበት" የረኘም ልቦለዶች ስብስብ መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤

"በደረትና ትከሻዋ አካባቢ ቁጥር ያለ የውሃ እንክብል ከመታየቱም ባሻገር አሴት ብልት ላይ ካለው ስስ ወጉር ላይ ደግሞ በውርጭ ሰሞን ሳር ላይ የሚትየውን የመሠለ ትንንሽ የውሃ ነጠብጣብ ይታያል።

... ካርለት ወደ መስታወቱ ቀርብ እንዳለች ገጽታዋ ከሚያሻው መስታወት ውስጥ ተከፋፍሎ ታያት መስታወቱን ተወት አድርጋ በእጆቿ ጡቶቿን ጨበጥ ጨበጥ አደረገቻቸው ቀኝ እጇ ግን ወደ ታች እየተንሸላወሰ ገዛ ጀመረ ወደ ሴት ብልቷ እጇ የደረሰበትን በአይኗ ተመለከተችው። ....

ካርለትና ስቲቭ የስራ ቦታቸው በጣም የተራራቀና የትራንስፖርትም ችግር ያለበት በመሆኑ ተመልሶ ለመገናኘት ቢያንስ የሦስት ወር ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። በፍቅር አባዜ ለተያዙት ለእነዚህ ወጣቶች ደግሞ ጊዜው የትየለሌ ነው - ፋቅ። ስለመለያየተቸው እንጂ ስለመገናኘትቸው የማይተማመኑት ፍቅረኞሞች በወሲብና በፈቅር ጨዋተ ሰዓታቸውን በሚገባ ለመጠቀም በአንድ ወጥ ስሜት ጥረዋል። ድብቅነት በሌለው ንፁህ የፍቅር ጨዋታ ልባቸውን ስልትና ቃናው በሚጣፍጥ

*ቅላፄ እያስጨፈሩ ራሳቸውን በመሆን በፍቅር ባሕር ከመዋኘት አልፈው ዘቅጠውበት አድረዋል።*

እነዚህ ለአብነት የቀረቡት ሁለት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተማሪዎቹ በመርሐትምሕርቱ ላይ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ እንዲተገብሩ አያስችሉም። ተማሪዎቹ ምንባቦቹ ከቀረቡበት ቋንቋ ይልቅ ለይዘቶቻቸው ቅድሚያ እንዲሰጡ ያደርጋሉ። ከዚህም ባሻገር ከዚህ ቀደም አድርገውት ወይም አስበውት የማያውቁትንና እድሜያቸው የማይፈቅደውን ልቅ የሆነ የተቃራኒ ፆታ ግንኙነቶች በተግባር እንዲፈጽሙ የሚያሳሱ ሊሆኑ ይችላሉ። በተመሳሳይ በተከታዮቹ ርዕሶች ሥር የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም ከላይ የተጠቆመው ዓይነት ችግር ተስተውሎባቸዋል፤

- ጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል፣ በገጽ 83-84 ላይ፣ ርዕስ ያልተሰጠው ተውኔት፣ ከመንግስቱ ለማ "ያላቻ ጋብቻ" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- ጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 175-186፣ "ጅብነች" በሚል ርዕስ የቀረበ አጭር ልቦለድ፣ ከታደሰ ሊበን "መስከረም" የአጭር ልቦለድ መድብል የተወሰደ

### *ለ. ከተማሪዎቹ ዝንባሌ፣ መዝናኛ ወይም ዓላማ አንፃር ሲታዩ ተገቢነት የሌላቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች*

የተማሪዎቹ የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያ ተግባራት (መዝናኛዎች)፣ ዝንባሌ እና ዓላማ ከግምት ውስጥ ሳይገባ የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች 5 ያህል ሲሆኑ በነዚህ ሥራዎች ውስጥ የሚገኙት ገፀባሕርያት እድሜያቸው ከተማሪዎቹ ዕድሜ በላይ በመሆኑና የሚያከናውኗቸው ተግባራትና የሚወያዩባቸው ርዕሰጉዳዮች ከተማሪዎቹ የአእምሮ ብስለት ጋር ስለማይዛመዱ፣ በ7ኛ ወይም በ8ኛ የክፍል ደረጃ ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች የማይመጥኑ ናቸው። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፤

ምሳሌ 1፦ ለጋምቤላ ክልል በተዘጋጀው የ7ኛ ክፍል መጽሐፍ በገጽ 27-29 ላይ "የአማላጁ መልዕክት" በሚል ርዕስ፣ ከይልማ ሀብተየስ "ደላላው" ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ የተወሰደ፤

*ቅዳሜ ምሽት ገና አንድ ሰአት ቢሆን ነው ደረጀ አለመ. ከአንድ ዘመናዊ ሀንፃ ከሶስተኛ ፎቅ ላይ ከተከራየው ውብ አፓርትመንት ውስጥ ውስኪ በመለኪያ ቀድቶ መዚቃ እየሰማ ብቻውን ከአንደኛው ሶፋ ላይ ተቀምጦ ይዝናናል። ደረጀ የሃያዘጠኝ ዓመት ወጣት ነው። የዳበረ*

*ሰውነትና ጥሩ ቁመና አለው። መልከመልካምና ወጉረ ሉጫ ሲሆን አፍንጫው ቀጥ ያለ ሆኖ ከንፈሮቹ ስስ ናቸው። የጥርሶቹ አበቃቀል መስመራቸውን ከመጠበቃቸውም በላይ ሲጃራ እንደሚያጨሱ ሳይሆን ንጣታቸው አይን ይማርካል። ደረጃ ከመጠጡ ሊጎነጭ ሲል የደውል ድምጽ ሥለሰማ መለኪያውን አስቀምጦ በሩን ሲከፍተው ከተፈራ በላይ ጋር አይን ለአይን ግጥም አሉ።*

*ተፈራ በላይ ቁመቱ አጭር ሲሆን ሰውነቱም ፈርጠም ያለ ነው። ወጉሩ ከግራና ቀኝ ወደኋላ መሸሽ ቢጀምርም እድሜው ከሰላሳ አይበልጥም... (ሙሉ ይዘቱን ከአባሪው ይመለከታል)።*

በዚህ ምንባብ ውስጥ የተገለጹት ሁለት ገጸባሕርያት በ29 እና 30 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሲሆኑ የዕረፍት ጊዜያቸውንም መጠጥ በመጠጣትና ሲጋራ በማጤስ እንደሚያሳልፉ በታሪኩ ላይ ተጠቁሟል። ከዚህ በተጨማሪ የሚወያዩበት ርዕሰ ጉዳይም ስለ አንዲት በቀጠሮው ሰዓት ስላልደረሰች ሴት ነው። ከዚህ አንፃር ይህ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከተማሪዎቹ ዝንባሌ፣ ዓላማ ወይም የእረፍት ማሳለፊያ ተግባራት ጋር የማይገናኝ በመሆኑ ተገቢነት የለውም ለማለት ይቻላል። በተመሳሳይ የሚከተሉት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ተገቢነት የሌላቸው ሆነው ተገኝተዋል፤

- ጋምቤላ ክልል፣ 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 103-108፣ "እንባ እፈልጋለሁ" በሚል ርዕስ የቀረበ ምንጩ ያልተገለጸ ተውኔት፤
- ደቡብ እና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች፣ 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 35 እና 37፣ "ደፋሩ አሸብር" በሚል ርዕስ፣ ከሲሳይ ንጉሱ "ረቂቅ አሻራ" መጽሐፍ የተወሰደ፤
- ደቡብ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች፣ 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 76 እና 74፣ "ገዳምነሽ" በሚል ርዕስ፣ ከአብዱራህመቶ "መሸራውና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች" መጽሐፍ የተወሰደ፤
- ደቡብ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች፣ 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 113-114 እና 107-108፣ "ውለታ" በሚል ርዕስ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" ረጅም ልቦለድ መጻሐፍ ላይ የተወሰደ፤

### *ሐ. ለዛ፣ ውበት፣ ማራኪነት ወይም መስሕብ የሌላቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች*

የፈጠራ ሥራዎች ሁሉ የተማሪዎችን ቀልብ ይስባሉ ማለት አይቻልም። ለቋንቋ ማስተማሪያነት የምንመርጣቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተማሪዎችን ስሜት በመቆጣጠር (በመግዛት) ወደታቀደው የትምህርት ዓላማ የሚያሸጋግሩ ሊሆኑ ይገባል።

በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ 6 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግን ከዚህ ርዕሰጉዳይ አንፃር መቅረብ የማይገባቸው ሆነው ተገኝተዋል። ለምሳሌ በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል በገጽ 126-128 ላይ፣ "ንብና ትንኝ" በሚል ርዕስ የቀረበው "ግጥም" የግጥም ባሕሪ ፍጹም የማይታይበትና ከግጥም ይልቅ ወደ ኢልቦለዳዊ (ዝርው) ጽሑፍ የሚያደላ ሥራ ነው። ለአብነት የተወሰኑ ስንኞችን እንመልከት፡-

## *ንብና ትንኝ*

*ከዕለታት አንድ ቀን በመስከረም ወር*
*ድንገት መጣሁና ንፋስ ለመቀበል።*
*አንዲት ንብ አየሁኝ በሰማይ ስትበር*
*እንደምታውቁትም መስከረም ሲጠባ*
*ይፈላለጋሉ ንቢትና አበባ።*
*የዝናብ ጊዜ አልፎ ስትወጣ ፀሀይ፣*
*ትንኝ ይወለዳል ከየቆሻሻው ላይ።*
*ስለዚህ በዚህ ወር የትንኝ መንጋ*
*በጣም ያስቸግራል ባየር ላይ ሲንጋጋ።*
*ወይዘሮ ንቢትም አበባ ስትቃኝ።*
*ድንገት አገኘቻት አዲሲቷን ትንኝ።*
*ከዚህም በኋላ ሁለቱም ነፍሳት፣*
*ክፉ ጠብ አነሱ እዚያው እኔ ፊት*
*እኔም በዚህ ጊዜ ቢጨንቀኝ ቢጠበኝ*
*ልረዳ ተነሳ ለወይዘሮ ትንኝ።*
. . .

(ግጥሙ በሁለት ገጽ የቀረበ ነው፤ ሙሉ ይዘቱን ከአባሪው ይመለከቷል።)

ይህ ከላይ የቀረበው ጽሑፍ ግጥም ሊያሰኘው የቻለው ከግራና ቀኝ ገባ ብሎ መቅረቡ ብቻ ነው። ምክንያቱም በቀረበው ሥራ ላይ ምንም ዓይነት ቃላት ሳይታከሉበት እንደሚከተለው በዝርው (ወደገሙ ተጽፎ) ሊቀርብ ይችላል፤

*ከዕለታት አንድ ቀን በመስከረም ወር ንፋስ ለመቀበል ድንገት መጣሁና አንዲት ንብ በሰማይ ሰትበር አየሁኝ። እንደምታውቁትም መስከረም ሲጠባ ንቢትና አበባ ይፈላለጋሉ። የዝናብ ጊዜ አልፎ ፀሀይ ስትወጣ ከየቆሻሻው ላይ ትንኝ ይወለዳል። ስለዚህ በዚህ ወር የትንኝ መንጋ በአየር ላይ ሲንጋጋ በጣም ያስቸግራል። ወይዘሮ ንቢትም አበባ ስታቃኝ አዲሲቷን ትንኝ ድንገት አገኘቻት። ከዚህም በኋላ ሁለቱም ነፍሳት እዚያው እኔ ፊት ክፉ ጠብ አነሱ። እኔም በዚህ ጊዜ ቢጨንቀኝ ቢጠበኝ ለወይዘሮ ትንኝ ልረዳ ተነሳሁ።. . .*

ግጥሙ ዘወትሯዊ ቃላትን ብቻ ከመጠቀሙም ባሻገር ምጣኔውን (ዜማውን) ያልጠበቀና ለዚህ የክፍል ደረጃ ተማሪዎች ተገቢነት የጎደለው ነው። በተመሳሳይ ተከታዮቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም ማራኪነት ኖሯቸው ተማሪዎችን ወደታቀደው የትምህርት ዓላማ የማሸጋገር ሀይል ስለሌላቸው ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ተገቢነት የላቸውም፤

- "ብርቱ ፍቅር" ደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 18 እና 17፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" የተወሰደ፤
- "ስርቅታ" ጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 62-64፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" የተወሰደ፤
- "ሞልቶት" ጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 111-112፣ ምንጩ ያልተገለጸ አጭር ልቦለድ፤
- "ሁለቱ ጓደኞሞች" ጋምቤላ 8ኛ ክፍል፣ ገጽ 19-20፣ ምንጩ ያልተገለጸ ተውኔት፤
- "ነገ ጥሩ ቀን ነች" ጋምቤላ 8ኛ ክፍል፣ ገጽ 79፣ ከሀይሉ ፀጋዬ የመጽሐፉ ርዕስ - ያልተገለጸ ግጥም፤

### 4.1.1.4 ከተማሪዎቹ ሥነልሳናዊ ተክህኖ ዳራ አንፃር

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በየክፍል ደረጃው የሚገኙ ተማሪዎችን ሥነልሳናዊ ተክህኖ ዳራ ያገናዘቡ መሆን ይኖርባቸዋል። የተማሪዎችን የአንብቦ መረዳት ብቃት የሚቀንሱ እንደ ዘዬአዊ ቃላት፣ ሞያዊ ቃላት፣ የአራዳ ቋንቋ ቃላት እና ያልተዘወተሩ ፈሊጣዊ፣ ምሳሌያዊና ዘይቤአዊ አገላለጾች ተመጥነው መቅረባቸውን በጥንቃቄ መፈተሽ ያስፈልጋል። ከዚህም ባሻገር ለመረዳት አስቸጋሪ የሆኑ ውስብስብ እና በጣም ረጋሾም ዓረፍተነገሮችን በተጨማሪ ሰዋስዋዊ ግድፈት ያለባቸው አገላለጾች መኖር አለመኖራቸውን መመርመር እንደሚገባ የተለያዩ ምሁራን ገልፀዋል። ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡትን

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ስንፈትሽ በተረት፣ በግጥም እና በተውኔት መልክ በቀረቡት ሥራዎች ላይ ችግሩ ጎልቶ ባይታይም፣ ከረዥም ልቦለዶች ላይ በተወሰዱት ቅንጫቢ-ታሪኮችና በአጭር ልቦለዶቹ ላይ ለአፈ-ፈት ተናጋሪዎችም ሆነ ለኢ አፈ-ፈት (ሁለተኛ ቋንቋ) ተናጋሪዎች ግልጽነት የጎደላቸው የአገላለጽ ስልቶችን እናገኛለን። ለአብነት ያህል የሚከተሉትን እንመልከት፤

*ሀ. ውስብስብ ወይም የተንዛዙ ሐሳቦችን የያዙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች*

ከቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለሁለተኛ ደረጃ (ለ9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች) ተማሪዎች ቢቀርቡ ግልፅነት የጎደላቸው፣ ውስብስብ ወይም የተንዛዙ ሐሳቦችን የያዙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተካተዋል። ተከታዮቹ ይህን የሚጠቁሙ ናቸው፤

ምሳሌ 1፡- ጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 132 ላይ፣ "ደብዳቤ አንድ" በሚል ርዕስ በቀረበው አጭር ልቦለድ ውስጥ ተከታዩን እናገኛለን፤

*... መጠየቅ የማወቅ በር ነው፣ ሲያሸልብ የኖረ አእምሮ እያዘጋ መክፈቱ የሚታወቀው የዚህችን አለም ማራኪ በይው አስቀያሚ እውነታ የሚያየው ሀሊናሽ የመጠየቅ ብረት ለድልድይ መስሪያ ሲዘጋጅ ነው። የሚገርመኝ ግን እኔ ያንቺን እጥፍ እድሜ ኖሮኝ እንኳን ስለማንነቱ የማልጠይቅ ጅል የነበርሁ መሆኔ ነው።*

*. . . ትናንት ኖረን ነበር በትላንት ላይ ሞተን ዛሬ ላይ ደርሰናል። . . . ታዋቂ ሰው ሁሉ አዋቂ ባይሆንም አዋቂ ሆኜ ታዋቂ መሆን እፈልጋለሁ።*

ምሳሌ 2፡- በደቡብ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል በ7ኛ ክፍል ላይ፣ በገጽ 51 እና 52 ላይ፣ "ብቸኝነት" በሚል ርዕስ፣ ከአሰፋ ገብረማርያም "እንደወጣች ቀረች" ረጅም ልቦለድ ላይ የተወሰደ፤

*ላባቶቻችን ነፍስ መታሰቢያ ደማቸው የፈሰሰት ቦታ የመታሰቢያ ሀውልት ቁሞበት ለምለም ሆኖ እንዲኖር ታላላቅ ዛፎች ፀድቀውና ለምተው ላያቸው ደስ ያሰኛሉ። በእውነት የጠፋውን በቦታው ለመመለስ*

*በሚደረገው የመውጣት የመውረድ ድካም አንቺን የማስታውስበት ጊዜ የለኝም ነበር። የማይቀረው ቀን አልፎ የማይቀረው ሌሊት ሲተካ አንዳንድ ጊዜ አካል አርፎ ነፍስ መድከሟን አታቋርጥም የመጀመሪያው የድካሜ እንቅልፍ ሲያልፍ ያንቺ ክኔ መለየት ትዝ እያለኝ ሀዘኔ ይበረክታል።*

*የሰው ምኞት የሚምላለት ችግሩን የሚያዋየው ረዳት ጓደኛ ሲኖረው መሆኑ የታወቀኝ ዛሬ እድሜዬ ይበልጥ እየጠና ያለፈውንና ያሁኑን እያወዳደርኩ በዚህ አካኋን ብቻዬን እስክመቼ እኖራለሁ ብዬ ግራ ሲገባኝ ነው። ቀን ከኔ ጋር ሲደክመ የዋሉ ሰዎችና እንስሶች ማታ ሲሆን ሁሉም ወደማደሪያ ቤታቸው ሲበታተኑ ዥር ባለው ሌሊት ውስጥ እኔና ሀሳብ ገላጋይ በሌለበት ቦታ ግንባር ለግንባር ትግል እየገጠምን ከሁለት አንዳችን መጣል እየተሳነን ነጋም ያው በመሆኑ ተቸገርኩ አንቺስ ውሎሽ ከብዙ ጋር ሆነና ልብሽ ጠና፣ ያም ብዙ ክፉና ደግ ያየሽበት ምድር አልናፍቅሽ አለ።...*

ምሳሌ 3፡- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 173 ላይ፣ "ምንባብ ሶስት" በሚል ርዕስ፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ" ረጅም ልቦለድ ላይ የተወሰደ፤

*... "ይኸው ራሴን ከፈትኩት፣ ስለ እኔና አንተ የሚናገር ሰነድ በውስጤ የለም። እንደቆረፈደ ቆዳ ብቸኝነት ለምን ጨባበጠን . . . ወንድዬ? . . .*

*ሌሎች የዋጋ ተመን ይገባናል፣ "በዚህች አለም ላይ ያለ ነገር ሁሉ የሚሸጥና የሚገዛ ነው የሚሉት ደግሞ ሰውን ጤነኛና በሽታኛ የሚያደርገው ኪሱ ነው፤ ሌላው ነገር ሁሉ እንደ ኑግ በገንዘብ ሲወቀጥ የሚቅለጠለጥ አልባሌ ነው።" ይላሉ።*

ከላይ በቀረቡት ሦስት ምሳሌዎች ውስጥ ፍልስፍናዊ ሐሳቦችንና የተንዛዙ አገላለጾችን በማካተታቸው ምክንያት ማስተላለፍ የተፈለገውን ሐሳብ በቀላሉ ለመረዳት ያዳግታል። ስለዚህም ተማሪዎች አጠቃላይ የምንባቡን ይዘት ከመረዳት ይልቅ እነዚህን በመሳሰሉ አገላለጾች ላይ በማተኮር፣ አላስፈላጊ ምርመራ ውስጥ ገብተው ጊዜያቸውን-ሊያባክኑ ይችላሉ። ከዚህ የከፋው ሌላው አሳሳቢ ጉዳይ ግን በተለይ ይህ (ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል) መጽሐፍ የተዘጋጀው ለኢአፈ-ፊት (አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች በመሆኑ አንዳንድ ዘይቤአዊ አገላለጾችን ቃል በቃል በመተርጎም

የተሳሳተ ግንዛቤ እንዲይዙ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ። በሌላ በኩል የአገላለጽ ስልቱን እንደ መደበኛ የቋንቋ አጠቃቀም በመውሰድ ሊገለገሉም ይችላሉ። በተመሳሳይ ይህን መሰል ውስብስብና አመራማሪ የአገላለጽ ሥልት የሚገኙባቸው ምንባቦችም የሚከተሉት ናቸው፣

- ደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ 7ኛ ክፍል ገጽ 113-114 እና 107-108፣ "ውለታ" በሚል ርዕስ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" ልቦለድ መጽሀፍ የተወሰደ፤
- ጋምቤላ ክልል፣ 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 113-115፣ "ጉዱ ካሳ" በሚል ርዕስ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" ልቦለድ መጽሐፍ የተወሰደ፤
- ደቡብ ክልል፣ 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 8፣ "ያባት ምርቃትና አደራ" በሚል ርዕስ፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "ከቡስካ በስተጀርባ" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤

### *ለ. ዘዬያዊ፣ ምያዊ፣ የአራዳ ቃላትና ያልተዘወተሩ ቃላትን (ሐረጋትን) ያካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች*

በዚህ ምድብ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ዘዬያዊ፣ ሙያዊ፣ የአራዳ ቃላትን ወይም ያልተዘወተሩ ቃላትን በብዛት በመጠቀማቸው የተማሪዎቹን የንበት ሂደት የሚገቱ ናቸው። የሚከተሉት ለአብነት ቀርበዋል፤

ምሳሌ 1፡- ጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 62-64 ላይ፣ "ስርቅታ" በሚል ርዕስ በቀረበው ረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ ታሪክ ውስጥ የሚከተሉትን ዘዬያዊና እንግዳ ቃላት ተደጋግመው እናገኛለን፤

- ሻርዴ (አራት ጊዜ)
- ዳባ (ሦስት ጊዜ)
- የሚያባጥለው
- የሚያሳለድፍ
- መበያው
- ማንኩዋረፍ
- ጋሬጣ (ሁለት ጊዜ)
- በቅሎዋን አራግፎ
- የተመረገ
- ቀፎ አውራጆች
- የኋሊት
- አጋደሚቸው
- ለቃውንት

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ዘዬያዊና መደበኛ ያልሆኑ እንግዳ ቃላትና ሐረጋት በአንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራ ውስጥ የሚገኙ ናቸው። እነዚህን ቃላትና ሐረጋት ለኢአፈ-ፈት (ሁለተኛ ቋንቋ) ተናጋሪ ተማሪዎች ቀርቶ አፈ-ፈት ለሆኑ የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ፍችዎቻቸውን በቀላሉ ይረዷቸዋል ለማለት አያስደፍርም። ስለዚህም

ተማሪዎቹ ምንባቡን በፍጥነት አንብበው በመረዳት፣ አንብቦ መረዳትና ሌሎች መልመጃዎችን ለመተግበር እንቅፋት ሊፈጥርባቸው ይችላል። በሌላ በኩል አንዳንዶቹን ዘዬአዊ ቃላት እንደመደበኛ ቃላት ወስደው በዕለት ተዕለት ንግግራቸው ላይ ሊገለገሉባቸውም ይችላሉ።

ምሳሌ 2፡- በደቡብ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ 8ኛ ክፍል፣ በገጽ 79-83 እና 29-64 ላይ፣ "የፈውስ ሐዋርያዎች" በሚል ርዕስ ለቀረበው፣ ምንጩ ያልተገለጸ ተውኔት የሚከተሉት የአራዳ ቋንቋ ቃላት (ሐረጋት) ተደጋግመው ቀርበዋል፤

- ፎራፊነትህን
- ነቁብህ
- ይሸወዳል (4 ጊዜ)
- ግግም ያሉ (3 ጊዜ)
- ቀለም አጠባ (ትምህርት መማር ለማለት)
- ፋራ (2)
- ቀፋፊ
- በእጃቸው የሚሄዱ (ጉቦ የሚሰጡ ለማለት)
- በአይናቸው ጥራት (በኩረጃ ለማለት)
- ገገማ (2 ጊዜ)
- ጀለስ (2 ጊዜ)
- ምርጥ ጀለስህ
- ነቅንቀህ ታልፋለህ
- ጭልጥ ያለው ፋራው
- እዚች ጋ እጥፍ ማለቱ . . .

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የአራዳ ቋንቋ ቃላትና ሐረጋት የተናጋሪውን ማንነት (ሰብዕና) ለመቅረጽ ያገለግላሉ፤ ቢሆንም በአንባቡ ይህ ምንባብ የተመረጠላቸውን ተማሪዎች ሥነልሳናዊ ዳራዊ ዕውቀት መዘንጋት አይገባም። በተወሰኑ የአራዳ ቋንቋ ቃላት ብቻ በመጠቀም ፍቻቸውን በዓውድ እንዲተረጉሟቸው ማድረግ ሲቻል በአንድ ምንባብ ውስጥ ከመጠን በላይ ተደጋግመው መቅረባቸው በተማሪዎቹ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣሉ። ከነዚህ ተጽዕኖዎች ውስጥ ቀዳሚው በንባብ ሂደታቸው ላይ እንቅፋት መፍጠር ሲሆን ከዚህ የከፋው አሳሳቢ ችግር ደግሞ የቃላቱን ትርጓሜ በተለያዩ ስልቶች ከተረዱም በኋላ እንደ መደበኛ ቃላት ለመገልገል መሞከር ሊሆን ይችላል። ከዚህም ባሻገር ተማሪዎቹ (ኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎች ከመሆናቸው አንፃር) እነዚህን መሰል ቃላት እንደ መደበኛ የቋንቋው ቃላት በመቁጠር፣ ቋንቋውን አክብደው በማየትና መጥላት ደረጃ ላይ እንዲደርሱ ምክንያት ሊሆን ይችላል።

ምሳሌ 3፡- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 78 ላይ፣ "ምንባብ አንድ" በሚል ርዕስ የቀረበው፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" የተወሰደ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ. የሚከተሉትን ዘያዊና ብሉይ (በአገልግሎት ላይ የሌሉ) ቃላትን አካቷል፤

- ጉልት
- ስንቅ
- ባልደራሶች
- ጀሌዎች
- የጭን ገረድ
- በየእርስቱ
- ማለፊያ ቤት

ይህ ምንባብ በሀገራችን ከብዙ ዓመታት በፊት በነበረው የፊውዳል ሥርዓተ ማኅበር ውስጥ የባለባቶችና የጭሰኞችን ግንኙነት የሚተርክ ነው። በዚህም ምክንያት ከላይ ለአብነት የቀረቡት ቃላትና ሐረጋት በዘመናችን ለሚገኙ የ7ኛ ክፍል ኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎች ይቅርና ከዚህ የክፍል ደረጃ በላይ ለሚገኙ ተማሪዎችም ቢሆን (የማይዘወተሩ ቃላትና ሐረጋት በመሆናቸው) ፍችዎቻውን በቀላሉ ተገንዝበው በሕሊናቸው ምሰል ይፈጥሩላቸዋል ብሎ ለመናገር ያስቸግራል። በተመሳሳይ፤

- ጋምቤላ ክልል፣ 7ኛ ክፍል፣ ገጽ 119 "እሱም አለቀሰ" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም፤
- ጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል ገጽ 122 "ሰላም ይሰፈን" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም፤

በነዚህ ሁለት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ ከላይ የተገለጸው አይነት ጉድለቶች ተስተውሎባቸዋል።

### *ሐ. የሆሄያት ግድፈት ያለባቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች*

በሦስቱ ክልሎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ ጎልቶ ከተስተዋሉት ሥነልሳናዊ ግድፈቶች ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዘው የሆሄያት ግድፈት ነው። ይህን ችግር እጅግ አሳሳቢ የሚያደርገው ደግሞ መጻሕፎቹ የተዘጋጁት ለኢአፈ-ፈት ተማሪዎች መሆናቸው ነው። ምክንያቱም አፈ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ባመዛኙ የቃላቱን ትክክለኛ ንበት ተከትለው ስለሚያነቡ አንዳንድ ግድፈቶችን አቃንተው ሊያነቧቸው ይችላሉ። በአንፃሩ ኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽእኖ ሊያደርግባቸው ስለሚችልና ቃላቱን

አዘወትረው ስለማይገለገሉባቸው፣ ግድፈቶቹን አርመው ከማንበብ ይልቅ እንደ ትክክለኛ ቅርጻቸው (እንደ መደበኛ ቃላት) በመቁጠር ሊገለገሉባቸው ይችላሉ።

ለምሳሌ " 'ሸልንጌን' /ልብወለድ/" በሚል ርዕስ፣ ለጋምቤላ ክልል፣ 8ኛ ክፍል በገጽ 93-97 ላይ በቀረበው አጭር ልቦለድ ውስጥ የሚከተሉትን የሆሄያት ግድፈቶች እንገኛለን፤

| *ግድፈት ያለበት* | *ትክክለኛው ቅርጽ* | *ግድፈት ያለበት* | *ትክክለኛ ቅርጽ* |
|---|---|---|---|
| - በባቡሩ | የባቡሩ | - ወጥር | ውጥር |
| - በቡሩ | ባቡሩ | - አንቷን | አንጀቷን |
| - ጨኸች | ጮኸች | - ነቅት | የክት |
| - ራቫን | ራሷን | - ውስዕ | ውስጥ |
| - የራር | የረር | - ሺገባ | ሲገባ |
| - በጭሸኝነት | በጭሰኝነት | - ባሩ | ባቡሩ |
| - ብቻዋንነ | ብቻዋን | - በሸሚ | በሸማዋ |
| - ዳሌ | ዳሌዋ | - ጠረጋ | ጠርጋ |
| - ደመዝ | ደሞዝ | - በስመሮች | መስመሮች |
| - ግንነ | ግን | - ከልበሷ | በልብሷ |
| - ብትለለትም | ብትለምናትም | - እስኪሞላት | እስኪሞላላት |
| - እንደሚታየኝ | እንደምታይኝ | - ከሸልማት | ከልማት |
| - ብትለምናት | ብትለምናት | - ሰጥቷል | ሰጥታት |
| - ገና | ግን | - ይኸው | ይኸው |
| - ባሳለችለት | በሳለችለት | - እንቅቡ | እንቅቡን |
| - መርጭቁ | መንጭቁ | - ገፋለት | ገፋላት |
| - ሯሷ | ራሷ | - አንቀረፋ | አንቀራፋ |
| - ሪሱን | ራሱን | - የጢሸኛ | የጢሻና |
| - ባሻቀ | በሸቀ | - እንዲያላይ | እንዳይታይ |
| - አወረዱትለ | አወረዱለት | - ካለው | ያለው |
| - ባሱ | በሱ | - የአረግ | የሐረግ |
| - የሚያልፈውን | የሚያልፈውን | - ጣቶችን | ጣቶቿን |
| - ሸልንግ | ሸልንግ | | |

ከላይ ከተዘረዘሩት ምሳሌዎች መረዳት እንደምንችለው፣ በሆሄያት ግድፈት ምክንያት አንዳንድ ቃላት ፍች አልባ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከዓውዳቸው ጋር ፍጹም የማይዛመድ ሌላ ፍች ይዘዋል። ቀሪዎቹም የመስተዋድድ ስህተቶች በማስከተላቸው የሰዋስው ሥርዓት እንዳይጠበቅ ምክንያት ሆነዋል። በርግጥ ይህ ስሕተት- የሚከሰተው ሥነጽሑፋዊ ሥራው ከተመረጠ በኋላ ስለሆነ ከአመራረጥ ሂደቱ ጋር ቀጥተኛ ተዛምዶ የለውም የሚል ሐሳብ ሊነሳ ይችል ይሆናል። ነገር ግን አንድ በጥንቃቄ የተመረጠ ሥነጽሑፋዊ ሥራ

የታለመውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግቡ ሊያደርስ የሚችለው የመጽሐፍ አዘጋጆችም ሆኑ አርታኢያን መጽሐፉ ተማሪዎች እጅ እስኪደርስ ድረስ ተገቢውን እርማትና ማስተካከያ ማድረግ ያለባቸው መሆኑን የሚያሳስብ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን ያመላክታል። የሚከተሉት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም በተመሳሳይ ጎልተው የሚታዩ ጉድለቶች ተስተውሎባቸዋል፤

- በጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል፣ በገጽ 83-84 ላይ፣ ከመንግስቱ ለማ "ያላቻ ጋብቻ" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፣ ርዕስ ያልተሰጠው ተውኔት፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 78-80 ላይ፣ "ምንባብ አንድ" በሚል ርዕስ የቀረበ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 132-137 ላይ፣ "ደብዳቤው አንድ" በሚል ርዕስ የቀረበ ምንጩ ያልተገለጸ አጭር ልቦለድ፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 171-172 ላይ፣ "ምንባብ ሶስት" በሚል ርዕስ የቀረበ፣ ከክፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ" ልቦለድ መጽሐፍ የተወሰደ፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 175-186 ላይ፣ "ጅብ ነች" በሚል ርዕስ የቀረበ፣ ከታደሰ ሊበን "መስከረም" የአጭር ልቦለድ መድብል የተወሰደ፤

### *4.1.1.5. ከተማሪዎች ሥነጽሑፋዊ ዳራ አንፃር*

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተማሪዎቹን ሥነጽሑፋዊ ዳራ ያገናዘቡ ሊሆኑ ይገባል። አንዳንድ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነልሳናዊ አቀራረባቸው በጣም ግልፅ ሆኖ በአንባሩ የደራስያኑን ወይም የገጣምያኑን ያማኅፍ ስልት ካለመገንዘብ የተነሳ መልዕክታቸውን በቀላሉ ለመረዳት አዳጋች ሊሆን ይችላል። እንደ ቋንቋ ምሁራን ገለፃ ይህ ችግር የሚከሰተው ቋንቋውን ካለማወቅ ወይም በቃላት ክብደት ምክንያት ሳይሆን የተለያዩ በርካታ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን የማንበብ ልምድ ካለመኖር ጋር በተያያዘ ነው። ከዚህ አንፃር በሦስቱ ክልሎች በተዘጋጁት መጻሕፍት በተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ አብዛኞቹ ቅንጫቢዎች የተወሰዱት በሀገራችን ታዋቂ ከሚባሉት ደራስያን (ከሀዲስ አለማየሁ፣ ከበአሉ ግርማ እና ከክፍቅረማርቆስ ደስታ) ልቦለድ መጽሐፎች ላይ ነው። ነገር ግን የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ላቅ ያለ ደረጃ ላይ መገናኘት ተማሪዎቹ የቀረቡላቸውን ምንባቦች በፍጥነት አንብበው ጭብጣቸውን ወይም ታሪካቸውን በቀላሉ እንዲረዷቸው አላስቻላቸውም። ስለዚህ በሚመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ የሚገኙት ዘይቤዎች፣ ፊሊጦች እና የአፃፃፍ ቴክኒኮች ከተማሪዎቹ የቀደመ ሥነጽሑፋዊ ግንዛቤ አንፃር በጥንቃቄ መፈተሽ ያሻል። ከዚህ ርዕሰጉዳይ አንፃር በተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ የሚከተሉት ችግሮች ታይተዋል፤

በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 175-186 ላይ፣ "ጅብ ነች" በሚል ርዕስ የቀረበው፣ ከታደሰ ሊበን "መስከረም" የአጭር ልቦለድ መድበል ላይ የተወሰደ ምንባብ፣ ከተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዳራ ጋር አይመጣጠንም። የዚህን ሥነጽሑፋዊ ሥራ የአፃፃፍ ቴክኒክ ለማወቅ ስለአጭር ልቦለድ ባህርያት ሰፊ ግንዛቤ መያዝን ይጠይቃል። በተጨማሪም በልቦለዱ አለባውያን ላይ ተማሪዎቹ ውይይት ማካሄድ የሚችሉት አስቀድመው ስለ እያንዳንዱ አላባውያን ምንነትና ባሕሪ ግንዛቤ ሲኖራቸው ነው።

በቀረበው ልቦለድ ውስጥ ያለው ግጭት ለምሳሌ ብንመለከት በግልጽ የሚታይ አካላዊ ግጭት (ሰው ከሰው ጋር የሚያካሄደው) ሳይሆን የታሪኩ ዋና ገፀባሕሪ (አሰፋ) ከራሱ ጋር የሚያደርገው (ህሊናዊ) ግጭት ነው። ነገር ግን በ7ኛ የክፍል ደረጃ ላይ ሥለአጭር ልቦለድ ባሕርያትና አላባውያን ምንነት የቀረበላቸው ይዘት አናገኝም። በዚህም ምክንያት "ከፊረሱ ጋሪው..." እንደሚባለው ምንባቡ እንዳለቀ ስለአጭር ልቦለድ ምንነትና ባሕሪ አጭር ማብራሪያ እንዲቀርብ ተደርጓል። ይህን ማብራሪያ ተገን በማድረግም ተማሪዎቹ በቀረበው አጭር ልቦለድ ውስጥ የሚገኙትን "ጭብጡን፣ ገፀባሕሪውን፣ መቼቱን፣ ታሪኩን፣ ግጭቱን፣ ሴራ/ ትልሙንና አንባር በተናጥል ለማየት ሞክሩ። በመቀጠልም መምህራችሁ ሥራችሁን እንዲገመግሙላችሁና አብራርተው እንዲያስረዷችሁ አድርጉ።" የሚል መልመጃ ቀርቧል። ከዚህ መልመጃ ውጭ የተማሪዎችን የክሂል ዘርፎች የሚያጎለብቱ ተግባራት አልቀረቡም። ስለዚህም ይህ ምንባብ የቀረበው ቋንቋን ለማስተማር ሳይሆን ሥነጽሑፍን ለማስተማር ከመሆኑም ባሻገር የተማሪዎቹን የቀደመ ሥነጽሑፋዊ እውቀት ያላገናዘበ ነው ማለት ይቻላል። በተመሳሳይ ሁኔታ፤

- በደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ ክፍል በገጽ 18 እና 17፣ "ብርቱ ፍቅር" በሚል ርዕስ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- በደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ ክፍል በገጽ 51 እና 52፣ "ብቸኝነት" በሚል ርዕስ፣ ከአሰፋ ገ/ማርያም "እንደወጣች ቀረች" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- በደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 113-114 እና 107-108፣ "ውለታ" በሚል ርዕስ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- በደቡብ ክልል 8ኛ ክፍል፣ በገጽ 191-192 ላይ፣ "ሱጴ" በሚል ርዕስ፣ ከበዓሉ ግርማ "የህሊና ደውል" መጽሐፍ ላይ የወሰደ፤

- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 27 ላይ "የአማላጁ መልዕክት" በሚል ርዕስ ከይልማ ሀብተየስ "ደላላው" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 62-64 ላይ፣ "ስርቅታ" በሚል ርዕስ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃብር" መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የወሰደ፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 80-84 ላይ፤ "ምንባብ ሁለት" በሚል ርዕስ፣ ከበአሉ ግርማ "ከአድማስ ባሻገር" መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 119 ላይ፣ "እሱም አለቀሰ" በሚል ርዕስ የቀረበ ምንጩ ያልተጠቀሰ ግጥም፤
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 167 ላይ፣ "ምንባብ አንድ" በሚል ርዕስ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "ኢቫንጋዲ" መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ
- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 171-175 ላይ፣ "ምንባብ ሶስት" በሚል ርዕስ፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ" መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ፣

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቀረቡበት ቋንቋ በአመዛኙ ቀላል ይመስላል፤ ቃላቱን በተናጥል ስንመለከታቸው ተዘውታሪ ናቸው። ነገር ግን አንዳንዶቹ የገቡት በፍካሬያዊ ፍችያቸው በመሆኑ ኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎች ቀጥተኛ ፍችዎቻቸውን በመውሰድ የተሳሳተ ግንዛቤ ሊጨብጡ ይችላሉ። የተወሰኑት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ደግሞ ያልተዘወተረ ሰዋስዋዊ የቃላት ስደራን የተከተሉ በመሆናቸው ብዙ የማንበብ ልምድ የሌላቸው ኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎች በቀላሉ ሊረዷቸው አይችሉም። በሌላ በኩል አብዛኞቹ ከረዥም ልቦለድ ላይ ተቀንጭቦው የተወሰዱት ምንባቦች ታሪክ ተያያዥነት ያለውና ፍሰቱን የጠበቀ ባለመሆኑ በተለይ ለኢአፈ-ፈት ተማሪዎች የተጠቃለለ መደምደሚያ ላይ በመድረስ የተገነዘቡትን ፍሬ ነገር ለመናገር ሊያዳግታቸው ይችላል። በተመሳሳይ ተለዋጭ ዘይቤዎች እና ተምሳሌታዊ ዘይቤን በብዛት ያካተቱ (ለምሳሌ "እሱም አለቀሰ" በሚል ርዕስ እንደቀረበው ግጥም) ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተማሪዎችን ሥነጽሑፋዊ ዳራ ያላገናዘቡ ናቸው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ተለዋጭ ዘይቤ፣ ተምሳሌታዊ ዘይቤ፣ ምፀታዊ ዘይቤ፣ ንቡር ጠቃሽ ዘይቤን፣ በጥልቀት የሚማሩት ከ9ኛ ክፍል በላይ ነው። በእንዛሩ ምንባቦቹን ተከትለው የሚቀርቡትን ማብራሪያዎችና ገለፃዎችን ተከትለው የሚቀርቡት መልመጃዎች ተማሪዎቹ ሁሉንም የዘይቤ ዓይነቶች እንዲለዩ የሚጠይቁ ናቸው። እነዚህ የተማሪዎችን ሥነጽሑፋዊ ዳራዊ ግንዛቤ ያላገናዘቡ ሥራዎች በብዛት የሚገኙት በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል መጽሐፍ ላይ መሆኑን ከላይ ከቀረበው ዝርዝር መረዳት ይቻላል።

ባጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ወንድወሰን (1995፣42)፣ "ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በሥነጽሑፍ ባለሞያዎች በሚሰጣቸው ትልቅ ግምት ብቻም በመመራት ደረጃቸውን ሳይመጥኑ መወንገር ተማሪው ገና ከጅምሩ ለቋንቋው ትምህርት

አንገቱን እንዲያጠን ከማድረግ ሌላ ትርፍ አይኖረውም" በማለት ላቀረቡት ሐሳብ ጥሩ ማሳያዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ከ49 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ 20ዎቹ የተወሰዱት ከሀዲስ አለማየሁ፣ ከበዓሉ ግርማ፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታና ከሲሳይ ንጉሱ ረዥም ልቦለዶች ላይ ሲሆን ችግሩም የተስተዋለው በአብዛኛው ከነዚህ ዕውቅ ደራስያን ተቀንጭበው በተወሰዱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ ነው።

### *4.1.1.6. የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ዳራ አንፃር*

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የታቀደውን የቋንቋ ትምህርት ዝርዝር አላማዎች ያሳኩ ዘንድ ባሕላዊና ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠይቃል። በምዕራፍ ሁለት በስፋት ከቀረበው የተለያዩ ምሁራን ገለፃዎች የምንገነዘበው የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አንድን ሃይማኖት በበጎም ይሁን በክፉ የሚያነሱ፣ አንድ ማኅበረሰብ በይሁን የተቀበለውን ባህሉንና ልማዱን (ጎጂም ይሁን ጠቃሚ) ቀጥተኛ በሆነ ስልት የሚተች፣ የሚነቅፍ ወይም ከባህል ጋር የሚጋጩ አገላለጾች አለመካተታቸውን መመርመር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጻሕፎቹ ውስጥ በተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ ባህላዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ተገቢነት የጎደላቸው ሥራዎች ባያጋጥሙም ሐይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ ግን ትኩረት ያልተሰጣቸው አሳሳቢ ችግሮች ተስተውለዋል። የሚከተሉት ምሳሌዎች ይህን የሚያረጋግጡ ናቸው።

- በጋምቤላ 7ኛ፣ "ምንባብ አንድ" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ ገጽ በገጽ 78-80 ላይ ፣

  *... በረቡ ቀን ለዘመቻ መነሳት ደግ አይደለም። ረቡዕ አይሁድ ጌታን ለመያዝ የሞከሩበት ቀን ስለሆነ የክሃዲዎች፣ ያመፀኞች ቀን ነው፣ የጌታ ቀን አይደለም። ... ሐሙስ የሚካኤል ዕለት ሆነ...*

- በጋምቤላ 7ኛ፣ "ሞልዶት" በሚል ርዕስ በቀረበው ምንባብ ውስጥ፣ ገጽ 112፤

  *... የአቡነ ዘበሰማያት ጦር ሲዋጋ እንጂ ሲወረወር አይታይም እያሉ ሲያወሩ እሰማ ነበር።*

- በጋምቤላ 7ኛ፣ "ጉዱ ካሳ" በሚል ርዕስ በቀረበው ሥነጽሑፋዊ ሥራ፣ በገጽ 114-115 ላይ፤

  *...ጣኦት ሰርቶ የሰሩትን ጣኦት በፈጣሪ ቦታ እንደማስቀመጥና እንደማምለክ ነው።*

➢ በጋምቤላ 7ኛ ክፍል፣ "ምንባብ ሶስት" በሚል ርዕስ በቀረበው ሥነጽሑፋዊ ሥራ፣ ገጽ 172፤

*እንስሳትን ይወዱ ነበር ስለሚባሉትና ዝቋላ ላይ ለዘመናት ስለኖሩት አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ አሰበ። ገብረመንፈስ ቅዱስ ለሶስት መቶ አመታት ምንም ሳይመገቡ ለእንስሳት ይጸልዩ የነበሩና እንዲያውም የተጠማች ወፍ አጋጥሟቸው እንባቸውን እንድትጠጣ የማድረጋቸው "አፈታሪክ ይሆን እውነት" አያውቀውም ብቻ ትውስ አለው።*

*ከዚህ ውጪ ስለ አቡነገብረመንፈስ ቅዱስ ሌላ ነገር አሰበ። ጀርመን ሀገር ለሀሳናት በተጻፈ መጻሕፍ ገብረመንፈስ ቅዱስ ኢትዮጵያ ውስጥ የኖሩ ጀርመናዊ ናቸው የሚል ትውስ አለው ፈገግ አለ።...*

➢ በደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 82 እና 80 ላይ፣ "እንማር" በሚል ርዕስ በቀረበው ግጥም፤

*... ሰው ሁሉ ከአዳም ከሄዋን ፈለቀ።...*

➢ በጋምቤላ 8ኛ ክፍል፣ በገጽ 83 ላይ፣ ርዕስ ያልተሰጠው ተውኔት፤

*በለጠች፡-* *የቤተሰቢያኑን መረዋ መቺም አይሰሙት ብዬ ነው ... ቤተሰቢያን ስመው አስቀድሰው የሚመለሱትን መቀበል ...*

*ባሕሩ፡-* *ቅዳሴ ወጡ እንዴ?*

*በለጠች፡-* *ድርገት ከወረዱ ስንትና ስንት ዘመናቸው።*

➢ በጋምቤላ 8ኛ ክፍል፣ ርዕስ ያልተሰጠው፣ በገጽ 88 ላይ፣ የቀረበው ግጥም ውስጥ

*አባ ታጠቅ ካሳ ታቡቱ ታቡቱ*
*አንድ ሰባራ ብረት ሳይሰጠው አባቱ*
*እሱ እንደክርስቶስ አንድ ነው ለናቱ*
*ዳር እስከዳር ይዞ የገሣው ንጉሱ*
*...*

እነዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሃይማኖታዊ ጉዳዮች በሀገራችን ውስጥ ከሚገኙት ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች (እምነቶች) ውስጥ በአንዱ ላይ (ኦርቶዶክስ) ላይ ብቻ ያተኮሩ ናቸው ለማለት ይቻላል። በአንባሩ በእነዚህ መጻሕፍት የሚማሩ ተማሪዎች የተለያየ እምነትና አመለካከት ካላቸው ማኅበረሰቦች የተገኙ ሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህ አንባር የሚከተሉት አበይት ችግሮች ሊከሰቱ ይችላሉ ብሎ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል፤

1ኛ. የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ያልሆኑ ተማሪዎች የእነሱ እምነት ባለመጠቀሱ ምክንያት የበታችነት ሥሜት ሊያድርባቸው ይችላል፤

2ኛ. የእምነቱ (የኦርቶዶክስ) ተከታይ የሆኑ ተማሪዎችም ታሪኩ ተዛብቶ ቀርቧል ወይም እዚህ ላይ መቅረብ አልነበረበትም በማለት ጥላቻ ሊያድርባቸው ይችላል፤

3ኛ. የዚህ እምነት ተከታይ ያልሆኑ ተማሪዎች ለቀረበው ሐሳብ (አረፍተ ነገር፣ ወይም አንቀጽ) ባይተዋር ስለሚሆኑ ምን ለማለት እንደተፈለገ በቀላሉ ላይረዱት ይችላሉ፤

4ኛ. ግልጽ ያልሆነላቸው ተማሪዎች የሚያነሷቸው ጥያቄዎች፣ ተማሪዎቹንና መምህራኑን አላስፈላጊ ወደሆኑ ክርክሮችና ምርምሮች ውስጥ ሊያስገቧቸው ይችላሉ። በዚህም ምክንያት ተማሪዎቹ ከቋንቋ ትምህርት ዓላማ በማፈንገጥ በምንባቡ ይዘት ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ሰበብ ሊሆኑ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ለአብነት በቀረቡት በነዚህ አራት ምክንያቶች ሳቢያ የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የታቀደው የትምህርት ዓላማ ግቡን እንዳይመታና ተማሪዎቹም የቋንቋ ትምህርቱን ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር በማዛመድ ትምህርቱን ሊጠሉት ይችላሉ። ለዚህም ነው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች መካተት የለባቸው በማለት የተለያዩ ምሁራን የሚያሳስቡት።

### *4.1.1.7. በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከርዝማኔ ምጠና አንፃር*

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ለትምህርቱ የተመደበውን የክፍለ ጊዜ መጠን እና የተማሪዎቹን የንባብ ፍጥነት ያገናዘቡ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ተማሪዎቹ የተመረጠውን ምንባብ ለማንበብ ብቻ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ክፍለ ጊዜያት የሚወስድባቸው ከሆነ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ለመተግበር አዳጋች ይሆናል። ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተካተቱት 49 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ 32 ያህሉ ለኢአፈ-ፈት ተማሪዎች ተመጥነው የቀረቡ ናቸው። ምክንያቱም ከአንድ እስከ ሁለት የገጽ ብዛት ላይ ቀርበዋል። ቀሪዎቹ 17 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግን ርዝማኔያቸው ምጣኔ ይጎድለዋል፤ ከ3 እስከ 11 የገጽ ሽፋን ተሰጥቷቸው ቀርበዋል። ከነዚህ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መካከል አፈ-ፈት ለሆኑ ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እንኳን ረዥም ጊዜ የሚጠይቁና አሰልቺነት ያላቸው ሥራዎች ተካተዋል። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፤

"ድብነች" በሚል ርዕስ፣ ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የቀረበው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ከገጽ 175 እስከ 186 ማለትም 11 ገጾች ሽፋን አግኝቶ ቀርቧል። ይህ አጭር ልቦለድ ሥነጽሑፋዊ ይዘቱም ይሁን ርዝማኔው ለኢአፈ-ፈትተማሪዎችም ሆነ አፈ-ፈት ለሆኑት የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች አይመጥንም። ይኸው አጭር ልቦለድ በ1998 ዓ.ም በተዘጋጀው (አሁንም በሥራ ላይ በሚገኘው) የ12ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ገጽ 113 ላይ ቀርቦ እንገኘዋለን። ከዚህ የምንረዳው የ12ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች ምንባቡ ላቅ ያለ የቋንቋ ችሎታን ይጠይቃል የሚል ዕምነት ያላቸው መሆኑን ነው። "ምንባቡ መመረጡ ለተነደፈው የትምህርት ዓላማ አማራጭ የማይገኝለት ነው" የሚል ሐሳብ ቢኖር እንኳን በቅንጫቢ መልክ ወይም ማሻሻያ ተደርጎበት መቅረብ ይችል ነበር።

"ሙሉ ልብስ" በሚል ርዕስ ለደቡብና ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች 8ኛ ክፍል በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ ከገጽ 218 እስከ 223 እና ከ147 እስከ 158 ላይ (በስድስት ገጾች) የቀረበው አጭር ልቦለድ ርዝማኔው ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች አይመጥንም። ተማሪዎቹ በአንድ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ምንባቡን አንብበው በመረዳት የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ለመተግበር የሚተርፍ በቂ ጊዜ ሊኖር አይችልም። ስለዚህም ይህ ምንባብ ኢአፈ-ፈት ተማሪዎችን እና አፈ-ፈት የሆኑት ተማሪዎችን ባማከለ ሁኔታ ተመጥኖ መቅረብ ነበረበት።

በተመሳሳይ የሚከተሉት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችም ከርዝማኔ ምጣኔ አንፃር እጅግ የሳላ ችግር ተስተውሎባቸዋል፤

- በደቡብ ክልል እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 8ኛ ክፍል፣ ከገጽ 79-83 እና ከገጽ 59-64 ላይ፣ "የፊውስሐዋርያዎች" በሚል ርዕስ የቀረበ ምንጩ ያልተጠቀሰ ተውኔት፤
- በጋምቤላ 7ኛ ክፍል፣ ከገጽ 132-137፣ "ደብዳቤ አንድ" በሚል ርዕስ የቀረበ፣ "ብዕር" ከተሰኘ የደብዳቤ መድብል የተወሰደ አጭር ልቦለድ፤
- በጋምቤላ 7ኛ ክፍል፣ ከገጽ 171-175፣ "ምንባብ ሶስት" በሚል ርዕስ የቀረበ፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- በጋምቤላ 8ኛ ክፍል፣ ከገጽ 93-97፣ "ምንባብ ሶስት" በሚል ርዕስ የቀረበ፣ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ" መጽሐፍ ላይ የተወሰደ፤
- በጋምቤላ 8ኛ ክፍል፣ ከገጽ 93-97 - "ሽልንጌን" በሚል ርዕስ የቀረበ፣ ምንጩ ያልተገለጸ አጭር ልቦለድ፤

### 4.1.1.8. በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተተግባሪነት

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መመረጥ ያለባቸው በቋንቋቸው ማራኪነት ወይም በአገዛናኝነታቸው ተመዝነው ሳይሆን በመርሐትምህርቱ ላይ ከተቀረጸው ዓላማ አንፃር ተግባራዊ ፋይዳቸው ተጠንቶ ሊሆን ይገባል። ዓላማዎቹን ለመተግበር የሚያስችሉ ምን ያህል መልመጃዎችን ማዘጋጀት እንደሚቻል እንዲሁም በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ላይ የቀረበውን ታሪክ ተማሪዎቹ በምልዐት ይገነዘቡት ዘንድ አጋዥ የሆኑ ልዩ ልዩ መረጃ መሣሪያዎችና ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የሚመረጡባቸው የሕትመት ውጤቶች (መጻሕፍት፣ መጽሄቶች፣ ጋዜጦች . . . ) በምን ያህል መጠን ተማሪዎቹ ሊያገኟቸው እንደሚችሉ አስቀድሞ ማረጋገጥ እንደሚገባ በዚህ ጥናት በምዕራፍ ሁለት (ንዑስ ክፍል 2.3.9) ላይ ተጠቅሷል።

ከዚህ ርዕሰጉዳይ አንፃር የተመረጡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የመረጃ ምንጮች ስንመለከት በተጨማሪም የቀረቡ አጋዥ ሥዕላዊ መግለጫዎችንና ምስሎችን ስንመረምር በርካታ ጉድለቶችን እናስተውላለን። ለአብነት ያህል ተከታዮቹን እንመልከት፤

*ሀ. የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን የመረጃ ምንጮች በተመለከተ*

ከቀረቡት 49 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ 20 ያህሉ ከታተመ ረዥም አመታትን ካስቆጠሩና አንዳንዶቹም በአሁኑ ወቅት በገበያ ላይ ሊገኙ ከማይችሉ መጻሕፍት ናቸው። አንዳንድ የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችም በቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ እንዳረጋገጡት (ዝርዝሩን ከአባሪው ይመለከታል) መጻሕፍቱን በቤተመጻሕፍት ውስጥ ስለሌሉ በግላቸው በማፈላለግ መገልገላቸውን ጠቁመዋል። በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መረጣ ሂደት ወቅትም ዋነኛ ችግራቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የሚገኙባቸው መጻሕፍት እጦት መሆኑን በጋምቤላ ክልል የ8ኛ ክፍል መጽሐፍ አዘጋጅ ከሆኑት ውስጥ አቶ መላኩ መሐሪ የተባሉት ገልጸውልኛል። ከዚህ የምንገነዘበው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የተወሰዱባቸውን-መጻሕፎች ተማሪዎቹም ሆኑ መምህሮቻቸው በበቂ መጠን (በቀላሉ) ሊያገኟቸው እንደማይችሉ ነው።

በሌላ በኩል ከቀረቡት 49 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ 14 ያህሉ ከየት እንደተወሰዱ የመረጃ ምንጫቸው አልተገለጸም። የመረጃ ምንጮች አለመጠቀስም ከላይ የተጠቀሰውን ችግር ያጎላዋል፤ ተማሪዎቹ በቅንጫቢ መልክ የቀረቡላቸውን ምንባቦች የበለጠ ለመረዳት ቢፈልጉ ወይም ቀሪ የታሪኩን ክፍል የማንበብ ጉጉት ቢያድርባቸው፣ መጻሕፍቱን ለማግኘት ፍጹም አዳጋች መሆኑ አያጠራጥርም። ይህ ችግር በተለይ ለጋምቤላ ክልል በተዘጋጀው የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጻሐፍ ላይ ጎልቶ ይታያል፤ ከቀረቡት 20 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ 8 ያህሉ ምንጮቻቸው አልተገለጸም።

*ለ. መርጃ መሣሪያዎችን በተመለከተ*

በተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ አላስፈላጊ የሆኑ ሥዕላዊ መግለጫዎች ሲካተቱ በአንዳንድ መካተት የነበረባቸው ሥዕላዊ መግለጫዎች ተዘንግተዋል። ለምሳሌ ለጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ "ትንሿ መንደር" (ከገጽ 54-56) በሚል ርዕስ የቀረበው ሥነጽሑፋዊ ሥራ አንዲት ትንሽ መንደር የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ አካታል። በአንዳንድ በዚሁ መጽሐፍ ላይ "ሽልንጌን" በሚል ርዕስ፣ ከገጽ 93 - 96 የቀረበው ምንባብ (ስለ አንዲት ነጋዴና "ሽልንጎን" ይዞ ስለተሰወረው ባቡር የሚተርክ አጭር ልቦለድ) ሥዕላዊ መግለጫ የለውም። ነገር ግን እነዚህ ሁለት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቀረበላቸው ተማሪዎች ባይተዋርነታቸው (ተጨማሪ መረጃ የሚፈልጉት) በአንድ ትንሽ መንደር ውስጥ ስለሚገኙ ጎጆ ቤቶች መኪና፣ ተራራና ዛፎቹ ሳይሆን በአንድ የባቡር ጣቢያ ላይ ስለሚገኙ ነገሮች (ባቡር ወይም ፉርጎና፣ ሐዲድ...) ምንነት ነው። ስለዚህም ሥዕላዊ መግለጫ የሚያሻው "ትንሿ መንደር" ለሚለው አጭር ልቦለድ ሳይሆን "ሽልንጌን" በሚል ርዕስ ለቀረበው ምንባብ ነበር።

### 4.1.2. *በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት*

በተገቢው መስፈርት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በአንድ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሲቀርቡ ተጠያቂዊ በሆነ ስልት መደራጀት ይኖርባቸዋል። በመርሐትምህርቱ ላይ የተተለሙትን ዓቢይና ንዑሳን የትምህርት ዓላማዎች ማሳካት የሚቻለውም በተለያዩ-ምሁራን የተጠቀሱትን የአደረጃጀት መርሆዎች መተግበር ሲቻል ነው። በምዕራፍ ሁለት ከተጠቆሙት ከነዚህ መርሆዎች አንፃር፣ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት በዚህ ንዑስ ክፍል ለማየት ተሞክሯል።

### 4.1.2.1. የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከፋይዳቸው ሚዛን-ደፊነት አንፃር

የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በፋይዳቸው ሚዛን ደፊነት አንፃር መደራጀት ይኖርባቸዋል ሲባል ከተማሪዎቹ አኳያ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን በማስቀደም፣ ከዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ጋር ብዙም የማይዛመዱትን አንፃራዊ በሆነ መልኩ በማስከተል ማደራጀትን እንደሚመለከት ቀደም ሲል በምዕራፍ ሁለት ከቀረበው የተለያዩ ምሁራን ገለፃ መገንዘብ ይቻላል። ከዚህ የአደረጃጀት መርህ አንፃር በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ስንመረምር ፍጹም ትኩረት አላገኙም ማለት ይቻላል። ምክንያቱም ከመነሻ እስከመድረሻ ይህን መርህ ተከትለው የቀረቡ (በፋይዳቸው ሚዛን ደፊነት የተደራጁ) ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ያካተተ መማሪያ መጽሐፍ በምሳሌነት መጥቀስ ያዳግታል። በአንፃሩ መቅደም የነበረባቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመጽሐፉ የመጨረሻ ክፍል ላይ ቀርበው ከተማሪዎቹ የዕለት ተዕለት ህይወት በጣም የራቁ ርዕሰጉዳዮችን የያዙ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግን ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እናገኛለን የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፤

ምሳሌ 1፡- በጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 27 ላይ፣ "የአማላጁ መልዕክት"፣ ከይልማ ሀብተየስ፣ "ደላላው" መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የቀረበው ጽሑፍ፤

ባለታሪኮቹ ተፈራ በላይ እና ደረጀ ዓለሙ የተባሉ የ29 እና የሠላሳ ዓመት ወጣቶች በዕረፍት ጊዜያቸው ውስኪ በመጠጣት በቀጠሮ ሰዓት ስላልተገኘች አንዲት ሴት የሚያካሂዱትን ምልልስ ያቀርባል። በተመሳሳይ ገጽ 103 ላይ፣ "እንባ እፈልጋለሁ" በሚል ርዕስ የቀረበው ተውኔት በአንድ የሥራ ቅጥር ሂደት ላይ ስለተፈጸመ የሙስና ተግባር ያሳያል። በአንፃሩ ገጽ 171 ላይ "ምንባብ ሶስት" በሚል ርዕስ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "አቻሜ" መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የቀረበ ታሪክ ተናጌ የተባለች ገፀባሕሪ የአባቷን (የአቻሜን) ጭንቀትና ችግር ምን እንደሆነ በመጠየቅ መፍትሄ ለመፈለግ የምታደርገውን ጥረትና ዘወትር ግልጽ ያልሆነላትን ጉዳይ ለአባቷ ጥያቄ እንደምታቀርብ ያሳያል። በተጨማሪም በገጽ 187 ላይ የቀረበው ርዕስ ያልተሰጠው ተረት በአንድ ላይ እየተጋገዙ ይኖሩ የነበሩ "ከአንድ እናትና ከአንድ አባት የተወለዱ" እህትና ወንድም አንድ ቀን እህት በወንድሟ ላይ

በፈፀመችው በደል ምክንያት እሷም ከባድ ችግር ውስጥ እንደገባች በማሳየት በመጨረሻ ሁለቱም ከስተታቸው ተመልሰው በሰላም መኖር እንደጀመሩ በመግለጽ፣ በቤተሰብ መካከለ ተንኮል መፈጸም ራስን እንደሚጎዳ ያሳያል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሙት አራት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከፋይዳቸው አንፃር ሲደራጁ መቅደም የነበረባቸው በመጨረሻ ላይ የቀረቡት የእህትና ወንድም፣ እንዲሁም የአባትና የልጅ ግንኙቶችን የሚተርኩት ሲሆኑ ስለሥራ ቅጥር ሂደትና ስለወጣቶቹ የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያ የሚተርኩት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ወደ መጨረሻ ላይ በቅደም ተከተል መደራጀት ነበረባቸው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ከአካባቢያቸው ወይም ከቤት ውጭ ከሚፈጸሙ ክንዋኔዎች በፊት በአንድ ቤተሰብ (በቤታቸው ውስጥ) የሚፈጸሙ እውነታዎች የበለጠ ከሕይወታቸው ጋር የተቆራኙ ናቸው ማለት ይቻላል።

ምሳሌ 2፡- በደቡብ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ 7ኛ ክፍል፣ በገጽ 35 እና 37 ላይ፣ "ደፋሩ አሸብር" ከሲላይ ንጉሱ "ረቂቅ አሻራ" የተወሰደ የረኸርም ልቦለድ ቅንጫቢ፤

በዚህ ታሪክ አሸብር የተባለው ዋና ገፀባሕሪ በተቀጠረበት መሥሪያ ቤት ውስጥ የሚፈጸሙ የሙስና ተግባራትን ተከታትሎ ለማጋለጥ የሚያደርገውን ጥራት ይተርካል። በአንባሩ በገጽ 42 እና 43 ላይ፣ "ተከስተና ወይዘሮ ጽጌ" በሚል ርዕስ፣ ከሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከመቃበር" ላይ ተቀንጭቦ የቀረበው ምንባብ በተከሰተ (ሕፃን ልጅ) እና በወይዘሮ ጽጌ መካከል የሚካሄደውን ቤተሰባዊ ጭውውት ያቀርባል። በተመሳሳይ ገጽ 60 ላይ "የከፋው አባት ደብዳቤ" በሚል ርዕስ በሙላቱ ገብሩ የቀረበ አጭር ልቦለድ አባት ልጃቸው ስለእናቱ ማሰብ ያለበት ከሞቱ በኋላ ሳይሆን በሕይወት እያሉ መሆን እንዳለበትና ባጠቃላይም ልጆች ሰዎችን መርዳት ያለባቸው በሕይወት ዘመናቸው መሆን እንዳለበት ያስገነዝባል።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሙት ሦስት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከፋይዳቸው አንፃር ሲደራጁ "ተከስተና ወይዘሮ ጽጌ" ቀድሞ "የከፋው አባት ደብዳቤ" በመከተል "ደፋሩ አሸብር" ወደ መጨረሻ ላይ መቅረብ ነበረበት። ባጠቃላይ ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት አይነት ችግሮች (ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በፋይዳቸው ሚዛን ደፊነት አለማደራጀት) በሁሉም መማሪያ መጻሕፍት ላይ ተስተውሏል።

### 4.1.2.2 የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከክብደት-ቅለታቸው አንፃር

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲቀርቡ ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቅቅ ወይም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ በሚሄድ ሁኔታ መደራጀት ይኖርባቸዋል። በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ለመግለጽ እንደተሞከረው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች እኩል ክብደት ወይም ቅለት የላቸውም። በአንባራዊነት ሲታዩ አንዱ ከሌላው በይዘቱ ወይም በቋንቋ አጠቃቀሙ ይለያል። በምዕራፍ ሁለት (ንዑስ ክፍል 2.4.2) ላይ እንደተገለጸው ተረቶችና አጫጭር ልቦለዶች ቀድመው የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢዎች ቢከተሉና ተውኔቶችና ግጥማዊ ሥራዎች ወደመጨረሻ ላይ ቢመጡ ተመራጭነት ይኖራቸዋል።

ከላይ ከተጠቀሙት መስፈርቶች አንፃር በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ የተደራጁ አይደሉም። ተከታዮቹ ለአብነት ያህል ቀርበዋል፤

ሀ. በጋምቤላ ክልል ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከክብደት-ቅለታቸው አንፃር

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት 20 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተረቶችን፣ አጭር ልቦለዶችን፣ የረጅም ልቦለዶች ቅንጫቢዎችን፣ ተውኔትና ግጥሞችን ያካተቱ ሲሆኑ ሲደራጁ ግን የክብደት ቅለታቸው ደረጃ ከግምት ውስጥ አልገባም። ለምሳሌ በገጽ 27-28 "የአማላጁ መልዕክት" በሚል ርዕስ የቀረበው የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ፣ ገጽ 35-37 "ካርለት" በሚል ርዕስ የቀረበ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ እና ገጽ 62-64 "ስርቅታ" በሚል ርዕስ የቀረበውን የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ ታሪክ፣ ስንመለከት ሦስቱም የአፃፃፍ፣ ቴክኒካቸውና የቋንቋ አጠቃቀማቸው ገጽ 111-112 "ሞልቶት" በሚል ርዕስ ከቀረበው ተረት እና ገጽ 187-189 ላይ ከቀረበው ርዕስ ካልተሰጠው ተረት ጋር ሲነፃፀሩ እጅግ ከባድ ናቸው ለማለት ይቻላል። ምክንያቱም ተረቶቹ ግልጽ እና ዘወትራዊ በሆነ ቀላል ቋንቋ በትረካ ሥልት ሲቀርቡ በአንፃሩ የረጅም ልቦለዶቹ ቅንጫቢዎች ግን ትረካን፣ ገለፃንና ምልልስ

የአማኳፍ ቴክኒኮችን እያፈራረቁ ከመገልገላቸው በላይ በዘይቤአዊ አገላለጾች የቀረቡ ናቸው። ስለዚህም ሲደራጁ ተረቶቹ ቀድመው የረኞርም ልቦለዶቹ ቅንጫቢዎች መከተል ነበረባቸው።

### ለ. በደቡብ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከክብደት-ቅለታቸው አንፃር

በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች 13 ያህል ሲሆኑ ከተውኔት በስተቀር ተረቶችን፣ አጭር ልቦለዶችን፣ የረኞርም ልቦለዶች ቅንጫቢዎችን እና ግጥሞችን አካተዋል። አጠቃላይ አደረጃጀታቸው (ከክብደት ቅለታቸው አንፃር) በጋምቤላ ክልል ከተዘጋጀው የተሻሉ ቢሆኑም እስከመጨረሻ ድረስ ወጥነትን አልተከተሉም። ለምሳሌ፦ በገጽ 51 - 52 ላይ "ብቸኝነት" በሚል ርዕስ የቀረበው የረኞርም ልቦለድ ቅንጫቢ በቋንቋ አጠቃቀሙ እና በአማኳፍ ቴክኒኩ፣ በገጽ 66-67 ላይ፣ "ወርቅ ላበደረ..." በሚል ርዕስ ከቀረበው ተረት እና በገጽ 86-88 ላይ፣ ከቀረበው ቃላዊ ግጥሞችና ማብራሪያ ጋር ሲነፃፀር ከባድ በመሆኑ መቅደም አልነበረበትም። በተመሳሳይ ገጽ 105 ላይ "ከባሌ መልስ" በሚል ርዕስ የቀረበው ቅንጫቢ ታሪክ በቋንቋ አጠቃቀሙም ሆነ ርዕሰ-ጉዳዩ ለተማሪዎቹ ካለው ቅርበት አንፃር (ከአካባቢያዊ ገለፃ ) ገጽ 8፣ (ለደቡብ ክልል በተዘጋጀው ላይ ብቻ የሚገኝ ነው) "ያባት ምርቃትና አደራ" በሚል ርዕስ ከፍቅረማርቆስ ደስታ "ከቡስካው በስተጀርባ" ከተወሰደው ሥነጽሑፋዊ ሥራ መቅደም ነበረበት። ምክንያቱም ተማሪዎቹ ከሀመር ባህልና አካባቢ ይልቅ የባሌን አካባቢና ባህል በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ።

### ሐ. በጋምቤላ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከክብደት-ቅለታቸው አንፃር

በዚህ መጽሐፍ የቀረቡት 10 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተረትን፣ አጭር ልቦለዶችን፣ የረኞርም ልቦለድ ቅንጫቢን፣ ተውኔቶችን እና ግጥሞችን ያካተቱ ሲሆን አደረጃጀታቸው ግን ክብደት-ቅለታቸውን ያገናዘበ አይደለም። ለምሳሌ ገጽ 4 "ጽጌረዳና ደመና" በተጨማሪም ገጽ 26 ላይ "ማነው ተጠያቂው" በሚሉ ርዕሶች የቀረቡት ሁለት ግጥሞች ገጽ 79 ላይ "ነገ ጥሩ ቀን ነች" በሚል ርዕስ ከቀረበው ግጥም በታላት መረጣ፣ በዘይቤአዊነታቸው፣ እና ከሚያነሱት ርዕሰ-ጉዳይ አንፃር ጠንከር ያሉ በመሆናቸው "ነገ ጥሩ ቀን ነች" የሚለው ከሁለቱም ቀድሞ መቅረብ ነበረበት። በሌላ በኩል ገጽ 54 ላይ "ትንሿ መንደር" በሚል ርዕስ

የቀረበው አጭር ልቦለድ በሚያነሳው ርዕሰጉዳይ እና በቋንቋ አቀራረቡ ገጽ 10 ላይ "ሁለቱ ጓደኞሞች" በሚል ርዕስ ከቀረበው ተውኔት እጅግ ግልጽ በመሆኑ ተማሪዎች በአንባራዊነት በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ። በአንባሩ ይህ ("ሁለቱ ጓደኞሞች" በሚል ርዕስ የቀረበው) ተውኔት በገጽ 83-84 ላይ ከቀረበው ርዕስ የሌለው ተውኔት መቅደመ ተገቢነት አለው። ምክንያቱም "ሁለቱ ጓደኞሞች" በሚለው ተውኔት ውስጥ የተጠቀሱት ገፀባህርያት (አካባቢያዊ መጠሪያ ያላቸው) እና የሚወያዩበት ርዕሰጉዳይ ለተማሪዎቹ ቅርበትና ግልፅነት ሲኖረው ገጽ 83-84 ላይ የቀረበው (በመንግሥቱ ለማ ጠልፎ በኪስ ተውኔት ላይ የተቀነጨበ) ግን ርዕሰጉዳዩም ሆነ የገፀባሕርያቱ ማንነት ከተማሪዎቹ ዳራዊ ግንዛቤ (የሕይወት ልምድ) የራቀ ነው።

ባጠቃላይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከቀላል ወደ ከባድ ወይም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ የማደራጀቱ ተግባር ተዘንግቷል ለማለት ይቻላል።

መ. በደቡብ ክልል እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከክብደት-ቅለታቸው አንፃር

በነዚህ መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት 6 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አጫጭር ልቦለዶችን፣ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎችን፣ ተውኔትና ግጥምን ያካተቱ ሲሆን ከክብደት-ቅለታቸው አንጻር የተጠና የአደረጃጀት ስልት አልተከተሉም። ለጋምቤላ ክልል ከተዘጋጀው አንባር የተሻለ አደረጃጀት ቢታይበትም ከመነሻው ላይ ግን ጎላ ያለ ችግር ተስተውሎበታል፤ የመጀመሪያው ሥነጽሑፋዊ ሥራ የቀረበው በተውኔት ቅርጽ ከመሆኑም በላይ ቋንቋው በርካታ የአራዳ ቋንቋ ቃላት የሚገኙበትና 5 ገጽ ያህል ሽፋን የተሰጠው አሰልቺ ምንባብ ነው። ይህ ተውኔት በገጽ 79-83 እና በገጽ 59-64 ላይ "የፈውስ ሐዋርያዎች" በሚል ርዕስ ቀርቧል። በአንባራዊነት ሲታይ ገጽ 218-223 እና 147-153 ላይ "ሙሉ ልብስ" በሚል ርዕስ የቀረበው አጭር ልቦለድ ከአተራረኩ አንባር፣ የመወያያ ርዕሰጉዳዩ ለተማሪዎች ካለው ቅርበት አንባር እና ከቋንቋው ግልጽነት አኳያ በአንባራዊነት ለተማሪዎቹ ቀለል ስለሚል ከተውኔቱ መቅደም ነበረበት።

ባጠቃላይ ከላይ ለአብነት ያህል ባጫጭሩ ከቀረቡት ማብራሪያዎች ለመገንዘብ እንደሚቻለው፣ ለሦስቱም ክልሎች በተዘጋጁት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ከክብደት ቅለታቸው አንባር ፍፁም ትኩረት እንዳልተሰጣቸውም ለማለት ይቻላል። ምናልባት ይህ ሊሆን

የቻለው አዘጋጆቹ መርሐትምህርቱን ተከትለው ስለሚያዘጋጁ ነው የሚል ሐሳብ ሊነሳ ይችላል። ነገር ግን በመርሐትምህርቱ ላይ የቀረቡትን ዝርዝር የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ስንመረምር ስለሚመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዘት፣ ርዕሰጉዳይ፣ የቋንቋ አጠቃቀምና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ የሠፈረ ሐሳብ አናገኝም። ስለዚህም ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር የሚታወቁትንና የማይታወቁትን ወይም ቀላሉንና ከባዱን ለይቶ የመምረጥና የማደራጀቱ ኃላፊነት የመጽሐፉ አዘጋጆች መሆኑን ልብ ይሏል።

### *4.1.2.3. ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ሁኔታ*

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት ሊኖራቸው ይገባል። ይዘቶቹ ተከታታይነት ይኑራቸው ሲባልም በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ በትምህርቱ መጀመሪያ የቀረበ ይዘት ሳይቆራረጥ በየምዕራፉና በየክፍል ደረጃው መቀጠል እንዳለበት የሚያስገነዝብ ሲሆን በሌላ በኩል ተለጣጣቂነት ማለት ጎናዊም (በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ) ሆነ ተዋረዳዊ (ከአንዱ የክፍል ደረጃ ወደሌላው) ድግግሞሽ ሥፋትና ጥልቀት እያሳየ መሄድ እንዳለበት የሚጠቁም መሆኑን በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ንዑስ ክፍል 2.4.3 ላይ ተገልጿል።

ከነዚህ ከምሁራኑ ንድፈሐሳባዊ መርሆዎች አንፃር በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንደሚከተለው ለማየት ተሞክሯል፤

ሀ. ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት፤

#### 1. ተከታታይነት

ጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ድግግሞሽ ስንቃኝ፡- 3 ተረቶች፣ 2 አጭር ልቦለዶች፣ 10 የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢዎች፣ አንድ ተውኔትና 4 ግጥሞች ቀርበዋል። ከዚህ አሀዝ የምንረዳው የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ድግግሞሽ ሚዛናዊነቱን አለመጠበቁን ነው። ከረጅም ልቦለድ ላይ

የተወሰዱት ከአጠቃላዩ ቁጥር ግማሽ ያህሉን ሽፋን (10) ሲይዙ፣ በአንባሩ ለተውኔት እና ለአጭር ልቦለዶች የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው። በሌላ በኩል በነዚህ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥር በመልመጃነት የቀረቡትን ይዘቶች ተከታይነት ስንመረምር፣ አንበቦ መረዳት 12 ያህል ሽፋን ሲሰጠው፣ የቃላትና ሐረጋት ትምህርት በ6 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ቀርቧል። በሌላ በኩል ስርዓተ ነጥብ፣ የዘይቤአዊ አነጋገር፣ ግጥም እና የልቦለድ ትምህርቶች ሁለት ሁለት ጊዜ ያህል ቀርበዋል። በአንባሩ የቃላት ምስረታና እርባታ (ሥነ ምዕላድ)፣ የቃል ክፍሎች፣ የአንቀጽ ምንነት፣ ተውኔት፣ ላልተውና ጠብቀው የሚነበቡ ቃላት እና የፊሊጣዊ አነጋገር ትምህርቶች አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ቀርበዋል። ከቀረበው አሀዝ የምንረዳው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በአመዛኙ የዋሉት ለአንበቦ መረዳትና ለቃላት ትምህርት መሆኑ ነው። በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አማካይነት አንድን የትምህርት ይዘት በተለይ ለኢአፈ-ፈት ተማሪዎች ስናስተምር፣ ተከታታይነት መኖር እንዳለበት የተጠቆመ ቢሆንም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ግን ለአይነት አንድ ግዜ ብቻ ብልጭ ብለው የሚጠፉ የትምህርት ይዘቶች ከፍተኛ ቁጥር መያዛቸው ተገቢነት የለውም።

በአጠቃላይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተደጋግሞ በተከታታይነት የቀረበው ሥነጽሑፋዊ ሥራ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ ሲሆን በሥነጽሑፍ አማካኝነት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶችን በተከታታይነት የማስተማሩ ተግባር ትኩረት ተነፍጎታል። አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ለአንበቦ መረዳት እና ለቃላትና ሐረጋት ፍች። ማስተማሪያነት ሲውሉ፣ በአንባሩ አብዛኞቹ ይዘቶች አንድ ግዜ ብቻ መቅረባቸው ተገቢነት የለውም። በተጨማሪም አንዳንዶቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አንድ የትምህርት ዓላማን ብቻ ለመተግበር የቀረቡ በመሆናቸው ይዘቶቹ በተከታታይነት ተደጋግመው እንዳይቀርቡ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችላሉ።

## 2. ተለጣጣቂነት

ቀደም ሲል በንዑስ ክፍል 4.1.2.2 ሥር እንደተገለጸው፣ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ይዘት፣ መልመጃዎችም ሆኑ የቃላት፣ የዘይቤ፣ የምሳሌያዊ አነጋገር፣ ወዘተ. ትምህርቶች ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ ሄደዋል ብሎ ለመናገር አይቻልም። እንደየ-ምንባቦቹ የቋንቋ ክህደትና ቅለት በስራቸው የቀረቡት ይዘቶችም አንድ ወጥ በሆነ አካሄድ ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ አልተደራጁም።

የሥነጽሑፍ ትምህርትን በተመለከተ ለምሳሌ፣ ተማሪዎቹ ስለተውኔት ከመማራቸው በፊት ስለ አጭር ልቦለድ በተመሳሳይ ግጥምን ከመማራቸው አስቀድሞ ተውኔትን ቢማሩ ሥነጽሑፋዊ ግንዛቤአቸው ስፋትና ጥልቀትን እያገኘ እንደሚሄድ በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ሥር በምሁራኑ ከቀረበው ገለፃ መረዳት ይቻላል። ነገር ግን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ተማሪዎቹ መጀመሪያ ገጽ 103-108 ላይ ስለተውኔት ተምረው፣ ተውኔት እንዲያቀርቡ ከተደረገ በኋላ በገጽ 122-123 እና በገጽ 125 ላይ በተከታታይ ሁለት ግጥሞች ቀርበውላቸዋል። በመጨረሻም በገጽ 175 ላይ ስለአጭር ልቦለድ ምንነትና ባሕርያት እንዲማሩ ተደርጓል።

በሌላ በኩል በተከታታይ "እሱም አለቀሰ" ገጽ 119፣ "ሰላም ይስፈን" ገጽ 122-123፣ "ነፃነት" ገጽ 125 እና "ንብና ትንኝ" ገጽ 126-127 በሚሉ ርዕሶች የቀረቡት 4 ግጥሞች ተለጣጣቂነት አይታይባቸውም። ምክንያቱም ቀዳሚው "እሱም አለቀሰ" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም ውስጥ "ብዕር" በሰው ተመስሎ (በሰውኛ ዘይቤ) የቀረበ ከመሆኑም ባሻገር ያልተዘወተሩ እንግዳ ቃላት ተካተዋል። (ሙሉ ይዘቱን ከዚህ ጥናት በገጽ 96 ላይ፣ ይመለከታል)።

በአንባሩ ተከታዩ "ሰላም ይስፈን" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም ከርዕሱ ጀምሮ አጠቃላይ ይዘቱ በተዘውታሪ ቃላት የቀረበ እና ዘይቤ አልባ ነው። ስለዚህም ከተለጣጣቂነት አንባር "እሱም አለቀሰ" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም መጨረሻ ላይ ቢቀርብ የተሻለ አደረጃጀትን ይይዝ ነበር።

ለ. ለጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል በተዘጋጀው አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት፤

## 1. ተከታታይነት

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አንድ ተረት፣ 2 አጭር ልቦለዶች፣ አንድ የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ፣ 2 ተውኔቶች እና 4 ግጥሞች ተካተዋል። በአንባራዊት ሲቃኝ ለ7ኛ ክፍል ከቀረበው የተሻለ ሚዛናዊ ድግግሞሽ አሳይታል። ነገር ግን ለግጥም ከፍተኛ ትኩረት ሲሰጥ ለረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ ዝቅተኛ ሽፋን ተሰጥታል። ከይዘት አንባር ያለውን ድግግሞሽ ስንመለከት አንብቦ መረዳት 9፣ የቃላትና ሐረጋት ትምህርት 7፣ ግጥም 2 ጊዜ ሲቀርብ፣ በአንባሩ ሥርዓተ ነጥብ፣ አንቀጽ ምንነት፣ ተውኔት፣ ጠብቀውና ላልተው-

የሚነበቡ ቃላት፣ በምሕላረ ቃላት መጻፍ፣ በአያያዥ ቃላት መጠቀም፣ የሕይወት ገጠመኝ መጻፍ፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ፊሊጣዊ አነጋገሮች፣ ድርብ ቃላትን መመስረት፣ ግጥምን ወደ ስድንባብ (ዝርው) መለወጥና ለሥነምዕላድ ትምህርቶች አንድ ግዜ ብቻ እድል ተሰጥቷቸዋል።

ከቀረበው ዝርዝር መረጃ የምንገነዘበው የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ድግግሞሽ ሚዛናዊነትን የተጠበቀ ቢሆንም በሥሮቻቸው የተደራጁት ይዘቶች ግን ተከታታይነት አይታይባቸውም፤ ለ7ኛ ክፍል እንደቀረበው መጽሐፍ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የዋሉት በቀዳሚነት ለአንብቦ መረዳት እና ለቃላትና ሐረጋት ትምህርቶች ነው። ቀሪዎቹ ይዘቶቹ ግን ከአንድ ጊዜ በላይ አልቀረቡም። ስለዚህም በሥነጽሑፍ አማካይነት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በተከታታይነት የማስተማሩ ተግባር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ተግባራዊ አልተደረገም ማለት ይቻላል።

## 2. ተለጣጣቂነት

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀትን እያሳዩ በሚሄድ መልኩ አልተደራጁም። ለምሳሌ በገጽ 4 ላይ፣ "ጽጌረዳና ደመና" በገጽ 22 ላይ፣ "ማነው ተጠያቂው" በተመሳሳይ በገጽ 79 ላይ "ነገ ጥሩ ቀን ነች" በሚሉ ርዕሶች የቀረቡት ግጥሞች ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ የሚሄዱ አይደሉም። የመጀመሪያው ግጥም አሊጎሪ በተባለው የዘይቤ አይነት የቀረበ ሲሆን ሁለተኛው ግጥም በዘይቤ ባይቀርብም ዘወትሯዊ ያልሆኑ ቃላትን አካቷል። በአንፃሩ "ነገም ጥሩ ቀን ነች" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም በሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቋንቋ አጠቃቀሙ እጅግ ግልፅነት ይታይበታል።

ስለዚህም ሲደራጁ ይህን ባሕሪያቸው ባገናዘበ መልኩ፣ መጨረሻ ላይ የቀረበው ("ነገ ጥሩ ቀን ነች") ቀድሞ ሁለተኛው ግጥም (ማነው ተጠያቂው) ተከትሎ በመጀመሪያ ላይ የቀረበው (ጽጌረዳና ደመና) ደግሞ በስተመጨረሻ ቢመጣ የተሻለ ስፋትና ጥልቀት ያገኝ ነበር።

### *ሐ. ለጋምቤላ ክልል 7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች የተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ተዋረዳዊ አደረጃጀት፤*

ከላይ ለሁለቱ የክፍል ደረጃዎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ጎናዊ አደረጃጀት በተመለከተ ተከታታይነታቸውን እና ተለጣጣቂነታቸውን ለመፈተሽ ተሞክሯል። በዚህ ንዑስ ክፍል ጎናዊ አደረጃጀታቸው ከተዋረዳዊ ግንኙነታቸው ጋር ያለውን መስተጋብር ወይም ጽምረት ለመመልከት እንሞክራለን፤

## 1. ተከታታይነት

በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች መጻሕፍት ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል የሚከተሉት በድግግሞሽ (በተከታታይ) ቀርበዋል ወይም በሁለቱም መጻሕፍት ውስጥ ይገኛሉ፤

አንብቦ መረዳት፤

- የቃላትና ሐረጋት ትምህርት
- ሥርዓት ነጥቦች የአንቀጽ አፃፃፍ
- ተውኔት
- ግጥም
- ጠበቀውና ላልተው የሚነበቡ ቃላት
- ፊሊጣዊ አነጋገሮችና
- ሥነምዕላድ (የርባታ እና የምስረታ ምዕላዶች)

እነዚህ የተዘረዘሩት የትምህርት ይዘቶች በተከታታይ መቅረባቸውና ተማሪዎቹም በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ቋንቋን አይረሴ በሆነ መልኩ መማራቸው በቋንቋው የተሻለ ተጠቃሚዎች ያደርጋቸዋል። ስለዚህም ከተከታታይነት የአደረጃጀት ስልት አንዣር በጠንካራ ጎን የሚታይ ነው። በአንዣሩ በሰባተኛ ክፍል ላይ ቀርበው በ8ኛ ክፍል ግን ትኩረት የተነፈጋቸው ይዘቶችን እናገኛለን። እነሱም፤

- የቃላት እርባታና ምሥረታ
- የቃል ክፍሎች
- ዘይቤአዊ አነጋገሮች
- ልቦለድ (አጭርና ረዥም)

ናቸው።

በተመሳሳይ የሚከተሉት ይዘቶች በ7ኛ ክፍል ላይ ሳይቀርቡ 8ኛ ክፍል ላይ ቀርበው እናገኛቸዋለን፤

- በምህፃረ ቃላት መጻፍ
- አያያዥ ቃላት
- ምሳሌያዊ አነጋገሮች
- ጥምር ቃላትን መመስረት
- ግጥምን ወደ ዝርው ጽሑፍ መቀየር
- ውጥን ታሪክን መጨረስ

እነዚህ ይዘቶች በ7ኛ ክፍል ላይ ተመጥነው ቢቀርቡ ተማሪዎቹ የተሻለ ግንዛቤ እንዲያገኙ ይረዳቸው ነበር። ባጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ዝርዝር ጉዳዮች መገንዘብ እንደሚቻለው 9 ያህሉ ይዘቶች ተከታታይነት ያላቸው ሲሆኑ 10 ያህሉ ግን በአንድ ክፍል ደረጃ (በ7ኛ ወይም በ8ኛ ክፍል) ላይ ብቻ የቀረቡ ናቸው። ስለዚህም ተዋረዳዊ ግንኙነታቸውን የጠበቀ ትስስር የማይታይባቸውና ተከታታይነት የሌላቸው ይዘቶች ቀርበዋል ለማለት ይቻላል።

## 2. ተለጣጣቂነት

በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግመው (በተከታታይ) የቀረቡት የይዘቶች ተለጣጣቂነት የላቸውም። በአንፃሩ ለ7ኛ ክፍል የተዘጋጀው መጽሐፍ ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ቢቀርብ እና ለ8ኛ ክፍል የተዘጋጀው መጽሐፍ ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ቢቀርብ ለተለጣጣቂነት ምሳሌ የሚሆኑ በርካታ ይዘቶችን ማቅረብ በተቻለ ነበር። ምክንያቱም ለ7ኛ ክፍል የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በአፃፃፍ ቴክኒካቸው፣ በቃላት አጠቃቀማቸው፣ በዘይቤአዊነታቸው፣ በፈለጣዊና በምሳሌያዊ አነጋገር ብስለታቸው፣ በአጠቃላይም በቋንቋ አጠቃቀማቸው በ8ኛ ክፍል ከሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አንፃር ሲመዘኑ በአንድ እርከን ከፍ ያሉ በመሆናቸው ነው። በተመሳሳይ በእነዚህ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ላይ ተመሥርተው የቀረቡት ልዩ ልዩ ተግባራት ስፋትና ጥልቀት የሚያሳዩ ናቸው። ተከታዮቹ ለምሳሌነት ቀርበዋል፤

ምሳሌ 1፡- ለ7ኛ ክፍል የቀረበ ግጥም

## *እሱም አለቀሰ*

አለቀሰ ብዕር ...
በዱምዱም ቢቀርጹት ...
ብዕር አለቀሰ
ጥቁረ ቀለም ሳይሆን
ደም እያፈሰሰ...
ያላሰበው ሲጻፍ ...
ያሰበው ተውጦ
እውነት ስትጨነግፍ ...
እብለት ሲታይ በልጦ
ውሸት ነፍስ ዘርቶ ...
ገዘፎ ... ደምቆ... ገዘፎ...ጎልቶ
ቢባባሉ አበጀህ በእንባው ሲጠቀሙ
ቅጥፈት ሲሆን ቤቱ
ህጉ መገጥገጡ መላ መጀምጀሙ ...
ቢሰለቸው ጊዜ አታካች
ስብከቱ...
ጥቁር ቀለም ሳይሆን ...
ደም አያፈሰሰ...
ብዕር አለቀሰ።

(ምንጩ ያልተጠቀሰ፣ ገጽ 119)

ምሳሌ 2፡- ለ 8ኛ ክፍል የቀረበ ግጥም

## *"ነገ ጥሩ ቀን ነች"*

አበበች አበበው ፍቅር ይነዛሉ፣
ሰማያት አብርተው ወንዞች ይጠራሉ፣
ውብ ዜማ እያሰሙ አዕዋፍ ይበራሉ፣
አስደሳች ዜማቸው ሰውን ያነቃሉ፣
ኮረዶች አጊጠው ድንቅ ይጨፍራሉ፣
ጎረምሶች በሳቅ ይንከተከታሉ፣
ከለመለመው መስክ ልጆች ይሄዳሉ፣
በሕብረት ቀለማት ያሸበርቃሉ፣
በባይባይ ጥላ ስር ከበው ይመክራሉ፣
እንስሶች ግመሎች ይፈነጥዛሉ፣
ነገ ጥሩ ቀን ነች ይመሰክራሉ፣
ለዛሬው ቀን ፍልሚያ የሕይወት ጦርነት፣
መልስ የኮረዶች ያጣ በሷ እምነት፣
አሸነፍኩኝ በቃኝ ምን ያደርግልኛል፣
የሚል የዋህ ሰነፍ ጂል ሞቱን ይመኛል፣
አሁን ጭጋግ ብትለብስ ጎላ ትበራለች፣
የምታስለቅስ አድራ ታለቅሳለች፣
...

(ከሀይሉ ፀጋዬ፣ ገጽ 79)

ከቀረቡት ምሳሌዎች መረዳት እንደሚቻለው ለ7ኛ ክፍል የቀረበው ግጥም በአላባፍ ቴክኒኩ፣ በቃላት መረጣው (አጠቃቀሙ)፣ በዘይቤአዊነቱና በሚያነሳው ርዕሰ ጉዳይ ለ8ኛ ክፍል ከቀረበው ግጥም ስፋትና ጥልቀት አለው ለማለት ይቻላል። 7ኛ ክፍል "እሱም አለቀሰ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም ያነበበ አንድ ተማሪ 8ኛ ክፍል ላይ "ነገ ጥሩ ቀን ነች" በሚል ርዕስ የቀረበውን ግጥም አንብቦ ስለግጥም ምንነት ባህሪ ከቀድሞ የተሻለ ግንዛቤ ያገኛል ተብሎ አይታሰብም። ስለዚህም ይህ በተከታታይ የቀረበው የግጥም ትምህርት የተለጣጣቂነት መርህን ተከትሎ የተደራጀ አይደለም። ከአጭር ልቦለዶቹ ላይ እና ከረዥም ልቦለዶቹ ላይ በተወሰዱት ቅንጫቢዎች ላይ የተስተዋለው የተለጣጣቂነት ችግር፣ ከላይ በምሳሌነት ከቀረበው ጋር በእጅጉ ተመሳሳይ ነው።

### *መ. በደቡብ እና በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት*

## 1. ተከታታይነት

በመጻሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙት 13 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መካከል 2 ተረቶች፣ 1 አጭር ልቦለድ፣ 8 የረዥም ልቦለዶች ቅንጫቢዎች እና 2 ግጥሞች ቀርበዋል። ከቀረበው አህዝ የምንረዳው ከተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ተደጋግሞ የቀረበው የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ ሲሆን ለአጭር ልቦለድና ለግጥም አነስተኛ ትኩረት ተሰጥቷል። በአንባሩ ለተውኔት ፍጹም ትኩረት አልተሰጠውም። ከዚህ አንባር ድግግሞሹ ሚዛናዊነትን የጠበቀ አይደለም ለማለት ይቻላል።

በነዚህ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥር የቀረቡትን ይዘቶችና ተግባራት ተከታታይነት ስንመለከት፣ አንብቦ መረዳት 9፣ የቃላትና ሐረጋት ትምህርት 12፣ አንቀጽ መጻፍ 3፣ ጊዜ ተደጋግመው ሲመጡ፣ ድርብ ቃላትን መመሥረት 2፣ ሥነምዕላድ 2 ጊዜ ቀርቧል። በአንባሩ ሥርዓተ ነጥብ፣ ዘይቤ፣ ግጥም፣ የሚጠብቁና የሚላሉ ቃላት፣ ምህላፈቃላት፣ ምሳሌያዊ አነጋገር፣ ጽሑፍን ማሳጠር፣ ሥነድምፅ፣ ውይይት አዘገጃጀት እና ሥነቃል ትምህርቶች አንድ ጊዜ ብቻ ቀርበዋል። ከዚህ የምንረዳው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ በተከታታይ የቀረቡት የአንብቦ መረዳትን እና የቃላትን (የሐረጋትን) ፍቺ ለማስተማር ተግባር መሆኑ ነው። በአንባሩ ሌሎቹ የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በተከታታይ አልቀረቡም።

## 2. ተለጣጣቂነት

በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ምንጭነት ተከታትለው በመምጣት የተደራጁት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ የሚንዘሙ አይደሉም፤ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥር በተከታታይነት የቀረቡት የአንብቦ መረዳት እና የቃላት ትምህርት ይዘቶች አንዳራዊ የሆነ ስፋት ወይም ጥልቀት በሚያሳይ መልኩ አልተደራጁም። ለምሳሌ፣ ገጽ 66 ላይ "ወርቅ ላበደረ" በሚል ርዕስ ሥር የቀረቡት የቅላት ትምህርት እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ቀደም ሲል ተማሪዎቹ በገጽ 42 እና 43 ላይ "ተከስተና ወይዘሮ ጽጌ" በሚል ርዕስ ከቀረበው የአንብቦ መረዳት እና የቃላት ትምህርት ከተማሩት ይዘት የተሻለ ግንዛቤ የሚሰጣቸው አይለደም። ይልቁንም ገጽ 66 ላይ በቀረበው ተረት አንብቦ መረዳትን እና ቃላትን ከተለማመዱ በኋላ ገጽ 42 እና 43 ላይ በቀረበው የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ አማካኝነትም የአንብቦ መረዳት እና የቃላት ትምህርትን ቢማሩ የተሻለ ግንዛቤን (እድገት በሚያሳይ መልኩ) ይጨብጡ ነበር ለማለት ይቻላል።

በተመሳሳይ በተናጥል የቀረቡትን ይዘቶች ተለጣጣቂነት ስንመለከት ዕድገት በሚያሳይ መልኩ አልተደራጁም። ለምሳሌ ተማሪዎቹ "የበዩዎች አለመስማማት ለተበዩ ይበጃል" በገጽ 1-2 ላይ፣ በሚለው ሥነጽሑፋዊ ሥራ ምንጭነት ጽሑፍን ማሳጠር ከመማራቸው በፊት በገጽ 60 ላይ "የከፋው አባት ደብዳቤ" በሚለው ሥነጽሑፋዊ ሥራ መሠረት የቀረበላቸው የአንቀጽ ትምህርት ሊቀድም ይገባው ነበር።

እነዚህ ከላይ ለአብነት ያህል የቀረቡትን ዓይነት (መሰል) የተለጣጣቂነት ጉድለቶች በአብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችና በስሮቻቸው በተደራጁት ልዩ ልዩ ይዘቶች ላይ ተስተውሏል።

### ሠ. በደቡብ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ለ8ኛ ክፍል በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት

### 1. ተከታታይነት

በመጻሕፍቱ ውስጥ ከሚገኙት 6 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መካከል 2 አጭር ልቦለዶች፣ 2 የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢዎች፣ ተውኔት እና ግጥም ተካተዋል። ከዚህ አህዛዊ መግለጫ የምንረዳው ሚዛናዊነቱን የጠበቀ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ድግግሞሽ

መኖሩን ነው። ከዚህ አንፃር ከሁሉም የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል፤ ምንም እንኳን የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቁጥራቸው አነስተኛ ቢሆንም ተመጣጣኝ የሆነ ድግግሞሽ መኖሩ አደረጃጀቱን በአመንታዊነት እንዲታይ ያደርገዋል።

በነዚህ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ምንጭነት የቀረቡትን የተለያዩ የትምህርት ይዘቶች ድግግሞሽ በተመለከተም አንብቦ መረዳት 6፣ ቃላትና ሐረጋት ትምህርት 2፣ ድርሰት 2፣ ፊሊጣዊ አነጋገር 2 ጊዜ ሁለት ጊዜ ሲቀርቡ በአንፃሩ ተውኔት፣ ዘይቤ፣ ግጥም፣ ልቦለድና ምህፃረቃላት አንድ ግዜ ብቻ ሽፋን ተሰጥቷቸዋል። ከዚህ በፊት እንደቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በዚህ መጽሐፍም ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሠጠው ለአንብቦ መረዳት ትምህርት ሲሆን የቃላትና ሐረጋት ትምህርት ግን ከሌሎቹ ይዘቶች ጋር ተመጣጣኝ ድግግሞሽ ተሰጥቶታል። በአንፃሩ አብዛኞቹ ከላይ የተዘረዘሩት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በተከታታይነት አልቀረቡም።

## 2. *ተለጣጣቂነት*

በነዚህ *መማሪያ መጻሕፍት* ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዘትና በሥራቸው የቀረቡት ንዑሳን የትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት በሚያሳይ መልኩ አልተደራጁም። ለምሳሌ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትንም ሆነ የቃላትን ዓውዳዊ ፍችዎች በቀላሉ ሊረዷቸው በሚችሉት ሥራዎች (በአጭር ልቦለዶችና የረዥም ልቦለዶች ቅንጫቢዎች) አማካይነት እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ በተውኔቶችና ግጥሞች፣ በቀጣይነትም እንዲማሩ በደረጃ ድግግሞሹ አንፃራዊ የሆነ እድገት እያሳየ ይንዝ ነበር። ነገር ግን በነዚህ *መማሪያ መጻሕፍት* ውስጥ የዚህ ተቃራኒ አደረጃጀት እናገኛለን፤ ሥነጽሑፋዊ ሥራ መቅረብ የጀመረው በገጽ 79-83 እና 59-64 ላይ በቀረበው "የፊውስ ሐዋርያዎች" ተውኔት ሲሆን እሱን ተከትሎ ገጽ 175 እና 122 ላይ ርዕስ የሌለው ግጥም ቀርቧል። ተማሪዎቹ ከመነሻቸው ላይ በነዚህ ሁለት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ምንጭነት (መነሻነት) አንብቦ መረዳት፣ ተውኔት፣ ግጥም እና ድርሰት መጻፍ ከተማሩ በኋላ ገጽ 218-223 እና 147-153 ላይ "ሙሉ ልብስ" በሚል ርዕስ በቀረበ አጭር ልቦለድና ገጽ 226-228 "ቀኝ አገዛማች አላጌ" በሚል ርዕስ በቀረበ የረዥም ልቦለድ ቅንጫቢ አማካይነት አንብቦ መረዳት፣ ቃላት (ሐረጋት)፣ የልቦለድ ባሕርያትና ፊሊጣዊ አነጋገሮች እንዲማሩ ተደርጓል። ነገር ግን የተማሪዎቹ ግንዛቤ ስፋት እና ጥልቀት

እያሳየ አንዲሄድ ከተፈለገ በአጭር እና በረዥም ልቦለድ ቅንጫቢው ሥር የቀረቡት ይዘቶች ቀድመው፣ በተውኔቱና በግጥሞቹ ሥር የተደራጁት ንዑሳን ይዘቶች መከተል ነበረባቸው።

ባጠቃላይ ለነዚህ ሁለት ክልሎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተለጣጣቂነት መርህን ተከትለው (ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ) ተደራጅተዋል ለማለት አያስደፍርም።

*ረ. በደቡብ እና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍሎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት ተዋረዳዊ አደረጃጀት፣*

በተጠቀሱት ሁለት ክልሎች የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ጎናዊ አደረጃጀት (ተከታታይነታቸውንና ተለጣጣቂነታቸውን) በተመለከተ ከላይ በቀረበው በ "መ" እና "ሠ" ንዑስ ክፍል ለማየት ተሞክሯል። በዚህ ንዑስ ክፍልም ከተዋረዳዊ አደረጃጀታቸው አንፃር ያላቸው ጽምረት ይቃኛል።

### *1. ተከታታይነት*

በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች መጻሕፍት ውስጥ ከቀረቡት ይዘቶች መካከል የሚከተሉት በድግግሞሽ (በተከታታይ) ቀርበዋል፣

- አንብቦ መረዳት
- የቃላትና ሐረጋት ትምህርት
- የአንቀጽ አጣጣፍ
- ተውኔት
- ዘይቤ
- ግጥም
- ምህላረ ቃላት

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ላይ መቅረባቸው ተማሪዎቹ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መሣሪያነት ሳይቆራረጥ እንዲተገብሩ ስለሚያስችል በአዎታዊነት የሚታይ ተግባር ነው። በአንፃሩ ተማሪዎቹ በ7ኛ ክፍል በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ምንጭነት የተማሯቸው የሚከተሉት ይዘቶች በ8ኛ ክፍል ላይ እንዲቀጥሉ አልተደረገም፤

- ቃላት ምሥረታና እርባታ (ሥነምዕላድ)
- ሥርዓተ ነጥቦች
- ላልተውና ጠብቀው የሚነበቡ ቃላት
- ምላሌያዊ አነጋገሮች
- ድርብ ቃላትን መመስረት
- ጽሑፍን አሳጥሮ መጻፍ
- የድምፅ ምስለትና መዋጥ (ሥነድምፅ)
- ውይይት አዘገጃጀትና አቀራረብ
- ሥነቃል

ተማሪዎች እነዚህን የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች በሥነጽሑፍ መሣሪያነት አይረሴ በሆነ መልኩ እንዲገነዘቧቸው በማድረግ የታቀደውን የትምህርት ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ የሚቻለው ተከታታይነት ባለው መልኩ ሲቀርብላቸው ነው። ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህ ተዋረዳዊ ግንኙነት የላላ ነው ለማለት ይቻላል። በሌላ በኩል ተማሪዎቹ በ7ኛ የክፍል ደረጃ ላይ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መሣሪያነት ያልተማሯቸውን የትምህርት ይዘቶች በ8ኛ የክፍል ደረጃ ላይ እንዲማሯቸው ተደርጓል። እነዚህ ይዘቶች፤

- የልቦለድ ምንነት
- ድርሰት
- ፊሊጣዊ አነጋገሮች

ናቸው።

እነዚህ ሦስት ይዘቶች በአንድ የቋንቋ የትምህርት ዓላማ ውስጥ በንዑሳን የዕውቀት ዘርፎች ሥር የሚመደቡ ከመሆናቸው አኳያ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ትኩረት ተሰጥቷቸው በተከታታይነት ሊቀርቡ ይገባ ነበር። በአጠቃላይ በሥነጽሑፍ አማካይነት ቋንቋን ለማስተማር የቀረቡት ይዘቶች በነዚህ ሁለት መጻሕፍት ውስጥ ተከታታይነት ባለው መልኩ አልቀረቡም ለማለት ይቻላል።

## 2. ተለጣጣቂነት

በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍሎች መጻሕፍት ውስጥ ተደጋግመው (በተከታታይ) ከቀረቡት 7 ይዘቶች ውስጥ አንበበ መረዳት፣ የቃላት (ሐረጋት) ትምህርትና ግጥም በአንባራዊነት እድገት በሚያሳይ መልኩ ቀርበዋል። በአንባሩ አንቀጽ አባባፍ፣ ዘይቤ፣ ተውኔትና የምህፃረ ቃላት ትምህርቶች አደረጃጀት ተለጣጣቂነት አይታይባቸውም። የሚከተሉትን ለአብነት እንመልከት፤

ለ7ኛ ክፍል "እንማር" በሚል ርዕስ በገጽ 82 (ደቡብ) እና ገጽ 8 (ቤኒሻንጉል) ላይ የቀረበው የግጥም ትምህርት እና ለ8ኛ ክፍል በገጽ 175 ላይ፣ በገጽ 122 ላይ፣ የቀረበው የግጥም ትምህርት ተለጣጣቂነት አለው። ተማሪዎቹ በ7ኛ ክፍል ላይ የግጥም እና የዘርው ዕሑፍን ልዩነቶች በተጨማሪም የሥንኝና የሐረግና ምንነት እንዲለዩ ከተደረገ በኋላ በ8ኛ ክፍል ላይ ግን ሥለሥነግጥማዊ ቃላት ብያኔ (ቤትመታ፣ቤትደፋ፣ መነሻ ሐረግ፣ መድረሻ ሐረግ...) እንዲገነዘቡ በማድረግ በግጥሙ ውስጥ የቀረቡትንም መነሻና መድረሻ ሐረጎች እንዲለዩ፣ በመጨረሻም ተዘበራርቀው የተቀመጡ የግጥም ሐረጎችን እንደገና አስተካክለው እንዲጽፉ የሚጠይቁ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ተደርጓል። ከዚህም ባሻገር ለግጥም ትምህርቱ መነሻ የሆኑት ሁለት ግጥሞች ተለጣጣቂነት አላቸው፤ ለ8ኛ ክፍል የቀረበው ግጥም ለ7ኛ ክፍል ከቀረበው በሚያነሣው ርዕሰጉዳይ ክብደት (ረቂቅነት) እና በአጻጻፍ ስልቱ በአንድ እርከን ይበልጣል። ከነዚህ እውነታዎች በመነሣት በሁለቱ የክፍል ደረጃዎች ላይ የቀረበው የግጥም ትምህርት የተለጣጣቂነት መርህን ተከትሎ የቀረበ ነው ለማለት ይቻላል።

በአንባሩ "የከፋው አባት ደብዳቤ"፣ "ወርቅ ላበደረ" እና "ውለታ" በሚሉ ርዕሶች ሥር በቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መነሻነት ለ7ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጀው የአንቀጽ ትምህርት እና ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች "የአንድ ቀን ውሎ" በሚለው ምንባብ መነሻነት የቀረበላቸው የአንቀጽ ትምህርት፣ የይዘት እድገት የማያሳይ ወይም ተለጣጣቂነት የሌለው ነው። ምክንያቱም ተማሪዎቹ በ7ኛ ክፍል ላይ ጅምር ዓረፍተነገሮችን በማሟላት፣ የቀረበላቸውን ርዕስ፣ እና የዓረፍተ ነገሮችን ቅደም ተከተል በማስተካከል አንቀጽ መጻፍ እንዲለማመዱ ከተደረገ በኋላ በ8ኛ ክፍልም በተመሳሳይ ተማሪዎቹ የተሰጧቸውን አረፍተነገሮች በማስፋፋት አንቀጽ እንዲጽፉ ተደርጓል። በነዚህ ሁለት የክፍል ደረጃዎች ላይ የቀረበውን የአንቀጽ ትምህርት ይዘቶች ስንቃኝ

ስፋትና ጥልቀት በሚያሳይ መልኩ አልተደራጁም፤ በ7ኛ ክፍልም ሆነ በ8ኛ ክፍል ላይ ከአንድ አንቀጽ በላይ እንዲጽፉ ካለመደረጉም ባሻገር የተለያዩ የአንቀጽ ማስፋፊያ ሥልቶችን በየክፍል ደረጃው ላይ በሥነጽሑፍ ሥራዎች አማካይነት እንዲማሩ አልተደረገም።

በተመሳሳይ በ7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች ላይ የቀረበው የዘይቤ ትምህርት ተለጣጣቂነት የለውም። ተማሪዎቹ በ7ኛ ክፍል "ከባሌ መልስ" በሚለው ምንባብ መነሻነት አንባቢ ዘይቤንና፣ ተለዋጭ ዘይቤን "ሴትየዋ ጎበዝ ሠራተኛ ናት" እና "ሴትየዋ ንብ ናት" በሚሉት ምሳሌዎች መሠረት እንዲለማመዱ ከተደረገ በኋላ በ8ኛ ክፍል "ሱጴ" በሚል ርዕስ ከቀረበው ምንባቡ ውስጥ ተማሪዎቹ "ህይወት በጋዲ የታሰራች ይመስላል።" በሚለው አንባቢ ዘይቤ ምሳሌነት ቀሪዎቹን (በምንባቡ ውስጥ የቀረቡትን አንባቢ ዘይቤዎች) እንዲያወጡ ተደርጓል። ከዚህ የምንረዳው ተማሪዎቹ ዘይቤን በተመለከተ 7ኛ ክፍል ከተማሩት የተለየ ግንዛቤን 8ኛ ክፍል ላይ አለመጨበጣቸውን ነው ተለጣጣቂነት እንዲኖር ከታሰበ፣ ለምሳሌ ተማሪዎቹ በ7ኛ ክፍል ላይ አንባቢ ዘይቤ ምንነት ጠንቅቀው ከተረዱ በኋላ በ8ኛ ክፍል ደግሞ ተለዋጭ ዘይቤን በተጨማሪነት እንዲማሩ ቢደረግ ተማሪዎቹ ወደፊትም የተሻለ ግንዛቤ እያገኙ እንደሚሄዱ በማሰብ የቋንቋ ትምህርቱን በፍላጎት እንዲማሩት ለማድረግና መሰላቸትን ለማስወገድ ይቻል ነበር።

ባጠቃላይ ከላይ በተናጥል ከቀረቡት ማብራሪያዎች መረዳት እንደሚቻለው፣ በሥነጽሑፍ አማካኝነት ቋንቋ ለማስተማር ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍሎች የተመረጡት ይዘቶች ሲደራጁ ተከታታይነትና ተለጣጣቂነት እንዲኖራቸው አልተደረገም።

### 4.1.2.4. በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው የመደራጀታቸው ሁኔታ

ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመርሐትምህርቱ ላይ የተተለሙትን ዓላማዎች ሊያሳኩልን የሚችሉት፣ ተማሪዎቹ ምንባቦቹን በጉጉት (በፍላጎት) ማንበብ ሲችሉ ነው። ከዚህ አንፃር ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው መደራጀታቸው፣ ተማሪዎቹ ሁለቱንም በንጽጽር የማየት

አጋጣሚ ስለሚፈጥርላቸው፣ ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ልዩ ትኩረት እንዲኖራቸውና መለላቸት እንዳይኖር ይረዳሉ። በአንባሩ ተመሳሳይ ሥራዎችን (ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ወይም ሥነጽሑፋዊ ይዘት የሌላቸውን) በተከታታይ ማቅረቡ የመሰላቸትን ስሜት ሊፈጥር እንደሚችል በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሁለት ለመግለጽ ተሞክሯል።

በዚህ ንዑስ ክፍል በሶስቱ ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች፣ ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው መቅረብ - አለመቅረባቸውን እንመለከታለን፤

## *ሀ. ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ*

በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 20 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችና 15 ሥነጽሑፋዊ ያልሆኑ ሥራዎች ቀርበዋል። የሁለቱም ቁጥር ተቀራራቢ በመሆኑ አፈራርቆ ለማደራጀት አመቺ ቢሆንም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ግን በትክክል ተሰባጥረው አልተቀመጡም። ለምሳሌ ከገጽ 103 ጀምሮ እስከ ገጽ 143 ድረስ 9 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በተከታታይ ቀርበዋል፤ ሥነጽሑፋዊ ያልሆነ ሥራ የምናገኘው ገጽ 130 ላይ ብቻ ነው። በተመሳሳይ ከገጽ 143 እስከ ገጽ 160 ድረስ 6 ሥነጽሑፋዊ ያልሆኑ ሥራዎች ተከታትለው ሲቀርቡ፣ ከገጽ 167 እስከ ገጽ 188 ደግሞ 4 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን እናገኛለን። ቀሪዎቹ 7 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከገጽ 1 እስከ ገጽ 103 ድረስ አንባራዊ በሆነ መልኩ ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው ቀርበዋል።

በሌላ በኩል ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ እርስበርሳቸው (አንዱ ከሌላው ጋር) ተሰባጥረው አልቀረቡም፤ የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢዎች እና ግጥሞች ተከታትለው ቀርበው። ለምሳሌ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት 4 ግጥሞች በተከታታይ ከገጽ 119 እስከ ገጽ 127 ቀርበዋል። ይህ አደረጃጀት በተማሪዎቹ ዘንድ የመሰላቸትን ስሜት ሊፈጥር ስለሚችል ከአጭር ልቦለዶቹና ከረጅም ልቦለዶቹ ጋር ተሰባጥረው ቢቀርቡ የተሻለ ይሆን ነበር።

## *ለ. ለጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ*

በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 10 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችና 18 ሥነጽሑፋዊ ያልሆኑ ሥራዎች ቀርበዋል። ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ በቁጥር አነስተኛ

ቢሆኑም ተሰባጥረው አልተደራጁም፤ 6ቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከገጽ 69 እስከ ገጽ 96 (እስከ መጨረሻው ገጽ) ድረስ በተከታታይ ቀርበዋል። ቀሪዎቹ 4 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግን አንባራዊ በሆነ ሁኔታ ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው ቀርበዋል ለማለት ይቻላል።

በሌላ በኩል የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን የርስበርስ ስብጥር ስንቃኝ በተከታታይ የቀረበ አናገኝም፤ ግጥም ተውኔት፣ የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ፣ ተረትና አጭር ልቦለድ ተሰባጥረው ቀርበዋል።

### *ሐ. ለደቡብ ክልል 7ኛ ክፍል የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ*

በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 13 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችና 19 ሥነጽሑፋዊ ያልሆኑ ሥራዎች ቀርበዋል። አደረጃጀታቸውን በተመለከተም ከመነሻ ላይ (ከገጽ 1-8) ሁለት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በተከታታይ ቀርበው ተከታዮቹ 6 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው ከገጽ 18 እስከ ገጽ 71 ድረስ ተደራጅተዋል። ነገር ግን 3 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ከገጽ 76 እስከ 86 ድረስ በተከታታይ ቀርበው እናገኛለን። በተመሳሳይ ገጽ 108 እና ገጽ 113 ላይ ሁለት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታትለው ቀርበዋል።

በሌላ በኩል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ከቀረቡት 8 የረጅም ልቦለድ ቅንጫቢ ታሪኮች ውስጥ 5 ያህሉ ከገጽ 8 እስከ 51 ድረስ (በመካከላቸው ሌሎች የሥነጽሑፍ አይነቶች ሳይቀርቡ) ተከታትለው ቀርበዋል። በተመሳሳይ ግጥሞቹም በተከታታይ ቀርበዋል።

### *መ. ለደቡብ ክልል 8ኛ ክፍል የተዘጋጀ መማሪያ መጽሐፍ*

በዚህ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ 6 ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ሥራዎች እና 29 ሥነጽሑፋዊ ይዘት የሌላቸው ሥራዎች ቀርበዋል። ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ በቁጥር ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት አንባር ሲታዩ እጅግ አነስተኛ ቢሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ ግን በአግባቡ ተሰባጥረው አልቀረቡም። ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የቀረቡት ከገጽ 79 ጀምሮ ሲሆን ከሁለቱ በስተቀር 4 ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከገጽ 191 እስከ ገጽ 226 (እስከመጨረሻው ምንባብ) ድረስ በመካከላቸው ገጽ 210 ላይ "ከባቢ አየር" በሚል ርዕስ አንድ ሥነጽሑፋዊ ያልሆነ ሥራን ብቻ በማካተት በተከታታይ ቀርበዋል።

## ሠ. ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች የተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት

ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች የተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ለደቡብ ክልል በተዘጋጁት ላይ መጠነኛ ማሻሻያ ተደርጎባቸው የቀረቡ ከመሆናቸው አንፃር በአደረጃጀታቸው ላይ የታየ ልዩነት የለም። ልዩነታቸው የተወሰነ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መቀነሳቸውና በተመሳሳይ ሥነጽሑፋዊ ያልሆኑ ሥራዎች ላይ መጠነኛ ለውጥ መደረጉ ነው። ለምሳሌ ለደቡብ ክልል 7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መጽሐፍ ላይ "የደቡብ ብሔር ብሄረሰቦች ሕዝቦች ክልል ገጽታ" ገጽ 117 በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ፣ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል 7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መጽሐፍ ላይ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ገጽታ" ገጽ 111 በሚል ተተክቶ ቀርቧል። ስለዚህም ከላይ በ"ሐ" እና በ"መ" ሥር የቀረበው ማብራሪያ በዚህ ክልል የተዘጋጁትን መጻሕፍትም ይመለከታል።

በአጠቃላይ ከላይ በተናጠል ለመግለጽ እንደተሞከረው ለሦስቱ ክልሎች 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው እንዲደራጁ (እንዲቀርቡ) አልተደረገም። ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አፈራርቆ ከማደራጀት አንፃር ግን ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል የተዘጋጀው መጽሐፍ የተሻለ መሆኑን ከላይ ከቀረበው ማብራሪያ መገንዘብ ይቻላል።

## 4.2. ለመምህራን ከቀረበ የጽሑፍ መጠይቅ እና ከቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትንተና

የዚህ ጥናት ዐቢይ ትኩረት የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ክልሎች ለ7ኛ እና ለ8ኛ ክፍል ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ እና አደረጃጀት መመርመር ነው። በመሆኑም በቀዳሚነት በሀገራችን እና በውጭ ሀገራት ምሁራን የቀረቡትን የአመራረጥና የአደረጃጀት መርሆዎች መሠረት በማድረግ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ሰፊ ትንታኔ ቀርቧል። ይህን ትንታኔ የበለጠ አስተማማኝ (ተጨባጭ) በማድረግ ተጠየቃዊነቱን ለማጉላት ይቻል ዘንድም ከመምህራን በጽሑፋዊ መጠይቅ አማካይነት መረጃዎችን ማሰባሰቡ እጅግ ጠቃሚ መሆኑ ስለታመነበት ተግባራዊ ተደርጓል። የመምህራኑን ሰፊ ግንዛቤ በብቃት መጠቀም ይቻል ዘንድም ከተለያዩ አቅጣጫዎች ያነጣጠሩ እና የጥናቱን የትኩረት አቅጣጫ ያልሳቱ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል። ጥያቄዎቹ ሦስት አበይት ክፍሎች አሏቸው። እነዚህም የመጀመሪያው ክፍል (ከዚህ በመቀጠል የሚቀርበው) የመምህራኑን አጠቃላይ ዳራ የሚያስቃኝ ሲሆን፣ ሁለተኛው አበይ ክፍል ዘርዘር ያሉ ነጥቦችን የያዙ 47 ጥያቄዎችን አካቷል። ሶስተኛው ክፍልም መምህራኑ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥና አደረጃጀት ላይ ያስተዋሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመጠቆም ወደፊት መወሰድ ያለበትን ጥንቃቄ በጽሑፍ እንዲገልጹ የሚጋብዙ 5 ጥያቄዎችን የያዘ ነው። የመጠይቁ የመጀመሪያ ክፍል እንደሚከተለው ይቀርባል፤

## ሠንጠረዥ 2፡- መጠይቁን የሞሉ መምህራን አጠቃላይ ዳራዊ መግለጫ

| | | | ጋምቤላ ክልል | ደቡብ ክልል | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የሠለጠኑበት የትምህርት ዘርፍ | አቢይ | አማርኛ | 10 | 7 | 10 | 27 |
| | | እንግሊዘኛ | - | 3 | - | 3 |
| | ንዑስ | እንግሊዘኛ | 10 | 7 | 8 | 25 |
| | | አማርኛ | - | 3 | - | 3 |
| ፆታ | ወንድ | | 5 | 4 | 5 | 14 |
| | ሴት | | 5 | 6 | 5 | 16 |
| ዕድሜ | 26-30 | | 1 | 1 | - | 2 |
| | 31-35 | | 8 | 1 | 3 | 12 |
| | 36-40 | | - | 4 | 5 | 9 |
| | 41-45 | | - | 4 | 1 | 5 |
| | 46-50 | | 1 | - | 1 | 2 |
| የትምህርት ደረጃ | የመጀመሪያ ዲግሪ | | - | 4 | - | 4 |
| | ዲፕሎማ | | 10 | 6 | 10 | 26 |
| የአፍ መፍቻ ቋንቋ | አማርኛ | | 6 | 10 | 7 | 23 |
| | ኦሮምኛ | | 3 | - | 3 | 6 |
| | ከፍኛ | | 1 | - | - | 1 |
| የአገልግሎት ዘመን | 1-10 | | 2 | 2 | - | 4 |
| | 11-20 | | 7 | - | 6 | 13 |
| | 21-30 | | 1 | 8 | 4 | 13 |
| መማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት | የተሳተፉ | | 2 | - | - | 2 |
| | ያልተሳተፉ | | 8 | 10 | 10 | 28 |

ከሠንጠረዥ 2 መገንዘብ የሚቻለው፣ የጽሑፍ መጠይቁን የሞሉት መምህራን በአማርኛ ቋንቋ የትምህርት ዘርፍ የሠለጠኑ እና የኮሌጅ ዲፕሎማና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያላቸው በመሆናቸው የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ለማስተማር ብቁ ናቸው ለማለት ይቻላል። ከዚህም በተጨማሪ የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል ሁለቱ በመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ላይ ተሳትፈዋል። እነዚህ በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የተሳተፉ መምህራን መኖራቸው በተለይ በክፍት ጥያቄዎች ላይ ለጥናቱ ጠቃሚ ሐሳቦችን በጽሑፍ ለመሠንዘር ይረዳቸዋል ተብሎ ይታመናል። በሌላ በኩል መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል ሰባት ያህሉ በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፈ-ፈት መሆናቸው ተማሪዎቻቸውን በተመለከተ ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች ከራሳቸው ተሞክሮ ጋር በማቀናጀት ምላሽ ለመስጠት ሊረዳቸው ይችል ይሆናል። የአገልግሎት ዘመናቸውን በተመለከተም አብዛኞቹ ከአሥር ዓመት በላይ በመምህርነት ሞያ ላይ የቆዩ ናቸው።

ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ሥራዎች በመምረጥ በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ለማካተት ቀዳሚው መስፈርት ከተማሪዎቹ አጠቃላይ ዳራ አንፃር ተገቢነታቸውን መፈተሽ ነው። የተማሪዎችን ማንነት በቅርብ ሊከታተሉና ሊረዱ የሚችሉት ደግሞ በዋነኛነት መምህሮቻቸው ናቸው። ከዚህ አንፃር መምህራን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ትግበራ ላይ (በተለይ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች በተመለከተ) ያስተዋሏቸውን እውነታዎች መነሻ በማድረግ ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ተገቢነት በተመለከተ፣ የጽሑፍ መጠይቅ ቀርቦላቸው የሰጡትን መልስ ከተከታዩ ሠንጠረዥ እንመልከት፤

## ሠንጠረዥ 3፣- የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ዝንባሌ፣ ፍላጐትንና ግንዛቤ አንፃር

| ተ.ቁ | የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ከተማሪዎቹ ዕድሜ፣ ዝንባሌ፣ ፍላጎትና ግንዛቤ አንፃር፤ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | * 5፣4 | ** 3 | *** 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣ |
| 1.1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ማለትም አጭር ልቦለዶች፣ ረዥም ልቦለዶች፣ ተውኔቶች፣ ግጥሞችና ተረቶች ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር ይጣጣማሉ። | 1 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 | 5 | - | - | 3 | - | 2 | 5 | - | - | 2 | 2 | 1 |
| 1.2 | ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከተማሪዎቹ የዕድሜ ደረጃ ጋር አይመጣጠኑም። | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 2 | - | 3 | 2 | - | 3 | 3 | - | 2 | 3 | 1 | 1 |
| 1.5 | ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ሲያነቡ ወይም ሲነበብላቸው በጉጉት፣ በደስታ ስሜትና በንቃት እስከመጨረሻው ይከታተላሉ። | - | 1 | 4 | 2 | 1 | 2 | 5 | - | - | 3 | - | 2 | 4 | 1 | - | 2 | 1 | 2 |
| 5.10 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቀረቡት አጫጭርና ረጃጅም ልቦለድ ታሪኮች ውስጥ የሚገኙት ገጸባሕርያት ከተማሪዎቹ እድሜ ጋር የተቀራረቡ ናቸው። | - | 1 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 | - | 2 | - | 1 | 4 | 2 | 1 | 2 |
| 5.11 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አጫጭር ልቦለዶችና ከረጃጅም ልቦለዶች ላይ የተወሰዱት ታሪኮች ከተማሪዎቹ የሕይወት ልምድ ጋር የማይቀራረቡ ናቸው። | 3 | - | 2 | 3 | - | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | - | 2 | 1 | 3 | 1 |

* 5 በጣም እስማማለሁ
4 እስማማለሁ

** 3 መወሰን ያስቸግረኛል

***2 አልስማማም
1 ፍፁም አልስማማም

ሠንጠረዥ 3 በግልጽ እንደሚያመለክተው፣ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር ያላቸውን ስምረት በተመለከተ፣ ለ7ኛ የክፍል ደረጃ የተዘጋጀውን ስንቃኝ፣ በጋምቤላ 3 መምህራን አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ በአንፃሩ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና የደቡብ ክልል መምህራን 5 አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ለዚሁ ጥያቄ የ8ኛ ክፍልን መማሪያ መጽሐፍ አስመልክቶ 3 የጋምቤላ እና 3 የደቡብ ክልል መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

በሌላ መልኩ "የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ የዕድሜ ደረጃ ጋር አይመጣጠኑም" ተብሎ የቀረበውን ሐሳብ 7ኛ ክፍልን በተመለከተ በጋምቤላ ክልል 3 መምህራን እና በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል 3 መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ በንፃሩ ከደቡብ ክልል 3 መምህራን ሐሳቡን አልተቀበሉም። የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተም፣ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል እና 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ 3 መምህራን ከደቡብ ክልል አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።

የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር ያላቸውን ተገቢነት ለማረጋገጥ "ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች ሲያነቡ ወይም ሲነበብላቸው በጉጉት፣ በደስታ ስሜትና በንቃት እስከመጨረሻው ይከታተላሉ።" የሚለውን ሐሳብ ከደቡብና ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች አብዛኞቹ መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ 4 የጋምቤላ ክልል መምህራን ግን አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይኸው ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ ከደቡብ ክልል 3 መምህራን አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ የጋምቤላና የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎችን መማሪያ መጻሕፍት በተመለከተ ግን አዎንታዊ እና አሉታዊ ምላሽ የሰጡት መምህራን ተመጣጣኝ ሆነዋል። ይህ መሰል ምላሽ ሊገኝ የቻለው ምናልባት መምህራን ምንባቦቹ በክፍል ውስጥ ሲነበቡ በተማሪዎቻቸው ገጽታ ላይ ከሚያስተውሏቸው የተለዩ ስሜቶች በመነሳሳት ሊሆን ይችላል። ስለዚህም አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት መምህራን አፈ-ፈት ተማሪዎችን ከግምት ውስጥ አስገብተው መልስ ሲሰጡ፣ አሉታዊ መልስ የሰጡት ግን ለኢአፈ-ፈት ተማሪዎች ቀዳሚውን ትኩረት ስለሰጡ ሊሆን ይችላል።

"በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ለቀረቡት አጫጭርና ረጃጅም ልቦለድ ታሪኮች ውስጥ የሚገኙት ገጸባሕርያት ከተማሪዎቹ እድሜ ጋር የተቀራረቡ ናቸው።" በሚል ለቀረበው ጥያቄ 4 ለጋምቤላ፣ 2 የደቡብና 4 የቤኒሻንጉል ክልሎች 7ኛ ክፍል መምህራን አሉታዊ መልስ ሲሰጡ ለዚሁ ጥያቄ 3 የ8ኛ ክፍል መምህራን ከደቡብ ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር በመማሪያ መጻሕፍቱ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተገቢነት በተመለከተ በመጨረሻ ላይ ለመምህራኑ የቀረበላቸው ሐሳብ

"ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከተማሪዎቹ የሕይወት ልምድ ጋር የማይቀራረቡ ናቸው" የሚል ሲሆን ለዚህ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ፣ 7ኛ ክፍልን በተመለከተ 3 መምህራን ከጋምቤላ፣ 2 መምህራን ከደቡብ እና 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። የ8ኛክፍል መማሪያ መጻሕፍን በተመለከተ ግን 3 የጋምቤላ ክልል መምህራን ብቻ አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል።

በመማሪያ መጻሕፍቱ (በ7ኛ እና 8ኛ ክፍል) የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ተገቢነት፣ ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር ለመፈተሽ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ለመምህራኑ ከቀረቡት የግንዛቤ ጠያቄዎች የተገኙት ምላሾች ሲጠቃለሉ የሚጠቁሙን በሦስቱም ክልሎች በተዘጋጁት መጻሕፍት ላይ መምህራኑ ችግሮች ማስተዋላቸውን ነው። በንፃራዊነት ሲታይ ግን ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል የተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ከተማሪዎቹ ዳራ እጅግ ያፈነገጠ መሆኑን መምህራኑ ከሰጡት መልስ መረዳት ይቻላል። ይህ እውነታም ቀደም ሲል በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ከተሰጠው ትንታኔ ጋር የሚዛመድ ነው።

ይህን ንዑስ ክፍል ከማጠቃለላችን በፊት ከላይ መምህራኑ በዝግ ጥያቄዎች ከሰጡት ምላሽ በተጨማሪ ሐሳባቸውን በጽሑፍም (በክፍት ጥያቄ) እንዲገልጹ ጥያቄ ቀርቦላቸው ከሠፈሩት ውስጥ፣ ተከታዮቹ ከጋምቤላ እና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መምህራን የቀረቡት መልሶች በተጨማሪ ማስረጃነት ቀርበዋል፤

> *ሁሉም ምንባቦች የተዋጣላቸው ናቸው ለማለት አያስደፍርም በተለይ የቋንቋና የዕድሜ ጉዳይ ትልቅ ግምት ሊሰጠው ይገባል። በአሁኑ ወቅት 7ኛና 8ኛ ክፍል የሚደርሱ ተማሪዎች ዕድሜ አናሳ በመሆኑ ስለገሀዱ አለም ሠፊ ራዕይ የላቸውም። ርዕዩተ-አድማሳቸው ጠባብ ነው። ስለዚህ በጣም የተመጠነ፣ አካባቢያዊ የሆነ፣ የገፀባህሪያት ሥም እንኳ በአካባቢው ባሕልና ወግ አጠራር የሚያውቋቸው ስሞች ቢሆኑ ይመረጣል። ይህን ለማድረግ ደግሞ የግድ የበሳል ደራሲያንን ሥራዎች ማፈላለግ ብቻ መፍትሔ አይሆንም። በአካባቢው የቋንቋ ባለሙያዎች አጫጭር ድርሰት ሥራዎችን ሊያዘጋጁ የሚችሉ ሰዎች አይጠፉም (የ8ኛ ክፍል መምህር፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል)።*

> *በመሠረቱ ቋንቋን በተመለከተ በክልሉ ያሉ ተማሪዎች ማለት የአማርኛ ቋንቋን በተመለከተ ሁሉም ማለት ይቻላል የሚቀላቸው ነገር የለም። ሆኖም ግን የመጽሐፉ አዘገጃጀት ለተማሪዎች አባድ በጣም አባድ ነው የሆነባቸው (7ኛ ክፍል መምህር ጋምቤላ ክልል)*

## ሠንጠረዥ 4፦ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዳራ አንፃር

| ተ.ቁ | የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዳራ አንፃር፤ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 1.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው። | - | 1 | 4 | 3 | - | 2 | 1 | 4 | - | 1 | 2 | 2 | 5 | - | - | 3 | - | 2 |
| 1.4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች የተማሪዎችን የተለያዩ እምነቶች (ሃይማኖቶች) ከግምት ውስጥ ያስገቡ አይደሉም። | 1 | 1 | 3 | 3 | - | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3 | 3 | - | 2 | 3 | - | 2 |
| 1.8 | በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዘቶቻቸው ከተማሪዎቹ የዕለት ከዕለት ኑሮ ጋር የሚቀራረቡ ርዕሰጉዳዮችን የያዙ ናቸው። | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | - | 4 | 2 | - | 3 | 3 | - | 1 | 1 | 1 | 3 |

ከሠንጠረዥ 4 መገንዘብ የምንችለው መምህራኑ ከተማሪዎቹ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዳራ አንጻር በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ተገቢነት የሰጡትን ምላሽ ነው። ከዚህ አንፃር በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙት "ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው።" በሚል የቀረበውን ሐሳብ፣ 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተ 4 የጋምቤላ ክልል መምህራን አሉታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ 5 የቤኒሻንጉል ጉሙዝ መምህራን አዎታዊ መልስ ሰጥተዋል። ጥያቄው ከቀረበላቸው አብዛኞቹ የደቡብ ክልል መምህራን ግን ለመወሰን መቸገራቸውን ጠቁመዋል። ይህን ያህል መምህራን መልስ ከመስጠት የተቆጠቡበት ምክንያት ምናልባትም የሚያስተምሩበትን መጽሐፍ ከአካባቢው ባሕል አንፃር ስላልፈተሹት ወይም በክልሉ ከሚገኙት ልዩ ልዩ ባህሎች ምክንያት ሰፊ መረጃ ስላሻቸው ሊሆን ይችላል።

ተከታዩ ጥያቄም፣ "በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች የተማሪዎችን የተለያዩ እምነቶች (ሃይማኖቶች) ከግምት ውስጥ ያስገቡ አይደሉም።" የሚል ሲሆን የ7ኛ ክፍልን መማሪያ መጽሐፍ በተመለከተ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል ሲቃወሙ፣ 3 የደቡብ እና 3 የቤኒሻንጉል ክልል መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ በጋምቤላ ክልል መምህራን የተሰጠው ምላሽ ከተጨባጭ እውታው ጋር የሚጋጭ ሐሳብ ነው። በዚህ ጥናት በበቂ ማስረጃ ለመጠቆም እንደተሞከረው ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ በገጽ 112፣ 78-80፣ 114-115 እና 172 ላይ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች መቅረባቸው የተረጋገጠ ጉዳይ መሆኑ በንዑስ ክፍል 4.1.1.6 ከቀረቡት ማሳያዎች ጋር ማገናዘብ ይቻላል።

በተመሳሳይ ሁኔታ ይኸው ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ 3 መምህራን ከጋምቤላ እንዲሁም 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ በአንፃሩ 3 መምህራን ከደቡብ ክልል አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከተማሪዎቹ የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር የሚቀራረቡ ናቸው። በሚል ለቀረበው ሃሳብ 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል በተመሳሳይ 4 መምህራን ከደቡብ ክልል አሉታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ክልል አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይኸው ጥያቄ ለሶስቱም ክልሎች 8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦላቸው አብዛኞቹ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።

ከላይ በመምህራኑ የተሰጠውን ምላሽ ስናጠቃልለው፣ ከባህላዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መጽሐፍ ላይ የጎላ ችግር መስተዋሉን እንረዳለን። በተመሳሳይ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችንም በተመለከተ ለጋምቤላ 7ኛ እና ለደቡብ ክልል 8ኛ ክፍል ከተሰናዱት መጻሕፍት በስተቀር በቀሪዎቹ ላይ ችግር መኖሩን መምህራኑ በሰጡት መልስ አረጋግጠዋል። እዚህ ላይ መምህራኑ ለጋምቤላ ክልል በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፉ ላይ ለምን አሉታዊ መልስ እንደሰጡ ግልፅ አይደለም። በተጨባጭ ያለው እውነታና ለዝግ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ይጋጫል። መማሪያ መጽሐፉ ላይ ስለሚገኙት ተጨባጭ ማስረጃዎች ከላይ የተጠቆመ ሲሆን በተጨማሪም አንዳንድ መምህራን በጽሑፍ ካሰፈሩት ምላሽ ውስጥ ተከታዩን እናገኛለን፤

> *ምንም አይነት ግንኙነት የላቸውም ክልላችን ማለትም ክልል 12 (በጋምቤላ) አምስት ዋና ዋና ብሔረሰቦች ሲኖሩ ሁሉም ማለት ይቻላል። የሚከተሉት የፓሮቴስታንት ሃይማኖት ተከታይ ነው። ሆኖም በመጽሐፉ ውስጥ (በመማሪያው ማለት ነው) ያለው ስለድቁና፣ ስለቆሎ-ተማሪ ይገልፃል። ይህን የክልሉ ተማሪዎች ጭራሽ አያውቁትም አይገነባቸውም።*

ይህ በጽሑፍ የሠፈረ ሐሳብ ከጋምቤላ ክልል የ7ኛ ክፍል መምህር የቀረበ ነው። መምህሩ በዚህ ሁኔታ ሐሳባቸውን የገለጹት ምናልባት በመማሪያ መጽሐፉ ትግበራ ላይ ካጋጠማቸው ችግር አኳያ ሊሆን ይችላል። እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ አንዳንድ መምህራን ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች አንፃር ተገቢነት አለው የሚል ምላሽ የሰጡት ምናልባትም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተጠቀሱትን ሃይማኖታዊ ጉዳዮች እንደ ትክክለኛ እና መደበኛ ተግባር በማየት ከተለያዩ አቅጣጫዎች ስላላጠየቋቸው (ስላልተመለከቷቸው) ሊሆን ይችላል። ይህ ቸልተኛነት በመምህራን ላይ ብቻ ሳይሆን በመማሪያ መጻሕፍቱ አዘጋጆችና አርታኢያንም ላይ ጎልቶ ይስተዋላል ለማለት ይቻላል። ለምሳሌ በመማሪያ መጽሐፉ ትንታኔ ላይ ከቀረቡት (ንዑስ ክፍል 4.1.1.6) በተጨማሪ የሚከተሉት እንመለከት፤

- መንግስተሰማያት በሚለው ዐነገሩ ሥሩ። (7ኛ ክፍል፣ ደቡብ ክልል ገጽ 42-43)
- "ህይወት ከሞት በኋላ አለ?" በሚለው ርዕስ ላይ ተዘጋጅታችሁ ንግግር አቅርቡ። (7ኛ ክፍል፣ ጋምቤላ፣ ገጽ 103-108)

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት ተግባራት የቀረቡት "ተከስተና ወይዘሮ ጽጌ" እንዲሁም "እንባ እፈልጋለሁ" በሚሉ ርዕሶች ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከቀረቡ በኋላ በአንብቦ መረዳትን እና የንግግርን ክሂል ለማጎልበት ነው። ይህን ጉዳይ በተመለከተ ከላይ ከተጠቆሙት መጻሕፍት ውስጥ የአንደኛው አርታኢ ለነበሩት ተከታዩ ጥያቄ በቃለመጥቅ ቀርቦላቸው ነበር፤

ጥያቄ፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ ከተማሪዎቹ ባህላዊ ሃይማኖታዊና ሥነልሳናዊ የቋንቋ ግንዛቤ ወይም ክህሎት ጋር እንዳይጋጭ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ?

መልስ፡- *"አዎ እንደ አዘጋጅም እንደ ኤዲተርም ሆነህ ስታየው በጣም ነው ጥንቃቄ የሚደረገው ለምሳሌ ስዕሎች ላይ ራሱ ሃይማኖታዊ ነክ የሆኑ ስዕሎችን ላለማውጣት በጣም ይጠነቀቃሉ። ሲያዘጋጁም ኤዲተሮችም ያያሉ። የባህል የሃይማኖት ተዕዕኖ እንዳይኖር በጣም ነው ጥንቃቄ የምናደርገው የቃላት አጠቃቀም ሁሉ በዚህ ደረጃ ይሄን ቃል ማስቀመጥ አግባብ ነው ወይ ይሄንን ቃል በዚህ ቃል ቢተካ አይሻልም ወይም የሚል አስተያየት ይሰጣል እና በጣም በጥንቃቄ የሚሰራ ነገር ይመስለኛል። በዚህ ዙሪያ ሃይማኖታዊ ባህላዊ ቋንቋ ግንዛቤና አቅም በሚለው በጣም በጥንቃቄ የሚሰራ ይመስለኛል..."*
*(የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አርታኢ፣ ደቡብ ክልል)*

በመጽሐፉ አርታኢ ከቀረበው ገለፃ መረዳት እንደምንችለው በጉዳዩ ላይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የሚዘጋጅ መሆኑን ነው። በአንባሩ በዚህ ጥናት ለማመላከት እንደተሞከረው በተጨባጭ ችግሮች ተስተውለዋል። ይህ የሚጠቁመን በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በተለይም ከሥነጽሑፋዊ ሥራዎችና በሥራቸው ከሚዋቀሩት ተግባራት አንፃር የሃይማኖታዊ ጉዳዮች መካተት ወይም አለመካተት ድንበሩ የት ድረስ ነው? ለሚለው አበይ ጥያቄ በአንዳንድ የሞያው ባለቤቶችም መልስ ያልተሰጠበት ጉዳይ መሆኑን ነው።

## ሠንጠረዥ 5፦ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ አጠቃላይ ዳራ አንፃር

| ተ.ቁ | የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቹ አጠቃላይ ዳራ አንፃር፤ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 1.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ግንዛቤ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። | 5 | - | - | 4 | 1 | - | 3 | 1 | 1 | 2 | - | 3 | 3 | 1 | 1 | 4 | 1 | - |
| 1.7 | ተማሪዎቹ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አንብበው መልዕክቱን በቀላሉ ይረዳሉ። | - | - | 5 | - | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 3 | - | 2 | 2 | 2 | 1 | - | 3 | 2 |
| 1.9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ አጠቃቀም (ለምሳሌ ቃላት) ከክፍል ደረጃው ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ጋር ይመጣጠናል። | - | - | 5 | - | 1 | 4 | 3 | 1 | 1 | 3 | - | 2 | 4 | - | 1 | - | 1 | 4 |
| 1.10 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቋንቋ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። | 3 | - | 2 | 3 | - | 2 | 2 | - | 3 | 5 | - | - | 2 | 1 | 2 | 3 | - | 2 |

ከሠንጠረዥ 5 የምንረዳው የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አመራረጥ ተገቢነት መምህራኑ ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር እንደ መደምደሚያ ሐሳብ የሰጧቸውን ምላሾች ነው። በዚህም መሠረት "ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዳራ ጋር አይጣጣሙም" ተብሎ የቀረበላቸውን ሐሳብ የ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተ፣ 5 መምህራን ከጋምቤላ ክልል፣ 3 መምህራን ከደቡብ ክልል እንዲሁም 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ አሉታዊ ምላሽ የሰጡት መምህራን ግን ቁጥራቸው አነስተኛ ነው። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦላቸው፣ 4 መምህራን ከጋምቤላ ክልል በተመሳሳይ 4 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው መምህራን ከሁለቱም ክልሎች አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። በአንፃሩ 3 መምህራን ከደቡብ ክልል አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።

ከዚሁ ጥያቄ ጋር በተያያዘ "ተማሪዎቹ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አንብበው መልዕክቱን በቀላሉ ይረዳሉ" በሚል የቀረበላቸውን ጥያቄ፣ 7ኛ ክፍልን በተመለከተ 5 መምህራን ከጋምቤላ ክልል አሉታዊ መልስ በመስጠት ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አንብበው ለመረዳት እንደሚቸገሩ ሲጠቁሙ፣ በአንፃሩ 3 መምህራን ከደቡብ ክልል አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። በሌላ በኩል 2 መምህራን ብቻ ከቤኒሻንጉል ክልል አዎንታዊ መልስ መስጠታቸውና ለመወሰን የሚያስቸግራቸው መምህራን አሉታዊ መልስ ከሰጡት ጋር ተደምሮ ቁጥራቸው ከፍተኛ መሆኑ፣ መምህራኑ የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሙሉ በሙሉ የተዋጣላቸው ናቸው ብለው እንደሚያስቡ ያስገነዝበናል። የ8ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍን በተመለከተ ግን 3 መምህራን ከደቡብ ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ በቀሪዎቹ ሁለት ክልሎች ግን ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው የገለጹት መምህራን ቁጥራቸው ከፍተኛ ነው። ይህ ሊሆን የቻለው ምናልባት አፈ-ፈት ተማሪዎቹ ምንባቦቹን በቀላሉ ሲረዷቸው በአንፃሩ ኢአፈ-ፈት የሆኑት ተማሪዎች ግን ምንባቦቹን ለመረዳት መቸገራቸውን ስላስተዋሉ ሊሆን ይችላል። የነዚህን መምህራንን ሃሳብ ግልጽ የሚያደርግልን ለተከታዩ ጥያቄ (በጥያቄ ቁጥር 1.9) የሰጡት አሉታዊ ምላሽ ነው። "በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ አጠቃቀም ከክፍል ደረጃው ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ጋር ይመጣጠናል" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ 7ኛ ክፍል በተመለከተ፣ 5

መምህራን ከጋምቤላ ክልል አሉታዊ መልስ በመስጠት ከተማሪዎቹ የቋንቋ ችሎታ ጋር እንደማይመጣጠኑ ሲገልጹ፣ በአንዳሩ 3 መምህራን ከደቡብ፣ እንዲሁም 4 መምህራን ከቤኒሻንጉል ክልል አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። 8ኛን በተመለከተ ግን ከደቡብ ክልል ብቻ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መምህራን አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል።

እንደ ማጠቃለያ ሐሳብ ‹‹በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቋንቋ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ /ኢአፈ-ፈት/ ተማሪዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም›› በሚል ለቀረበው ጥያቄ ከደቡብና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች (መጠይቁን ከሞሉት) የ7ኛ ክፍል መምህራን በስተቀር በቀሪዎቹ የሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን አዎንታዊ መልስ ተሰጥቷል። ይህ የመምህራኑ ተቀራራቢ መልስ ከላይ በዝርዝር ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡት መልሶች በጥቅሉ ለመመዘን ፍንጭ ይሰጣል።

ስለዚህም ከላይ በዝርዝር የተሰጡት ምላሾች ሲጠቃለሉ የሚጠቁመው ለ7ኛ ክፍል በጋምቤላ ክልል የተዘጋጀው መጽሐፍ ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር አፈ-ፈትንም ሆነ ኢአፈ-ፈት ተማሪዎችን ከግምት ውስጥ ያላስገባ መሆኑ ነው። በአንፃሩ ለደቡብ ክልል 7ኛ ክፍል የተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፉ ከተማሪዎቹ አጠቃላይ ዳራዊ ዕይታ አንፃር የተሻለ መሆኑን መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ እንገነዘባለን። ይህ የመምህራኑ ምላሽ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ከተካሄደው ትንታኔ ጋር የሚዛመድ ነው።

## ሠንጠረዥ 6፦ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ሂደት የትምህርቱን ዓላማ ከማሳካትና ከመርሐትምህርቱ ጋር ከመጣጣም አንፃር

| ተ.ቁ | የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ሂደት የትምህርቱን ዓላማ ከማሳካትና ከመርሐትምህርቱ ጋር ከመጣጣም አንፃር | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 2.1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የክሂል ዘርፎችን (የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍን) ብቃት የሚያጎለብቱ ናቸው። | 1 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 | 4 | 1 | - | 4 | - | 1 |
| 2.2 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች በመርሐትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት፣ የዘይቤና የፊሊጣዊ ይዘቶች ትምህርት ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3 | 4 | 1 | - | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 3 |
| 2.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በሥሮቻቸው ከሚገኙት መልመጃዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። | 4 | 1 | - | 3 | - | 2 | 3 | - | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 1 | - | 3 | 1 | 1 |
| 2.10 | የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የክሂል ዘርፍ የሆኑትን (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) ሚዛናዊነታቸውን ጠብቀው (በእኩል ደረጃ) በመልመጃነት አላቀረቡም። | 3 | 1 | 1 | 3 | - | 2 | 3 | - | 2 | 3 | - | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | 3 | 1 |

ሠንጠረዥ 6 የሚያስረዳን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ተገቢነት በተመለከተ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ለማሳካትና ከመርሐትምህርቱ ጋር የተገናዘበ ስለመሆንና አለመሆኑ የሰጡትን አስተያየት ነው። ከዚህ አኳያ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የተማሪዎችን ክሂሎች የሚያጎለብቱ መሆናቸውን ተጠይቀው 7ኛ ክፍልን በተመለከተ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል አሉታዊ መልስ በመስጠት ክሂሎቻቸውን እንደማጎለብቱ ሲጠቁሙ በአንፃሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ደቡብ ክልልን በተመለከተ ግን አዎንታዊና አሉታዊ ምላሽ የሰጡት መምህራን ቁጠር እኩል ነው። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ በሦስቱም ክልሎች አዎንታዊ ምላሽ ተሰጥቷል።

‹‹በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመርሐትምህርቱ ላይ ከተጠቀሱት ልዩ ልዩ ይዘቶች ጋር አይጣጣሙም›› በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ፣ አንድ መምህር ብቻ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። በንፃሩ 3 መምህራን ከደቡብ እና 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይኸው ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦላቸው 3 መምህራን ከጋምቤላ እንዲሁም 4 መምህራን ከደቡብ ክልል አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ፣ በአንፃሩ 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሉታዊ መልስ በመስጠት ከመርሐትምህርቱ ይዘት ጋር እንደሚጣጣሙ ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በስራቸው ከተደራጁት መልመጃዎች ጋር የሚገናኙ ስለመሆናቸው ጥያቄ ከቀረበላቸው የ7ኛ ክፍል መምህራን ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የሶስቱም ክልል መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በተመሳሳይ ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ አብዛኛው ቁጥር የያዙት የጋምቤላና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። እነዚህ ‹‹በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥር የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋ ትምህርት ዓላማን ከማሳካት አንፃር ሚዛናዊነታቸውን ጠብቀው አልቀረቡም››

በሚል ለቀረበው የማጠቃለያ ጥያቄ ከቤኒሻንጉል 8ኛ ክፍል መምህራን በስተቀር በሶስቱም ክልሎች ምላሽ የሰጡ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መምህራን የክሂሎች ሚዛናዊነት አለመጠበቁን ጠቁመዋል። ለዚህ ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ በሰንጠረዥ 6 ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች የተሰጡትን መልሶች ለማጠቃለል መነሻ ሊሆን ይችላል።

ከላይ መምህራኑ የሰጧቸው ምላሾች ሲጠቃለሉ ክሂሎችን ከማጎልበት አንፃር ከጋምቤላ 7ኛ ክፍል በስተቀር ቀሪዎቹ የተሻሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ። በአንፃሩ ለመጨረሻው ጥያቄ (2.10) በሰጡት መልስ ክሂሎች ሚዛናዊ ሆነው አለመቅረባቸውን ገልፀዋል። እነዚህ ምላሾች ይቃረናሉ። ይህ ሊከሰት የቻለው ምናልባት መምህራኑ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ በተደጋጋሚ የቀረቡት የአንብቦ መረዳትን ጥያቄዎች ለመተግበር ስለሆነ (በመጻሕፍቱ ላይ በቀረበው ትንታኔ መረዳት እንደሚቻለው) መምህራኑ ይህን እውነታ በማሰብ የሰጡት መልስ ሊሆን ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ አብዛኞቹ መምህራን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ በስሮቻቸው ከሚገኙት መልመጃዎች ጋር የጠበቀ ዝምድና መኖሩን የገለጹት የአንብቦ መረዳትን ክፍል ብቻ ከግምት በማስገባት የሰጡት ምላሽ ሊሆን ይችላል። ምክንያቱም አብዛኞቹ መልመጃዎች ከምንባቡ ያፈነገጡ መሆናቸውን በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ በተካሄደው ትንታኔ (በተጨባጭ) ተረጋጋጧል። በቀሪዎቹ ጥያቄዎች ላይ የተሰጡት መልሶች ግን በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ የቀረበውን ትንታኔ የሚያጠናክሩ ሆነው ተገኝተዋል።

## ሠንጠረዥ 7፦ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ተገቢነት ከተተግባሪነታቸው አንፃር

| ተ.ቁ | የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ ተገቢነት ከተተግባሪነታቸው አንፃር፣ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 2.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ርዝማኔያቸው የተመጠነ በመሆኑ በክፍል ውስጥ ለመተግበር አመቺ ናቸው። | 2 | - | 3 | 2 | - | 3 | 3 | 1 | 1 | - | - | 5 | 4 | 1 | - | 4 | - | 1 |
| 2.4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ለማጠናከር የሚረዱ መርጃ መሣሪያዎች፣ ለምሳሌ የተቀረጹ ድምፆች፣ ሥዕሎች፣ ቻርቶች፣ ፊልሞች፣ ወዘተ. በበቂ መጠን ማግኘት አይቻልም። | 4 | - | 1 | 4 | - | 1 | 3 | - | 2 | 4 | - | 1 | 3 | 1 | 1 | 4 | - | 1 |
| 2.5 | የቀረቡትን ልዩ ልዩ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግልጽ ሊያደርጉ የሚችሉ የቃላት መፍቻዎች፣ ማብራሪያዎች፣ ማስታወሻዎችና መግለጫዎች በበቂ መጠን መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ። | 2 | - | 3 | 2 | - | 3 | 2 | - | 3 | 5 | - | - | 3 | 1 | 1 | 2 | - | 3 |
| 2.6 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች የተዘጋጁት ልዩ ልዩ መልመጃዎች ግልጽ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ የላቸውም። | 2 | 1 | 2 | 1 | - | 4 | 1 | - | 4 | 1 | 1 | 3 | 1 | - | 4 | - | 1 | 14 |
| 2.8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን አጫጭር ልቦለዶች፣ ረጃጅም ልቦለዶች፣ ግጥሞችና ተውኔቶች የያዙ የተለያዩ ደራስያንና ገጣምያን መጻሕፎችን ተማሪዎቹ በቤተመጻሕፍት ውስጥ በቀለሉ ሊያገኟቸው አይችሉም። | 4 | 1 | - | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 4 | - | 1 | 3 | - | 2 | 5 | - | - |

በሠንጠረዥ 7 ላይ የቀረበው መረጃ መምህራን የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን በትግበራ ሂደት ካጋጠሟቸው እውነታዎች አንፃር ተገቢነታቸውን የፈተሸበት ነው። ከዚህ አኳያ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች በክፍል ውስጥ ለመተግበር ያላቸውን አመቺነት ተጠይቀው፣ 7ኛ ክፍልን በተመለከተ 3 መምህራን አሉታዊ፣ 2 መምህራን አዎንታዊ መልስ ከጋምቤላ ክልል ሲሰጡ፣ የደቡብና የቤኒሻንጉል ክልሎች መምህራን ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው መምህራን አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። 8ኛ ክፍልን በተመለከተም ከጋምቤላ ክልል እና ከደቡብ ክልል፣ አዎንታዊ ምላሽ የሰጡት ከፍተኛ ቁጥር ሲይዙ በአንፃሩ አብላጫውን ቁጥር የሚይዙት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መላሾች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አጋዥ የሆኑ ልዩ ልዩ መርጃ መሣሪያዎችን በበቂ መጠን አለመገኘታቸውን በተመለከተ፣ መምህራን ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፣ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙ መምህራን ከሦስቱም ክልሎች አዎንታዊ መልስ በመስጠት በበቂ መጠን ለማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን ጠቁመዋል። በተመሳሳይ ከሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ጋር የሚዛመዱ ማብራሪያዎች፣ የቃላት መፍቻዎች (መዝገበ ቃላት)፣ ማስታወሻዎችና መግለጫዎች በበቂ መጠን በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ መገኘታቸውን በተመለከተ ጥያቄ ቀርቦላቸው አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የጋምቤላና የደቡብ ክልል መምህራን አሉታዊ ምላሽ በመስጠት በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቂ ማብራሪያዎች፣ መግለጫዎች፣ ወዘተ. አለመኖራቸውን ሲያረጋግጡ፣ በአንፃሩ 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦላቸው፣ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የጋምቤላና የቤኒሻንጉል ጉመዝ ክልሎች መምህራን አሉታዊ መልስ በመስጠት፣ በቂ አይደሉም ሲሉ በአንፃሩ ጥያቄው የቀረበላቸው 5 የደቡብ ክልል መምህር አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል።

ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን በክፍል ውስጥ ለመተግበር በሥሮቻቸው የቀረቡት መልመጃዎች ግልጽ ትዕዛዝ የላቸውም፣ በሚል ለቀረበው ጥያቄ ከጋምቤላ ክልል የ7ኛ ክፍል መምህራን በስተቀር (በሶስቱም ክልሎች ጥያቄው ከቀረበላቸው መምህራን መካከል) አብዛኛውን ቁጥር የያዙት ግልጽ መመሪያና ትዕዛዝ ያላቸው መሆኑን ጠቁመዋል። የጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል መምህራን አዎንታዊና አሉታዊ መልስ የሰጡት መምህራን እኩል ቁጥር የያዙበት ምክንያት ምናልባት መልመጃዎቹ ግልጽ ትዕዛዛት ቢኖራቸውም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከተማሪዎች ዳራ አንፃር ከባድ በመሆናቸው፣ በመልመጃዎቹ ተተግባሪነት ላይ ጥርጣሬ ስላላቸው ሊሆን ይችላል።

በመጨረሻም "በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ያካተቱና ሌሎች መሠል መጻሐፍትን ተማሪዎቹ በቤተመጻሕፍት ውስጥ በቀላሉ ሊያገኟቸው አይችሉም::" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መምህራን በቤተመጻሕፍት ውስጥ እንደማይገኙ አረጋግጠዋል::

ከላይ መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው የአብዛኞቹ መምህራን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን በክፍል ውስጥ አስፈላጊ በሆነ መርጃ መሣሪያዎች አስደግፎ ለማቅረብ አስቸጋሪ መሆኑ ነው:: ይህን መምህራኑ በዝግ ጥያቄዎች የሰጡትን መልስ በጽሑፍም አረጋግጠዋል:: "በአጠቃላይ ወደፊት በሚካሄደው የመማሪያ መጽሐፉ ማሻሻል ተግባር ላይ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አመራረጥና አደረጃጀት በተመለከተ መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ያለዎትን አስተያየት ቢገልጹልኝ" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተዋል፤

*በዚህ ላይ ያለኝ አሰተያየት ቢኖር የሥነጽሑፍ ሥራዎችን በተመለከተ በብዛት ቢካተቱ እያንዳንዱ ምዕራፍ በሚዘጋጅት ጊዜ የክፍለጊዜው ብዛት በትክክል ቢወሰን በአብዛኛው በምዕራፉ የተካተቱት በሚሰጠው ክፍለጊዜ ለመሸፈን አስቸጋሪ ይሆናል:: ሌላው ለሥነጽሑፍ ሥራዎች አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ዋቢ መጻሕፍት በመጽሐፉ መጨረሻ ቢዘረዘሩ ትምህርት ቤቱ ባይኖረውም መምህሩ/ሯ የራሳቸውን ጥረት አድርገው የሚያኙበትን ሁኔታ ቀድመው እንዲያመቻቹ ያደረጋቸዋልና::" (ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የ8ኛ ክፍል መምህር)*

*አጥር ምጥን ያለ ሥነጽሑፍ እንጂ ምንባቡ ብቻ 3 ገጽ (4) የሆነ ከሆነ የተማሪዎች የአንብቦ መረዳት፣ የመጨረስና ታሪኩን ለማስታወስ ያዳግታቸዋል:: በተለይ አማርኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ የሚማሩ ተማሪዎች ... የሚቀርቡት ፅሁፎች የገጽ ብዛት (ሥፋት) የተማሪዎችን ብቃት ደረጃ እና ሌሎችንም መሠረታዊ ነጥቦች ያገናዘቡ (ያሟላ) ቢሆኑ ምክንያቱም ፊደላትን ጠንቅቆ ባለወቀበትና ለማንበብ በመንገዳገድ ላይ ባለት የቀረበው ሠፊ ገጽ ያካተተ ፅሁፍ አንብቦ ይረዳል፣ ተገቢውን ለውጥ ያመጣል ብሎ ማመን ያዳግታል (ጋምቤላ ክልል የ7ኛ ክፍል መምህር)*

በአጠቃላይ ከላይ መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ እና በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ከቀረበው ትንታኔ ማረጋገጥ እንደተቻለው በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች (በተለይ ረዥም ልቦለድ ላይ ተቀንጭበው የወሰዱት) በክፍል ውስጥ ለመተግበር ከርዝማኔያቸውና ከመረጃ መጻሕፍት እጦት አንፃር አዳጋች መሆኑን ነው::

## ሠንጠረዥ 8፡- በመማሪያ መጻህፍቱ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነት

| ተ.ቁ | ሀ. በመማሪያ መጻህፍቱ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተከታታይነት | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 3.4 | በሥነጽሑፋዊ የፈጠራሥራ ዓይነቶች ማለትም በልቦለዶች፣ በግጥሞች፣ በተውኔቶችና በተረቶች ቋንቋን ሲማሩ የመጀመሪያቸው ሳይሆን በቀደመው የክፍል ደረጃ ላይ በዚሁ ስልት ተምረዋል። | - | - | 5 | 4 | 1 | - | - | 4 | 1 | 3 | - | 2 | 2 | 1 | 2 | - | 2 | 3 |
| 3.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች (አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድ፣ ተውኔት ወይም ድራማ፣ ግጥምና ተረት) ቁጥራቸው አነስተኛ ነው። | 4 | - | 1 | 3 | - | 2 | 3 | - | 2 | 4 | - | 1 | 4 | 1 | - | 5 | - | - |
| 3.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ይዘት ከሌላቸው ምንባቦች ጋር ተሰባጥረው (ተቀላቅለው) አልቀረቡም። | 4 | - | 1 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 | - | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 |

በሠንጠረዥ 8 የቀረበው መረጃ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አደረጃጀት በተመለከተ ከተከታታይነታቸው አንፃር የመምህራኑን ምላሽ ይገልፃል። በዚህም መሠረት ተማሪዎቹ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አማካይነት፣ ተዋረዳዊ በሆነ መልኩ ተምረዋል በሚል ለቀረበው ሐሳብ፣ አብዛኞቹ የጋምቤላ ክልል መምህራን አሉታዊ መልስ ሲሰጡ ከደቡብ ክልል መላሾች 4 መምህራን ለመወሰን የተቸገሩት፣ ምናልባት በቀደመው የክፍል ደረጃ መጽሐፍ ሥላልተገለገሉበት ሊሆን ይችላል በአንፃሩ እኩል ቁጥር ያላቸው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ መምህራን አሉታዊና አዎንታዊ መልስ የሰጡት "ተማሪዎቹ በቀደመው የክፍል ደረጃ ላይ በተወሰነ መልኩ በመማራቸው ሊሆን ይችላል" ብሎ የዚህ ጥናት አቅራቢ ያምናል። 8ኛ ክፍልን በተመለከተ ግን አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የጋምቤላና የደቡብ ክልል መምህራን አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ግን አብዛኞቹ መላሾች አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን ጎናዊ ድግግሞሽ በተመለከተ "የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ቁጥር አነስተኛ ነው።" ተብሎ ለቀረበው ሐሳብ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የ7ኛም ሆነ የ8ኛ ክፍል መምህራን አዎንታዊ ምላሽ መስጠታቸውን ከላይ በሠንጠረዥ የቀረበው መረጃ ያስረዳል። ይህ እውነታ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ከተሰጠው ትንታኔ ጋር ይዛመዳል። የጎናዊ ክትትሉሹን ተገቢነት ለመጠየቅ "ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር ተሰባጥረው አልቀረቡም" በሚል የቀረበውን ሐሳብ ከጋምቤላ ክልል 4 መምህራን አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ በተመሳሳይ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መምህራን መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ 3 መምህራን ከደቡብ ክልል አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ አዎንታዊና አሉታዊ ምላሽ የሰጡት የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መምህራን ቁጥር ደግሞ ተመሳሳይ ነው።

ባጠቃላይ ከላይ በመምህራኑ የተሰጡት ምላሾች ሲጠቃለሉ የሚጠቁሙን የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ተዋረዳዊ አደረጃጀት ከ7ኛ ወደ 8ኛ ክፍል በአንፃራዊ መልኩ ተከታታይነት የሚታይበት ሲሆን በሌላ በኩል በጎናዊ አደረጃጀታቸው ግን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር በጥንቃቄ ተሰባጥረው አለመቅረባቸውን፣ ለዚህ ጥያቄ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች ከሚገኙ መምህራን ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው አሉታዊ መልስ አለመስጠታቸው ጥቆማ ይሰጣል። በመማሪያ መጻሕፍቱ ትንታኔ ላይ የተረጋገጠውን ይህን እውነታ መምህራኑ በከፍተኛ ቁጥር ሊያረጋግጡት ያልቻሉት ምናልባት ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ አንፃር መጻሕፍቱን በጥልቀት መመልከት ስለሚገባቸው ሊሆን ይችላል።

## ሠንጠረዥ 9፦ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተለጣጣቂነት

| ተ.ቁ | ለ. በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተለጣጣቂነት | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 3.1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመጀመሪያ ላይ ቀላሎቹን በማስቀደም ከባዶቹ በመጨረሻ ላይ ቀርበዋል ወይም ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅተዋል። | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 1 | 4 | - | 1 | 2 | - | 3 | 3 | 2 | - | 2 | 1 | 3 |
| 3.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተደራጁት ከተማሪዎቹ የሕይወት ልምድ ጋር የቀረቡትን እና በቀላሉ የሚያውቁትን ርዕሰጉዳይ በማስቀደም ነው። | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | - | 1 | 2 | - | 3 | 3 | 1 | 1 | 1 | - | 4 |
| 3.5 | በተከታታይ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዘቶቻቸው ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ የሚያድጉ አይደሉም። | 1 | 3 | 1 | 2 | - | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 | 2 |

ሠንጠረዥ 9 የሚያመለክተው መምህራን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከተለጣጣቂነት እና ከክብደት - ቅለታቸው አንፃር መደራጀታቸው በተመለከተ የሰጡን ምላሽ ሲሆን "ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅተዋል" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ 7ኛ ክፍል በተመለከተ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል ለመወሰን እንደሚያስችግራቸው ሲገልጹ፣ 4 መምህራን ከደቡብ እንዲሁም፣ 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ለ8ኛ ክፍል መምህራን ይህ ጥያቄ ቀርቦላቸው፣ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የደቡብ ክልል እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል።

በተመሳሳይ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ ተደራጅተዋል። በሚል ለቀረበው ጥያቄ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የደቡብ ክልል እና የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መምህራን (7ኛ ክፍል) አዎንታዊ መልስ በመስጠት ከቀላል ወደከባድ ተደራጅተዋል ብለው ሲመልሱ በአንፃሩ ከጋምቤላ ክልል መልስ ሰጪዎች አብዛኛውን ቁጥር የያዙት አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የደቡብ ክልል እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መምህራን አሉታዊ መልስ ሲሰጡ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው የጋምቤላ ክልል መላሾች አዎንታዊ እና አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ መምህራኑ በአንድ መማሪያ መጽሀፍ ላይ አደረጃጀትን በተመለከተ ሁለት ፍጹም የማይገናኙ መልስ መስጠታቸው መማሪያ መጽሐፉን ምናልባት ከዚህ ርዕሰጉዳይ አንፃር በጥልቀት ስላልፈተሹት ወይም ተለጣጣቂነት በሚለው ፅንሰሀሳባዊ ብያኔ ላይ ያላቸው ግንዛቤ ውሱን በመሆኑ ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል ‹የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አደረጃጀት ተለጣጣቂነትን አልተከተለም›› ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ 3 መምህራን ከጋምቤላ ክልል ለመወሰን እንደሚያስችግራቸው ሲገልጹ፣ በንፃሩ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦላቸው አብዛኞቹ የጋምቤላና የደቡብ ክልል መምህራን አሉታዊ መልስ በመስጠት፣ ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ እንደሚጓዙ ጠቁመዋል። የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች

ግን ለመወሰን የተቸገሩት እና አሉታዊ መልስ የሰጡት መምህራንን እኩል ቁጥር ያላቸው በመሆኑ የአብዛኞቹን ሐሳብ ለመወሰን ያዳግታል።

ከላይ መምህራኑ የሰጡት መልስ ሲጠቃለል የሚያስረዳን የጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሐፍ አደረጃጀት ላይ መምህራኑ አስተያየት ለመስጠት የተቸገሩ መሆናቸውን ነው። ለደቡብና ለቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልሎች የተዘጋጁት ግን መምህራኑ በአንፃራዊነት የተሻሉ መሆናቸውን አመላክተዋል። ይህ የመምህራኑ አስተያየት በተጨባጭ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር ይላመዳል ምክንያቱም (ቀደም ሲል በዚህ ጥናት እንደተጠቆመው) ለጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አብዛኞቹ ከተመሳሳይ መጽሐፍ ("ፍቅር እስከመቃብር") የተወሰዱ በመሆናቸው በክብደት ቅለት ለማስቀመጥ አስቸጋሪ ናቸው። በአንፃሩ ለቤኒሻንጉል ጉሙዝና ለደቡብ ክልል በተዘጋጁት መጻሕፍት ውስጥ ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም በአንፃራዊነት ሲታዩ ቀላል ሊባሉ የሚችሉ ሥራዎች ተካተው እናገኛለን። የመምህራኑም ምላሽ ከነዚህ እውነታዎች የመነጨ ሊሆን ይችላል።

## ሠንጠረዥ 10፦ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ክሂሎችን ማጎልበታቸውን በተመለከተ

| ተ.ቁ | ሀ. የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ክሂሎችን ማጎልበታቸውን በተመለከተ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 4.1 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከመቅረባቸው በፊት የቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ከምንባቡ ይዘት ጋር የሚገናኙ ናቸው። | 2 | - | 3 | 5 | - | - | 4 | 1 | - | 4 | 1 | - | 5 | - | - | 3 | - | 2 |
| 4.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች የተማሪዎችን የንባብ ክሂል የሚያሳድጉ ናቸው። | 4 | 1 | - | 5 | - | - | 5 | - | - | 3 | - | 2 | 4 | - | 1 | 5 | - | - |
| 4.4 | ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ከሌላቸው (ኢልቦለዶች) ምንባቦች ይልቅ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች የማንበብ ፍላጐትና ጉጉት አላቸው። | 4 | 1 | - | 4 | - | 1 | 3 | 2 | - | 3 | 2 | - | 4 | 1 | - | 3 | 1 | 1 |
| 4.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ የሚያበረታቱ አይደሉም። | 1 | 1 | 3 | 1 | 1 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | - | 3 | - | 2 | 3 | 1 | - | 4 |
| 4.9 | በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ተማሪዎቹ ከክፍል ውጪ ሌሎች ተጨማሪ ልቦለድ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን፣ ተረቶችን፣ ወዘተ. እንዲያነቡ የሚያነሳሱ ናቸው። | 3 | - | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | - | 4 | 3 | - | 2 | 3 | 2 | - | 1 | 3 | 1 |

ሠንጠረዥ 10 የሚያስረዳን በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ ትምህርት ዓቢይ ዓላማ ከሆኑትን የክሂል ዘርፎች ውስጥ የአንብቦ መረዳትና የጽሕፈት ክሂሎችን ከማሳልበት አንፃር በተገቢነታቸው ላይ የሰጡትን ምላሽ ነው። ከዚህ አኳያ የተማሪዎቹን የንባብ ተነሳሶት ስሜት ከማነቃቃት አንፃር "የቅድመ መወያያ ጥያቄዎች ከምንባቦቹ ጋር ተዛምዶ አላቸው" በሚል ለቀረበው ጥያቄ የጋምቤላ ክልል 7ኛ ክፍል መምህራን ብቻ አሉታዊ መልስ የሰጡት በቁጥር ሲበልጡ በቀሪዎቹ የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል አብዛኞቹ መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። "ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የተማሪዎቹን የንባብ ክሂል ያጎለብታሉ።" በሚል ለቀረበው ጥያቄ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች (7ኛ ና 8ኛ) ላይ ከሚያስተምሩ መምህራን አብዛኞቹ መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። ይህ የመምህራኑ ምላሽ በመጻሕፍቱ ላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር በእጅጉ ይዛመዳል።

"ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ከሌላቸው ምንባቦች ይልቅ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች የማንበብ ፍላጎትና ጉጉት ያሳያሉ" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በተመሳሳይ አብዛኞቹ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። በሌላ በኩል "ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ አያበረታቱም።" በሚል ለቀረበው ጥያቄ ከደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል መምህራን በስተቀር ቀሪዎቹ መላሾች አብዛኞቹ አሉታዊ መልስ በመስጠት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከንባብ በተጨማሪ የጽሕፈትንም ክሂል እንደሚያጎለብቱ አረጋግጠዋል።

በመጨረሻም ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ተማሪዎች ሌሎች ተጨማሪ መጻሕፍትን እንዲያነቡ ያነሳሳሉ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄዎች፣ 7ኛ ክፍልን በተመለከተ አብዛኞቹ የጋምቤላ ክልል እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ በአንፃሩ አብዛኞቹ የደቡብ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል፤ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ተማሪዎቹን ለተጨማሪ ንባብ እንደማያነሳሱ ጠቁመዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦላቸው አብዛኛውን ቁጥር የያዙ የጋምቤላ ክልል እና የደቡብ ክልል መላሾች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለመወሰን እንደሚቸገሩ ገልጸዋል።

ከላይ በዝርዝር በመምህራኑ የተሰጡትን ምላሾች ስናጠቃልል የምናገኘው ዐቢይ ጉዳይ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በዋነኛነት የንባብን ክሂል የማያጎልበት ብቃት ያላቸው እና የጽሕፈትንም ክሂል ከዚሁ ጎን ለጎን የሚያሳድጉ መሆናቸውን ነው። ይህ የተጠቃለለ የመምህራኑ ምላሽ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር የተዛመደ ነው።

## ሠንጠረዥ 11:- ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ማጐልበታቸውን በተመለከተ

| ተ.ቁ | ለ. ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የማዳመጥና የመናገር ክሂሎችን ማጐልበታቸውን በተመለከተ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፤4 | 3 | 2፤1 | 5፤4 | 3 | 2፤1 | 5፤4 | 3 | 2፤1 | 5፤4 | 3 | 2፤1 | 5፤4 | 3 | 2፤1 | 5፤4 | 3 | 2፤1 |
| 3.2 | በሥነጽሑፋዊ ምንባቡቹ ሥር የተደራጁት መልመጃዎች ተማሪዎቹ በምንባቡቹ ይዘት ላይ በግልና በቡድን እንዲሳተፉ የሚያስችሉ አይደሉም። | 2 | - | 3 | 1 | - | 4 | 2 | - | 3 | 4 | - | 1 | 1 | - | 4 | - | - | 5 |
| 4.5 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች በክፍል ውስጥ ከተነበቡ በኋላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ላይ አብዛኞቹ ተማሪዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ። | - | - | 5 | 2 | - | 3 | 4 | - | 1 | 3 | 1 | 1 | 4 | - | 1 | 2 | - | 3 |
| 4.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተማሪዎቹ ሓሳባቸውን በንግግር እንዲያቀርቡ የሚያበረታቱ ናቸው። | 3 | 1 | 1 | 4 | - | 1 | 4 | - | 1 | 3 | - | 2 | 5 | - | - | 3 | 1 | 1 |
| 4.8 | በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል ሊያጐለብቱ አይችሉም። | 1 | 1 | 3 | - | - | 5 | 1 | 1 | 3 | 1 | - | 4 | - | 1 | 4 | - | 1 | 4 |
| 5.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የክሂል ትምህርት እንጂ ሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን የሚያስጨብጡ አይደሉም። | 5 | - | - | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | - | - | - | 5 | 5 | - | - | 2 | 1 | 2 |

በሠንጠረዥ 11 ላይ የቀረበው መረጃ የትምህርቱን ዓላማ ከማሳካት አንፃር ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የመናገርን እና የማዳመጥን ክሂል የማጎልበት ብቃታቸውን በተመለከተ ከመምህራን የተሰጠውን ምላሽ ነው። በዚህ መሠረት "በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥር የተደራጁት መልመጃዎች ተማሪዎቹ በግልና በቡድን እንዲሳተፉ የሚያስችሉ አይደሉም።" በሚል የቀረበላቸውን ጥያቄ አብዛኛው ቁጥር ያላቸው የሁለቱም የክፍል ደረጃዎች መምህራን አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። በሌላ በኩል ‹‹ምንባቦቹ በክፍል ውስጥ በንባብ ከቀረቡ በኋላ አብዛኞቹ ተማሪዎች አንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ላይ ይሳተፋሉ።›› በሚል የማንበብና አዳምጦ መረዳትን ክሂል ማጎልበት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከጋምቤላ ክልል መላሾች ውስጥ አብዛኞቹ አሉታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ አብዛኞቹ የደቡብ ክልል እና የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ተጠያቂዎች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል።

በሌላ በኩል ‹‹ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ የተማሪዎችን የንግግር ክሂል ያጎለብታሉ›› ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኛውን ቁጥር የያዙ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መምህራን (ከሦስቱም ክልሎች) አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ በተመሳሳይ የማዳመጥን ክሂል የማጎልበት ብቃታቸውን በተመለከተ "የማዳመጥ ክሂልን ሊያጎለብቱ አይችሉም" በሚል ለቀረበው ጥያቄ በሶስቱም ክልሎች 7ኛ እና 8ኛ ክፍልን ከሚያስተምሩ መላሾች ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር የያዙት አሉታዊ መልስ በመስጠት የማዳመጥን ክሂል እንደሚያጎለብቱ መስክረዋል።

በመጨረሻም በሠንጠረዥ 10 እና በሠንጠረዥ 11 ላይ በዝርዝር የቀረቡትን ጥያቄዎች በሚያካልል ሁኔታ "አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የክሂል ትምህርትን እንጂ ሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን አያስጨብጡም።" በሚል ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ለየትኛው ዓላማ እንደዋሉ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የጋምቤላ እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ 7ኛ ክፍል መምህራን መልስ ሰጭዎች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ አብዛኞቹ መላሾች ከደቡብ ክልል አሉታዊ መልስ በመስጠት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ክሂሎችን ከማዳበር በተጨማሪ ሥነጽሑፍንም ለማስተማር ተግባር እንደዋሉ ገልጸዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ አብዛኛውን ቁጥር የያዙ የጋምቤላ

ክልል መላሾች አመንታዊ መልስ ሲሰጡ በአንባሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የደቡብ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ በመስጠት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥነጽሑፋዊ እውቀትን ለማስጨበጥ ዓላማም እንደቀረቡ መስክረዋል።

ባጠቃላይ መምህራኑ የሰጧቸውን መልሶች ስናጠቃልል የምናገኘው መልስ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የመናገርን እና የማዳመጥ ክሂልን የሚያጎለብቱ ናቸው የሚል አስተያየት ያላቸው መሆኑን ነው። እዚህ ላይ የጋምቤላ ክልል የ7ኛ ክፍል መምህራን የሰጡት ምላሽ ቀደም ሲል በሠንጠረዥ 5 ላይ (ከተማሪዎቹ ዳራ አንፃር) ከሰጡት ምላሽ ጋር በተጨማሪም በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር የሚጋጭ ምላሽ ሰጥተዋል። ምክንያቱም አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ አቅም (አጠቃላይ ግንዛቤ) በላይ መሆናቸውን ካረጋገጡ የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የመናገርና የማዳመጥ ክሂሎቻቸውን እንዴት በብቃት ሊያጎለብቱላቸው ይቻላቸዋል። ከዚህ ተጨባጭ እውነታ አንፃር መምህራኑ የጡት መልስ ተጠየቃዊነት ይጎድለዋል።

## ሠንጠረዥ 12፦ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥነልሳንን ለማስተማር ያላቸው እገዛ

| ተ.ቁ | ሀ. ሥነልሳንን ለማስተማር ያላቸው እገዛ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 |
| 4.2 | ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች በፍጥነት አንብበው መልዕክታቸውን ያለ መምህራን እርዳታ በቀላሉ ሊገነዘቧቸው አይችሉም፡ | 4 | - | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | - | 3 | 1 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 |
| 5.1 | ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች ሲያነቡ የሚያጋጥሟቸውን ከባድና አዳዲስ ቃሎች ከአውዳቸው በቀላሉ ሊያውቋቸው ይችላሉ። | - | - | 5 | 2 | - | 3 | 1 | - | 4 | 4 | - | 1 | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | - |
| 5.2 | በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ተማሪዎቹ ለሚገኙበት አካባቢ እንግዳ የሆነ ዘዬ (አካባቢያዊ ቃላት) ወይም ሙያዊ ቃላት በብዛት አይገኙም። | 4 | - | 1 | 3 | - | 2 | 2 | - | 3 | 3 | 1 | 1 | 5 | - | - | 4 | - | 1 |
| 5.3 | በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተማሪዎቹ የተለያዩ ቃላትን በአውዳቸው እንዲማሩዋቸው እገዛ አያደርጉም። | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | - | 4 | 5 | - | - | 2 | - | 3 | 1 | - | 4 |
| 5.4 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች የወጡ የቃላትን ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ የሚያለማምዱ መልመጃዎች ቀርበዋል። | 5 | - | - | 5 | - | - | 5 | - | - | 5 | - | - | 5 | - | - | 4 | - | 1 |
| 5.8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቀረቡት ግጥሞች ውስጥ የሚገኙት ቃላት ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው። | - | 1 | 4 | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 | 1 | 3 | 2 | - | - | 1 | 4 | 2 | 2 | 1 |

ከላይ በሠንጠረዥ 12 የቀረበው መረጃ የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ ሥነልሳናዊ ግንዛቤ አንፃር ተገቢነታቸውን በተመለከተ የሰጡትን ምላሽ ነው። የመጀመሪያው ጥያቄም "ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን በፍጥነት አንብበው ያለመምህራን እገዛ መልዕክቶቻቸው በቀላሉ ሊረዱ አይችሉም።" በሚል ሐሳብ ለቀረበላቸው ጥያቄ 7ኛ ክፍልን በተመለከተ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የጋምቤላ ክልል መላሾች አዎንታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መልስ ሰጪ መምህራን አሉታዊ መልስ በመስጠት ተማሪዎቹ ካለመምህራን እገዛ ምንባቦቹን አንብበው እንደሚገነዘቧቸው ገልጸዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል ቀርቦ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙ የጋምቤላ ክልል እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ተጠያቂ መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ በአንፃሩ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙ የደቡብ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።

በተመሳሳይ ቃላትን በተመለከተ "ተማሪዎቹ በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ውስጥ የሚያጋጥሟቸውን እንግዳ ቃላት ከአውዳቸው በቀላሉ ፍቻቸውን ይረዳሉ።" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የ7ኛ ክፍል ጋምቤላ ክልል እና ደቡብ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ በመስጠት አዳዲስ ቃላትን በቀላሉ ከአውዳቸው ለመረዳት እንደሚቸገሩ ሲመሰክሩ በአንፃሩ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል። ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ - አብዛኛውን ቁጥር የያዙ የጋምቤላ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ ሲሰጡ በአንፃሩ ከፍተኛ ቁጥር የያዙ የደቡብ ክልል መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። በሌላ በኩል 3 መምህራን ከቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ለመወሰን መቸገራቸውን ገልፀዋል።

እነዚህ በጥያቄ 5.1 የተጠቀሱት "እንግዳ ቃላት በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በብዛት አይገኙም" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ከደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል መምህራን መላሾች በስተቀር በሶስቱም ክልሎች የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል ተያቂ መምህራን አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው መላሾች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል።

ይህ የመምህራኑ ምላሽ ሙሉ በሙሉ በመጻሕፍቱ ላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር ይዛመዳል። በተመሳሳይ "የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተማሪዎች ቃላትን በዐውዳቸው እንዲማሩ አያስችሉም" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ፣ 7ኛ ክፍልን በተመለከተ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የደቡብ ክልል እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች አሉታዊ ምላሽ ሲሰጡ 8ኛ ክፍልን በተመለከተም አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት የጋመቤላ ክልል እና የደቡብ ክልል መምህራን አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል፡ በአንፃሩ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መምህራን አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል።

## ሠንጠረዥ 13:- ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፍን ለማስተማር ያላቸው እገዛ

| ተ.ቁ | ለ. ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥነጽሑፍን ለማስተማር ያላቸው እገዛ | ጋምቤላ | | | | | | ደቡብ | | | | | | ቤኒሻንጉል ጉሙዝ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | | 7ኛ | | | 8ኛ | | |
| | | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2፣1 | 5፣4 | 3 | 2 |
| 5.5 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መካከል ፈሊጣዊ አነጋገሮች በዓውዳቸው ለማስተማር የሚያገለግሉት ምንባቦች የሉም። | 2 | 2 | 1 | 2 | - | 3 | 3 | - | 2 | 5 | - | - | 2 | 2 | 1 | 3 | - | 2 |
| 5.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በዓውዳቸው ለማስተማር የሚያገለግሉ ይገኛሉ። | 2 | 1 | 2 | 4 | - | 1 | - | 1 | 4 | 3 | - | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | - | 3 |
| 5.9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ግጥሞች ዜማዊነታቸውን ያልጠበቁ በመሆናቸው ተማሪዎቹ በደስታና በጉጉት ስሜት አያነቧቸውም። | 2 | 1 | 2 | - | - | 5 | 1 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 |
| 2.9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ለተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን የሚያስጨብጡ ናቸው። | 1 | 4 | - | 5 | - | - | 3 | 2 | - | 4 | 1 | - | 5 | - | - | 2 | 2 | 1 |

በሠንጠረዥ 13 ላይ የቀረበው መረጃ መምህራን ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች መካከል አንዱ የሆነውን ሥነጽሑፋዊ ግንዛቤ ከማስጨበጥ አንፃር በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ላይ የሰጡትን ምላሽ ነው። የመጀመሪያው ጥያቄ፣ ‹‹ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በዐውዳቸው ለማስተማር የሚያስችሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አልተካተቱም›› በሚል ቀርቦላቸው አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የደቡብ ክልል 7ኛ ክፍል መምህራን አዎንታዊ ምላሽ ሲሰጡ የጋምቤላና የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል መላሾች ግን አብዛኛውን ቁጥር የያዙት አዎንታዊ መልስ የሰጡት ለመወሰን ያስቸግረናል ካሉት ጋር ተመሳሳይ ቁጥር አላቸው ይህ የመምህራኑ ምላሽ በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ ከቀረበው ትንታኔ ጋር ይዛመዳል፡ “ሰብለወንጌል” (ጋምቤላ፣ 7ኛ፣ ገጽ 118) እና “ከባሌ መልስ” (ደቡብ እና ቤኒሻንጉል፣ 7ኛ፣ ገጽ 105፣100) በሚል ርዕስ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ፈሊጣዊ አነጋገር ለማስተማር የቀረቡ ቢሆኑም በምንባቦቹ ውስጥ ግን ምሳሌዎችን አናገኝም። ስለዚህም የመምህራኑ መልስ ተገቢነት አለው።

ይኸው ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ የጋምቤላ ክልል መላሾች በቁጥር የሚበልጡት ‹‹ፈሊጣዊ አነጋገሮችን በአውዳቸው የሚያስተምሩ አሉ›› በማለት ሲመልሱ በአንፃሩ አብዛኛውን ቁጥር የያዙት የደቡብ እና የቤኒሻንጉል ክልሎች መልስ ሰጪዎች አዎንታዊ መልስ ሰጥተዋል። እዚህ ላይ የደቡብ ክልል መላሾች የሰጡት መልስ ከተጨባጭ እውነታው ጋር ይዛመዳል። ፈሊጦችን ለማስተማር የተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ “ሉጴ” (ደቡብ፣ 7ኛ፣ ገጽ 191-192) በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን ፈሊጣዊ አነጋገሮችን ግን አላካተተም። ትምህርቱም የተሰናዳው ከአውድ ውጭ በቀረቡ ፈላጣዊ አነጋገሮች ነው። በተመሳሳይ “ከበሮ ሲያዩት ያምር” (ጋምቤላ፣ 7ኛ፣ 74-75) በሚል ርዕስ የተመረጠው ሥነጽሑፋዊ ሥራ የፈሊጣዊ አነጋገር ትምህርትን ለማስተማር የቀረበ ቢሆንም በምንጭነት አላገላገለም፣ ትምህርቱም የቀረበው ከአውድ ውጭ በቀረቡ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ነው። መምህራኑ የጋምቤላ ክልል አሉታዊ መልስ ሊሰጡ የቻሉት ምናልባት ትምህርቱ በይዘትነት በመካተቱ ብቻ ሊሆን ይችላል።

በሌላ በኩል ‹‹ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በዐውድ ለማስተማር የሚያስችሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተመርጠዋል።›› በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የደቡብ ክልል መላሾች አሉታዊ መልስ በመስጠት አለመኖራቸውን ሲጠቁሙ በአንፃሩ አዎንታዊ እና አሉታዊ ምላሽ የሰጡት የጋምቤላና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች ቁጥራቸው እኩል መሆኑን ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት ይቻላል።

ሁለት የተለያዩ ምላሾች ሊገኙ የቻሉት ምናልባት የሉም በማለት ምላሽ የሰጡት መምህራን የታቀደውን የትምህርት አላማ ሊያሳኩ የሚችሉ በቂ ምሳሌአዊ አነጋገሮች በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ውስጥ ባለመገኘታቸው ሊሆን ይችላል። ነገር ግን በአንባራዊነት ሊቃኙ የመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከፊሊጦች ይልቅ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በመጠኑም ቢሆን አካተዋል።

ይህ ጥያቄ ለ8ኛ ክፍል መምህራን ቀርቦ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መላሾች አብዛኞቹ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በውድ የሚያስተምሩ ይገኛሉ በማለት ሲመልሱ በአንባሩ የያቡብ እና የጋምቤላ ክልል መላሾች አለመኖራቸውን ገልጸዋል።

ከሥነጽሑፍ ትምህርት መካከል አንዱ የሆነውን ግጥምን በተመለከተ "በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡት ግጥሞች የግጥምን ባሕርያት አያሟሉም" በሚል የቀረበላቸውን ጥያቄ የጋምቤላ ክልል 8ኛ ክፍል መምህራን ብቻ የግጥምን ባሕርያት ያሟላሉ፣ በማለት የመለሱት ከፍተኛውን ቁጥር ሲይዙ፣ በአንባሩ ቀሪዎቹ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መምህራን መልስ ሰጪዎች ለመወሰን እንደሚያስቸግራቸው የጠቆሙት አብዛኛውን ቁጥር ይይዛሉ። ለመወሰን መቸገራቸውን የገለጹበት ምክንያት ምናልባት ግጥሞቹን በጥልቀት መመርመር እንዳለባቸው በማመናቸው ሊሆን ይችላል።

ባጠቃላይ መምህራኑ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ለተማሪዎች ሥነጽሑፋዊ እውቀትን ከማስጨበጥ አንፃር ያላቸውን ፋይዳ እንዲገልጹ ተጠይቀው አብዛኛውን ቁጥር ያላቸው የጋምቤላ ክልል የ7ኛ ክፍል መምህራን መላሾች ለመወሰን መቸገራቸውን ገልጸዋል። መምህራኑ ይህን መልስ ሊሰጡ የቻሉት ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከመነሻው ለተማሪዎቹ የማይመጥኑ በመሆናቸው ሊሆን ይችላል። ቀሪዎቹ የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍል መልስ ሰጪ መምህራን ግን ሥነጽሑፋዊ እውቀትን ያስጨብጣሉ" በማለት ምላሽ ሰጥተዋል።

ከላይ በመምህራኑ የሰጡት ዝርዝር ምላሾችና ከማጠቃለያ ጥያቄው ምላሽ የምንገነዘበው፣ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በሥነጽሑፍ ትምህርትነት የሚካተቱትን ይዘቶች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ አለማቅረባቸውን ሲሆን፣ ነገር ግን በጥቅሉ ሲታዩ ለተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ግንዛቤን የሚያስጨብጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መኖራቸውን የሚስማሙበት ጉዳይ መሆኑን ነው።

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳቦች

በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ ውጤት ማጠቃለያና ከጥናቱ ጋር የተዛመዱ የመፍትሔ ሐሳቦች በቅደምተከተል ይቀርባሉ፤

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ የነበረው የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ክልሎች ለመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (በ7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች) ተማሪዎች በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት መመርመር ሲሆን ወደዚህ አበይ አላማ ለመድረስም፤

1. ሥነሑፋዊ ሥራዎች በተሻሻሉት የመርሐትምህርቶች ብሎም በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ምን ያህል ሽፋን ተሰጥቷቸዋል?
2. ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሲመረጡ ለሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ መሠረት የሚሆኑ መርሆዎች ባገናዘበ መንገድ ነውን?
3. የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ሲደራጁ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አደረጃጀት መርሆዎች ባገናዘበ መንገድ ነውን?
4. በመርሐትምህርቱ ውስጥ የተቀረጹት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ እንዴት ተተግብረዋል?

የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች ይዞ ነበር።

## 5.1. ማጠቃለያ

ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ለማግኘት የተሰበሰቡ መረጃዎች ተተንትነው ያስገኙት ውጤት እንደሚያስረዳው፣ በስድስቱም የጥናቱ ተተኳሪ መጻሕፍት ውስጥ በጠንካራ ጎንነት የሚፈረጁ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ስልቶች የተስተዋሉ ሲሆን የዚያኑ ያህል ድክመቶች አልታጡም። ይህንኑ የጠቆመት የጥናቱ ውጤቶች ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው፤

በመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ እርከን (7ኛ እና 8ኛ ክፍሎች) የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት አንፃር ሲታዩ ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጣቸው በጥናቱ ተረጋግጧል። በመጻሕፍቱ የተካተቱትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ለመምረጥ ሁለት ዋና መስፈርቶች በአገልግሎት ላይ መዋላቸው (በጥናቱ) ተደርሶበታል። አንደኛው ሥነጽሑፋዊ ሥራው ከሀገራችን ዕውቅ ደራሲያን ሥራዎች ላይ የተወሰዱ መሆናቸው አዘጋጆቹ እንደ መስፈርት ሲወስዱ፣ ሁለተኛው አዘጋጆቹ በግል የማመዛዘን ችሎታቸው ላይ ተመሥርተው፣ ኢአፈ-ፈት ተናጋሪዎችን ከግምት ባላስገባ መልኩ የሥነጽሑፋዊ ሥራውን የክብደት ደረጃ በመገመት ይመጥናል ያሉትን የመረጡበት መስፈርት ነው።

በአንዳንዱ የመስኩ ምሁራን የሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አመራረጥ በተመለከተ ከሠነዘሯቸው መስፈርቶች መሀል ጥቂት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተወሰኑትን መስፈርቶች አሟልተው ቢቀርቡም አብዛኞቹ ግን በተለይ የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ ከማሳካት አንፃር፣ ከመርሐትምህርቱ ጋር ከመጣጣም አኳያ፣ ለክፍል ደረጃው ተማሪዎች ካላቸው ተገቢነት አንፃር፣ የኢ-አፈ-ፈት ተማሪዎች ሥነልሳናዊ ብቃትና ዳራ ከማገናዘብ አንፃርና ከርዝመኔ ምጠና አኳያ ተገቢ ትኩረት እንዳልተሰጣቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

በሌላ በኩል የተወሰኑት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በሥራቸው ለተደራጁት መልመጃዎች በምንጭነት ማገልገላቸው ባይካድም በአንዳንዱ አብዛኞቹ በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግን ቋንቋን ለማስተማር በምንጭነት ሲያገለግሉ አልተስተዋለም።በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ሥር የቀረቡት በርካታ መልመጃዎች ከምንባቦቹ የወጡ ሳይሆኑ ምንባቦቹን ተገን አድርገው ከሚቀርቡት ማብራሪያዎችና ገለፃዎች መሆኑን በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ በተካሄደ ጥናት ተረጋግጧል። በተጨማሪም አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተማሪዎቹን ልዩ ልዩ የቋንቋ ክሂሎች ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ከማጎልበት ይልቅ በከፍተኛ ደረጃ ትኩረት የሰጡት ለአንብቦ መረዳትና ለቃላት (ሐረጋት) ትምህርት መሆኑን ጥናቱ አመልክቷል።

የትምህርት እርከኑን የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አደረጃጀት በተመለከተም የሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን ጎናዊና ተዋረዳዊ አወቃቀራቸው ከቀላል ወደከባድ፣ ከተጨባጭ ወደ ረቂቅ ወይም ከሚታወቅ ወደማይታወቅ በሚጓዝ መልኩ የማቅረቡ

ተግባር በሁሉም መማሪያ መጻሕፍት ላይ ትኩረት ተነፍጎታል። ከዚሁ ጋር በተያያዘም አዘጋጆቹ ይህ ነው የሚባል የአደረጃጀት ሥልትን አለመጠቀማቸው የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

በተመሳሳይ በአብዛኞቹ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን በፋይዳቸው ሚዛን ደፊነት መሠረት የማደራጀቱ ሂደት የተማሪዎቹን ዳራዊ ግንዛቤ ባገናዘበ መልኩ በአንድ የክፍል ደረጃም ሆነ (ጎናዊ) በተከታታይ የክፍል ደረጃዎች (ተዋረዳዊ) ላይ ተግባራዊ አለመደረጉን በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል።

በሌላ በኩል የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ስልታዊ በሆነ መንገድ በትምህርቱ መጀመሪያ የቀረበ ይዘት ሳይቋረጥ እስከ (ትምህርቱ) መጨረሻ ስፋትና ጥልቀት በሚያሳይ መልኩ በተከታታይ የማቅረቡ ተግባር በሁሉም መጻሕፍት ላይ ትኩረት ያላገኘ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

አንዳራዊ በሆነ መልኩ ተከታትለው (በአንድ የክፍል ደረጃም ሆነ በተከታታይ የክፍል ደረጃ) የቀረቡትም የትምህርት ይዘቶች ስፋትና ጥልቀት በሚያሳዩ መልኩ ሳይሆን በአጋጣሚ መደራጀታቸውን መረጃዎች አመልክተዋል። ይህ ችግር በተለይ ጎልቶ የታየው ለጋምቤላ ክልል 7ኛ እና 8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አሳይቷል።

ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ካልሆኑት ጋር አሳባጥሮ ማቅረቡና ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹንም አንዱን ከሌላው ጋር (እርስበርስ) አፈራርቆ የማቅረቡ ተግባር የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑት ሁሉም መማሪያ መጻሕፍት ላይ አለመተግበሩን ከየመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ የተሰበሰቡት መረጃዎች አሳይተዋል። በዚህም ምክንያት የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አጓጊነት የቀነሰ ሊሆን መቻሉን ጥናቱ አሳይቷል። ይህ ችግር በስፋት የተስተዋለውም ለ7ኛ ክፍል በተዘጋጁት መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ እንደሆነ በጥናቱ ውጤት ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች

በማጠቃለያው ክፍል የተገለጹት የጥናቱን ውጤቶች መሠረት በማድረግም፣ መቀጠል የሚገባቸው የመጻሕፍቱ ጠንካራ ጎኖች መኖራቸው ሳይዘነጋ፣ ችግር በታየባቸው (መስተካከል በማገባቸው) የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥና አደረጃጀት ሂደት ላይ አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች ሰንዝሯል፤

1ኛ. በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መሣሪያነት ቋንቋን የማስተማሩ ተግባር በተለይ ለኢአፊ-ፊት ተናጋሪዎች (ተማሪዎች) የሚኖራቸውን ከፍተኛ ጠቀሜታ ልዩ ትኩረት በመስጠት በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ሚዛናዊ በሆነ መልኩ እንዲካተቱ ቢደረግ፣

2ኛ. ለቋንቋ ማስተማሪያነት የሚያገለግሉ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ በተቻለ መጠን አብዛኞቹ የቋንቋ ምሁራን የተስማሙባቸው የአመራረጥ መርሆዎች (መስፈርቶች) ተለይተው ተገቢው ትኩረት እንዲሰጣቸው ጥረት ቢደረግ፣

3ኛ. ተገቢውን መስፈረት አሟልተው በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ እንዲካተቱ የተመረጡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲደራጁም፣ በመስኩ ምሁራን የተጠቆሙትን የአደረጃጀት መርሆዎች የተከተሉ እንዲሆኑ ማድረግ ቢቻል፣

4ኛ. እነዚህ ከላይ የተጠቀቀሙትን ዐበይት ጉዳዮች ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድም በመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጅነት፣ አርታኢነት ወይም አሻሻይነት የሚመደቡ (የሚመረጡ) ባለሙያዎች፣

- በመምህርነት ሙያ ላይ ለረዥም ዓመታት ያገለገሉ፣
- በመማሪያ መጽሐፍ አዘገጃጀትና በአርትኦት ሥራ ላይ ተገቢውን ሥልጠና የወሰዱ፣
- መማሪያ መጻሕፍቱ የሚዘጋጁላቸው ተማሪዎች የሚገኙበትን አካባቢ ማሕበረሰብ ባሕል፣ ሃይማኖት፣ የአኗኗር ዘይቤና መልክዐምድራዊ አቀማመጥ፣ ባጠቃላይም የአካባቢውን ተጨባጭ ሁኔታ ጠንቅቀው የተረዱ፣

መሆናቸው ቢረጋገጥ፣

5ኛ. የመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ወይም ማሻሻል ተግባር ልዩ ጥንቃቄን የሚፈልግ ተግባር ከመሆኑ አንፃር፣ ሥራው ከመጀመሩ በፊት አስፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ቢደረግና በዝግጅት ወቅትም አዘጋጆቹ በቂ ጊዜ ተሰጥቷቸው እንዲያከናውኑ ቢደረግ፣ (ምክንያቱም አንዳንድ አዘጋጆች በቃለመጠይቁ ላይ እንደገለጹት መጽሐፉን ለማዘጋጀት የሰጣቸው አንድ ወር ብቻ መሆኑንና አስፈላጊው መረጃ መጻሕፍት ባለመኖራቸው በግል ጥረታቸው ለማሰባሰብ እንደሞከሩ ጠቁመዋል።)

6ኛ. ለተከታታይ የክፍል ደረጃዎች የሚዘጋጁ መጻሕፍት አንድ ወጥ አካሄድን ተከትለው፣ የትምህርት ይዘቶችን ተከታታይነት እና ተለጣጣቂነት መጠበቅ

ይቻል ዘንድ፣ በአዘጋጆቹ መካከል የልምድ ልውውጥ የሚካሄድበት ሁኔታ ቢመቻች፣ (ምክንያቱም በአዘጋጆቹ መካከል ያለው ሰፊ የአመለካከት ልዩነቶች በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ በተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥ እና አደረጃጀት ሂደቶችም ላይ ሊንፀባረቅ ይታያል።)

7ኛ. በመማሪያ መጻሕፍቱ ላይ የተስተዋሉት አንዳንድ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ችግሮች መንስኤዎቻቸው አስቀድሞ በተዘጋጀው መርሐትምህርት ላይ በሚያስተዋሉ ተገቢነት የጎደላቸው አደረጃጀቶችና ግልጽነት ማጣት ሰበብ በመሆኑ፣ የመርሐትምህርት ነዳፊዎች ለይዘቶች አመራረጥ እና አደረጃጀት ሂደት ልዩ ትኩረት እንዲሰጡ ለማስቻል ከመምህራንና ከመጽሐፍ አዘጋጆችም ጋር ግልጽ ውይይቶች የሚያካሂዱበት መንገድ ቢመቻች፣

8ኛ. መማሪያ መጻሕፍቱ ከተዘጋጁም በኋላ በአርታኢያኑ ከሚደረገው ማሻሻያ በተጨማሪ በተለይ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን አመራረጥ ተገቢነት ከተማሪዎቻቸው ዳራ አንፃር እንዲገመግሙት፣ በመጽሐፉ የሚገለገሉና በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ መምህራን አስተያየት እንዲሰጡበት በማድረግ ተገቢ የማሻሻያ ሥራ ቢከናወን፣

9ኛ. ከሀገራችን ተጨባጭ እውነታ አንፃር እስካሁን ለቋንቋ ማስተማሪያነት ታቅደው (ሆነ ተብሎ) የሚቀርቡ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎችን የሚያዘጋጁ ባለሞያዎች ባለመኖራቸው ምክንያት የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆችን ጫና (ችግር) መቅረፍ ይቻል ዘንድ የየክልሉ የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተትምህርት ባለሙያዎች እና መምህራን በክልላቸው ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስረተው የሚቀርቡ ልዩ ልዩ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በሥነጽሑፍ ክበብ የአባላትና በሚኒሚዲያዎች የሚቀርቡበትንና ለህትመት የሚበቁበትን ሁኔታዎች ቢያመቻቹ፣

10ኛ. የተማሪዎችን የንባብ ክህሎት የሚያጎለብቱና በአጋዥ መርጃ መሣሪያነት የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ የተረት፣ የአጭር ልቦለድ፣ የረጅም ልቦለድ የግጥምና የተውኔት መጻሕፍት፣ መጽሔቶችን፣ ጋዜጣዎችን፣ ወዘተ. በቤተመጻሕፍት ውስጥ ተማሪዎቹ በበቂ መጠን የሚያገኙበት መንገድ ቢቀየስ፣

የሚሉት በዋነኛነት ተጠቁመዋል።

# ዋቢ ጽሑፎች


መላኩ መሐሪ እና አለማየሁ ዘሪሁን፡፡(1997)፡፡ *አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ* 8ኛ ክፍል፡፡ በጋምቤላ/ሕ/ብ/ክ/መ/ት/ም/ቢሮ፣ ሥ/ት/ም/ዝ/ጥ/ም/መምሪያ፡፡

ስለሺ ኩራ እና አብደላ ሙሰማ፡፡ (1997)፡፡ **አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል**፡፡ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡ ***በስነጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር***፡፡ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ተስፋዬ ሽዋዬ (1982)፡፡ "ሥነልሳንና ቋንቋን ማስተማር"፡፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡፡ (ያልታተመ)

ታከለ መኮንን እና እስክንድር ቸርነት፡፡ (1997)፡፡ **አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 8ኛ ክፍል**፡፡ ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ የሥ.ት.ዝ.ጥ.ም.መምሪያ፡፡

----------፡፡ (1998)፡፡ **አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል**፡፡ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ትምህርት ቢሮ፣ የሥ.ት.ዝ.ጥ.ም. መምሪያ፡፡

ክንፈሚካኤል ሱጋ፡፡ (1995)፡፡ «ስነዕሁፋዊ ይዘቶች የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂልና የሥነጽሑፍ ዕውቀት ለማሳደግ ያላቸው እገዛ በ1993 እና በ1994 ዓ.ም. ለ10ኛና ለ11ኛ ክፍል መማሪያነት በተግባር ላይ በዋሉት መፃሕፍት፡፡" ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፣ አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ኢ.አ.ዩ፡፡ (ያልታተመ)

አበበ ከበደ እና ዘለቃ ስዩም፡፡ (1997)፡፡ **አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል**፡፡ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት ትምህርት ቢሮ፣ ት.መ.ማ.ማ.ድ፡፡

ጣሰው ታደሰ እና ሌሎች፡፡(1997)፡፡ **አማርኛ መማሪያ መጽሐፍ 7ኛ ክፍል፡፡** በጋምቤላ/ሕ/ብ/ክ/መ/ት/ም/ቢ.ሮ፣ ሥ/ት/ም/ዝ/ጥ/ም/መ/ም/ሪያ፡፡

ጥላሁን ገብረክርስቶስና ሌሎች፡፡ (1991)፡፡ **የአማርኛ ቋንቋ መርሐ ትምህርት 7ኛ ና 8ኛ ክፍል፡፡** አዲስ አበባ፣ ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፡፡

----------፡፡ (1995)፡፡ **አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ እንደሁለተኛ ቋንቋ መርሀ-ትምህርቶች ከ7ኛ-8ኛ ክፍል፡፡** (ተሻሽሎ የተዘጋጀ)፡፡ አዲስ አበባ፣ ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም ኢንስቲትዩት፡፡

ወንድወሰን አዳነ፡፡ (1995)፡፡ «አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የሥነጽሑፍ ይዘቶች ፋይዳ፣ አመራረጥና አደረጃጀት፡፡» አማርኛን በሁለተኛ ቋንቋነት ለማስተማር የተቀረጹትን የ7ኛ እና የ8ኛ ክፍሎች መርሃትምህርቶች ለማሻሻል በተዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ የቀረበ፡፡ አዲስ አበባ፣ ሥ/ት/ዝ/ጥ/ም/ ኢንስቲትዩት፡፡ (ያልታተመ)

ዘመንፈስ ባራኪ፡፡ (1991)፡፡ «በስነጽሑፍ አማካይነት አማርኛ ቋንቋን በማስተማር የአጭር ልብለወድ ሚና፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት፡፡» ለኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት አዲስ አበባ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል፣ ኢ.አ.ይ፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ (1992)፡፡ ***የሥነጽሑፍ መሠረታውያን፡፡*** አዲስ አበባ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ (1991)፡፡ «አንዳንድ ነጥቦች ስለሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች፣ ስለመማሪያ መጻሐፍትና ሥነጽሑፍ ሚና በቋንቋ ትምህርት (1944-1983)፡፡» ለቋንቋ ጥናት ተቋም ዘጠነኛ ዓመታዊ ሰሚናር የቀረበ፣ ኢ.አ.ይ፡፡

Bearne, E. (1996). "Mind the Gap". In M.Styles E.Beavne, and V.Waston (Eds.), **Voices.** London: Cassell. pp 310-329.

Billows, F.L. (1961). **The Techniques of Language Teaching**. London: Green Co.Ltd.

Bretz, M.L. (1990). Reaction: Literature and Communicative Competency: A Springboard for the Development of Critical Thinking and Aesthetic Appreciation, **Foreign Language Annals**. Vol. 23, No.4. pp.335-338.

Brown W. and Olmasterd, S. (1962). ***Langauge and Literature***. New York: Yale University.

Brownne, A. (1996). ***Developing Language and Literary 3-8*** London: Paul Chapman Pulbisher.

Brumfit, C.J. and R.A. Carter. (1986). ***Literature and Language Teaching.*** Oxford: Oxford University Press.

Cairns, HS and Cairns, CE, (1976). **Psycholinguistics: A Cognitive View of Language.** New York: Holt Rinehart and Winson.

Carter, R.A. and Mcre. (1996). ***Language, Literature and the Learner***. New York: Addison Wesely Longam Ltd.

Carter, R.A. and M. N. Long. (1991). ***Teaching Literarue***. London: Longman Group UK Limited.

Celce-Murcia, M. (1991). ***Teaching English as a Second or Foreign Langauge.*** Heinle; Heinle Publisher.

Celce-Murcia, M. and H. Sharon (1987) **Techniques and Resources in Teaching Grammar.** Oxford: Oxford University Press.

Fowler, WS, (1971). "Literature for Adult Students of English as a Foreign Language" **ELT Journal**. Vol.XXII, No.1.

Ghosn, J. (2002). Four Good Reasons to Use Literature in primary School ELT. **ELT Journal**, Vol. 56, No.1 PP. 172-179.

Hall, G. (2005). **Literature in Language Education**, New York: Palgrave Macmillan.

Hill, J. (1986). ***Using Literaure in Language Teaching.*** London: Macmillan Publishers Ltd.

Lazar, G, and Malley, A. (1991). **Literature in Language Teaching: A Guide for Teachers and Trainers**. London: Cambridge University Press.

Lazar, G. (1993). ***Literature and Language Teaching.*** Cambridge: Cambridge University Press.

McKay, S. (eds.). (1996). "Literature in the Languge Classroom" in Brumift, C. J and R.A. Carter ***Literature and Langauge Teaching.*** Hong Kong: Educational Low-Priced Books Scheme with Oxford: University press.

Meek, M. (1995). The Critical Challenge of the World in Books for Chilldren ELT. Children's Literature in Education, **ELT Journal**. Vol. 26, No. 1. pp 5-23.

Richards, J. (2001). **Curriculum Development in Language Teaching**. Cambridge: Cambridge University Press.

Rodger, A. (1983). "Language for Literature" in Brumfit, C.J. **Teaching Literature Overseas.** Oxford: Pergamon Press.

Schulz, R.A. (1981).Literature and Readability: Bridging the Gap in Foreign Language Reading. ***Modrn Lanaguge Jornal***. Vol.65, No.1, pp. 43-53.

Seldon, R. (1989). **A Reader's Guide to Contemporary Literary Theory**. Harvester: Harvester Wheatsheaf.

Widdowson, H.B. (1975). ***Styletics and the Teaching of Literatuer.*** London: Longman Group Ltd.

# አባሪዎች

# አባሪ 1

## አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

## የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል

## የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

### በ7ኛ እና በ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሚሞላ መጠይቅ

**መግቢያ፡- ውድ መምህር፡-**

የዚህ መጠይቅ ዓቢይ ዓላማ በክልሉ የትምህርት ቢሮ ለ7ኛ እና 8ኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች አመራረጥና አደረጃጀት ሁኔታ ለመረዳት ይቻል ዘንድ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ነው፡፡ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በማቀናጀት የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ፣ የተስተዋሉት አዎንታዊ ሥነጽሑፋዊ ስራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ሂደቶች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በአንባሩ መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮች ከመምህራኑ በሚገኘው ጥቆማ መሠረት ተሻሽለው ተማሪዎቹ ወደፊት በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መሣሪያነት ቋንቋውን በመማር የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ የታቀደ ነው፡፡

በ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ላይ የተካተቱት ይዘቶች (ምንባቦች፣ ማስታወሻዎች፣ መልመጃዎች፣ ወዘተ.) በኢልቦለድ እና በልቦለዳዊ ወይም በሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች ሊመደቡ የሚችሉ ቢሆኑም ይህ ጥናት የሚያተኩረው በሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች ላይ ብቻ ነው፡፡

<u>*ማስታወሻ*</u>፦ በዚህ ጥናት ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች ተብለው የሚታዩት አጭር ልቦለድ፣ ከረጅም ልቦለድ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ ሥራ፣ ተውኔት ወይም ድራማ፣ ግጥምና ሥነቃላዊ የፈጠራ ሥራዎችን፣ ለምሣሌ ተረቶችን ያጠቃልላል፡፡

የጥናቱ ለውጤት መብቃት መማሪያ መጽሐፉን በቅርብ በተግባር የሚያውቁትን የሙያው ባለቤቶች ድጋፍ የሚጠይቅ ስለሆነ እርስዎ ይህንን የጽሑፍ መጠይቅ በመሙላት የበኩልዎን ሙያዊ ትብብር ያደርጉልኝ ዘንድ በታላቅ ትህትናና አክብሮት ስጠይቅ ጊዜዎን መስዋዕት አድርገው ለሚያደርጉልኝ እገዛ በቅድሚያ እጅግ አመሰግናለሁ፡፡

<u>*ማሳሰቢያ*</u>፦ በመጠይቁ ላይ ስምዎን መጻፍ አያስፈልግም፡፡

## ክፍል አንድ ፣ የግል ሁኔታ

እባክዎ በጽሑፍ መልስ የሚያስፈልገውን በክፍት ቦታዎቹ ላይ አስተያየትዎን በመጻፍ በተጨማሪም በሳጥን መልክ በተዘጋጀው ባዶ ቦታ ይህንን ☑ ምልክት በማድረግ ምርጫዎን ያመልክቱ።

1. የትምህርት ቤቱ ስም _____

2. ፆታ፡- - ወንድ ☐ - ሴት ☐

3. ዕድሜ፡ - ከ20-25 ☐ - ከ36-40 ☐ - ከ51 በላይ ☐
   - ከ26-30 ☐ - ከ41-45 ☐
   - ከ31-35 ☐ - ከ46-50 ☐

4. የትምህርት ደረጃ፡-
   - 12 +1 ☐ - የኮሌጅ ዲፕሎማ ☐ - የመጀመሪያ ዲግሪ ☐
   - ከነዚህ የተለየ ከሆነ ቢጠቀስ _____

5. የሠለጠኑበት የትምህርት ዓይነት፡-
   - ዓቢይ _____ - ንዑስ _____

6. የአፍ መፍቻ ቋንቋ _____

7. የአገልግሎት ዘመን _____
   - ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል _____ - ከ7ኛ እስከ 8ኛ ክፍል _____
   - ከ5ኛ እስከ 6ኛ ክፍል _____ - ከነዚህ ከተለየ ይጠቀስ _____

8. በዚህ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዝግጅት ሂደት ላይ ተሳትፈዋል?
   - ተሳትፌያለሁ ☐ - አልተሳተፍኩም ☐

9. በመማሪያ መጽሐፍ ዝግጅት ሂደት ላይ የተሳተፉ ከሆነ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው የፈጠራ ሥራዎች አመራረጥና አደረጃጀት ሂደት ላይ በተካሄዱ ውይይቶች ውስጥ የተነሱ ዋና ዋና ነጥቦች ካሉ ቢጠቁሙኝ።

_____
_____
_____
_____
_____
_____

# ክፍል ሁለት

❖ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ምርጫዎን ይህንን ✓ ምልክት በማድረግ ያመልክቱ።

**አማራጭ መልሶች፡-**

5 ⟶ በጣም እስማማለሁ

4 ⟶ እስማማለሁ

3 ⟶ መወሰን ያስቸግረኛል

2 ⟶ አልስማማም

1 ⟶ ፍፁም አልስማማም

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 |
|---|---|---|---|---|---|
| | ***1. ከተማሪዎች የቀደመ ግንዛቤ (ዳራ) ጋር በተያያዘ*** | | | | |
| 1.1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ማለትም አጭር ልቦለዶች፣ ረዥም ልቦለዶች፣ ተውኔቶች፣ ግጥሞችና ተረቶች ከተማሪዎቹ ፍላጎትና ዝንባሌ ጋር ይጣጣማሉ። | | | | |
| 1.2 | ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ ከተማሪዎቹ የዕድሜ ደረጃ ጋር አይመጣጠኑም። | | | | |
| 1.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከተማሪዎቹ ልዩ ልዩ ባህላዊ ጉዳዮች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው። | | | | |
| 1.4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች የተማሪዎችን የተለያዩ እምነቶች (ሃይማኖቶች) ከግምት ውስጥ ያስገቡ አይደሉም። | | | | |
| 1.5 | ተማሪዎች በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ሲያነቡ ወይም ሲነበብላቸው በጉጉት፣ በደስታ ስሜትና በንቃት እስከመጨረሻው ይከታተላሉ። | | | | |
| 1.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ከተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ግንዛቤ ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። | | | | |
| 1.7 | ተማሪዎቹ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች አንብበው መልዕክቱን በቀላሉ ይረዳሉ። | | | | |
| 1.8 | በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዘቶቻቸው ከተማሪዎቹ የዕለት ከዕለት ኑሮ ጋር የሚቀራረቡ ርዕሰጉዳዮችን የያዙ ናቸው። | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1.9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የቋንቋ አጠቃቀም (ለምሳሌ ቃላት) ከክፍል ደረጃው ተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ ጋር ይመጣጠናል። | | | | |
| 1.10 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቋንቋ በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን ያልፈቱ ተማሪዎችን ከግምት ውስጥ ያስገባ አይደለም። | | | | |
| | **2. <u>የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አመራረጥ ሂደት በተመለከተ</u>** | | | | |
| 2.1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የክሂል ዘርፎችን (የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍን) ብቃት የሚያጎለብቱ ናቸው። | | | | |
| 2.2 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች በመርሐትምህርቱ ውስጥ ከቀረቡት የቃላት፣ የዘይቤና የፈሊጣዊ ይዘቶች ትምህርት ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። | | | | |
| 2.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ርዝማኔያቸው የተመጠነ በመሆኑ በክፍል ውስጥ ለመተግበር አመቺ ናቸው። | | | | |
| 2.4 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ለማጠናከር የሚረዱ መርጃ መሣሪያዎች፣ ለምሳሌ የተቀረጹ ድምፆች፣ ሥዕሎች፣ ቻርቶች፣ ፊልሞች፣ ወዘተ. በበቂ መጠን ማግኘት አይቻልም። | | | | |
| 2.5 | የቀረቡትን ልዩ ልዩ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ግልጽ ሊያደርጉ የሚችሉ የቃላት መፍቻዎች፣ ማብራሪያዎች፣ ማስታወሻዎችና መግለጫዎች በበቂ መጠን መማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ። | | | | |
| 2.6 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች የተዘጋጁት ልዩ ልዩ መልመጃዎች ግልጽ መመሪያ ወይም ትዕዛዝ የላቸውም። | | | | |
| 2.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በሥሮቻቸው ከሚገኙት መልመጃዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው። | | | | |
| 2.8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን አጫጭር ልቦለዶች፣ ረጃጅም ልቦለዶች፣ ግጥሞችና ተውኔቶች የያዙ የተለያዩ ደራስያንና ገጣምያን መጻሕፎችን ተማሪዎቹ በቤተመጻሕፍት ውስጥ በቀለሉ ሊያገኟቸው አይችሉም። | | | | |
| | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 |
|---|---|---|---|---|---|
| 2.9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ለተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን የሚያስጨብጡ ናቸው። | | | | |
| 2.10 | የተመረጡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የክሂል ዘርፍ የሆኑትን (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) ሚዛናዊነታቸውን ጠብቀው (በእኩል ደረጃ) በመልመጃነት አላቀረቡም። | | | | |
| | **3. <u>አደረጃጀታቸውን በተመለከተ</u>** | | | | |
| 3.1 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመጀመሪያ ላይ ቀላሎቹን በማስቀደም ከባዶቹ በመጨረሻ ላይ ቀርበዋል ወይም ከቀላል ወደ ከባድ ተደራጅተዋል። | | | | |
| 3.2 | በሥነጽሑፋዊ ምንባቦቹ ሥር የተደራጁት መልመጃዎች ተማሪዎቹ በምንባቦቹ ይዘት ላይ በግልና በቡድን እንዲሳተፉ የሚያስችሉ አይደሉም። | | | | |
| 3.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የተደራጁት ከተማሪዎቹ የሕይወት ልምድ ጋር የቀረቡትን እና በቀላሉ የሚያውቁትን ርዕሰጉዳይ በማስቀደም ነው። | | | | |
| 3.4 | በሥነጽሑፋዊ የፈጠራሥራ ዓይነቶች ማለትም በልቦለዶች፣ በግጥሞች፣ በተውኔቶችና በተረቶች ቋንቋን ሲማሩ የመጀመሪያቸው ሳይሆን በቀደመው የክፍል ደረጃ ላይ በዚሁ ስልት ተምረዋል። | | | | |
| 3.5 | በተከታታይ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ይዘቶቻቸው ስፋትና ጥልቀት እያሳዩ የሚያድጉ አይደሉም። | | | | |
| 3.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች (አጭር ልቦለድ፣ ረጅም ልቦለድ፣ ተውኔት ወይም ድራማ፣ ግጥምና ተረት) ቁጥራቸው አነስተኛ ነው። | | | | |
| 3.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሥነጽሑፋዊ ይዘት ከሌላቸው ምንባቦች ጋር ተሰባጥረው (ተቀላቅለው) አልቀረቡም። | | | | |
| | **4. <u>ክሂሎችን ማጎልበት በተመለከተ</u>** | | | | |
| 4.1 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከመቅረባቸው በፊት የቀረቡት የመወያያ ጥያቄዎች ከምንባቡ ይዘት ጋር የሚገናኙ ናቸው። | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 4.2 | ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች በፍጥነት አንብበው መልዕክታቸውን ያለ መምህራን እርዳታ በቀላሉ ሊገነዘቧቸው አይችሉም። | | | | | |
| 4.3 | በመማሪያ መጽሐፉ ላይ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች የተማሪዎችን የንባብ ክሂል የሚያሳድጉ ናቸው። | | | | | |
| 4.4 | ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ከሌላቸው (ኢልቦለዶች) ምንባቦች ይልቅ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች የማንበብ ፍላጐትና ጉጉት አላቸው። | | | | | |
| 4.5 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች በክፍል ውስጥ ከተነበቡ በኋላ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ላይ አብዛኞቹ ተማሪዎች ተሳትፎ ያደርጋሉ። | | | | | |
| 4.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በጽሑፍ እንዲገልጹ የሚያበረታቱ አይደሉም። | | | | | |
| 4.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተማሪዎቹ ሐሳባቸውን በንግግር እንዲያቀርቡ የሚያበረታቱ ናቸው። | | | | | |
| 4.8 | በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች የተማሪዎቹን የማዳመጥ ክሂል ሊያጐለብቱ አይችሉም። | | | | | |
| 4.9 | በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ተማሪዎቹ ከክፍል ውጪ ሌሎች ተጨማሪ ልቦለድ ታሪኮችን፣ ግጥሞችን፣ ተውኔቶችን፣ ተረቶችን፣ ወዘተ. እንዲያነቡ የሚያነሳሱ ናቸው። | | | | | |
| | **5. ሥነልሳንና ሥነጽሑፍን ማስተማር በተመለከተ** | | | | | |
| 5.1 | ተማሪዎቹ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች ሲያነቡ የሚያጋጥሟቸውን ከባድና አዳዲስ ቃሎች ከአውዳቸው በቀላሉ ሊያውቋቸው ይችላሉ። | | | | | |
| 5.2 | በሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ውስጥ ተማሪዎቹ ለሚገኙበት አካባቢ እንግዳ የሆነ ዘዬ (አካባቢያዊ ቃላት) ወይም መደበኛ ቃላት በብዛት አይገኙም። | | | | | |
| 5.3 | በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ተማሪዎቹ የተለያዩ ቃላትን በአውዳቸው እንዲማሩዋቸው እገዛ አያደርጉም። | | | | | |
| 5.4 | ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች የወጡ የቃላትን ተመሳሳይ ወይም ተቃራኒ ፍቺ የሚያለማምዱ መልመጃዎች ቀርበዋል። | | | | | |
| | | | | | | |

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | 5 | 4 | 3 | 2 |
|---|---|---|---|---|---|
| 5.5 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች መካከል ፊሊጣዊ አነጋገሮች በዓውዳቸው ለማስተማር የሚያገለግሉት ምንባቦች የሉም። | | | | |
| 5.6 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች ውስጥ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በዓውዳቸው ለማስተማር የሚያገለግሉ ይገኛሉ። | | | | |
| 5.7 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አብዛኞቹ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች የክሂል ትምህርት እንጂ ሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን የሚያስጨብጡ አይደሉም። | | | | |
| 5.8 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቀረቡት ግጥሞች ውስጥ የሚገኙት ቃላት ከተማሪዎቹ ችሎታ ጋር ተመጣጣኝ ናቸው። | | | | |
| 5.9 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ግጥሞች ዜማዊነታቸውን ያልጠበቁ በመሆናቸው ተማሪዎቹ በደስታና በጉጉት ስሜት አያነቧቸውም። | | | | |
| 5.10 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በቀረቡት አጫጭርና ረጃጅም ልቦለድ ታሪኮች ውስጥ የሚገኙት ገጸባሕርያት ከተማሪዎቹ እድሜ ጋር የተቀራረቡ ናቸው። | | | | |
| 5.11 | በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አጫጭር ልቦለዶችና ከረጃጅም ልቦለዶች ላይ የተወሰዱት ታሪኮች ከተማሪዎቹ የሕይወት ልምድ ጋር የማይቀራረቡ ናቸው። | | | | |

# ክፍል ሶስት

❖ እባክዎ ከዚህ በታች ለቀረቡት የጽሑፍ መጠይቆች በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ መልስዎን በጽሑፍ በማስፈር ይተባበሩኝ::

3.1 ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ይዘት ያላቸው ምንባቦች (አጭር ልቦለዶች፣ ረጅም ልቦለዶች፣ ግጥሞች፣ ተውኔቶች ወይም ተረቶች) ከተማሪዎቹ ባህል፣ እምነት፣ የቋንቅ ችሎታ፣ ዕድሜ፣ ወዘተ. ጋር ምን ያህል የተስማሙ ናቸው ብለው ያስባሉ? _____

3.2 በሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አመራረጥ ሂደት ላይ ያስተዋሏቸው ጠንካራ ጐኖች ካሉ ቢገልጹልኝ? _____

3.3 በተመረጡት ሥነጽሑፋዊ የፈጠራ ሥራዎች ላይ መሻሻል የሚገባቸው ጉዳዮች ካሉ ቢገልጹልኝ? _____

3.4 የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹ አደረጃጀት በተመለከተ፣ ለምሳሌ ከቀላል ወደ ከባድ፣ ከሚታወቅ ወደማይታወቅ ወይም ተከታታይነት ያላቸው ስለመሆን-አለመሆናቸው የሚሰጡት አስተያየት ካለ ቢገልጹልኝ? _____

3.5 በአጠቃላይ ወደፊት በሚካሄደው የመማሪያ መጽሐፉ ማሻሻል ተግባር ላይ የሥነጽሑፋዊ ሥራዎቹን አመራረጥና አደረጃጀት በተመለከተ መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች ያልዎትን አስተያየት ቢገልጹልኝ? _____

_____ /// _____

ውድ ጊዜዎን ሰውተው ላደረጉልኝ ቀና ትብብር አሁንም በድጋሚ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ::

ዳዊት ፍሬሕይወት

# አባሪ 2

**ለ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች የሚቀርቡ ጥያቄዎች**

**በቅድሚያ ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ በመሆንዎ ከልብ አመሰግናለሁ::**

1. ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ማካተቱ ምን ፋይዳ አለው ብለው ያስባሉ?
2. በአንድ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሥነጽሑፋዊ /የፈጠራ / ይዘት ካላቸው ምንባቦች እና ኢልቦለዳዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች ቋንቋን በማስተማር ሂደት የበለጠ ጠቀሜታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን ?
3. ኢ-ልቦለዳዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦችና ልቦለዳዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች ተማሪዎች ይበልጥ በንቃትና በጉጉት የሚከታተሉት የትኞቹን ነው ? ምክንያቱን ቢገልጹልን?
4. ለአንድ የክፍል ደረጃ በሚዘጋጅ የተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ሲመረጡ የመምረጫ መስፈርቱ ምንድን ነው?
5. ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከተመረጡ በኃላ እንዴት ይደራጃሉ? የአደረጃጀት ቅደም ተከተል አላቸው ወይስ በአጋጣሚ ነው የሚደራጁት?
6. ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች መርጦ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በማካተት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ ቢገልጹልን?
7. ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች የሚወጡ መልመጃዎች ዓቢይ ዓላማ የሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን ለተማሪዎች ለማስጨበጥ ነው ወይስ የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር ታቅደው የተዘጋጁ ናቸው?
8. ለስምንተኛ እና ለሰባተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በቂ ናቸው ብለው ያስባሉ?
9. በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቀዳሚው ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው ዓይነት ሥነጽሑፋዊ ሥራ ነው (ለአጭር ልቦለድ፣ለረጅም ልቦለድ፣ ለግጥም፣ ለተውኔት (ድራማ) ወይስ ከዚህ የተለየ)?
10. በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ (የፈጠራ) ሥራዎችን በመምረጥና በማደራጀት ተግባር ላይ የመርሐትምህርቱ አዘገጃጀት ሁኔታ የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች ካሉ ቢገለጹ?
11. በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ የሚካተቱቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ ከተማሪዎቹ ባህላዊ ፣ ሃይማኖታዊና ሥነልሳናዊ የቋንቋ ግንዛቤ ወይም ክህሎት ጋር እንዳይጋጩ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ?
12. ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የሥነጽሑፍ ወይም የፈጠራ ሥራዎች ምን? ምን? ዓይነት ችግሮች አሉባቸው ብለው ያስባሉ?

# አባሪ 3

## በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ናሙና

3 (ሀ)፡- ከአቶ ስለሺ ኩራ፣ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ መምህርና የደቡብ ክልል የ7ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ ጋር የተካሄደ ቃለ ምልልስ

ጥያቄ 1፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ማካተቱ ምን ፋይዳ አለው ብለው ያስባሉ?

መልስ፡- *እሺ ሥነፅሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች ማቅረቡ አንደኛ ትምህርቱን አጓጊ ሊያደርገው ይችላል። የተለመደ ነገር አይደለም ሁለተኛ በምንፈልገው ማቅረብ የምንችልበት ሁኔታ ይኖራል ማለት ነው። ለዚህ እንጠቀምበታለን እና ክሂሎችን ከማስጠበቅ አኳያ ጥሩ ሚና ይኖረዋል ብዬ አስባለሁ።*

ጥያቄ 2፡- በአንድ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሥነጽሑፋዊ (የፈጠራ) ይዘት ካላቸው ምንባቦች እና ኢልቦለዳዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች ቋንቋን በማስተማር ሂደት የበለጠ ጠቀሜታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን?

መልስ፡- *እሺ ሁለቱም ጠቀሜታ ይኖራቸዋል እንደ ትምህርቱ ይዘት፣ አቀራረብ ማለት ነው። ለምሳሌ የዳሰሳ ንባብ በማድረግ መረጃዎችን ለማሰባሰብ የምንፈልግ ከሆነ በውስጡ ያሉትን መረጃዎች ተማሪዎች ማግኘት እንዲችሉ እነዛም የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። ኢልቦለድ ዕሁፎች ሌሎቹም ሥነፅሑፋዊ ይዘት ያላቸው ደግሞ የራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ ይኖረዋል እና አንዱ ካንዱ የበለጠ ነው ለማለት ትንሽ ያስቸግረኛል እና እያንዳንዳቸው የየራሳቸው የሆነ ጠቀሜታ አላቸው።*

ጥያቄ 3፡- ኢ-ልቦለዳዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦችና ልቦለዳዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች ተማሪች ይበልጥ በንቃትና በጉጉት የሚከታተሉት የትኞቹን ነው? ምክንያቱን ቢገልጹልን?

መልስ፡- *ለልቦለድ ተማሪዎች ትንሽ ለየት ያለ ግምት ይሰጣሉ ምክንያቱም ልቦለድ ዕሁፎች የፈጠራ ሥራዎች ናቸውና ተማሪዎቹ ዋናው መምረጡ ላይ ነው። የሚመረጠው ሰነጽሑፋዊ ወይም ልቦለድ ዕሑፍ ከምንመርጠው የትምህርት ይዘት አንፃር መቅረቡ ነው። ዋናው ልጆቹ ግን የሚሰቡት በልቦለድ ጽሑፍ ላይ ነው። አዎ በቋንቋ አጠቃቀሙም ሊሆን ይችላል እንደገና ደግሞ የፈጠራ ስራ በመሆኑ ብዙ ጊዜ ከህይወታችን ጋር የሚያያዙ ነገሮች ይኖራሉና እኛ የምናቀርባቸው የፈጠራ ስራዎች ግን ለተማሪዎች መጣኝ ከሆነ ያንን ልንረዳ የምንችለው ያ በመሆኑ ይመስለናል።*

ጥያቄ 4፡- ለአንድ የክፍል ደረጃ በሚዘጋጅ የተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ሲመረጡ የመምረጫ መስፈርቱ ምንድን ነው?

*መልስ፡- እሺ ይሄ እንደሚቀርበው የትምህርት ይዘት የሚለያይ ይመስላል ለምሳሌ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ ፈሊጣዊ አነጋገርና ዘይቤያዊ ስናስተምር የምንመርጣቸው ምንባቦች እንደዚሁ የተለያዩ ናቸው እና ለመስፈርቱ ትልቁ ሚና የሚጫወተው የምናቀርበው የትምህርት ይዘት ነው።*

ጥያቄ 5፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከተመረጡ በኃላ እንዴት ይደራጃሉ? የአደረጃጀት ቅደም ተከተል አላቸው ወይስ በአጋጣሚ ነው የሚደራጁት?

*መልስ፡- እሺ ሥነፅሁፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባብ ከመርጥን በኋላ የግድ ሙሉ ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያለውን ምንባብ አይደለም እንትን የምንለው ለማስተማር እንደፈለግነው ለማቅረብ እንደፈለግነው የትምህርት ይዘት ቅንጫቢውን ወስደን ለዛ ስራ እናውለዋለን ማለት ነው። በዛ መልክ ይመስለኛል የምናቀርበው የምናደራጀው። "Ok" እንግዲህ እኛ የምናቀርበው ምንድን ነው መርሐትምህርት አለ በመርሐትምህርቱ ላይ የሚቀርቡ የትምህርት ይዘቶች አሉ እነዛን ሊያግዝ መሣሪያ ማለት እኮ ነው ምንባቡ። እነዛን ሊያግዝ በሚችል መልኩ ነው የምንመርጠው እና ትክክል ነው። ያም ታሳቢ ሊሆን ይችላል አሁን አንተ ያልከው።*

ጥያቄ 6፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች መርጦ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በማካተት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ ቢገልጹልን?

*መልስ፡- አዎ ችግሩ ምንድን ነው የሚመደበው ክፍለ ጊዜና ለማቅረብ የሚፈለገው ነገር ተመጣጣኝ ላይሆን ይችላል። ለምሳሌ አማርኛ ክፍለ ጊዜ በሳምንት ያለው ሁለት ምናልባት ከዚያ በላይ ሦስት ሊሆን ይችላል። እና ይሄንን ለማመጣጠን ትንሽ ችግር አለ በምንፈልገው መጠን ለማቅረብ ችግር ይኖራል ማለት ነው። ችግሩ ክፍለጊዜና ለማቅረብ የምንፈልገው ነገር ያለመጣጠን ይመስለኛል።*

ጥያቄ 7፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች የሚወጡ መልመጃዎች ዓቢይ ዓላማ የሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን ለተማሪዎች ለማስጨበጥ ነው ወይስ የቋንቋ ኪሂሎችን ለማስተማር ታቅደው የተዘጋጁ ናቸው?

መልስ፡- እሺ እዚህ ላይ ያው የቋንቋ ክሂሎቶችን ለማስጨበጥ ነው ዋናው ዓላማ እና ከዚያ በተጨማሪ ሥነጽሑፋዊ ዕውቀቶችን ለማስጨበጥም የምንሄድበት ሁኔታ አለ እና ከነዚህም ጐን ለጐን የምናካሂዳቸው እንጂ ተማሪዎች የሥነጽሑፍ ፀሐፊዎች እንዲሆኑም አይደለም እና ክሂሎችን ለማስጨበጥ አንሣር ነው።

ጥያቄ 8፡- ለስምንተኛ እና ለሰባተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በቂ ናቸው ብለው ያስባሉ?

መልስ፡- እሺ በርግጥ አሁን ጊዜው ረዘም ይላል የሆነው ሆኖ በተቻለ መጠን በቂ ናቸው ብለን እናሳስባለን ሲዘጋጅም ጥድፊያ ስለነበረ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ነው ያዘጋጀነው እና ያም ያም ጭምር ስላለ ያንን ደግሞ ለመመዘን ትንሽ ያስቸግረኛ የሆነው ሆኖ ግን በተቻለ መጠን ጥረት አድርገናል በቂ ናቸው ብዬ አስባለሁ።

ጥያቄ 9፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቀዳሚው ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው ዓይነት ሥነጽሑፋዊ ሥራ ነው (ለአጭር ልቦለድ፣ ለረጅም ልቦለድ፣ ለግጥም፣ ለተውኔት (ድራማ) ወይስ ከዚህ የተለየ)?

መልስ፡- ቅድም እንዳልኩት የምንመርጠው መጽሐፍ በምናዘጋጅበት ጊዜ ለዛ የትምህርት ይዘት ይጠቅማል ብለን የምንወስዳቸው ቅንጫቢዎች ናቸው እና በዚህ ደረጃ ልጆች ግጥምን በግጥም በኩል የራሱ የሆነ እንትን አለ። ልቦለድ ዕሁፎችን እንደዚሁ የራሳቸው እንትን አለ። ድራማን በተመለከተ ግን እዛ ግን በመርሐ ትምህርት ወይ ሊለበስ ግን አላየንም እና እንደ ትምህርቱ ይዘት ነው የምንመርጠው ምርጫችን ማለት ነው እና ሙሉሰራውን ሳይሆን ቅንጫቢውን ነው። ... ግጥም በተወሰነ መልኩ አለው ልቦለድ ጽሑፎች አሉ በአብዛኛው ልቦለድ ፅሑፎች ናቸው እና እኛ የልቦለድ ዕሁፍ ለማስተር ሳይሆን እነዛን ስኪሎች ለማስተማር ጠቃሚ ናቸው ብለን ያስብናቸውን ቅንጫቢዎችን እየወሰድን በረጅም ልቦለድ፣ በአጭር ልቦለድም እየወሰድን ያደራጀናቸው አሉ።

ጥያቄ 10፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ (የፈጠራ) ሥራዎችን በመምረጥና በማደራጀት ተግባር ላይ የመርሐትምህርቱ አዘገጃጀት ሁኔታ የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች ካሉ ቢገለጹ?

መልስ፡- እሺ በመርሐትምህርቱ ሁሉንም እስኪሎች በሚያስጨብጥ መልኩ ተዘጋጅቷል አሁን የተማሪዎቹ ለምሳሌ የ7ኛ ክፍሎች ያሉ ተማሪዎች 5ኛ ክፈል ነው አማርኛ የሚጀምሩት አሁን እኛ ተማሪዎቹ ስናስብና የምናዘጋጀውን መጽሐፍ ስናስብ ጭራሽ የማይሆን ነገር ነው፣ የማይሆን ነገር ነው። የማይጣጣም ዓይነት ነገር ነው ምን ለማለት ነው ተማሪቻው ክ3ኛ ወይም ክ4ኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ስለሆነ ነው የሚጀምሩት እና አሁን እነዚህ ልጆች ከጀመሩ የ3ኛ ክፍል መፅሐፍ እንጂ የአንደኛ መፅሐፍ አይደለም የሚጀምት። ስለዚህ 7ኛ ክፍል ሲደርሱ አሁን እኛ የምናዘጋጀውን የትምህርት ይዘት ምን ያህል ይቀበሉታል የሚለውን ነው አሁን እኛ አዕምሮ ውስጥ የሚፈጠረው ልጆቹን እናቃቸዋለን ምን ደረጃ ላይ እንዳሉ ከአቅማቸው በላይ የሚሆንበት ሁኔታ አለ።

ጥያቄ 11፡- በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ የሚካተቱቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ ከተማሪዎቹ ባህላዊ ፣ ሃይማኖታዊና ሥነልሳናዊ የቋንቋ ግንዛቤ ወይም ክህሎት ጋር እንዳይጋጩ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ?

መልስ፡- በዚህ ላይ አሁን መጽሐፍቱ 2 አመት ሆኖታል ይመስለኛል እስካሁን ወይ መሻሻልም አልተደረገበትም ነገር ግን በተቻለን መጠን ይኼ ከሃይማኖት ነክ የሆኑ ጉዳዮችን እንዳይፈጠር በሃይማኖት በኩል የተማሪዎችን አመለካከት ሊጐዳ በማይችል መልኩ ነው ያዘጋጀነው እና እርግጥ ሲሻሻል ያ ነገር እየተገመገመ እንትን ሊል ይችላል ይሆል ግን እኛ ያንን አድርገናልን ብለን ነው የምናስበው። ከነዚህ ተፅዕኖዎች ውጪ በሆነ መልኩ።

ጥያቄ 12፡- ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የሥነጽሑፍ ወይም የፈጠራ ሥራዎች ምን? ምን? ዓይነት ችግሮች አሉባቸው ብለው ያስባሉ?

መልስ፡- አሁን ካየነው በኋላ እኔ አንዳንድ ችግር አለበት የምለው ነገር ማጠሩ አጫጭር ናቸው እነዛ ምን ያህል ተማሪዎችን የማንበብን አስኬል ከማስጨበጥ አኳያ በቂ ነወይ ሙሉ በሙሉ ሊያሳኩት ይችላሉ የሚለውን ነገር ስናይ እኔ ትንሽ ማጠር ይታይበታል ቅንጫቤዎችን እያሳጠርን ነው ያቀረብናቸው ይህ ዓይነት ችግር አለበት ።

3 (ለ)፡- **ከአቶ ታከለ መኮንን፣ የቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ትምህርት ቢሮ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ኤክስፐርት እና የ7ኛ እና 8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሐፍ አዘጋጅ ጋር የተካሄደ ቃለምልልስ**

ጥያቄ 1፡- **ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ማካተቱ ምን ፋይዳ አለው ብለው ያስባሉ?**

መልስ፡- *ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ያው እንደሚታወቀው አዝናኝ ሳቢ ናቸው ስለዚህ ተማሪዎችን የበለጠ የሚያስባቸው አድርጐ ለማስተማር አላማዎችንም ለማሳካት የበለጠ ጠቀሜታ አላቸው ልቦለድ ሥነቃል ስናካትት ቃላት ምስረታ ይሁን አንብቦ መረዳትን ይሁን ጥያቄዎችን የበለጠ ወደ ቋንቋው ይዘት ስናመጣ ሳቢነት ስለሚኖራቸው ጥሩ ፋይዳ አላቸው ብዬ አስባለሁ።*

ጥያቄ 2፡- **በአንድ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሥነጽሑፋዊ (የፈጠራ) ይዘት ካላቸው ምንባቦች እና ኢልቦለዳዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች ቋንቋን በማስተማር ሂደት የበለጠ ጠቀሜታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን?**

*መልስ፡- በንጽጽር ሁለቱም ጠቀሜታ ይኖራቸዋል። አንዱን ይበልጣል ብዬ ለመወሰን እኔ ይቸግረኛል ይመስለኛል ፈጠራም ይሁን ፈጠራ ያልሆነ ፅሑፎች የየራሳቸው ጠቀሜታ አላቸው ፈጠራም የሆኑ የበጠለጠ ይስባሉ ነው ያልነው በሳቢነታቸው የበለጡ ለመሰለን ይችላል ነገር ግን እንደ እኔ አረዳድ ኢ-ልቦለዳዊ የሆኑትን የቋንቋ አንዱ መልእክት ማስተላለፊያ ጽሁፎች ናቸውና እነሱን ነጥለን የፈጠራዎች ይበልጣሉ ማለት ይቸግረናል።*

ጥያቄ 3፡- **ኢ-ልቦለዳዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦችና ልቦለዳዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች ተማሪች ይበልጥ በንቃትና በጉጉት የሚከታተሉት የትኞቹን ነው ? ምክንያቱን ቢገልጹልን?**

*መልስ፡- ከላይ ከተጠየቀው ጋር ተያይዘው የተመለሱ ስለሆኑ የበለጠ ልቦለዳዊ የሆኑ ይሳባሉ። ሳቢነት ስላላቸው ስለሚያስፈልጉ የበለጠ ተማሪዎች ይከታተሏቸዋል።*

ጥያቄ 4፡- ለአንድ የክፍል ደረጃ በሚዘጋጅ የተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ሲመረጡ የመምረጫ መስፈርቱ ምንድን ነው?

መልስ፡- አንደኛ የተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ ይታያል ተማሪዎች አንብበው ከመረዳት አቅማቸው ጋር ሁለተኛ አጭርም ሆነ ረጅም የፈጠራ ጽሑፎች ካላቸው ጭብጥ አኳያ መንግስት ከሚከተለው ፖለቲካዊ ማህበራዊ የትምህርት ፖሊሲ አንፃር ጠቀሜታ አላቸው ወይ የሚል ታሳቢ የሚደረግ መስፈርቶች አሉ። በዛ መሰረት ነው መርጠን የምናካትተው።

ጥያቄ 5፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከተመረጡ በኃላ እንዴት ይደራጃሉ? የአደረጃጀት ቅደም ተከተል አላቸው ወይስ በአጋጣሚ ነው የሚደራጁት?

መልስ፡- በአጋጣሚ አይሆንም ሲለበሱ አለ የቋንቋው ሲለበስ የ7ኛና የ8ኛ ሲለበሱ በተቻለ መጠን ከቀላል ወደ ከባድ እንዲሄድ የተደረገ ነው። የሚገቡት ሥነጽሑፎች ደግሞ የት ቦታ ላይ ይመጣሉ ቅደም ተከተል አላቸው። እነዚህም ሥነጽሑፎቹ ያሏቸው ፓርት በሙሉ አይወሰድም ከተማሪዎቹ ደረጃ አኳያ የማጣጣም ስራ ይኖራል እንዳለ አንወስደውም በዛ መልኩ ነው

ጥያቄ 6፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች መርጦ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በማካተት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ ቢገልጹልን?

መልስ፡-ያጋጥማል የሚያጋጥመንም ምንድን ነው ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን መጽሐፍት ማግኘት በጣም ከባድ ነገር ነው። የተገኙትንም ቢሆን በተማሪዎች ደረጃ ለማጣጣም አሁን እኛ ጋር ቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል አማርኛ 2ኛ ቋንቋቸው ነው። ስለዚህ ከተማሪዎች ደረጃ ጋር ለማጣጣም ያላቸውን እንዳለ ለመውሰድ እንቸገራለን። ምክንያቱም የቃላት ምርጫ ሁሉ ጠጠር የሚልበት ሁኔታ አለና ያንን እንዳለ መውሰድ አንችልም። ስለዚህ ትንሽ የማጣጣም ስራው ላይ በጣም ችግር አለብን የታወቀ ነው።

ጥያቄ 7፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች የሚወጡ መልመጃዎች ዓቢይ ዓላማ የሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን ለተማሪዎች ለማስጨበጥ ነው ወይስ የቋንቋ ኪሂሎችን ለማስተማር ታቅደው የተዘጋጁ ናቸው?

መልስ፡- በመጀመሪያ ያው አላማ አለን አላማውን ማሳኪያ ይዘት አለን ስለዚህ 7ኛ እና 8ኛ ክፍል ላይ ያሉ ሲለበሶች ስናይ እንደ አላማዎቻችን እንወሰናለን ስነ ጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦችን ቃላትን መጀመሪያ አንብቦ መረዳት Exercise ለመስራት እንጠቀምበታለን የቃላት ተመሳሳይነት ተቃራኒነት የምንለው የቃላት ክምችታቸውን ለማዳበር ፍቺ አሉን ለማስተማር እንጠቀምበታለን፡፡ ከዚያ በኋላ ሲለበሱ ላይ-ያሉት ልቦለድ ሥነጽሑፍ ይዘቶች ሥነጽሑፍ አላማዎች አሉ፡፡ ልቦለድ ምንድን ነው? ሥነጽሑፍ ምንድን ነው ግጥም ምንድን ነው? ወዘተ... ሥነቃልስ የምንለው ለነሱ አላማ ሲባል ይሄ ይገባል የልቦለድ አላባውያን የምንላቸው እሱን ለማሳየት በተለይም ለ8ኛ ክፍል ላይ ይዘቱንም ስላለ... ለሁለቱም ቋንቋ በቋንቋነቱ ለማስተማር ሥነጽሑፎችን እንጠቀማለን ማለትም 4ቱን ክሂሎች እንደዚሁም ሥነጽሑፎቹ ለማስተማር ልቦለድ፣ ኢ ልቦለድ፣ ግጥምና ሥነቃል የምንላቸውን ለማስተማር ማለት ነው፡፡ ሲለበሱን ካላየነው መወሰን ይቸግረኛል ምክንያቱም ሲለበሱ ላይ እንደነገርኩህ ስነ ጽሑፋዊነት በሥነጽሑፋዊነቱ ለማስተማር የራሱ የሆነ አላማና ይዘት አለው፡፡ ሲለበሱ ላይ 7ኛ እና 8ኛ መነሻ ሲለበሱ ነው፡፡ ገገርው እሱ ነው፡፡

መልስ 8፡- ለስምንተኛ እና ለሰባተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በቂ ናቸው ብለው ያስባሉ?

መልስ፡- አሁን ባለፈው ባሻሻልናቸው መጽሐፍ በቂ ነው የሚል ግንዛቤ አለኝ ምንድን ነው የደረግነው ስናዘጋጅ በመጀመሪያ ለሲለበሱን እና ነባር መጽሐፍቶቻችንን ይዘን ቁጭ ብለን ከመምሕራን ጋር ከሚያስተምሩት የየክፍሉ መምህራን ጋር ቁጭ ብለን ምን ያህል የዱሮዎቹ መጻሕፍቶች ላይ ምን ያህል ልቦለድ ይሁን ሥነጽሑፋዊ የሆኑ ስራዎች ኢ ልቦለዳዊ የሆኑ ምን ያህል ምንባብ አለ ግጥም ምን ያህለ አለ የሚለውን ለማየት ሞክረናል ያን ከዳሰስን በኋላ ነው አዘጋጆች ወደ ስራው ሲገቡ በተወሰነ መልኩ ለማጣጣም የምመክረው አሁን ቁጥራቸውን መጥቀስ ይከብዳል እንጂ... መምህራን ተሳትፈዋል፡፡

ጥያቄ 9፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ ከተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ቀዳሚው ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው ዓይነት ሥነጽሑፋዊ ሥራ ነው (ለአጭር ልቦለድ፣ ለረጅም ልቦለድ፣ ለግጥም፣ ለተውኔት (ድራማ) ወይስ ከዚህ የተለየ)?

*መልስ፡- መጀመሪያ ለግጥም ከዚያ አጭር ልቦለድ አለ ረጅም ልቦለድ ብዙም አይደለም አሉ ግን ብዙም አላካተትንም ተረት ለዚህ ደረጃ ብዙም ስላልሆነ 7ኛ እና 8ኛ ደረጃቸው ትንሽ ክፍ ያለ ስለሆነ ብዙም አልሄድንበትም - በተረት ላይ*

ጥያቄ 10፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ (የፈጠራ) ሥራዎችን በመምረጥና በማደራጀት ተግባር ላይ የመርሐትምህርቱ አዘገጃጀት ሁኔታ የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች ካሉ ቢገለጹ?

*መልስ፡- የመርሐ ትምህርቱ አዘገጃጀት ልክ ነው አዎንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ ይኖረዋል ቅድም እንደገለጽኩት የአሁኑን አላወቅንም ከዚህ በፊት የነበረው የተሻሻለ መርሐ ትምህርት እነዚህን ስነ ጽሁፋዊ ይዘቶችን እንዲያካትት ትኩረት ተሰጥቶታል። ማሻሻል ሂደቱ ላይ እኔ አራሴ የመርሐ ትምህርት ማሻሻዮች ላይ አብሬ ተሳትፌ ነበር። ICDR ጋር ስለዚህ የተቻላቸውን ያህል ትኩረት ተሰጥቶታል።*

ጥያቄ 11፡- በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ የሚካተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ ከተማሪዎቹ ባህላዊ ፣ ሃይማኖታዊና ሥነልሳናዊ የቋንቋ ግንዛቤ ወይም ክህሎት ጋር እንዳይጋጩ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ?

*መልስ፡- በጽንሰሃሳብ ደረጃ የመማሪያ ማስተማሪያ መጽሐፍት ስናዘጋጅ የሚመረጡት ምንባቦች ኢልቦለዳዊ የሆኑ ልቦለደዊ ስነ ጽሁፍ እንደእነዚህ አሁን ላልካቸው ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ስነ ልቦናዊ ቋንቋዎች ግንዛቤ ያው ትኩረት ይሰጣል የተቻለውን ያህል ትኩረት አለ። ምናልባት ካመለጠን በኋላ ይኖራል አይካድም ግን በማሻሻል ይሰራል መልሶ ይካሄዳል መምህራን ፊድ ባክ ይሰጡታል። መጽሐፍ ላይ ተማሪዎች ወላጆችም እና የቻልነውን ያህል ባህልን ለመጠበቅ ሞክረናል ሃይማኖት እንደዚሁ ሥነልሳናዊ ቅድም ገልጫለሁ። አማርኛ 2ኛ ቋንቋቸው ነው ስለዚህ ተማሪዎች በአብዛኛው አምስት ነባር ብሔረሰቦች ናቸው ያሉት። እዚህ አሶሳ አካባቢ አፍ መፍቻ የሆነ ነባር ያልሆነ ብሔረሰብ ስላለ ስለዚህ እንደ*

2ኛ ቋንቋቸው ለማዘጋጀት ጥረት አድርገናል። ----- ቋንቋቸው በርታ የሚባል ብሔረሰብ አለ በርትኛ ነው ቋንቋቸው ጉሙዝ ብሔረሰብ አለ ጉምዝኛ ነው። ሺናሻ የምንላቸው ብሔረሰቦች አሉ ሺናሽኛ ነው። ማአ ማአኛ ኩመ ኩመኛ የምንለው 5 ቋንቋዎች ናቸው ያሉት። ሲለበሱ ሁለት ሲለበስ ነው ያለው አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ እና አማርኛ እንደ 2 ቋንቋ ሁለት ሲለበሱ አሉ 7ኛም 8ኛም ከ3 እስከ 8 ክፍል ይመስለኛል ካልተሳሳትኩ እና እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የምንለውን መጽሐፉን ስናዘጋጅ እንጂ ጽንሰ ሀሳቡን የተጠቀምንባቸው እንዳ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ነው። ምክንያቱም ምንድን ነው በኛ ክልል ላይ አማርኛ የስራ ቋንቋ ነው እስከ አሁን የነባር ብሔረሰቦችን ቋንቋ ተጠንተው የመማሪያም ቋንቋ አልሆኑም ትምህርት አይነቶቹም እራሱ እንደ ትምህርት አይነቱን መስጠት የተጀመረው ከ2 ዓመት በፊት ነው። ሁሉም አልተጠናቀቁም የተወሰኑ ቋንቋዎች አሁን በመከራ ላይ ነው ያሉት ስለዚህ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ሲማሩ የነበረው በአማርኛ ቋንቋ ስለነበር ከ1ኛ ክፍል ጀምሮ ስለሆነ በሚሰጣቸው ልክ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ ሊለበስ እንጠቀማለን ነገር ግን ዝግጅቱ ላይ ቅድም እንዳልነው ምን ያህል ይረዱታል የሚለውን እንደ 2ኛ ቋንቋ ተከትለን የምንሄው። አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ የሚለውን ነው የተጠቀምነው መጽሐፍ ዝግጅተ ላይ ግን ምንባባችን ስንመርጥ ምን ያህል ይረዳቸዋል የሚለውን ግንዛቤ እናስገባለን ..... ምክንያቱም የትምህርት መስጫው እና የስራ ቋንቋቸው የክልሉን ነባር ብሔረሰቦች ቋንቋ ሆኖ ቢኖር የግድ አማርኛ እንደ 2ኛ ቋንቋ የሚጀመረው ከ3ኛ ክፍል ጀምሮ ስለዚህ በዛ መሰረት መጓዝ እንችል ነበር። እንደጠቀስኩት ምክንያቶች ምንድን ነው የሥራ ቋንቋ በመሆኑ ተማሪዎቹ ሌሎች የትምህርት አይነቶችን ከ1ኛ እስከ 8ኛ ሲማሩ የነበረው በአማርኛ ነበር አሁን ግን ከ5 እስከ 8 በእንግሊዘኛ ተደርጓል። ከ2 አመት በፊት ጀምሮ ... ስለዚህ ሌሎች ትምህርቶችንም መማር እንዲችሉ ከ1ኛ ክፍል ጀምረን ነው ምክንያቱም አንድ እና ሁለት የአፍ መፍቻ አማርኛ እንደ 2ኛ የሚል የለም። ሲለበስ 3ኛ ክፍል ስለሚጀምር ስለዚህ የግዴታ አማርኛ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋ የሚለውን እንድንጠቀም አስገድደናል።

ጥያቄ 12፡- ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የተካተቱት የሥነጽሑፍ ወይም የፈጠራ ሥራዎች ምን? ምን? ዓይነት ችግሮች አሉባቸው ብለው ያስባሉ?

መልስ፡- መጽሐፎችን አዘጋጅተን ከጨረስን በኋላ የመፅሐፍቶችን ለማዘጋጀት መጀመሪያ ሊለበሱንና ነባር መፅሐፍቶቻችን በስራ ላይ የነበሩትን መጽሐፍ ከመምህራኖቻችን ጋር ቁጭ ብለን ክልል ውስጥ ካሉ መምህራን ጋር ከየት/ቤቱ አንድ አንድ መመህር ይዘን ክፍተታቸውን ለማየት ሞክረናል በዛ መሠረት ይሄ እንዲሻሻል ይሄ እዚህ ቦታ እንዲደረግ የሚለውን ሲለበሱን ጋር ይዘን ቁጭ ብለን ካየን በኋላ ነው ዝግጅቱን ያጠናቀቅነው ካዘጋጀንም በኋላ ክልሉ በጣም ወደ ኋላ ቀርቶ ስለነበር በማሻሻል ሂደቱ በቀጥታ ነው ወደ ስራ እንዲገቡ የተደረገው ከዚያ በኋላ ግን አስተያየቶች ይሰባሰባሉ ነገር ግን የስራ መደቡ ስለለቀኩኝ ብዙም information የለኝም እንደነገርከሀ አሁን የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ክፍተኛ ኤክስፖርት ነኝ ቀደም ሲል የቋንቋ ባለሙያ አማርኛ ላይ ነበር የምሰራው ነገር ግን ወደ ስራ እንደገቡ አንዳንድ አስተያየቶች ከመመህራን ነበሩ በየስራው አጋጣሚ ትንሽ አንዳንድ የሚከብዱ ቃላት አሉ ለዚህ ክልል ጠጠር የሚሉ ይገኛሉ ግን መጨረሻ ላይ በግሎሠሪነት ፍቺ ለማስቀመጥ ሞክረናል ከዚያ ያመለጡ ቃላት የሚከብዱ ይናራሉ። በተረፈ ግን የቀረ ዝርዝር የቀረበ አስተያየት ሊኖር ይችላል እኔ ጋር አሁን ያለኝም ምክንያቱም የስራ ዘርፍ ቀጥታ ከተጋራ የሚያገናኘን ስላልሆነ። ይሄ እንግዲህ መምሪያው ጋር ይመስለኛል የበለጠ መረጃ ልታገኝ የምትችለው የስርዓተ ትምህርትን ዝግጅት ጥናትና ምርምር መመሪያ የቋንቋ ባለሙያ አለ እዛ ጋር ምን እንደታሰበ አላውቅም በፊት በነበረው አሠራር ግን እንዳልከሀ በተቻለ መጠን መሐከለኛ እንዲሆን ነው የሞከርነው ምክንያቱም አሶሳ አካባቢ የተወሰነ ነባር ብሔረሰብ ቢኖርም ከሰፊራ አካባቢ የመጣ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ የሆነ አለ ፓዌ የምንለው አፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ የሆነ አለ ከዛ ውጪ ያሉት ግን ወረዳዎች በሙሉ አማርኛ ሁለተኛ ቋንቋቸው ነው ስለዚህ አብዛኛው የት ጋር ነው የሚያርፈው የሚለውን ለማየት ሞክረን ነው ለማዘጋጀት የሞከርነው ሁለቱንም ለማየት ሞክረናል ዝግጅቱ ላይ ያልከሀ ለዛ ነው። አማርኛ እንደ ሁለተኛ አማርኛ እንደ አንደኛ እንደ አፍ መፍቻ የሚለውን ለማየት የሞከርነው ምን ታስቧል የሚለውን እንግዲህ አላወከትም።

## 3 (ሐ)፡- ከወ/ሮ ሸዋዬ ተፈራ፣ የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህርት እና የደቡብ ክልል የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ አርታኢ ጋር የተካሄደ ቃለምልልስ

ጥያቄ 1፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ምንባቦች በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ማካተቱ ምን ፋይዳ አለው ብለው ያስባሉ?

*መልስ፡-ሥዕሑፋዊ ይዘት ያላቸውን ለሥነጽሑፋዊ ስንል ወደ ኢ-ልቦለድ፣ ግጥም፣ አጫጭር ልቦለዶች፣ ተረቶች እነዚህን ያካትታል እና በደረቅ ሁኔታ ከሚቀርብ ይልቅ እያዝናና የተሻለ ትምህርት በዚህ መንገድ ቢቀርብላቸው በተሻለ መንግድ ይገነዘቡታል የሚል ነገር አለኝ።*

ጥያቄ 2፡- በአንድ የመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ሥነጽሑፋዊ (የፈጠራ) ይዘት ካላቸው ምንባቦች እና ኢልቦለዳዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች ቋንቋን በማስተማር ሂደት የበለጠ ጠቀሜታ ያላቸው የትኞቹ ናቸው? ለምን?

*መልስ፡- እኔ እንግዲህ የፈጠራ ይዘት ያለው የተሻለ ነው የልብወለድ ያነሰ ነው የሚል ነገር የለኝም። በተመጣጠነ መልክ ቢቀርብ የኢ-ልብወለድ እንደ ኢ-ልብወለድ የፈጠራም እንደ ፈጠራ ጽሑፍነት ተመጣጥኖ ቢቀርብ የተሻለ ይመስለኛል . . . በዚያ መልክ ሊረዱ ስለሚችሉ።*

ጥያቄ 3፡- ኢ-ልቦለዳዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦችና ልቦለዳዊ ይዘት ካሏቸው ምንባቦች ተማሪች ይበልጥ በንቃትና በጉጉት የሚከታተሉት የትኞቹን ነው ? ምክንያቱን ቢገልጹልን?

*መልስ፡- ለነገሩ እንግዲህ ኢ-ልቦለድም ሆኖ አንዳንድ ወቅታዊ ጉዳዮች የሚያነሱ ምንባቦች አሉ ሆኖም ለምሳሌ በአሁኑ ሰለ "HIV AIDS" የሚገልፅ ኢ-ልቦለድ ፅሁፎችን በጣም ስሜታዊ ሆነው ሊከታተሉ ይችላሉ። በሌላም በኩል ደግሞ በፈጠራ ድርሰት እንደዚህ ሲሆን የበለጠ ከኢ-ልቦለድ ... ደረቅ ከሚይዝ ይልቅ ወደ ኢ-ልቦለድ ሊያመዝኑ ይችላሉ ኢ-ልቦለድ ሆኖም ግን ወቅታዊ፣ አጓጊና የሚያነሳሳ አፃፃፍ በሚሰብ መልኩ ከቀረበ በደንብ ሊከታተሉ ይችላሉ።*

ጥያቄ 4፡- ለአንድ የክፍል ደረጃ በሚዘጋጅ የተማሪዎች የመማሪያ መጽሐፍ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ሲመረጡ የመምረጫ መስፈርቱ ምንድን ነው?

መልስ፡- እኔ እንግዲህ የሚመስለኝ የልጆቹ የትምህርትና የዕድሜ ደረጃ በዛ የሚወሰን ይመስለኛል አንድ ለምሳሌ 11ኛ ና 12ኛ ክፍል ላለ ተማሪና ለ5ኛ እና 6ኛ ክፍል ላለ ተማሪ የምታቀርበው የልቦለድ አይነት፣ የግጥም አይነት ይለያያል ይዘቱ እና በትምህርትና በዕድሜ ደረጃ ሊወሰን ይችላል። ... ታሪኩ ራሱ በዕሁፍ የሚተላለፈው ከነሱ ጋር ምን ያህል ይመጥናል።

ጥያቄ 5፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች ከተመረጡ በኋላ እንዴት ይደራጃሉ? የአደረጃጀት ቅደም ተከተል አላቸው ወይስ በአጋጣሚ ነው የሚደራጁት?

መልስ፡- እንግዲህ መፅሐፍት ሲዘጋጅ ሲለበስ አለው በእያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት ዝርዝር ዓላማ አለው ዝርዝር ይዘት አለው በዚያ በይዘቱና በዓላማው መሰረት ዝርዝር ዓላማውን ሊያሳዩ የሚችሉ ሥነፅሑፋዊ ይዘት ያላቸው ኢ-ልቦለድ ሲሆን በዚያ መሰረት የሚመረጠው ሲለበሱ ላይ በሲለበሱ መሰረት የሚያስፈልግ ከሆነ ልቦለድ ኢ-ልቦለድ በቅደም ተከተል ማደራጀት የሚለው ነገር በአዘጋጅነትም፣ በኤዲተርነትም ሰሰራ ብዙም እንትን አልልም የምናየው ሲለበሱን ነው ሊለበሱ ውስጥ ይዘት አለ ዓላማ አለ ያንን ይዘት ዓላማ ሊያሳካ የሚችሉ ንባብ ነው የምንመርጠው።

ጥያቄ 6፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባቦች መርጦ በመማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በማካተት ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮች ካሉ ቢገልጹልን?

መልስ፡- እንግዲህ አሁን ብዙ ጊዜ መፅሐፍትን ስታነብ አይተህ ከሆነ ለደረጃው በሚመጥን መልኩ ተስተካክሎ የዘጋጀ የሚል ማስታወሻ በስሩ ይቀመጣል። ያ ማለት አንዳንድ ጊዜ ማስተካከያ ይደረጋል። አንዳንድ ጊዜ ቃላቱ በጣም የጠጠረ ውስጡ ያለው ታሪክም ቢሆን ለልጆቹ ትንሽ የማይመጥን ዓይነት ሲሆን። ይህ በሥነጽሑፋዊ ብቻ ሳይሆን በኢልቦለድ ውስጥ ያለ ነው እና ለዚህ ደረጀ ይመጥናል ተብሎ በአዘጋጅ እንደሚመች ተደርጎ የማሳጠር የማስተካከል ነገር አለ መሰረታዊ ሀሳቡን ሳይለቅ ማለት ነው። . . . እንግዲህ አዎ ስታዘጋጅ ብዙ ታነባለህ፣ የተለያዩ ተረቶችን፣ የልቦለዶች መጻሕፍት፣ ብዙ ሰው መጠይቅን፣ ላይብረሪ ገብቶ መፅሐፍት ማገላበጥን፣ ጋዜጣ ማንበብን ይጠይቃል። ጥረት ካደረክ ይገኛል መፅሐፍ ለማዘጋጀት ጥረት ማድረግ አለብህ።

ጥያቄ 7፡- ሥነጽሑፋዊ ይዘት ካላቸው ምንባቦች የሚወጡ መልመጃዎች ዓቢይ ዓላማ የሥነጽሑፋዊ ዕውቀትን ለተማሪዎች ለማስጨበጥ ነው ወይስ የቋንቋ ኪሂሎችን ለማስተማር ታቅደው የተዘጋጁ ናቸው?

መልስ፡- ለማዘጋጀት መሰረቱ መነሻው ሲለበሱ ነው። ሲለበሱ ላይ ለምሳሌ ክፍለ ትምህርት አንድ ልጆች ስለግጥም ባህሪያት ስንኝ ወይም ሐረግ ያውቃሉ የሚል ነገር ከተቀመጠ እዛ ጋር የምንዕፈው ስነጽሑፋዊ ይዘት ያላቸው ምንባብ ስንኝን ሐረግን እናስተምርበታለን። ባጠቃላይ ግን ከሥነጽሑፋዊ ይዘት ውጪ ቋንቋን ማስተማር ከሆነ ቋንቋን ብቻ ነው በምንባቡ አማካኝነት የምናስተምረው ይሄን የሚወስነው ሲለበሱ ነው በሲለበሱ ላይ ስለግጥም መማር አለባቸው ከተባለ ባቀረበው ግጥም አማካኝነት ስንኝነት ሐረግን ሌላም ነገር ሊማሩ ይችላሉ። በሊለበሱ ላይ እዚህ ክፍለ ትምህርት ላይ ስለልቦለድ አላባውያን ይማራሉ የሚል ካለ በቀረበው ልቦለድ አማካኝነት የልቦለድ አላባውያንን እናስተምራለን እና የሚመራን ሲለበሱ ነው።

ጥያቄ 8፡- ለስምንተኛ እና ለሰባተኛ ክፍል በተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ ከተካተቱት ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በቂ ናቸው ብለው ያስባሉ?

መልስ፡- አዎ ቅድም እንዳልኩህ እንግዲ ለዚህ ቃለመጥይቅ ቀደም ብዬ ተዘጋጅቼ ቢሆን ኖሮ ላያቸው እችላለሁ ግን ገም ብለህ ስታያቸው እዚህ ጋር ብዙ ልቦለድ አለ ለምሳሌ ደፋሩ፣ አሸብር ወ.ዘ.ተ የፈጠራ ስራዎች ናቸው የሥነጽሑፍ ይዘት ያላቸው ናቸው መመጣጠን አለባቸው የኢልቦለድ መብዛት አለበት የሚሉት ላይ በአሁኑ ዘመንና ሰዓት ያሉ ተማሪዎች ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው እንትን ያንሳል አነስተኛም ነው በደረቅ እውነታን ከምታስተምራቸው ይልቅ በፈጠራ መልክ ኢልቦለድ፣ ልቦለድ ስነግጥም የመሳሰሉትን በዛ መልክ ቢመራ የተሻለ ይሆናል ብዬ ነው የማስበው። መመጣጠን ጥሩ ነው።

ጥያቄ 9፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚካተቱትን ሥነ ጽሑፋዊ ሥራዎች ቀዳሚው ትኩረት የተሰጠው ለየትኛው ዓይነት ሥነጽሑፋዊ ሥራ ነው (ለአጭር ልቦለድ፣ለረጅም ልቦለድ፣ ለግጥም፣ ለተውኔት (ድራማ) ወይስ ከዚህ የተለየ)?

መልስ፡- በአብዛኛው እዚህ ጋር እንደምናየው በአጭር ልቦለድ ነው። ረጅም ልቦለድ ለመጽሐፍም አይመችም መጠኑም አይመችም አብዛኛው አጭር

ልቦለድ ነው። ... እንግዲህ አምን ረጅም ልቦወለድ አንብበህ ለመፅሐፍ ዝግጅት በሚመች መልክ ለማሳጠር ጊዜ፣ ጉልበትን የሚወስድ ነው። አጭር ልቦለድ ከሆነ ግን ሶስት፣ አራትና አምስት ገፅ አንብበህ ለክፍል ደረጃው በሚመጥን በማሳጠር ብዙ የሚከብድ አይደለም። ከዚህ አንፃር ይመስለኛል ብዙ ጊዜ መፅሐፍ ሲዘጋጅበተለይ በነዚህ በአንደኛ ደረጃ ላይ ረጅም ልቦለዶች አይታይም። አጭር ልቦለዶች ናቸው። ረጅሙን ልቦለድ በሁለት እና ሦስት ገፅ አሳጥረህ ለማስቀመጥ አዘጋጅ ስትሆን ጥረት ይጠይቃል። ይህኛውን ግን በቀላሉ አሳጥረህ በሚመጥን መልክ ማስቀመጥ ትችላለህ ምናልባት እሱ ይመስለኛል።

ጥያቄ 10፡- በመማሪያ መጻሕፍቱ ውስጥ የሚካተቱን ሥነጽሑፋዊ (የፈጠራ) ሥራዎችን በመምረጥና በማደራጀት ተግባር ላይ የመርሐትምህርቱ አዘገጃጀት ሁኔታ የሚያስከትላቸው አሉታዊ ተፅዕኖዎች ካሉ ቢገለጹ?

መልስ፡- አምን ብዙ ጊዜ መፅሐፍት ሲዘጋጅ የምናየው ችግር ምንድን ነው አሁን ይሄ ነገር ለደረጃ ይመጥናል ወይ እነዚህ ልጆች በዚህ ቢማሩት ይገባቸዋል፣ ይችሉታል ወይ? የሚለውን አልፎ አልፎ የምንነጋገርበት ነው በአብዛኛው ግን ከላይ ተዘጋጅቶ የመጣ ሊለበስ ስለሆነ በመርሐትምህርቱ መሰረት ነው። እኛ የምናዘጋጀው ነገር ግን አልፎ አልፎ የሄ ይዘት እዚህ ጋር ከበደ የሚል ነገር ስንሰራ እንነጋገራለን ከፍ ባለ ትምህርት ደረጃ የሚማሩት ወረደ የሚል ነገር አለ። ... እንግዲህ ቅድም እንዳልኩህ በዚህ ደረጃ መማር የሌለባቸው ነገር ለምሳሌ የ7ተኛ ወደ 8ተኛ ወደ 6ተኛ መሄድ ነበረበት የሚል ነገር አለ። ከዛ ውጪ ግን አንድ መፅሐፍ አዘጋጅ ሲያዘጋጅ መሠረት የሚያደርገው መርሐትምህርቱን ነው። ከመርሐትምህርቱ ውጪ ከሄደክ ኤዲተሩም እሺ አይልም ምክንያቱም ሄዲት ስታደርግ መነሻ የምታደርገው መርሐትምህርቱን ነው። መርሐትምህርቱ ላይ የሌለ ነገር እዚህ ጋር ተጽፎ ብታይ የሌለ ነገር ለምን ተፃፈ እንደገና የተፃፈ ነገር እዚህ ጋር ከተዘለለ መርሐትምህርቱን እና መነሻዎችን መርሐትምህርቱን ነው ከዚያ ውጪ ለመሄድ አይቻልም።

ጥያቄ 11፡- በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ የሚካተተቱ ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች ሲመረጡ ከተማሪዎቹ ባህላዊ ፣ ሃይማኖታዊና ሥነልሳናዊ የቋንቋ ግንዛቤ ወይም ክህሎት ጋር እንዳይጋጩ ምን ያህል ጥንቃቄ ታደርጋላችሁ?

መልስ፡- አዎ እንደ አዘጋጅም እንደ ኤዲተርም ሆነህ ስታየው በጣም ነው ጥንቃቄ የሚደረገው። ለምሳሌ ስዕሎች ላይ ራሱ ሃይማኖታዊ ነክ የሆኑ ስዕሎችን ላለማውጣት በጣም ይጠነቀቃሉ። ሊያዘጋጁም ኤዲተሮችም ያያሉ። የባህል የሃይማኖት ተፅዕኖ እንዳይኖር በጣም ነው ጥንቃቄ የምናደርገው። የቃላት አጠቃቀም ሁሉ በዚህ ደረጃ ይሄን ቃል ማስቀመጥ አግባብ ነው ወይ ይሄንን ቃል በዚህ ቃል ቢተካ አይሻልም ወይ የሚል አሰተያየት ይሰጣል እና በጣም በጥንቃቄ የሚሰራ ነገር ይመስለኛል በዚህ ዙሪያ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ ቋንቋ ግንዛቤና አቅም በሚለው በጣም በጥንቃቄ የሚሰራ ይመስለኛል።

ጥያቄ 12፡- ለሰባተኛ እና ለስምንተኛ ክፍል በተዘጋጁት የተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጸሕፍት ውስጥ የተካተቱት የሥነጽሑፍ ወይም የፈጠራ ሥራዎች ምን? ምን? ዓይነት ችግሮች አሉባቸው ብለው ያስባሉ?

መልስ፡- ይሄን ጥያቄ ሳስበው ለኔ እንደ ሄዲተር ወይም እንደ አዘጋጅ እኔ መጠየቅ ያለብኝም አይመስለኝም። ምክንያቱም መፅሐፉን አሁን እንዳልከው ሁለተኛው መንገድ ነው የኛ credit የሚሆነው መፅሐፉ ይዘጋጃል ክለል ት/ቤሮ የቋንቋ ዘርፍ ባለሙያ አለ የሚችለውን ያክል አስተያየት ይሰጥበታል፣ ይስተካከላል ከዚያ ወደ ህትመት ነው የሚሄደው feedback ከመምህሩ ከተማሪው ከተወሰነ ዓመት በኋላ ነው። እና ከተወሰነ ዓመት በኋላ ደካማ ጐን ጠንካራ ጐን የምናየው እኛ አይደለንም። የሚመለከተው አካል ነው። እኛ ለመጀመሪያ ጊዜ አዘጋጅተናል በዚህ መፅሐፍ ላይ ምን ምን ጠንካራና ደካማ አለው የሚለውን ነገር ቀጣይ ስራ ነው የሚመለከተው አካል አዘጋጅን ኤዲተሩ ሄዲት አደረገ፣ የሚመለከተው ክፍል አየውና አፅድቆት ለህትመት በቃ አሁን በዚህ መፅሐፍ ላይ ምን አይነት ችግር ነበረው የሚለውን እኔ አሁን ለመመለስ ትንሽ ያስቸግረኛል። በስራ ላይ ውሎ የታየበት ድክመት የቱ ጋር ነው የሚለውን እኔ አውን አላውቅም ምናልባት ግን እንደገና ሲታተም የሰሩት ሰዎች ድጋሚ ታትሞ ከሆነ አላውቅም እነሱ ናቸው የሚያውቁት።

## ስርቅታ

ይሁን በፍቃዱ፡ አባ፡ አለም፡ ለምኔን፡ እያሜወተ፡ እቤቱ፡ እንደደረሱ ከበቅሎ ሲያወርዳቸዉ፡ "እባክዎ፡ ቶሎ፡ ትንሽ፡ እህል፡ እንድቀምስ፡ ያድርጉኝ፡ በጣም ርቦኛል!" አሉ መነኩሴዉ የእዉነተኛ ስሜታቸዉን ለቀፎ አዉራጆች ባለመንገራቸዉ የተቀጡት ብርቱ ቅጣት ይሉኝታ የሚባለዉን ጥፋት እንዳደግሙ አስተምሯቸዉ::

"ቶሎ፡ እህል፡ ቶሎ፡ እህል!" አለ ይሁን በፍቃዱ ሚስቱ መምጣቱን አዉቃ ልትቀበለዉ እየሮጠች ስትመጣ::

የይሁን ባለቤት ባልዋ የሚመጣበትን ጊዜ ካለማወቋም ሌላ የምሳ ሰዓት አልፎ የራት ጊዜ ሳይደርስ አጉል ላይ እንግዳ ይዞ መምጣቱ ትንሽ ተደነጋገራትና በስራት የተሰናዳ ነገር የለም፣ የዋለ እንጀራ በተልባ ወይም፡ በእርጎ ይሆናል? " አለች እንግዳዉ እንዳይሰሙ ቀስ ብላ በጆሮዉ::

"ወጥ ገና አልተሰራም፡ አሉ አባቴ! እንጀራ በተልባ ወይም በዕርጎ ወይም ተልባና ዕርጎ አንድ ላይ ሆኖ በሻርዴ ቀምሰዉ ቢቆዩ ምን አለ? " አለ ይሁን::

"ሻርዴ? ጥሩ ነዉ እንጂ! ማንኛዉም ቢሆን ጥሩ ነዉ!

ራብ ባለበት ምርጫ አለ? ምርጫ ራብ ሳይኖር ነዉ! ምርጫ ምሳ በልቶ ራት ለደገመ ለተመቸዉ ሆድ ነዉ:: ራብ በስለት ለሚዘለዝለዉ ለሚያባጥለዉ ሆድ ዋና ምርጫዉ ቶሎ ተገኝቶ ራብን የሚያስታግስ፣ ትንሽ የሚያስተነፍስ ነገር ነዉ:: ከራብ ስቃይ የሚያሳርፍ፣ የራብን ስለት ጥርስ፡ የሚያጎለድፍ ከሆነ ማናቸዉም ቢሆን ጥሩ ነዉ::

ይሁን በፍቃዱ በቅሎዋን አራግፎና አስሮ ድርቆሽ ጥሎላት እስኪመለስ ሚስቱ ተልባዉን በዕርጎ መትታ ሻርዴ ካደረ እንጀራ ጋር ለመነኩሴዉ አቅርባላቸዉ ሲበሉ ደረሰ:: የይሁን ባለቤት ሁለት እንጀራ በትንሽ ሌማትና ሻርዴዉን አቅርባ እያወጣች ልትጋብዛቸዉ መጥታ እመነኩሴዉ ፊት ለፊት ስትቀመጥ በማመስገን፡ ፈንታ፡ ልባቸዉ ረገማት፤ በመዉደድ፡ ፈንታ፡ ጠሉዋት::



ያንጊዜ አባ አለም ለምኔ እንዲያ እርቧቸዉ ሳለ፤ እንዲያ እህል ሁለ የማይበቃቸዉ መስሏቸዉ ሳለ የተመኙት በርከት ያለ እንጀራ በምንም አይነት ወጥ አቅርቦ እጃቸዉ መቁረስ አፋቸዉ መጉረስ የሚችለዉን ያህል ቶሎ ቶሎ በልተዉ እራባቸዉን እንዲያስወግዱ ቤቱን የኋሊት ዘግቶባቸዉ የሚሸሽ ነዉ እንጂ ሁለት እንጀራ አቅርቦ እሱንም እንዴት እንደሚያጎርሱት እፊታቸዉ ተቀምጦ የሚመለከት ታዛቢ አልፈለጉም ነበር::

"ጠላ ልሰጥዎ ወይስ ወተት?" አለች ባለቤትዋ መበያዉን ካወጣችላቸዉ በኋላ::

"ወተት!" አሉ አባ ቶሎ ብለዉ:: ዋናዉ ነገር ቶሎ ከፊታቸዉ እንድትሄድ ነበር::

ወተት : ከጓዳ፡ ይዛላቸዉ፡እስክትመጣ አራት አምስት ጉርሻ በርከት እያደረጉ ጎርሰዉ ብዙም ሳያላምጡ የዋጡት የእህል ናፍቆታቸዉን ትንሽ መለስ አደረገላቸዉ:: በዚያ ላይ ከወተቱ ግማሹን ያክል እንደጠጡ ትንሽ በልተዉ አንዱን እንጀራ እንኳን ሳይጨርሱ ያ ሲቀርብ አንሶ የታያቸዉ እንጀራ በዝቶ አሸነፋቸዉ:: ወዲያዉ ራቡ ሲያልፍ እንቅልፍና ድካም አንድ ላይ ሆነዉ ያንገላቷቸዉ ጀመር:: መጨረሻ የጎረሱት ባፋቸዉ እንዳለ አንገታቸዉን ደፍተዉ ባፍንጫቸዉ ማንኩዋረፍ ስለጀመሩ ይሁንና ባለቤቱ በግድ ቀስቅሰዉ የጎረሱትን እንዲዉጡ አደረጉና እዚያዉ በተቀመጡበት ትራስ አምጥተዉ አጋደሟቸዉ::

"እንዲህ ሆነዉ የተኙተ እንቅልፍ ፣እረፍትም አይሆናቸዉ::" አለ ይሁን::

"እንዴት?"

" እግራቸዉ የተሸከመዉን አታይም? ይህን በደም፣ ባፈር፣ባሸዋ ጭምር የተመረገ ዳባ በእግራቸዉ ተሸክመዉ የተኙት እንቅልፍ የሚያሳርፍ ነዉ:?"

"ታዲያ ዉሃ ላመ·ቅና ልጠባቸዉ?"

"ቀዝቃዛ ነዉ እንጂ መ·ቅ ዉሃ አያነቃምኮ"

" እንግዲያዉስ አመ·ቂና እጠቢያቸዉ::"

ይሁን በፍቃዱ የመነኩሴዉን እግር በዳባ ተጠቅልሎ ከታሰረበት ሲፈታዉ በደም፣ ባፈር፣ ባሸዋ የተጨማለቀ ባዳ ከዉጭ እንደሚያሳየዉ የሚያስፀይፍና የሚያስፈራራ አይደለም:: እሾህና ጋሬጣ የወጣለት ከነደመ ፣ ያልወጣለት ከነጋሬጣዉና ከነሾሁ እንዳበጠ ይሁን እንጂ መልካም እግር የነበረ ለመሆኑ ምልክቱ አልጠፋም:: ይልቁንም የረጋዉ ደም ከሳዩ እያታጠበ በጠራ መጠን መልኩምክቱ ደህና ሆኖ እየታየ ሄደ::

" ዉዉዉ .... እባክህ ይህን እግር እይልኝ! አዬህ?! አሁን ይህን እግር ይዞ ገዝ ይኬዳል? " አለች በዛበሽ ዉበቱ የይሁን በፍቃዱ ሚስት::

" እንዴት? "

" የዉስጡን አለሳለስ ብታይ! ጭራሽ መሬት ነክቶ የማያዉቅ የወይዘሮ እግር ይመስላል:: ''

''ምን ነበር ያሉኝ? እባክሽ! አንድ ... ትልቅ ሸመት ሊሸመ የሚሄዱ ናቸዉ፤ የትልቅ ... መነኩሴ ልጅ ሳይሆኑ አይቀሩም:: "

"እንዲያ እንጂ የኛ ሰዉነት! ደግሞ ብለህብለህ መነኩሴ ልጅ ይወልዳል በል! አለች በዛብሽ እየሳቀች::

ሀዲስ ዓለማየሁ ከፍትር እስከ መቃብር መጽሐፍ ላይ ተቀንጭቦ የተወሰደ::

## መልመጃ አንድ

ቀጥለዉ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሰረት በማድረግ ምላሽ ስጡ::

ሀ. በአማርኛ ቋንቋ ዉስጥ ከምጠቀምባቸዉ ስርዓተ ነጥቦች ዉስጥ በዚህ ምንባብ ዉስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉት የትኞቹ ስርዓተ ነጥቦች ናቸዉ?

## መልመጃ አንድ

ፈልጋችሁ አንብቡና ከዚህ ከቀረበዉ ንግስት ጋር ከሚለዉ ግጥም ጋር ያለዉን ተመሳሳይነትና ልዩነት ግለፁ።

2. በመረጣችሁት ርዕስ አንድ አጭር ግጥም ግጠሙ።
3. በረጅምና አጫጭር ስንኞች የተገጠሙ ግጥሞች ሰብስቡና በክፍል ዉስጥ አንብቡ።

## ንብና ትንኝ

ከአለታት አንድ ቀን በመስከረም ወር፣
ድንገት መጣሁና ንፋስ ሮመቀበለ።
አንዲት ንብ አየሁኝ በሶማይ ስትበር።
ሳንድምታዉቀትም መስከረም ሲጠባ፣
ጉራሳለጋሉ ንቢትና ለበባ።
የዝናብ ጊዜ አልፎ ስትወጣ ፀሐይ፣
ትንኝ ይወለዳል ከየቆሻሻዉ ላይ።
ስለዚህ በዚህ ወር የትንኝ መንጋ፣
ቁጥሩም ያስጉራራል ባየር ላይ ሲንጋጋ።
ወይዘሮ ንቢትም ኑበባ ስትቃኝ፣
ድንገት አገኘቻት አዲስቷን ትንኝ።
ሳቢኒም ዘኂላ ሁለቱ ነፍሳት ፣
ዘፋ ጠፉ አንሱ እዚያዉ እኔ ፊት።
እኔም በዚህ ጊዜ ቢፈጌንቀኝ ቢጠሽኝ፣
ልረዳ ተነሳሁ ለወይዘሮ ትንኝ።
ግን ወይዘሮ ንቢት ኃይለኛ ፍጥረት፣
ከወደር አሉኝና ወዲያዉ በድንገት፣
መርሂን ብትለቅብኝ ነፍሴን አጣኋት።



ብዙኃነዉ ከረረ ከቱ አስተመሳሰሉ ም፣
ልንላግላችዉ በነገራም አልቻልኩም።
ትንኝም ተስፋኛ ቢኖይል ከፋኝ፣
በብዙ መከራ ሂድን ወደዳኛ።

## ትንኝ

ለከቡራን ዳኞች የማመሰክተዉ ፣
የደረሰብኝን ጉዳት ተመልክተዉ ፣
እንዲፈርዱልኝ ነዉ እኔ ምለምነዉ።
የተጣላንበት የጠቡ ሰበብ፣
አዘነ ስተስም መጣች አመት ንብ፣
ቦና ምላሳን ያዝ ሊታገበንብ።
ከዚያም ነደፈችኝ በሃይለኛ መርዟ፣
በጣም ቀስያለሁ በዚሁ መዘሃ።

## ንብ

በጣዛ ጥፋቷ አበሳዉን ነክታ ፣
በኃይለኛዉ መርዟ አራሳ ተመታ።
ከየቆሻሻዉ ላይ ጀርሞችን ሰብስባ፣
ሃሳቧ ነበረ ልታጠፋ አበባ።
ስራዉን ሳታዉቀዉ ዉን ዉን እያለች፣
አበባዉን ሁሉ ብክንቱ አበላሸች።
ስለዚህ ጊታዉ ጥፋቷ ነዉና፣
ይፍቀዱልኝ ልሃድ ስራ አሰቱቦኛ።

## ዳኞቹ

ነገሩን አዩና ክሳደ አስክ ታች፣
ፍርድ ሊሰጡ ነዉ እንግዲህ ዳኞች።

4. ለሚከተሉት ቃላት ተመሳሳይ ፊልጉላቸዉ.

ሀ. ለመቋቋም
ለ. ማንጠር
ሐ. መምዘግዘግ
መ. መገደብ
ሠ. መንጣለል
ረ. መሸርሸር
ሰ. ጅረት
ሸ. እንፋሎት
ቀ. አቅም
በ. መገፋፋት
ተ. ማንገዝ
ቸ. ማመንጨት
ኀ. መንከባለል
ነ. ማነማቸት
ኘ. ድህነት
አ. ማልማት
ከ. ኃይል

## ፲፩. የቃላት ትርጉም

ቃላት በቁማቸዉ ከአንድ በላይ ትርጉም /ፍቺ/ ይኖራቸዋል።

ምሳሌ፡- "ሳለ" የሚለዉ ቃል "ስዕል ሠራ፣ ሞረደ፣ አሳለዉ ወዘተ ትርጉሞች አሉት።

ላልተዉና ጠብቀዉ ሲነበቡም ከአንድ በላይ ትርጉም የሚይዙ ቃላት አሉ።

ምሳሌ፡- ገና - ሲላላ ያልተደረገ /ያልተፈፀመ/
ሲጠብቅ የገና ጨዋታ /በዓል/
በራ - ሲላላ መላጣ
ሲጠብቅ ብርሃን ሰጠ
በላ - ሲላላ ተናገር / እንዲናገር ማዘዝ/
ሲጠብቅ ተመገበ

## ካርለት

ባሻ ቤተ ዉስጥ ጠብ ጠብ ከሚለዉ የዉሃ ድምፅ በተጨማሪ ላይ ላይ የምትተነፍስ ሴት ድምፅ ይሰማል። የመታጠቢያ ገንዳዉ ዉሃ እስከ ወገቡ የደረሰ ሲሆን ናርለት ዉሃዉ ዉስጥ ጋደም ብላ ቀኝ እግሯን ገንዳዉ ከንፈር ላይ

ሰፊ ንጉሣዊ ሰንደቅ ዓላማ የአደ መታጠቢያው ከፍ ብሎ ደግሞ በዘፍሉ መቀት ሳቢያ የሚያሠርዉ መስተዋት አለ። የመታጠቢያ ክፍሉ ጠበብ ያለ ቢሆንም ንፁህና ዘመናዊ ነዉ። ከመግቢያዉ በር በስተግራ ካለዉ የቆሻሻ ልብስ ማስቀመጫ ቅርጫት ካኔትራ ሱሪና ጃኬት ተቀምጧል። ከሱ በላይ ሰፋና ረዘም ያለ በነጭና ሀምራዊ ቀለም የተሸፐንረንረ ፎጣ ተንጠልጥሏል።

ካርሰት የገዳዉን ዉሃ ቀይራ ሰዉነቷን በንፁህ ዉሃ ከተለቀለቀች በኋላ ከወንዴዉ ፀጉሯ ወደ ግንባሯ እየተንሸለለ የሚወርደዉ ዉሃ በቅንድቧ ስር እየሰረገ ተለትና ሰርጎ ያሰዉን ዓይንዋን ያራግባል። ዘፍረትና ትክሻዋ አካባቢ ቀጥ ያለ የዉሃ እንክብል ከመታየቱም ባሻገር ከሱና ብልታ ላይ ካለዉ ስስ ፀጉር ላይ ደግሞ በአፈርማ ሰሞን ሳር ላይ የሚታየዉን የመሰሰ ትንንሽ የዉሃ ነጠብጣብ ይታያል።

ካርሰት ወደ መስታወቱ ቀረብ እንደምትል ገፅታዋ ከሚያሠርዉ መስተዋት ዉስጥ ተከፋፍሎ ታያት መስተዋቱን ተመተ አድርጋ በእጆቿ ጡቶቿን ጨበጥ ጨበጥ አደረገቻቸዉ። ቀኝ እጇ ቀኝ ጡቷ ላይ ሲቀር ግራ እጇ ግን ወደታች እተንሸላወሰ ጉዞ ጀመረ ወደ ሴት ብልታ እጇ የደረሰበትን በአይኗ ተመለከተችዉ።

የሰፊዉ የመስተዋት መስኮትና ላዩ ላይ ከተንጠለጠለዉ ነጭና ቡና አይነት መጋረጃ አልፎ አልፎ ነፍ ብሎ የሚያልፍ የመኪና ድምፅ ይሰማል።

ዘነፍሉ ዉስጥ ካሉት ሁለት አልጋዎች መካከል አንድ ከመዲና አለ። ከመዲናዉ ላይ "ሶኒ" የሚል ምልክት ካለበት ሬድዮ ካሴት ዉስጥ ከዛሬ ሁለት መቶ ሃምሳ አመት በፊት በሞርዛት የተቀነባበረዉ ፒያኖ ሶናታ የሙዚቃ ስልት ድምፁን ሰለምለም ሞቅ ሞቅ ሰለምለም እያደረገ ይንቆረቆራል። ከመስኮቱ ጠርዝ አካባቢ ሁለት ሰፋና አንድ ጠረጴዛ ያለ ሲሆን ጠረጴዛዉ ላይ ከግማሽ በላይ የተጠጣለት የማር አረቄ ይታያል።



ሰፊዉ ማርቶን ያደረገዉ ጥቁረ ምድር አይናቱን ከርችም ያለ እንቅልፍ አጋድሞታል። በአዲስ አበባዉ ሂልተን ሆቴል በተዘጋጀዉ የብረ ንብዣ ላይ ሦስት ወንበር እንዲያዝላቸዉ በማዘዝ ሁለቱ የፍቅር ጓደኞሞች ከኪሱ ሆራ ጋር በመሆን ምሽቱን ከምግብ ጉዝጓዙ በኋላ መጎንጨቱንና በእፍሪቃዉያን መዚቃ መዉረግረጉ እስከ አኩለ ሌሊት ሲያስኬዱት ቆይተዉ ነዉ። ሁለቱ ፍትረኛ ሞችና ኪሱ ሆራ "መስመርህን ለይ" የተባባሉት።

ካርሰትና ስቲቭ የስራ ቦታቸዉ በጣም የተራራቀና የትራንስፖርትም ችግር ያለበት በመሆኑ ተመልሶ ለመገናኘት ቢያንስ የሦስት ወር ጊዜ ያስፈልጋቸዋል። በፍቅር አባዜ ለተያዙት ለእነዚህ ወጣቶች ደግሞ ጊዜዉ የትየለሌ ነዉ - ሩት። ስለመለያየታቸዉ እንጂ ስለመገናኘታቸዉ የማይተማመኑት ፍቅረኛሞች ዉሀሀብና በፍቅር ጨዋታ ሰዓታቸዉን በሚገባ ለመጠቀም በእንድ ወጥ ስሜት ጥረዋል። ድብቅነት በሌለዉ ንፁህ የፍቅር ጨዋታ ልባቸዉን ስልትና ቃናዉ በሚጣፍጥ ትላፄ እያስጨፈሩ ራሳቸዉን በመሆን በፍቅር ባህር ከመዋኘት አልፈዉ ዘቅጠዉበት አድረዋል።

ከፍቅረ ማርቆስ ደስታ፣ ድንግል ዉበት 1987 ፣ ገፅ 5-6 ተቀንጭቦ የተወሰደ

**መልመጃ አንድ**

ቀጥለዉ የቀረቡት ቃላት ከምንባቡ ተለቅመዉ የወጡ ናቸዉ። ምንባቡን መሰረት በማድረግ ለቃላቱ ትርጉማቸዉን ግለፀ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ባኛ | ሰ. እንክብል | ኀ. ስልት |
| ለ. ገንዳ | ሸ. ባሻገር | ነ. ይንቆረቆራል |
| ሐ. ሳቢያ | ቀ. መሰለ | ኘ. ብፈ |
| መ. ተሸርጎረጎረ | በ. እየተንሳወሰ | አ. የትየሌለ |
| ሠ. ተሳለ | ተ. ምና | |
| ረ. ር | ቸ. ኟ | |

ስትሉት እናንተዉ በገዛ እጃችሁ ሌላ ፍልጰስ በራሳችሁ ላይ እንዲፈጠርባችሁ ታደርጉ የለም ወይ? ....''

ከአበደ ሚሳኤል፤ ታላላት ሰዎች የተወሰደ

ከላይ ስለ ዴሞስቴን የቀረበዉ ምንባብ አንድ ሰዉ ሃሳቡን በአደባባይ ለመግለፅ በቅድሚያ የንግግር ልምምድ ማድረግ እንዳለበት የሚያሳይ ነዉ::

## መልመጃ

መምህራችሁ በሚሰጣችሁ የጊዜ ገደብ በመጠቀም ሁላችሁም ዉስጣዊ ስሜታችሁን፣ ፍላጎታችሁን፣ አመለካከታችሁንና የወደፊት እቅዳችሁን በተመለከተ ዝግጅት አድርጉና በክፍል ዉስጥ ለጓደኞቻችሁ ንግግር አድርጉ:: የክፍሉን ተማሪዎች እንደ አንድ ትልቅ ጉባኤ አድርጋችሁ ቁጠሩት::

### 3.2 ጭዉዉት

ንግግርን በጭዉዉት መልክ የበለጠ ማዳበር ይቻላል:: የሚከተለዉን ጭዉዉት በድራማ መልክ ሥሩት::

እንባ እፈልጋለሁ

- ዘበርጋ የመሥሪያ ቤቱ ኃላፊ፤ ሰራተኞችን አወዳዳሪና ቀጣሪ ነዉ::
- አለመ፣ ፍትርተ፣ እና ዝናቡ በመስሪያ ቤቱ ለመቀጠር ያመለከቱና ተወዳዳሪዎች ናቸዉ:: ዘበርጋ የሚከተለዉን ማስታወቂያ ያወጣል::

የሀገር ፍትር ቲያትር ለመድረክ ስራ ተዋንያንን አወዳድሮ መቅጠር ይፈልጋል::

- ለዉድድር የሚያስፈልግ መስፈርት
- በመ.ያዉ ቢያንስ 3 ዓመት የሰራ
- ዕድሜ 18ና ከዚያ በላይ
- በተለያዩ መድረኮች ላይ የተሳተፈ

- የትምህርት ደረጃ ሁለት ዓመት የኮሌጅ ዲፕሎማ ያጠናቀቀ
- ዕድ አይለይም
- ደመወዝ በስምምነት
- ቦታ አዲስ አበባ

የማመልከቻ ወቅት ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን በኋላ ባሉት ተከታታይ አስር የስራ ቀናት

ትዕይንት አንድ

ተወዳዳሪዎች ማመልከቻቸዉን ለፀሐፊዎ ሊሰጡ እየመጡ ነዉ።።

ትዕግስት ( የዘበርጋ ፀሐፊ)

ፍትርተ ማመልከቻዋን ይዛ መጣች

(በር ተንኳኳ

ትዕግስት፡- (ይግቡ)

ፍትርተ፡- (ቤና ይስኖልኝ፤ ለወጣዉ ማስታወቂያ ለመወዳደር ማመልከቻ ለማስገባት ነዘር)

ትዕግስት (ቤት መወዳደር አትችልም)

ፍትርተ፡- (ለምን? ማስታወቂያዉ ላይ እኮ ዕድ አይለይም ይላል)

ትዕግስት ( የእኔ እመቤት ስራዬን ልስራበት፤ ዕድ አይለይም የተባለዉ ሁሉም ሴራ ለባሽ ስለሆነ ብቻ ነዉ።።)

ፍትርተ (ተበሳጭታ ትመለሳለች)

አለሙና ዝና በበአንድነት መጡ

(በር ይንኳኳል)

ትዕግስት፡- ( ይግቡ)

አለሙ ( ይትርታ ማመልከቻ ለማስገባት ነበር)

ትዕግስት ( ይቻላል)

ዓለሙ ፡- (ማመልከቻዉን ሰጠና ወጣ)

ዝናቡ (ዝም ብሎ ሰላት)

ትዕግስት ( ስምህ ማነዉ?)

ዝናቡ (የእኔ?)

ትዕግስት፡- ( አዎ)

ዝናቡ፡- ( ዝናቡ) ስሙን ከገለፀ በኋላ ሲወጣ በሩ ላይ ሲደርስ ከኋላዉ ድምፅ ሰማና መለስ አለ

ትዕግስት፡- በአይኗ ጠቀሰችዉ)

ዝናቡ ፡- ( ቆንጆ መሆኗን አይቶ ወደዳት)

ትዕይንት ሁለት

ዉድድሩ ከመካሄዱ ሁለት ቀን በፊት ዝናቡ በዘገር ፍትር ቁአትር ቤት ይሄድና ከትዕግስት ጋር ይገናኛል። ከእሷ ጋር እያወራ ባለበት ሰዓት ስራ ለአስኪያጁ (አቶ ዘበርጋ) ይመጣሉ። ትዕግስት ትደነግጣለች። ዝናቡ ስለማያዉቀዉ ምንም አልመሰለዉም። ዘበርጋ ያያቸዉና ምንም ሳይናገር ተመልሶ ይወጣል። ትዕግስት፡- (ዝናቡ እኔ እኮ እንዳየሁህ ነዉ የወደድኩህ)

ዝናቡ ፡- (እኔም እንደዚያዉ ነዉ)

ትዕግስት ፡- (አንተ እንድትቀጠር ከፍተኛ ጥረት አደርጋለሁ አሁን የመጡት ቀጣሪያችሁ ናቸዉ። በጣም ሰላምንጋባ እንገራቸዋለሁ።

ዝናቡ፡- ( ፈተናዉን ሰርቀሽ አምጭልኝ)

ትዕግስት፡- (እሺ) ከዚህ በኋላ ሁለቱም ተያይዘዉ ይወጣሉ።

ትዕይንት ሦስት

የዉድድሩ እለት ነዉ

አቶ ዘበርጋ ቢሯቸዉ ገብተዉ ሰዓት እስኪሞላ ይጠብቃሉ።

ዓለሙና ዝናቡ ከዉጭ ቁጭ ብለዋል።

ሁለት ሰዓት ተኩል ሆነ

ከዉስጥ ከአቶ ዘበርጋ ቢሮ የደወል ድምጽ ተሰማ

ትዕግስት ወደ ቢሮ ገባች

ዘበርጋ፡- ( ተወዳዳሪዎቹ ቀርበዋል?)

ትዕግስት፡- (አዎ)

ዘበርጋ:- (ዝናቡ አለምነህን ግባ በይዉ)
ትዕግስት:- ከቢሮ ትወጣና ዝናቡን እንዲገባ ትነግረዋለች
ዝናቡ:- ( በር ያንኳኳል)
ዘበርጋ :- (ይግቡ)
ዝናቡ:- (ይገባል)
ዘበርጋ:- (ትኩር ብለዉ ያዩታል፤ በመቀጠልም ከሁለት ቀን በፊት የት ነበርክ?)
ዝናቡ:- (ገጠር ዘመዶቼ ጋ ሄጀ ነበር)
ዘበርጋ:- (ትዕግስት ምንህ ነች?)
ዝናቡ:- ( የአክስቴ ልጅ)
ዘበርጋዉ (ድራማ ሰርተህ ታዉቃለህ?)
ዝናቡ (ሰርቼ ነበር፤ ነገር ግን ገጠር ረስቼዉ መጣሁ)
ዘበርጋ:- ( መሄድ ትችላለህ)
ዝናቡ (ከቢሮ ወጣ)
ዓለሙ:- ተጠርቶ ገባ (የጠራዉ ዝናቡ ነዉ)
ዓለሙ:- (በር አንኳኳ)
ዘበርጋ:- ( ይግቡ)
ዓለሙ :- ወደ ዉስጥ ይገባል)
ዘበርጋ:- (እድሜህ ስንት ነዉ?)
ዓለሙ:- ( 120)
ዘበርጋ:- (የትምህርት ደረጃህ?)
ዓለሙ:- ( 10ተ12ተ15 = 37)
ዘበርጋ:- ( ቁመትህ ስንት ይሆናል)
ዓለሙ:- ( አስር ኪሎ ሜትር)
ዘበርጋ ( ድራማ ሰርተህ ታዉቃለህ?)
ዓለሙ:- (አዎ)

ዘበርጋ ( ዘፈንስ ትችላለህ?)
ዓለሙ (አዎ)
ዘበርጋ ( እስኪ የምትችለዉን ዘፈን ንገረኝ)
ዓለሙን:-( ባዴ፤ባዴ፤ባዴ፤ባዴ፤ባዴሳ)
ዘበርጋ ( አንዳች ያሳብድህ ሌላ)
ዓለሙ:- ( ሌላ! አልሄድም ሸንጎም አልዉል ምን ሆንኩኝ ብዬ ይበለኝ የእጀን ነዉ ያገኘሁት)
ዘበርጋ ( አሁን አንተ በመንገድ ላይ እየሄድክ ነዉ:: ድንገት የምትወዳትን ፍቅረኛህን አገኘሃት:: እንዴት ነዉ ሰላም የምትላት?)
ዓለሙ:- ( አዝናለሁ ፍቅረኛዬ ከሞተች 120 ዓመት አልፏታል)
ዘበርጋ:- ( ብትኖርና ብታገኛት ነዉ ያልኩህ)
ዓለሙ:- ( ብትኖር፤ ብትኖር፤ የለችም እንጂ ብትኖር ይልና ዘበርጋን እንቅ አድርጎ ይስመዋል::
ዘበርጋ:- ( ከራሱ ላይ በግድ ያስለቅቀዉና አሁን ደግሞ ሌላ ጥያቄ አቀርብልሃለሁ ይለዋል:)
ዓለሙ ( ዝህጁ ነኝ)
ዘበርጋ:- (አሁን አንተ በጣም የምትወዳት ፍቅረኛህ ድንገት ብትሞትብህ እንዴት ነዉ የምታለቅሰዉ?)
ዓለሙ:- ( ከሞተች እኮ ቆየች)
ዘበርጋ:- ( አሁን ድንገት ብትሞትብህ እንዴት እንደምታለቅስ አሳየኝ)
ዓለሙ:- ( ድንገት ብትሞት አለና ድምፁን ቀጠን አድርጎ እሪታዉን አቀለጠዉ)
ዘበርጋ:- ( ከመቀመጫዉ ብግድ አለና ፊቱን አየ እንባ የለም)ዓለሙ
ዓለሙ:- ( ዝም አለ)
ዘበርጋ:- ( እንባ እፈልጋለሁ)
ዓለሙ:- ( እንባ እፈልጋለሁ?)
ዘበርጋ:- (አዎ እንባ እፈልጋለሁ፤ ስለዚህም እንደገና አልቅስ)

ዓለመ፡- ( እንባ ለማዉጣት እራሱን በእጁ ያዘና ድም ዑን ጎርነን
አድርጎ በሚያስገመግም ሁኔታ ጮኸ)

ዘበርጋ፡- ( ብድግ ብሎ ፊቱን አየዉና ቁጭ ብሎ ዉጤት ሰጠ)

ዓለመ፡- ( አንገቱን ሰገግ አድርጎ ዉጤቱን አየ ግን አልቻለም)

ዘበርጋዉ ( አዝናለሁ ወድቀሃል)

ዓለመ፡- (አ! ወድቀሃል ነዉ ያልከኝ?)

ዘበርጋ፡- ( አዎ! ወድቀሃል)

ዓለመ ፡-( ትንሽ አሰበ አንተ ሚጋ አምፊ ቴአትር ከዛሬ ሦስት ዓመት
በፊት ተሰራ አልነበር?)

ዘበርጋ፡- (አዎ)

ዓለመ፡- ( ስምህ ዝናዉ አልነበረም?)

ዘበርጋ፡- ( ልክነህ፤ ነገር ግን አንተ ማን ነህ?)

ዓለመ፡- ( አንተ የአቶ አለማየሁ ልጅ ዝናዉ ነህ አይደለም?)

ዘበርጋ፡- ( አዎ ልክ ነህ)

ዓለመ፡- ( ዘና ብሎ የአባትህን ለቅሶ ተዉህ ነዉ እንዴ እዚህ ቁጭ
ያልከዉ? አባትህ እኮ እኛ ወዲህ ከመግባታችን በፊት ከጠዋቱ አንድ
ሰዓት ተኩል ላይ አርፈዋል፡)

ዘበርጋ፡- ( እስክርብቶዉን አስቀምጦ ከመቀመጫዉ ይነሳና እራሱን በእጁ
ይዞ ይጮሃል)

ዓለመ፡- ቶሎ ብሎ መቀመጫዉ ላይ ተቀምጦ እስክርብቶዉን ይይዝና
እንደፈታኝ ይሆናል)

ዘበርጋ፡-( ለቅሶዉን ቆም ያደርግና ''እርግጠኛ ነህ''? የእኔ አባት አርፏል?)

ዓለመ ( እንባ እፈልጋለሁ ይለዋል)

ተፈፀመ

ከላይ የቀረዉን ጭዉዉት መምህራችሁ ለሚሰጣችሁ መመሪያ መሰረት ተለማመዱና በክፍል ዉስጥ አቅርቡት። በምታቀርቡበት ሰዓት የፊታችሁን ገፅታ፤ የአካላችሁን እንቅስቃሴ፤ የድምፃችሁን አወጣጥ ሊያዝናና፤ ሊያስቅ በሚችል መልኩ መለዋወጥ ትችላላችሁ።

ነዉ። በዚህ አጋጣሚ አባታ የከደናቸዉን አይኖቹን ገልጦ መናገር ጀመረ።

ወንድ አያቱ ፒር ነጋርሽላ ይባላል። ፒር ነጋርሽላ ሰሜን ምዕራብ ሀገደ ገጅራት ዉስጥ መለስተኛ የከበረ ድንጋይ ማምረቻ ክፍት በአጭር ...

ምንጭ፡- ፍቅረ ማርቆስ ደስታ፤ አቻሜ፤ ገፅ 37-42

4.8.2 አጭር ልበ ወለድ

አጭር ልበ-ወለድ በ19ኛዉ ክ/ዘመን ብቅያለ የስነፅሑፍ ዘር ቢሆንም ከዚያ በፊት በወል ተለያዩ ባይተመጥም ሰዎች በአጭር በአጭሩ ለመገናኘት፣ ለመደሰት ወዘተ የተለያዩ ታሪኮችን ይሰፋ እንደነበር የስነፅሑፍ ታሪክ ያስረዳል።

አጭር ልብ-ወለድ እንደ ረጅም ልብ-ወለድ የገሃዱን አለም ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት አድርጎ የሚቀርብ የፈጠራ ዉጤት ነዉ። የስነ-ፅሑፍ ምናባዊ የፈጠራ ዉጤት ይህ ስነ-ፅሑፍ ከረጅም ልበወለድ ምናባዊ የፈጠራ ዉጤት የሚለይበት የራሱ የሆኑ ባህሪያት አሉት። ከልብ ወለድ አላባዊያን አንባር በረጅም ልብ-ወለድ ዉስጥ የሚገኙት አላባዊያን በሙሉ በአጭር ልብ ወለድ ዉስጥ ይገኛሉ። ነገር ግን በረጅም ልብ ወለድ ዉስጥ ሁሉ ስፋትና ጥልቀት ባላቸዉ ሁኔታ ሲቀር አጭር ልብ ወለድ ዉስጥ ግን ቁጥብነት ጥድፍያና ልብ አንጠልጣይነት ጎልቶ ይታያል። ይህን ሁኔታ ከሚከተለዉ አጭር ልብ ወለድ መመልከት ይቻላል።

ጅብ ነቺ

ልኑ ቅዳሜ ነበር። አሰፋ የአዲስ አበባ ከፍተኛ ትምህርት ቤት ተማሪ አድሜዉ ሃያ አመት የሆነዉ እናቱን ለመጠየቅ ከአዲስ አበባ 75 ኪሎ ሜትር በምስራቅ በኩል ርቃ በምትገኘዉ ከተማ ሸኖ ሄዶ ከስድስት ሰዓት ጀምሮ እናቱ ቤት ነበር።

ይመጣል ብለዉ ያልተጠባበቁት እናት ለጊዜዉ ቤት ያፈራዉን በተቻለ መጠን አጣፍጠዉ ከሸነገሉት በኋላ ለራቱ የሚሆን የዶሮ ወጥ ሊሰሩ ዶሮ አሳርደዉ የፊላዉ ዉሃ ከእሱ የሚጠበቀዉን ካደረሰ በኋላ እሳቸዉ ደግሞ

መንፋቱንና መለብለቡን ከዚያም በኋላ መፋቀንና መገነጣጠሉን ተራ በተራ ይዘዉ ነበር:: ታናሽ እህቱም አየለች ዉሃ በመጥለቅና ዕቃን በማቀበል እናቷን ለመርዳት እዚያዉ እስራቸዉ ነበረች::

አሰፋም ከመጣ ጀምሮ ወደ ዉጭ ሳይል ሦስት ሰዓት ሙሉ ከቤት ቁጭ ብሎ የናፈቃትን እናቱን ትንሹንም ትልቁንም ሲያጫዉታቸዉ ነበርና የቀየዉ ዘጠኝ ሰዓት እንደሆነ አገሩን ዉጭዉን ለማየትና ወዲያዉም ለመናፈስ በማሸብ ሊወጣ ብድግ አለ::

እናቱም ወይዘሮ አስገደች አይናቸዉን በስራቸዉና በልጃቸዉ ላይ ጣል አድርገዉ ኖሮ ልጃቸዉ መነሳቱን እንዳዩ ሥራዉን ቆም አድርገዉ:-

"ምነዉ አሰፋ የት ልትሄድ ነዉ?" ብለዉ ጠየቁት::

አሰፋም በዚህ ጊዜ ከበሩ ደርሶ ነበርና ከዚያዉ ከቆመበት መለስ ብሎ:-

"አገሩን ልይ ብዬ ነዉ?" ብሎ መለሰ::

"ቆይ እስ በኋላ ጥላዉ በረድ ሲል ነዋ ልጄ፤ በዚህ ጠራራማ ሰዓት ደግ አይደለም"

"ምን ይለኛል ብለሽ ነዉ?"

"እንዴ! አይሆንም:: ሽታዉ ደግሞ ይኸ ምናምኑ ፤ ምን ይታወቃል ብለህ ነዉ፤ የኛ አገር እንዳዲስ አበባ አይደለም ልጄ:: አተላዉ፤ አመዱ በያለበት ነዉ የሚፈሰዉ:: በዚህ ሰዓት ሽታዉ ደግ አይደለም::

**አሰፋም የእናቱን ሃሳብ በመቀበል እርምጃዉን ወደፊት ሳይቀጥል** እዚያዉ ከናቱ ደጃፍ ላይ ቆሞ ዉጭዉን ይመለከት ጀመር::

የእናቱም ቤት ከከፍተኛ ቦታ ላይ የተሰራ በመሆኑ ከበራፉም ላይ ሆኖ የሚታይ ብዙ ነገሮች ነበሩ:: በአንፃሩ ቡልጋና መገዘዝ ጠፈሩን የነኩ መስለዉ ከሩቅ በጭጋግ ተዉጠዉ እንደ ህልም ይታዩ ነበር:: ከዚያም ወዲህ ተራሮች በየከረብታቸዉ ያገሬዉን ቤት ሾመዉ በወገባቸዉም አዝመራን አዝለዉ የሚወጡና የሚወርዱት አያሌ ነበሩ:: ከዚያም በጣም ወዲህ ወደ ሸሮ ቀረብ ሲሉ ደግሞ የሚታየዉን ከከተማዉ ጥቂቱ ክፍል ነበር:: በዚሁ ከፍል የሚታዩት ቤቶች በድንጋይ ካብ ግድግዳና በሰንበሌጥ ክዳን የተሰሩ ነበሩ:: የአሰፋም አይን ይህንኑ ትርኢት ከሩቅ ሲከተተል ከመጣ በኋላ በእናቱ አጥር ግቢ አሳማኝ ካለዉ አጥር ግቢ ዉስጥ ከሚታየዉ ሰቀላ ቤት በር ወደ ዉጭ ሲወጣ የሚታየዉ ነገር እዉነተኛ ወይም ህልም መሆኑን ለማረጋገጥ አስቦ ደህና ሆኖ እንዲታየዉ በተመቸዉ አቅጣጫ አንጋዶ ወደዚሁ በር አተኩሮ ነበር::

ይህም ቤት ከሌሎቹ ቤቶች ትንሽ ለመለየትና ግማሽ በግማሽ ያዲስ ዘመን እቅድ ነክ በመሆን ጣሪያዉ አዲስ አበባን ( ቆርቆሮ)፤ ግድግዳዉ ሸኖን ( የድንጋይ ካብ) የሆነ ነበር:: ሆኖም አሰፋ አሁን በበሩ ብቅ ሲል ያየዉ ነገር እዉነተኛ እንጂ ህልም አልነበረም:: ከቤት ዉስጥ በበሩ ብቅ ያላችዉ አንድ ነጭ የቤት ፈትል ቀሚስ የለበሰች ሴት ልጅ ነበረች::

እሱም በዚያ ርቀት እንደሚያያት ልጅቷ ብስል ቀይ፤ ዓይኗ ጥራቱ ኩል የመሰለ፣ ፀጉራ ዞማ ከዘመናዊዉ ይዞታ እንዲም አይነት ሳይነካዉ እንደዚሁ በተፈጥሮዉ ብቻ ትከሻዋ ላይ ነጥሮ ለቀቅ ካለዉ ሽንጧ ላይ እንዲዘናፈል የተተዉ ቅንድቧና ሽፋሏ፣ አፍንጫዋና ከንፈሯ ይህ ቀራቸዉ የማይባሉ፤ የጠቷም አጎጠጎጤ ከቀሚሷ ዉስጥ መፈናጠሩ፣ የተፈጥሮ ሳይሆን ልብሷን ከሰሩት ልቃቂቶች መሀል ሁለት የዳበሩት ተመርጠዉ ቀርተዉ እንደ ወጋግራ እንዲወጥሩት የቆሙበት የሚመስል፣ ቁመቷ ደልዳላ፤ ዕድሜዋ ቢበዛ ሃያ ቢያንስ አስራ ዘጠኝ የሚሆን ነበረች::

**አሰፋም ወጥታለት እንዲህ ሙሉ በሙሉ እንዳያት ልቡ አለመጠን** መታ:: አይኖቿም አይኖቹ ላይ ሲያርፉ ከእግር ጥፍሩ እስከ ፀጉሩ ነዘረዉ:: አይኖቹንም ከእሷዉ ላይ ሳይነሳ እናቱን:-

"እማማ ይቺ ምን ናት?" ብሎ ጠየቀ::

ቁጭ ያሉትም እናት እዚያዉ እንደሆኑ ቀና ብለዉ:-

"የቷ ልጄ?" ብለዉ ጠየቁ::

"ይ- ይቺ!" አለ::

አሰፋ አሁንም ወደ እናቱ ዘወር ሳይል አዚያጪ ሰጪነት ላይ ለይናቱን ድርቀ አድርጎ እናቱም ዘዚህ መልስ ብድግ ብለጪ የልጽትጪ አይን እንዲህ የፈዘዘበትን አቅጣጫ ይዘጪ፣ የተጠቀሰችጪን ሴት ልጅ እንዳዞ ስትጥጥ ብለጪ፦

"አሰፋ! በል ቀስ ብለህ ንግ። ይህችን ልጅ ክእንግዲህ ወዲህ፣ አይንህ ፈፅሞ እንዳላያት ሁን። ብለጪ አዘዙ።

አሱም በዚህ ጊዜ ወደ እናቱ አይቶ፦

" ምነጪ ! ለምን እማማ? " ብሎ ጠየቀ።

"ቡዳ ነች! ልጅ። ያጪም እንዲህ እንዳትመስልህ ዋና ቀርጣፊዋ።"

አሰፋም የእናቱን ነገራቸጪን ሰሚታለል ሣቅ ብሎ፦

"አይ እማማ! አሱን ይ- ያ ነች ብሎ በፈገግታ ጠየቀ።

እናትየዋም ባፈገ[illegible] [illegible] [illegible] [illegible] አሩረረጪ።

"አምን አሷ በዚሁ ቅመልኔ አያተሰለች ነጪ ብዙጪን ጀግና ያጠፋች ጪ። ስማና አረፈጪ እንግዲህ በፈለግህ ማታ ማታ ጅብ ትሆናለች።"

አሰፋም በማዘን አነኒን ወደ እናቱ በሙሉ ዘወር ብሎ፦

"እማማ! እማማ! እንዲህማ አትበይ። ሰጪ የሰጪ ልጅ አንቺስ ብታስቢጪ እንዴት ጅብ መሆን ይችላል? ይህ እማማ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ያገራችን አፈታሪክ ነጪ። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሰጪ ተመልሶ ጅብ ሲሆን እንደማይችል መፅሐፍ ቅዱስ ደግሞም ሌሎች ከፍ ያሉ ትምህርቶች ያስረዱናል። እርግጥ አንዳንድ ሰዎች የአይናቸጪ ኃይል እያዩ ሆኖ ደከም ባለ ሰጪ ላያና በህሣናት ላይ ሲያርፍ ሊጎዳ ይችል ይሆናል። ነገር ግን ክዚህ አልፎ ተርፎ ሰጪ ማታ ጅብ ቀን ደግሞ ተመልሶ ሰጪ ይሆናል ማለት የማይሆን ነገር ነጪ" አሰ።

እናትየዋ በዚህ ጊዜ ደግሞ ይብልኖ ቱን ብለጪ፦

"ልጄ እንግዲህ ትሰማ እንደሆነ የወለድኩህ እኔ ነኝ አንተ አይደለህም፣ ስማኒ ጅብ ትሆናለች ስልህ ጅብ ትሆናለች ነጪ። ይሆን የአንተን አትሆንም የሚለጪን መፅሐፍ ለዚያጪ ላዲስ አበባህ አድርገጪ አሱ።

አሰፋ ዘዚህ ጊዜ አሱም በበኩሉ ናር ብሎ፦

"እሺ! አንቺስ ጅብ መሆኗን እንዴት ታስረጂኖለሽ? ሰለሽም ብሎ ጠየቀ።

እናትየዋም እንዲሁ አሳቸጪም በበኩላቸጪ በቁጣ የደም ስሮቻቸጪ ተገታትረጪ፦

"እንዴት ታስረጂኖለሽ ይላል! ይህ ሲያቅተኖ? ምነጪ አሁን ቆቅጪም ለት ከስምንት ቀን በፊት ድፍን ሽኖ አልተረዳጪም እንዴ! መገርሶ የ ሚባለጪን ወዳጅዋን አልጋዋ ላይ በመድሃኒቷ አፍንጫ እያቀኘች ከጅቦቹ ጋር ስትጋልብ እንግታ ስትመለስ አሱ መየሚ ጎዳቷ ቀርቶ አይኑም ቁሳ ባሰበችበት ጊዜ ዘፊት መገርሳ ነቅቶ አጪልቃ ጉቸቅቸጪ የራስ ቅሏን አግኝቶ አልደበቀጪም! እሺ አሱም ይቅር ሃጎኔ ቀን ሙሉ አልመልስላት ብሎ በሯን ዘግታ ስታለቅስ አልከረመችኖ። እሺ አሱም ደግሞ ይቅር ይህንኑ አሁን እንዲህ አላይዋ ላይ ወድቆ ያየኸጪን ፀጉራን አራሱኑ በነራስቅሏ በመገርሳ እጅ ሰኞ ገበያ ጪስጥ ሲዘር አሳየነጪም! ህም! ደግሞ እንዴት ታስረጂኖለሽ ! ባየህ አገር ግልብጥ ብሎ ወጥቶ አግዚኦ ብሎ ለምናት ነጪ የመለለላት። ምነጪ

አንቺ እያለች አትነግሪጪም ለዚህ ለወንድምሽ? በይ እኮ። የወይንቱን ፀጉር አመገርሳ እጅ አሳየሽጪም? አሏስ በሯን ዘግታ ሦስት ቀን ሙሉ ስታለቅስ አልሰማሻትም? " አሱ።

አየለችም የእናቷን ማምረር ተገንዝባ እንዲላትም ወዲያጪ ወንድሟን አይታ ፦

"አዎን ጋሼ እማማ ያለችጪ ሁሉ እጪነት ነጪ። ፀጉራን ጋሼ መገርሳ ሲያዞረጪ ሁላችንም አይተነዋል። " አለችጪ

አሰፋም ክዚህ በኋላ ምንም ሊል አልቻለም። ደንግጦ ገብቶ ቁጭ አለ። ክሰጪም ሰጪ የዚህች ልጅ ጭንትላት ክራሷ ወልቶ ተገንዶ በገበያ

[illegible] ታይቶዋላዉ ባርዶ አስራ አንድ ሰዓት እንደሆነለት ቢቻዉን ሰመሆን በማሰብ
በዚያ ፊት ነገሩን ላይ ነገ ብሉ አትረቦት ያነበረዉ ያመራት አሰ
ብሉዉ አመነኝቶ ሲወጣ ተነሳ።

እናቱም አደጀ ሚረስ ተከትለዉት ወጥተዉ።

"እንግዲህ እንደዉ አደራህን ልጅ ወደዚያ ቤት ፈፅመህ ዝር
አ[illegible] ብለዉ ሰመኑት።

አበራም የእናቱን ማምረር ተገንዝቡ።

"እሺ እማማ ።" ብሎ መለሰ

እ[illegible] እንዲያዉ ደንዝዉ መች አልሄዶም በልና እጅን ያ[illegible]
ያማን መጠበቅ።

አ[illegible] በዚህ በኋላ ለይምሰል አገሩን አጨነቅ እንደሚሄደ ሰዉ
ሰተማዉ በሞኅ ወላል ብሉ ከሚታይበት ክፍተቱኛ ቦታ ላይ ወጥቶ ነበር።
ነገር ግን አይኑ ከዋለበት ላይ ልቡ ስላልነበረ አንዱንም አላየም ነበር። ልቡ
በዚያችዉ ልጅ ላይ ነበር። በህይወቱ ሙሉ ለመጀመሪያ ጊዜ ልቡን
የማረከችዉ አሳዉ ልጅ ነበረች። አሰፋ በጣም ወዲት ነበር። ታዉቃላችሁ?
**የመጀመሪያ ፍቅራችሁን ለመጀመሪያ ጊዜ ስታይዋት ልባችሁ አለመጠን
ይመታል። አካላታችሁን በሞላ አንዳች ነገር ሲወራችሁ ይሰማችኋል።
ይህም ይበልጡን ጊዜ የሚሆነዉ ፍቅሩና መሳሳቡ ከሁለቱም በኩል የመጣ
ሲሆን ነዉ።**

አሰፋንም ቅድም አይናቷቹ ላይ ሲያርፉ እንደዚያ የገዘረዉ
ያሻዉ ሆኖ ነበር። አሰፋ አወቆታል ልጅቷም ወዳዋሰች።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እንደዚሁ እንዳልነዉ ፍቅሩና መሳሳቡ ሁለቱም
ዘንድ ደናቸዉ ልጅቷ ለነፋት ያገባች ወይም የታጨች ወይም ክብሯን ብራ
ከተራ ሰዉ ጋር የሚይቀላቅላት ሆኖ ራሷን ገዝታ ፈቷን መልሳ ቦራ
ትሄዳለች። በዚህ ጊዜም ሀዘን፣ ትካዜና ቅሬታ በተገፈዉ ልጅ ላይ
ይስፍራሉ።

አሰፈንም አፉን እንዳዩ [illegible]

ቢሆን ጥሩ ነዉ። ምነዉ እናቱ ቅድም ያገባች ናት ወይም ታጭታ ወ
ወይም የራሷ ፈጽ [illegible] ሰፋ ደፋር ነዉ። እንደምታዉ
ያፋርና ሚስ [illegible] ነገር ግን እናቱ አልፈዉ ተርፈዉ
ነች አሉት። አሰፋ ይህንን ሲሊናገሩ ሲያምነዉ ወይም ሲተነስፈ
አልቻለም። ለብቻዉ በሃሳቡ እንዴት አሳ ጀብ ትሆናለች? አሳ ከሰብአዊነት
ወደ ላላ ነገር ለመለወዋ [illegible] መልአክ ብትሆን እንጂ ጅብ አትሆንም
ይል ጀመር። ደግሞስ የሰዉ ልጅ እንደት [illegible] ጅብ ሆኖ ይሄዳል? ይህ በፍፁም አልሆ ያለ አይን ያወጣ ዉሸት
ነንት የደም ስሮች ስንት ጅማቶች [illegible]
ነንገራቸዉ። ልኑሱ ግን [illegible]
እንደተቀመጡ ያህል አስርሷል [illegible]
ፊኤርሶ ዉሸት ነዉ ለማለት ደግሞ [illegible] የልጅቷን ስም ማጥፋቱ ጥርነር ነዉሩም አንፍቅቷል። የታመመ ያህን
ጊዜ እምቢ ብላዉ ይሆናል አሱን እመነትም እንደት ብላ እሺ ትበለዉ።
ስሙ እንኳን ደስ አይልም። አንዳንድ ሴዎች እንደዚህ ናቸዉ። የገዘ
ነዉራቸዉን ለመደገፍ ሲሉ የሰዉን ስም ያጠፋሉ።" አገሉ ፣ አገሉንን
**ለምን ተዉካት?**

"አዬ የእኔ ወንድም እሳማ ይኸዉልህ እንደዚህ ነች።" መገርሳም
አይጠረጠርም ። የዚሁ ብጡ ነዉ። እንዲያዉ አሳን ጥይቀያት
አግኝቼአት።

ነገር ግን እንዴት አድርጌ ልጠይቀት እችላለሁ? እማማ እንዳልሄድ
አስምላኛለች። እማማ እንዳልሄድ ያስማለችኝ ጅብ ናት ልጅን ትበላባቸለች
ብላ ነዉ። አይ እሞኟ! እነዚህ እናቶች! ነገር ግን እኔ ስዉ ጅብ
እንደማይሆን ይህችም ልጅ ጅብ እንዳልሆነች አወቃለሁ። ምን አለ ታዲያ
ብሄድ? አምላኬ! እባክህ ልሂድ? ዛሬ አንደዉ አሳን አንድ ጊዜ ስሜያት ነገ
ጠዋት ንስሃ እገባለሁ እሺ ለእንተስ አስፈቀድሁ እማማንስ እንደምን አድርጌ
እሄዳለሁ? ወደዚያ እንኳን ሄጄና ዞር ብዬ ብታይ በእሪታ ሀዘር ታስነሳለች።

ማታ ‹‹ እምን ማታ›› አለ አሰፋ ለብቻዉ ሾክ ብሎ። ማታ ሁላችንም እንደተኛን ሮባን የጋሮዉን በር ክፈትልኝ ብሎ ሂዶ ክእኒዉ ጋር አድራ ጠዋት በሌሊቱ ደግሞ እማማ እንዲታይ ሳትነሳ ተመልሼ እቤት እንዳደረ ሰዉ ንብቼ አተኛለሁ። አሁን እንግዲያዉስ እቤት ሄደ ሮባን ልጅቷን ሄደህ ማታ እመጣለሁ ብሎሻል በልና ንገራት ልበለዉ። ምናልባት ሮባም እንደነሱዉ ጅብ ናት እኔ ምንም ቢሆን አልንግራትም አናትህ ይገድሉኛል ይለኝ ይሆናል። ነገር ግን አንድ ብር ከስጠሁትና አንድ ኮት አሸልምሃለሁ ካልኩት ወዲዉኑ ይሄዳል።

አሰፋም በዚህ ሀሳቡ ፀንቶ ክዚያ ወዲያዉኑ ወደ ቤት ተመልሶ ለአናቱ ገበረ ሰሮባ ጉርሻዉን አስቀድሞ ሰጥቶ የሚያደርገዉን ሁሉ ነገረዉ። እቅዱም እንደተፈለገዉ ክአንድ አስክ መጨኬረሻ ወዲዉኑ እየተስተካከለ መሥመር መስመሩን ያዘ። አራት በልተዉ እንደተኙም አናትየዋ እፎይ ተመስገን ጌታዬ ልጀን አለባብሼ አስተኝቼዋለሁ ብለዉ የማታ ፀሎታቸዉን አድርሰዉ ወገባቸዉን መሬት እንዳስነኩ አሰፋ ሽለብ ለማድረጊያቸዉ አስር ደቂቃ ብቻ ሰጥቶ ክዚያ በኋላ ወደ ወይኒቱ ቤት ኩቴዉን ሳያስማ ሹልክ ብሎ ሄደ።

**ወይኒቱ እሱ አንካኩቶ ሲገባ ደህና ደህና ልብሷን ለባብሳ አልጋዉ** አጠገብ ቁሟ ብላ ነበር።

‹‹ቅድም ልክ ሳይሽ ..... !››

‹‹እኔም ገና ላይህ .....!››

‹‹ሮባን ስልክዉ እሺ እሺ ና የምትይን አልመሰለኝም ነበር።››

‹‹እኔም ቅድም እናትህ ክዘሩ ላይ ወደ ዉስጥ ሲያስገቡህ ሁሉተኛ የምንተያይ አልመሰለኝም ነበር።››

እንደዚህ ነበር የሁለቱ ግንኙነት ለጥቂት ጊዜ የቆየዉ፣ የአሰፋና የወይንቱ የፍቅር ንግግር በኋላም ይህ ሁሉ አልፎ ለአሰፋም የቀኑ ህልም ተፈፅሞ ጎን ለጎን ተቀምጠዉ ስሚት ስማዉ፣ እንደዚሁ ደግሞ ሌላ ላበ

ነገር ሁሉ ሲያወሩና ሲጫወቱ ቆይተዉ ሌሊቱ እንደተራመደባቸዉ እንዳስተዋሉ ደገኖ፤ ኩራዙን አጥፍተዉ ተኝተዉ ነበር።

አሰፋንም ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ክባድ እንቅልፍ ወስዶት ወይኒቱ እጅ እግሩ ላይ ተኝታ እሱ በህልሙ ክሷዉ ጋራ በደስታና ፀንስም ዘዘ አገር፣ ቡዙዙ ቦታ ሲጓዝ ያይ ነበር። ነገር ግን አሰፋ በዚሁ በያዘዉ ሁኔታ ሌሊቱን በሞላ ሳያንጋ፣ ክሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ላይ ሲሆን በርጆት ክእንቅልፉ ብንን አለ። ብርዱም ደግሞ ያለምክንያት አልነበረም። ህልሙ ቅዠቱ፣ ፍቅሩ፣ ወይኒቱ ከጎኑ አልነበረችም። ፈጥኖም ወደ [illegible] ተመልከተ። እነሆ! በሩም መቀርቀሪያዉ ወልቆ ክፍቱን ተንከርክቦ ነበር። ሰዉነቱም ያሽመዉ ጀመር። አስተኝታኝ ክዚያዉ ክጅቦቿ ጎንድ ሄዳለች ማለት ነዉ። [illegible] ወደ እናቱ ቤት ሩጫ ሲጀመር [illegible] ሚያሳዉቅ ወንበር ላይ ሲያነሳ ዘወር ብሎ እቅን ሲያደ

[illegible]ም ዘየዉ ነገር ኮረንቲ እንደፈጨዉ ሰዉ ትኩር ነገር [illegible] ላይ ነጥር በሉላዉ ጎን በኩል ክመሬት ወርዶ ወደቀ። ስሩ [illegible] ወንበር በሱሪዉ ላይ የወይኒቱ ፀጉር እንዳለ ወልቆ ተቀምጦ ነበር።

ብርድ ሳንሳት፣ ድንጋጤ አሰፋን ሰበቱት። ክዚያም ቀስ [illegible] ላቡን እያንጠባጠበ ግድግዳዉን ጥግ አድርጎ ቆመ። ግድግዳዉም ዙሪያዉን ሁሉ የጅቦች ሽክሽክ የሚያዘምት መስለዉ ‹‹አሁን እንበላዋለን... እንጉሳዉስን ... ስን!›› በዚሁ ሁኔታ ምንም ያህል ሳይቆይ ወዲያዉኑ ደግሞ [illegible] ተጎሳበሰ። እንደ መልኩም ወዲያዉኑ እቤት ዉስጥ ገቡ። አሰፋም ያለበት መልክ [illegible] መልኩም ሚማሽ ወንኑ [illegible] ነበር። አንድም ቃል አልነበረበትም። የአሰፋና የዚሁ መልክ ለጉ [illegible] መልኩም ወዲያዉኑ ቀስ እያለ እርምጃዉን ወደ አሰፋ ሸኩለ [illegible]

አሰፋም በዚህ ጊዜ የሽሽት ግድግዳዉን የሙጭኝ በሁለት እጆች [illegible] በፍርሃት ድምፅ ጮኸ።

‹‹አትብጊኝ! አትብጊኝ ኋላ! ... አ-አ- አላለሁ!›› አለ።

መልኩም ዛቻዉን ፈርቶ ሳይቀም አሁንም ዝም ብሎ እንደዚያዉ እየተረበ በቀስታ፡-

''ለምን? '' ብሎ ጠየቀዉ::

አሰፋ አሁን ደግሞ ድምፁ የማን እንደሆነ ለየ:: ድምፁም የሷዉ የወይኒቱ ነበር::

''ጅብ ነሽ! '' እናቴ ስለ አንቺ የነገረችን ነገር ሁሉ እዉነት ነዉ:: አትጠጊኝ አትጠጊኝ ብያለሁ ኋላ! ''

ወይኒቱም በዚህ ጊዜ ከአሰፋ ዘንድ ተመልሳ ወደ አልጋዋ እያዘገመች ፯ሳ ባግርጌዉ ላይቁጭ አለች:: እንባም በጉንጮቿ ላይ ወዲዉኑ ይወርድ ጀመር:: ትንሽም በዚሁ ሁኔታ ዝም ብላ አንገቷን ደፍታ ስትንሰቀሰቅ [illegible] ወደ አሰፋ ተመልከታ፡-

[illegible] አንተም እንደሰዎቹ ጅብ ነሽ አልከኝ? ምን ኖሯል ሌሊት አቅፈሽኝ በክንዶችሽ ላይ ሳለሁ የነገርከኝ? መፅሐፍ ቅዱስ፣ ሳይንስ፣ ሰዉ ጅብ እንደማይሆን ያስረዳኛል:: ማንም ጅብ ነሽ ቢልሽ እኔ ከቶ አልልሽም አላልከኝም? አሁን ታዲያ...! ''

''አዎን ሌሊት እርግጥ እንደሱ ብዬሻለሁ:: ነገር ግን ማየት ማመን ነዉ:: አሁን እራሴ በአይኔ አየሁሽ:: ጅብ ነሽ::

በዚሁ ጊዜ ወይኒቱ ከልቧ ተንስቅስቃ፡-

''የለም አሰፍዬ አይደለሁም:: '' አለችዉ::

'' እንዴት አይደለሽም? እሺ ምንድን ነዉ ይኸ ራስሽ? ፀጉርሽስ እንዴት ቢሆን እነደዚህ ወለቀ? አንቺስ አሁን የት ነበርሽ?

አሁን ደግሞ ወይኒቱ ቀና ብላ እንባዋን ከፊቷ ላይ ጠራርጋ፡-

''እሺ ስማኝ አሰፍዬ ልንገርህ እንግዲያዉስ የት እንደነበርኩ:: ፀጉሬም እንዴት እንደዚህ እንደወለቀ:: '' አለችዉ:: ''አሁን ከአጠገብህ ያጣኸኝ ወደኋር ወጥቼ ነዉ:: ፀጉሬም እንደዚህ የወለቀዉ፤ የራሴ የተፈጥሮ አይደለም::

በዚህ ንግግር አሰፋ ደንግጦ፡-

ኧ!'' አለ ::

አሁን ደግሞ ወይኒቱ በጣም አልቅሳ፡-

''አዎን አሰፍዬ ስማኝ ታሪኬ ይህ ነዉ::'' አለችዉ::

''እናቴ ባሏ የእኔ የልጅዋ አባት ወዲያዉ እንደተወለድኩ ምቶባት ችግርና ማጣት በዚህ ዓለም ከፉኛ ያንገላታት ድሃ ሴት ነበረች:: የሚላስ የሚቀመስ ስላልነበረ እየዞረች ትለምን ነበር:: አንድ ቀን በተወለድኩ በአሙቱ እኔን ብቻዬን ከቤት ዉስጥ ዘግታብኝ እሷ ቃርሚያ ሄዳ ነበር:: ለካስ ፈቀቅ ብሎ ከተኛሁበት መደብ ስር የተዳፈነ ረመጥ ኖሮ ተንከባልዬ በአናቴ ወድቄበት ራሴ በሞላ ተጠበሰ:: እንደአጋጣሚ በዚያ በኩል ከሚያልፉ ሳዎች አንዱ ጩኾቴን ሰምቶ ባይደርስና ባያተርፈኝ ኖሮ ነድጂ አቀር ነበር:: ከዚያም ሆነ እናቴ ወዲያዉኑ ይዛኝ ጠፍታ አዲስ አበባ ገባች:: አዚያም ብዙ ሃኪሞች ዘንድ እየሰመነች ደርሳ እራሴን አሳየቻቸዉ:: ሁሉም ይኸ ፈፅሞ ተቃጥሏል:: ሁለቱኛ ፀጉር የሚሉት ነገር አያበቅልም አሏት:: እሷም እኔን ያለልክ ትወደኝ ነበርና መጨረሻ የሄደችበት ሀኪም እግሩ ላይ ወድቃ ምርር ባላ ብታለቅስባት ትልቅ ስትሆን ወደ እኔ ዘንድ አምጪያት አላት:: እናቴም ሳትርቅ ለዚያዉ ሀኪም ግርድና ገብታ ትሰራ ጀመር:: እኔም ሌላ ቦታ ላይ እሳት ስላልነካኝ ይህንኑ እራሴን ብቻ በቆብና በሻሽ እየሸፈንኩ አደርኩኝ:: በአስራ አምስት አመቴም ሀኪም ለእናቴ በሰጣት ተስፋ መሰረት ይህንን ፀጉር ከሀገሩ ተላልኮ አስመጥቶ ሰጠኝ:: ስለዚህ ማታ ማታ ስተኛ ከቀን ብዛት ከመኝታ የተነሳ ተሰባብሮ እንዳያልቅብኝ አዉልቄ አኖረዋለሁ::''

አሰፋም በዚህ ንግግር ልቡ ተነካ:: ወዲያዉኑ ወደ አልጋዉ ጠጋ ብሎ ፀጉሩን ከሱሪዉ ላይ አንስቶ በኩራዙ መረመረዉ:: እዉነትም ፀጉሩ ወይኒቱ እንዳለችዉ በሰዉ እጅ የተጎነጎነ ሰዉ ሰራሽ ነበር:: የአሰፋም እንባዉ ተንቆረዘዘ:: ፀጉሩን አልጋዉ ላይ አስቀምጦ ራሷን ደግሞ ሊያይ ኩራዙን ይዞ ወይኒቱን ተጠጋት:: እነሆ! እሱም እንደዚያዉ እሷዉ እንዳለችዉ በሞላ በእሳት የተቃጠለ ጠባሳ ነበር:: አሰፋም እንባ አነቀዉ:: ከንፈሩም ተንቀጠቀጠ:: ኩራዙንም ከቦታዉ አስቀምጦ መጥቶ ወይኒቱን በደረቱ ላይ ጥብቅ አድርጎ አቀፋት:: ሁለቱም አንገት ለአንገት ተያይዘዉ እኩል ተንሰቅስቀዉ አለቀሱ::

ምንጭ ታደሰ ሊበን፣ መስከረም ከሚለዉ የአጭር ልብ ወለድ
መደብለ ዉስጥ ተወሰደ ወጥ አጭር ልብ ወለድ

ማብራሪያ ሀሳብ

አጭር ልብ ወለድ በእጅጉ በተመጠነ ጊዜና ቦታ በሚንቀሳቀሱ ጥቂት (10) ባህሪያት ድርጊቶች አማካይነት ወደ ነጠላ ዉጤት መጣደፍ አለበት። ይህ አካሄድ ገና ከአጀማመሩ መወሰን የሚያሻዉ ነዉ። ለአጭር ልብ ወለድ አጀማመር የተወሰነ ህግ ባይኖረዉም ገና ከመነሻዉ የታሪኩን ሂደት የሚጠቁም የአንባቢን ስሜት የሚስብና የሚያጓጓ ማስተዋወቂያ ሊኖረዉ እንደሚገባዉ ይታመናል። ማስተዋወቂያዉ ከቀሪዉ ታሪክ ጋር የጠበቀ ቁርኝት ያለዉ ለታሪኩ ፍሰት አስተዋፅኦ የሚያደርግና ዋናዉን ገፀባህሪ የሚያስተዋዉቅ እንዲሆን ይፈለጋል። ከዚህ አንፃር ''የጅብ ነች'' አጀማመር ስናጤነዉ ዋናዎቹን ነጥቦች ይዞ እናገኘዋለን።

የመጀመሪያዉ አንቀፅ ዋናዉን ገፀባህሪና መቸቱን ያስተዋዉቀናል። ቦታዉ ሸኖ፣ ቀኑ ቅዳሜ, መሆኑንና አሰፋ የተባለዉ ሀያ አመት የሞላዉ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ እናቱን ለመጠየቅ መምጣቱን እንገነዘባለን። በዚህ የመጀመሪያ አንቀፅ የተሰጡንን ነጥቦች ይዘን ነዉ ታሪኩን ለመከታተል የምንዘጋጀዉ። በታሪኩ ሂደትም አሰፋ እንደ ሃያ ዓመት ወጣት በዘመኑ እንዳለዉ እንደ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪ ሲሆንና ድርጊት ሲፈፅም ማየት እንፈልጋለን።

## መልመጃ

''ጅብ ነች'' የሚለዉን አጭር ልብ-ወለድ መሰረት በማድረግ ጭብጡን፣ ገፀባህሪዉን መቼቱን፣ ታሪኩን፣ ግጭቱን፣ ሴራ/ትልምን ፣ አንግር በተናጠል ለማየት ምክሩ። በመቀጠልም መምህራችሁ ሥራችሁን እንዲገመግሙላችሁና አብራርተዉ እንዲያስረዷችሁ አድርጉ።

## ምንባብ አንድ

የልጃገረድ ጡት የመሰለዉ የሐመር ተራራ አፈዘዘዉ ። እና ያን ማራኪ ተራራ በአይኑ ጠባዉ... በሀሊናዉ አኘከዉ ጸ አጥ ጸ እያደረገ አጣጣመዉ።

ከቡስካ ተራራ ላይ ሆኖ የሀመርን ምድርና ቀዬ ፣ ከአድማስ ወዲህ የአስሌንና የቡሜን ተራራ ፣ በየኮረብታዉ ላይ የሚታዩትን የሀመር መኖሪያ ቀዬዎች እየተጠማዘዘ ከቡስካ ተራራ ስር ጀምሮ ቁልቁል ወደ ለም ወንዝ የሚጓዘዉን የከስኬን ወንዝ በአረንጓዴ ልምላሜ የተዋበዉን የሀመርን ጫካ ሊቃኝ፤ የከብቶቹን ግሳት ሲያዳምጥ ስሜቱ ዋለለ።

ደልቲ ዉስጡ እንደዚያ በደስታ ቢተራመስም ዉጫዊ እርጋታዉ ያዉ እንደወትሮዉ ነዉ። ዝም ! ጅንን።

አንባቢዉ በአዕዋፍ ድምፅ፤ በሽምልማል ንፋስ ሽዉሽዉታ ከዛፍ እዛፍ እየተንጨዋለሉ በሚቦርቁት ጉሬዛና ጦጣዎች... ደምቋል።

ደልቲ ገልዲ ዝግባ፤ ግራር፤ ጥድ... ካሰዋበዉ የቡስካ ተራራ ላይ ሆኖ የአባቱን ምድር የሐመርን ዉብ ተፈጥሮ ሊቃኝ ቆይቶ ከቆመበት ቦታ በስተግራ በኩል ካለችዉ ዉብ የግራር ዛፍ ስር ሄዶ በርኩታዉ ላይ ቁጭ አለ።

ገሃዱ አለም ላይ ዋና ፣ ሥራ፣ ጉዞ፣ ፍቅር፣ ጥላቻ...ይሆንና በሀሊና ከረጢት ደግሞ ትዝታ ይከማቻል። ትዝታ፣ ህልም፣ ትዝታ ... ምንም ከዚህ ክስተት ሊያመልጥ አይችልም። በገሀድ የፈፀመዉን በትዝታ ሞስሳ ያየዋል። ከዚያ ይፍነከነካል ወይ ይቆዝማል፣ ይቅበጠበጣል።

ወይ ይሸማቀቃል፣ አልያም ይስቃል ወይ ያነባል... ትዝታ! የተጻፈነዉን እዉነት እየጫረ ስሜትን ይለዋዉጣል።

ደልቲ እንዲህ ከተዋበዉ ስፍራ ዉስጥ ሆኖ ዛሬን ከገዛ ተቋድሶ ትናትን አለማት። ህልሟ ትናንት ደግሞ የትናንት ግሳንግሷን ይዛላት ከፊት ለፊቱ ተደቀነች። ጨዋታ፣ ጭፈራ፣ ጀግንነት፣ ፍቅር... አንዱ በሌላዉ ላይ እየተነባበረ ታየዉ። ገሃዱን አለም ከምናባዊ ትዉስታዉ ጋር አንዳንዴ

እየተጋጨ ሌላ ጊዜ እየተዋሃደ ተመለከተዉ የህይወት ዑደት የተፈጥሮ ባህሪ አንዱ ሌላዉን እየተካ ብት ጥልቅ እያለ ሲያልፍ ህሊናዉ የትናንት ትዝታዉን ወደኋላ ሲያጠነጥን ለማየት ተከተለዉ::

ጦጣና ጉሬዛዎች ከዛፍ ዛፍ እየዘለሉ ሲቦርቁ፤ አዕዋፍ ሽቅብ እየጓኑ ቁልቁል ሲወረወሩ የደልቲ የቦዙ አይኖች የሚያዩት ትናንትን ነዉ:: የትናንት ትዝታ ከሁሉም ገዝፎ በህሊናዉ ተንሰራፍቷል::

በዚህ የትዝታ ማቅ እየተዘፈቀ የቦዙ አይኖቹ እንግዳ ነገር ተመለከቱ አይኑ የሚንቦገቦግ ቀንዱ የሾለ፣ ሰዉነቱ የሚያንፀባርቅ ... ግን የደነበረ አዉሬ፤ ሰዉነቱ የሚንቀጠቀጥ መሸሽ ደግሞ ያቃተዉ አዉሬ::

ደልቲ ከትዝታ ማጡ ያለ የሌለ፣ ሀይሉን አስተባብሮ በመዉጣት የያዘዉን ክላሽንኮቭ በአዉሬዉ ግንባር ላይ አነጣጥሮ አመልካች ጣቱ ቃታዉን ከመሳቧ በፊት ስሜቱ ሲጣራ፣ ወስፋቱ ሲጮህ ሰማዉ:: የተጠበሰ ስጋ፣ ወጠጤ ጥብስ ትዝ አለዉ... ጎመጀ :: የራበዉ ሰዉ የሚበላ ሊመጣ አይገፋም:: ያዉም ካዉሬም የድኩላ ስጋ ምራቁ በአፉ ሞላ::

ድኩላዉን ከማሰናበቱ በፊት በመሣሪያዉ የማነጣጠሪያ ቀዳዳ ለመጨረሻ ጊዜ ተመለከተዉ:: ተሸብሯል፣ ፍርሃትም ያንዘፈዘፈዋል፤ ''ለማምለጥ መሞከር ሲገባዉ ለምን ተገትሮ ቀረ? አይኖቹስ ለምን ይማፀኑኛል?'' አለ በማይሰማ ድምፅ::

ደልቲ ግራ ገባዉ:: ቀጭኔ፣ ጎሽ፣ አንበሳ... ሲገድል እየተሯሯጠ አንዱ ለማምለጥ ሌላዉ ለማስቀረት እየተጣጣረ ... እየወደቀ ... እየተነሳ ... ነበር:: ድኩላዉ ግን አልተንቀሳቀሰም አልሮጠም ታዲያ ደልቲ እንዴት ደንግጦ የቆመ እንስሳ ይገድላል:: እንዴትስ ለሆዱ ብሎ ተሸብሮ ከፊቱ ለፊት እንደ በግ ቆሞ የሚማፀነዉን አዉሬ ገድሎ የአባቱን የጀግንነት ባህልና ታሪኩን ያበላሻል::

ዘገነነዉ፣ የራሱ የሆኑት ፍየሎች፣ በጎችና ከብቶች ታሰቡት:: የስጋ አምሮት የአባት ባህል በስሜትና በህሊና ትግል ዉስጥ ከተቱት:: ስሜቱ በለዉጥ ጥብስ ብላ አለዉ:: ህሊናዉ ፈርቶ ደንብሮ ጉያ ዉስጥ የገባዉን አዉሬ ተኩሶ መግደል የጀግና ሙያ አይደለም:: የመልካም ስም የደግነት ስራ ጠላቱ ከርስ ነዉ:: ሆዳምነት! እና ተወዉ አለዉ::

ደልቲ ይህን እያሰበ አይኖቹን ከድኖ ሲከፍት ደነገጠ:: ተምታታበት:: ድኩላዉ ከፊት ለፊቱ የለም:: በእሱ ቦታ የተተካዉን ማመን አቃተዉ:: አይኖቹን ጨፍኖ እንደገና ከፈታቸዉ:: ለዉጥ የለም:: ድኩላዉ የለም:: እሱን የተካዉ ግን ከፊት ለፊቱ ቆሟል::

'' ምን ጉድ ነዉ? '' ደልቲ ተሻበረ:: የሚያየዉን ማመን ተሳነዉ:: አይኖቹን ደጋግሞ እየከደነ ከፈታቸዉ:: አዎ! ቅዠት አይደለም:: እዉነት ነዉ:: ከፊት ለፊት የቆመዉ ሰዉ ነዉ:: ልጃገረድ ... ያዉም የደም ገንቦ::

ድኩላ ... ልጃገረድ ... ድኩላ ... ልጃገረድ... ህሊናዉ እዉነቱን ለማጣራት ሞከረ::

'' ለምን መጣች? ምን ጉዳይ ይኖራት ይሆን? ድኩላዉስ ለምን ቆመ? ለምን ደነገጠ? የትስ ሄደ? ለምን በእሱ ቦታ እሷ ተተካች ... '' ራሱን ለማሳመን ማጣፊያዉ አጠረበት::

ምንጭ ፍቅረ ማርቆስ ደስታ ኢሻንጋዲ

ገጽ 1-3

ከላይ የቀረበዉ ምንባብ የፈጠራ ስራ ነዉ:: ስነፅኹፋዊ ፈጠራ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ሌላ ምንባብ ይቀርብላችኋል:: በሁለቱ ምንባብ መካከል ያለዉን ልዩነት ለመረዳት ሞክሩ::

## ምንባብ ሁለት

ስነፅሑፍ በቋንቋ ትምህርት ዉስጥ የሚያበረክተዉን ከፍተኛ አስተዋፅኦ አስመልክቶ በርካታ ምሁራን ጠንካራ አስተያየቶችን ይሰነዝራሉ:: (ፈቃደ 1988፤ ሙሉ እመቤት 1989፤ ኮሴይና ስላተር 1987፤ ሂል 1986) :: ስነፅሑፍ በየትኛዉም ደረጃ ለሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት እዉነተኛና ተጨባጭ አዉድን እንደሚፈጥር ምሁራኑ በአፅንኦት ይገልፀሉ:: እንደ ፈቃደ (1988) እንደሚያስረዳዉ በስነ ፅሑፍ ሀሳብን በተሻለ መንገድ መግለፅ

ሀ. ሀገሪቱ ከምትከተለው ፖሊሲ አንጻር ሲታይ ከሚከተሉት ውስጥ ትክክለኛው የትኛው ነው?

ተናኜ ለደቂቃዎች በምታየዉ ነገር መንፈሷ ቢዝናናም ተመልሳ ግን ጭንቅንዝ አለት። አባቷ ግንባሩን ኮስተር! ኒሙን ፈተል... አያጀሪገ ያዝጂሳን ተራራ በርትት ያያል።

"እንስሳትን ይወዱ ነበር" ስለሚባሉትና ዝጂላ ላይ ለዘመናት ስለናሩት አቡነ ገብረመንፈስ ቅዱስ አሰቡ። ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለሦስት ሙቶ አመታት ምንም ሳይመገቡ ለእንስሳት ይፀልዩ የነበሩና እንዲ እንዲያዉም የተጠማች ወፍ አጋጥሚቸዉ እንባቸዉን እንድትጠጣ የማድረጋቸዉ "አፈ ታሪክ ይሆን እዉነት" አያዉቆብበም ብቻ ትዉስ አለዉ።

ክዚህ ዉጭ ስለ አቡቃብ የተባቡ ሌላ ነገር አሰቡ። ጀርመን ፣ሀገር ጠዝናት በተሣፈ መፅሐፍ ገብረ መንፈስቅዱስ ኢትዮጵያ ዉስጥ የሮሩ እርመኒዊ ናቸዉ "ብለዉ ትዉስ አለዉ። ፈገግ አሉ። እቻሜ "ዋሩ ግሩ ስለዉርፕዉያን" ብሎ በህሊናዉ እሹር ልጅን ተመለከታት... ተናኜ ገደ ግርጥት ብሏል።

"... ይሽዉ ራሴን ክፈትኩት፣ ስለ እኔና አንተ የሚናገር ሰነድ በዉስጤ የለም። እንደቆረፈደ ቆዳ ብቸኝነት ለምን ጨባበጠን... ወንድዬ? አንተ ማነህ? ... እኔስ ብሆን ማን ነኝ ልበል አለችዉ አባቷን በአይኗ ማየቱ ክብጂት መሬት መሬት እያየች።

እቻሜ በልጅ ሺህ ጥያቄ መጠየቁ ልማዱ ነዉ። የዛሬዉ ጥያቄ ግን አዲስ ሆነበት። የልጅ ጥያቄ ህሊናዉን ፈንክቶ አሳመመዉ፣ አስደነገጠዉ፣ አርበተበተዉ።

"ምን አንዲልሽ አዉቀሽዋል?" ብሎ ክተቀመጠበት ተነስቶ ክጠዋታ የህሀይ ፎራ ፊት ለፊት ቆመ። ታጠሉዋ አልተሰማዉም፣ ዉስጡ በብርድ ተዉጦ እየተንዘፈዘፈበት ነዉ። ማን ነኝ? ማን ነህ? አነማን ነን?..." ጥያቄዋ አዕምሮዉን አፈዘዘዉ፣ አካሉን አዛለዉ።

የሰዉን ልጅ ክዱላ ይልቅ አካሉን የሚያደቀዉ፣ ሞራሉን የሚፈታተነዉ፣ እንደአይጥ ወደጉድጓዱ የሚያስርጠዉ ካለዚያም እንደአንበሳ የሚያንገላሰዉ መልካምና መጥፎ ህሳብ ሲሰማ ወይም ኪሱ ሲጎድልና ሲሞላ ነዉ።

በራሳችን ጠንካራ እምነት አለን ባሮች ሁለተኛዉን ክመጀመሪያዉ ጋር ሲያወዳድሩ ሳይመጥን የተሰቀለ ተራ ነገር ያደርጉታል።

ሌሱች የዋጋ ተመን ይገባናል፣ "በዚህች አለም ላይ ያለ ነገር ሁሉ የሚሸጥና የሚገዛ ነዉ የሚሉት ደግሞ ሰዉን ጨነኛና በሽተኛ የሚያደርገዉ ኪሱ ነዉ፤ ሌላዉ ነገር ሁሉ እንደኑግ በገንዘብ ሲወቀጥ የሚችለጠጥ አልባሉ ነዉ" ይላሉ።

ለመኖር የሚገዛና የሚሸጥ አለ፤ ሰዉ ግን የሸቀጥ እቃ አይደለም፣ ገንዘብ ክገዛዉ ሰዉ ላይሆን ሱቅ ላይ የሚደረደር ሻማና ክብራት ማለት ነዉ ብሎ ያምናል አቻሜ ክመጀመሪያዉ የአስተያየት ሰጭዎች ጎን ሲሰለፍ ይህ እምነቱ ግን እየበሳሳዉ ካለዉ የልጁ ጥያቄ ሊገላግለዉ አልቻለም።

"እሳ ክየትኛዉ ናት...? መልስ የጎደለዉ ጥያቄ ራሱን ጠየቀ።

ስለዚህ ለጥያቄዋ መልስ ለመስጠት የጠዋታን ጨራ ተማፀናት፣ ክዚያ አረንጓጁዉን ሳር በጥንቃቄ እየረገጠ ተንጎራደደ መላ ለመፈለግ፣ ፍርሃቱ መጨመር እንጂ መዉጫ አለመኖሩን ስላወቀ ለዘመናት እንደ ማር መረጎ ያናረዉን ምስጢር ለመክፈት ወስኖ ወደ መቀመጫዉ ተመለሰ።

ተናኜ ፊቷ ቅጭም ብሏል። ፀጉሯ በሚነፍስዉ ነፋስ ክተጋጠረበት እየለቀቀ ይዉለበለባል። ማወቅ የምትፈልገዉ ጥያቄ ህሊናዋ ዉስጥ እንደወታደር በሰልፍ ተሰትሮ አሳርፎ ... ተጠንቀቅ ... ይባባልባታል።

እስክ ዛሬ የሚታዉቃቸዉ ብዙ ነገሮች አሉ። አባቷን ላለማሳቀቅ ግን ጥያቄዎቹን እንይወለዱ አድርጋ አርግዛቸዉ ኖራለች። አሁን ግን እንደ አሸን በዉስጧ በመራባት ጭንቅላቷን በስተዉ ክንፍ አዉጥተዉ በረሩባት...

ለማታዉቃቸዉ ነገሮች ምላሽ ካላገናኘች ስታይዋ ከሦትችለዉ በላይ እንዳይሆንባት ሰግታለች። በአርግጥ አባቷ ሊያዝን፣ ሊሸማቀቅ ይችላል። ግን ደግሞ አቅሟን መረዳት እንዳለበት ታምናለች። ምንም ቢሆን ክእሳ እሱ ይጠነክራል...

ነዉ። በዚህ አጋጣሚ አባቷ የከደናቸዉን አይኖቹን ገልጦ መናገር ቻመረ።

ወንድ አያቱ ፒር ነጋርሽዛ ይባላል። ፒር ነጋርሽዛ ስሜን ምዕራብ ህንድ ጉጅራት ዉስጥ መለስተኛ የከበረ ድንጋይ ማምረቻ ከፍቶ በእጥር ...

ሙሉዉ ሥነ - ...

"አዝናለሁ ወንድዬ! ... የጊዜ ዑደት እንደፈረሰኛ ጧሃ እያዳፋ እንተ

"ወንድማለም፣ ልጅ ናት ብሎህ እሁንም ታስነሳህ"? አለኝዉ እንደትቧ እንደበድን አለስልሳ ብትሆኝ ደስ ይለኝ ነበር። ማንም አባት ልጁ ቶሎ መንፃራቷን አምናአይቀበልም። እኔም ስትሉቹ ያላደገቺት አትክልቱ ሮጣ አፍርታ ሮጣ እንድትደርቅ ... አልመኝም። ሰዝዙ ጊዜ ለምልማ እሸት ሆና ዘንፈል ቱለኪ... ስትል ማየቱን አመረጣለሁ!" አላት።

"አዝናለሁ ወንድዬ! ... የጊዜ ዑደት እንደፈረሰኛ ጧሃ እያዳፋ እንተ ወደማትፈልገዉ ኩላ አድርሶኛል። አሁን ከላዉ ላይ ከመፈተሽ በፊት እኔ ራሴን መፈተሽ አለብኝ። ለዚህ ደግሞ የሚስጢሩ ቁልፍ ያለዉ አንተ እጅ ነዉ... ልጅህ አይደለሁም? ... እንደ ሴት እህት ምስጢረኛዬ አንተ አይደለህም?... ማነህ አንተ? እኔስ ... ማንኛዉ? መታወቂያዬን ስጠኝ?" አለችዉ እንባዋ ባይኖችዋ እየተንቸረፈፈ።

"መጠየቅ የማፍቀዉ ዘር ነዉ? ሲያሻሽ፣ ሃኒ እ ...ር አያባጋ መከፈቱ የማያመጣዉ የክህቸን አለም ማራኪ በደዉ አስተያየኒ እዉነታ የሚያየዉ... ሀሲናሽ የመጠየቅ ብረተ ለድልድይ መስሪያ ሲዘጋጅ ነዉ። የሚገርመኝ ግን እኔ የአንቺን አጥፍ እድሜ ናሮኝ እንኳን ስለማንነቴ የማልጠይቅ ጅል የነበርሁ መሆኔ ነዉ..." "ሲል፦

"ቢቃህ ወንዲ! ... ጊዜዉ አናጥፋ ... ዛሬ በሚያስፈልገድቅ አዉቅልህ እንደ ሁል ጊዜዉ እየቦረቅሁ እንዲያሸልበኝና አንተም አጋድመኝ እንድትሄድ አልፈቅድም፣ ይህ ዛሬ አይሆንም" አለችዉ ምርር ብላ።

አቾሜ ልጁ ነዘመኗ እንደ ፈንጣ ዘላ ወዳልጠቆቀዉ የህሊና ብስለት መድረሷን ተረዳ፣ ተይ ሊላት እንደማይችል አመነ። ተናኜም ብትሆን አባቷ እንደዶሮ ጫጪቱት ቅምጣ የደፋበትን ምስጢር ለምን ሊነግራት እንደማይፈልግ ግራ ገብቷታል።

የአባቷን ምስጢር አዉቃ ልታግዘዉ፣ ይበልጥ ልትቀርበዉ ቁርጣለች። ያን ለማድረግ ግን ከፍቶ እንዲነሳላት የምትፈልጋቸዉ ነገሮች አባቷ ህሊና ዉስጥ አሉ። ያን አለማወቋ ከአባቷ ጉያ እየገፈተራት



ትንሹ ኡቦያ እስከ ስምንተኛ ክፍል ድረስ ኩተግረ በኋላ በአባቱ ድንገተኛ ሞት ምክኒያት ትምህርቱን አቋረጠ። "አባቴ ከሞተ እናቴን፡ወንድሞቼን፡እህቶቼን ማን ይረዳቸዋል"? ብሎ አሰበ። እነሱ ከሚችገሩ ትምህርቱን ትቶ ወደ ሀገሩ መመለሱን መረጠ። እንዳሰበውም ደብተርና መፃህፍቶቹን ይዞ ጓዝ ጉዝጓዙን ጠቅልሎ ወደ ትውልድ መንደሩ ተመለሰ።

ከዚያም ቤተሰቦቹን ሲረዳ ቆየ። የኋላ ግን እርሱም ትዳር መስርቶ የራሱ ቤተሰብ ኃላፊ ለመሆን በቃ። በመንደሩ ውስጥም የሚወደድና የሚከበር ሰው ሆነ።

የመንደሩ ገበሬዎችና ሌሎች ሰዎች አቶ ኡቦያን በብልሀነቱና በጨዋታው ይወዱታል። ያከብሩታል። ስለ ሥራቸው ስለ ሌሎች ጉዳዮች ያማክሩታል። እሱም የሚያውቀውን ያህል መልስ ይሰጣቸዋል ከእነሱም ብዙ ነገሮችና ልምዶችን ለመማር ይጣጣራል።





ሀገሪ በተማ ውጣ ብላ የምትገኝ የጠጠሌ መንደር ናት። የተፈጥሮ አቀማመጧም ገራገር ይሰባል። በመንደሯም ቀን እርስ በእርስ የተያያዙ ጋራዎች ይታያሉ። በደንብ ለተመለከታችሁዋትና ሌሊት ቆመው የሚጠብቁ ዘቦች ይመስላሉ።

ከጋራዎቹ ዝት ብለው የሚገኙ ሰፋፊ ቦታዎች ዳገት ቁልቁለትና ገደላ ገደል የበዛባቸው ናቸው። ለልጆች ዘፈንና ጨዋታ የምትቀልደው የገደል ማሚቱም የምትገኘው በዚሁ አካባቢ ነው። ከዚያ ዝት ሲል ደግሞ ለተ ያለ ሜዳዎችና ሸለቆዎች በየቦታው ይታያሉ።

አንዳንድ የቦንጋ አካባቢዎች ነፋሻማ ናቸው። አብዛኛዎቹ ያሞቃሉ። ይህ የአየር ንብረት ለሰዎች፡ ለእንስሳትና ለዕፅዋት ተስማሚ ነው። ለም አፈሯም ለአካባቢው ገበሬ [illegible] ረድቷል።

[illegible] አቶ ኡቦያ ይባላል። ዛሬ እድሜው አርባ አምስት [illegible] ካላቸው ከወ/ሮ አቮላ አንድ ወንድና አንድ ሴት ልጆች ወልዷል። አቶ ኡቦያ [illegible] ጋደገው በአሳዳጊ ቤት ነበር። ያኔ ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ እያለ አንቱ ወደ [illegible] መንደሩ መጥተው ነበር። እዚያም ትንሽ ከሰነበቱ በኋላ ከቤተሰቦቹ ጋር ምክር አደረገ። ኡቦያ ብልህ ልጅ ስለሆነ ዘመናዊ ትምህርት ቢማር ጥሩ ነው። እኔ የምኖረውም ኩተማ መሰጀ ባስተምርላችሁስ? ብሎ ወላጆቹን ጠየቀ። እነሱም በጉጉት ተስማሙ። ኡቦያ ዘመዶቹንና ጓደኞቹን ተሰናብቶ በልጅነቱ የትውልድ መንደሩን ለቆ ሄደ።

ከዕለታት አንድ ቀን እሱና ጎረቤቶቹ ከዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው ይጨዋወቱ ነበር። በዚህ ጊዜ ኡቦያ ብድግ ብሎ ከመንደሩ ውስጥ ታዋቂ ከሆኑት አዛውንት ወደ አቶ ኡጁሉ ዞር ብሎ እርሶ ወጣት በነበሩበት ጊዜ መንደራችን እንዲህ እንደዛሬው ነበረች እንዴ? እስኪ እባክዎን ያኔ ምን እንደምትመስል ይንገሩኝ ብሎ ጠየቃቸው።

አቶ ኡጁሉም ትንሽ ትከዝ አሉና "እህ" እህ!" ብለው ጉሮሮአቸውን ጠረጉ። ከዚያም ልጄ ምን ትመስል ነበር አልከኝ? መንደራችን እንዲህ እንደዛሬው ስትራቆትና አመድ ሳትለብስ ያኔ በኛ ጊዜማ ማለፊያ ነበረች። አሉና ይተክዙ ጀመር። ቀጠል አድረገውም "ይኸውላችሁልጆቼ ያኔኮ መንደራችን ልዩ ነበረች። አዝመራው በሚዳው ላይ ፍራፍሬው ጓሮው ሲታይ ያስትመኝ ነበር። ታዲያ ምን ያደርጋል? ያ ሁሉ ቀረና ..." በማለት ንግግራቸውን ቁም አደረጉ።

ከተሰበሰቡት የመንደራቸው ሰዎች ውስጥ አንዱ ብድግ አለና ታዲያ እኛና ልጆቻችን ምን ስላደረግናት ነው ዛሬ እንዲህ ጓዳ ተራቁቶ አራዊት ከአገር ተሰደው ባዶ የሆነችው? ለኛ ነዋሪዎቹ ምህረት የማትሰጠን ብሎ በስሜት ጠየቃቸው። አዛውንቱም እርሷ የሁሉም መኖሪያ ናት፤ የሁሉም መሰብሰቢያናት። ነገር ግን "ሰብሉ አንድ ማሳ በላተኛው ሀምሳ" እንደሚባለው ነው። በማለት መለሱለት።

እሳቸው ወጣት በነበሩበት ጊዜ የመንደሯ ነዋሪና እንስሳቱ ቁጥር መጠነኛ፣ እንደነበረ፣ ጋራና ሸንተረሮችም ጥቅጥቅ ባለ ደን የተሸፈኑ እንደነበር አወጉት። በውስጣቸውም የተለያዩ የዱር አራዊትና ዓእዋፍ በሰላም ይኖሩ እንደነበር ነዋሪውም የአርሻ ቦታ ለማዘጋጀት ሲል ሳሜካውን በመመንጠር አራዊቶችን መግቢያ መጠለያ በማጣታቸው እንደተሰደዱ በሰፊው አብራሩለት። ወራጅ ወንዝና ምንጮች ያኔ አካባቢውን ሲያለሙና ሲያለመልሙ እንደነበር አወጉት።

አቶ ኡቢያና ሊሎቹም የመንደሩ ገበሬዎ ባዛውንቱ አነጋገር ልባቸው ተነካ። ሁሉም የዛሬዋንና የቀድሞውን መንደራቸውን በሀሳባቸው ያነፃፅሩ ጀመር። በተለይ አቶ ኡቢያ ሰብሉ አንድ በላተኛው ሀምሳ የሚለውን አባባል ይዘው እንደፀሎት ሲደጋግሙ ሰነበቱ።

ምንጭ፡- ሰብሉ አንድ ማሳ በላተኛው ሀምሳ

ከሺበሽ ለማ

ለማስተማሪያ ተሸሽሎ የቀረበ

1. የላኪው ሙሉ አድራሻ
2. የተቀባይ ሙሉ አድራሻ
3. ሰላምታ / መግቢያ/
4. ሐተታ / ዝርዝር ጉዳይ
5. መደምደሚያ
6. ፊርማ

መልመጃ አራት

1. በምንባቡ ውስጥ "ፈሪ ለእናቱ" የሚል አባባል ተጠቅሷል አባባሉን ከሰዎች ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ።
2. በተሰጣችሁ ደብዳቤ አፃፃፍ ስርዓተ መሠረት እናንተም የህይወት ገጠመኛችሁን እሩቅ ሀገር ላለ ጓደኛችሁ ፃፉና ክፍል ውስጥ አንብቡ።
3. በሰላምታ ደብዳቤና በስራ ደብዳቤ መካከል ያለው ልዩነት ዝርዝር አድርጋችሁ በፅሐፍ አቅርቡ።

## ከበሮ ሲያዩት ያምር

በአንድ ሀገር ውስጥ በጣም ተዋደውና ተስማምተው የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ። ትዳራቸውን አቃንተው የሚኖሩት ሴቷ በቤት ውስጥ ስራ ተወስና አባወራው ደግሞ ከውጭ መራቱን እያረሰ በሚያገኘው ገቢ ነበር።

ከለታት አንድ ቀን ባልየው በትንሽ ነገር ተቆጥቶ እኔ በእርሻ ደክሜ ከበሬ ጋር ስገባላታ እውላለሁ አንች ቤት ውስጥ የፀሐይ ቃጠሎ ሳይነካሽ ተቀምጠሽ ትውያለሽ ይህ ጎደለ ይህ እነሰ እያልሽ ትናገሪያለሽ ብዙ በሆነው ባልሆነው ይግረር ጀመር። በዚህ ጊዜ ባለቤቱ እባክህን አትግረር እኔ የምሰራውን ላንተ አንተ የምትሰራውን ለኔ እንለዋወጥና እንሞክረው። የግናችን ስራ ክባድ እንደሆነ እንረዳዋለን አለችው። እሱም ይህ ከሆንማ መልካም ነው። በግለት እድሌ ከብት ውስጥ ተቀምጬ አንቺ የምትሰሪውን ብሰራ ምን ያውከኛል አሁን ሂጅና የኔን ድካም እይው፣ ከበሬዎች ጋር ያለውን የሞፈሩን የቀንበሩን አያያዝ ሞክረው አላት። ባለቤቱም ሀሳቡን በደስታ በመቀበል የቤቱን ውስጥ ስራ እንዳታጓድል በግለጻ ተነስተህ ውሃ ቀድተህ ቤት ጠርገህ የከብቶቹን በረት ከፍተህ ላሞቹን ከጥጆቹ ጋር አገናኝተህ፣ እንዲሁም ከብቶቹን አሰማርተህ በምላ ሰዓት ምግብ እዘጋጅተህ እርሻ ቦታ ይዘህልኝ እንድትመጣ ብላ የስራውን ቅድመ ተከተል ነግራው ሁለቱም ወደ እለት ስራቸው ተሰማሩ።

እርሷም ቦታዉ ደርሳ ከብቶቹን ከበሬዎቹን እየነዳች ወደ እርሻ ቦታ ሄዳ እንደሙሉ ገበሬ በሬዎቹን ጠምዳና መሳሪያውን አሳግምታ ስራዋን ጀመረች። ቢሉዋም የቤት ስራውን ለመጀመር ውሃ ቀድቶ ቤት ከጠረገ በኋላ ወደ በረት ሄዶ ላቹን ከጥጆቹ ጋር አገናኝቶ ውተት አልቦ ሲመለስ የበረቱን በር ሳይዘጋው ቀርቶ ናሮ ከብቶቹ ከቡታያው ፍየሎቹ ደግሞ ከጓሮ አትክልት ውስጥ ገብተው ብዙ ጥፋት አድርሰውበት እርሱም ከብቶቹን አልቦ ከቤት እንደገባ ወተቱን ከጎረና ገለበጠና ስጋውን ቆራርጦ እሳት ላይ ለመጣድ ሲዘጋጅ የጎረቤት የጥሪ ድምፅ ሰማ። ወደ ውጭ ብቅ ብሎ ቢመለከት የበረቱ ከብቶች በሙሉ በእህሉና በአትክልቱ ተሰማርተው ተመለከተ።

ከዚያም ከብዙ ጩኸት በኋላ በጎረቤት ሰዎች ብርታት ከብቶቹ ተሰብስበው ከበረቱ ገቡለት። ወደ ቤት ሲመለስም ስጋውን ውሾች በልተውት ወተቱን ያመሙቶች ደፍተውበት በእሳት ላይ የጣደውን ውሃ ፈልቶ እሳቱን እጥፍጥብት እንጀው የህም በንዴት ላይ ንዴት ባድካም ላይ ድካም ጨመረበት እያዩዞም ስራውን ለራሳቸው የማይችለው በመሆኑ ከብቶቹ ላይሰማሩ በበረት ውስጥ እንደገና እንጀራ እማምጭ ቆያት።

ባለቤቱም የተሰጣትን ስራ በሚገባ ስታከናውን ውላ እንድ ነገር ላይጎልባት መሳሪያዎችን ተሸክማ በሬዎችን እየነዳች በተመለሰች ጊዜ ምነው ምላዱን ላታመጣልኝ ቀረህ አለችው እሱም ከተቀመጠበት ተነስቶ ማሪኝ፣ ድካምሽን እየሁት፣ ተረትቻለው እኔስ ያንችን ስራ ቀላል መስሎኝ ነበር። "ከበሮ ሲያዩት ያመካር ሲይዙት ያደናድር" ለካስ ቤት ውስጥ ያለው ልፋት ብዙ ናሯል ብሎ ምህረት ጠየቃት እርሷም የእትክልቱ መበላት፣ የቤቱ መበላሸት፣ የከብቶቹን ጓሮ መዋል ከተረዳች በኋላ ላትግረርና ላትበሳጭ እንደገና ስራ ጀምራ ለባለቤትዋ እና ለራስዋ ምግብ አሰናድታ፣ ለከብቶች ጎር ገፈራ ሰጥታ ስራዋን አጠናቀቀች።

በማግስቱም ሁለቱም ወደ ቀድሞ ስራቸው ተመለሱ። ከዚያ ጊዜ በኋላ ሁለቱም በተሰማቸው ስራ ሁሉ እየተረዳዱ ያለመሰልቸት በትዕግስት ተዳራቸውን ይመሩ ጀመር።

ቅድመ ንባብ የመያያዝ ነጥቦች

1. በቴሌቪዥን ከተመለከታችሁ የምታስታውሱትን ድራማ ለጓደኞችሁ ግለፁ፡፡

2. የተውኔትና ድራማ ልዩነት ምን እንደሆ ክፍል ውስጥ ተወያዩበት

ባህሩ፡. አንቺን እነኑው የምለው አንቺ

በለጠች፡. (መምታቷን አታቋርጥም) አቤት፡.

ባህሩ፡. ምንድነው በሌሊት የምታጮኸብኝ በይ?

በለጠች፡. በጧት ቀስቅሽኝ አላሉም እንዴ?

ባህሩ፡. እባክሽ ቀስቅሽኝ ብያለው ታዲያ

በለጠች፡.የቤተስኪያኑን መረዋ መቼም አይስሙት ብዬ ነው ይልቁን ተነሱ ፊትዎን ይታጠቡና ይልበሱ፡፡ ቤተስኪያን ስመው አስቀድሰው የሚመለሱትን መቀበል እንኳን እንደ ጥንቅ ነው፡፡

ባህሩ፡. ትዳሴ ወጡ እንዴ?

በለጠች፡. ድርግት ከወረዱ ስንትና ስንት ዘመናቸው!

ባህሩ፡. ( ድንግጥ ይላል) ከመቼው?

በለጠች፡. አዎ እዚያ ተጋድመው ይንጠራራሉ፡፡ አክስትዎ ይምጡለትና የጉድ አቦል ፊልዮ ሲገነፍል አረፋው ይታየኛል / አብሹን በዋንጫዬ ትቀዳለች/

ባህሩ፡. (ያዛግል በለጠች! በለጠች (አትመለስም፡፡ ዋንጫውን ጠርጋ አስተካክላ ጠረጴዛው

ላይ ታኖራለች) በለጠች አንቺን እኮነው የምጠራው!

በለጠች፡. (እጇን እየተለቃለቀች) ቤት፡፡ ዘሬ ምን ሆነዋል?

ባህሩ፡. ነይ እኮ ነው የምለው?

በለጠች፡. መጠሁ( አብሹን ትቀምስና ታጣጥማለች)

ባህሩ፡. ነይ! ነይና ላሚኝ ላትስሚኝ ሦስት ቀን አልፏል

በለጠች፡. እኔ ሥራ አለብኝ እቴ፡፡ ቀልዱን ሌላ ቀን አቆዩት ( መጋረጃውን ገልጣ ትገባለች፡፡) አብሹ ይደፋል፡፡) ምንነክቷቸዋል? አሆ እቴ! በሹክሹክታ ምን ሆነዋል አሁን ሰው ቢመጣስ? ሰው ይመጣል ይልቀቂኝ ! ቦጋለ ያይዋታል፡፡ (አምልጣ ትወጣለች)ወየው ጉድ እቴ ዛሬ አብደዋል ሰውየው ኢትዮጲያ

አገራቸው በገቡ በአንድ አመት ከመንፈቃቸው የፈረንጁ ልማድ ገና አለቀቃቸውም።

(መንግስቱ ለማ፣ ያላቻ ጋብቻ አዲስ አበባ 1957 ገፅ 21)

**መልመጃ አንድ**

1. በቀረበው ጽሑፍ መሠረት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ።

ሀ. በሁለቱ ባለ ታሪኮች መካከልስ ያለው ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

ለ. ቤተስኪያን ጥድቅ ተመንፈቃቸው የሚሉት በለጠች የቃላት አጠቃቀም ስለ በለጠች ማንነት የበለጠ ያሳውቁናልትላለኢሁ? እንዴ?

ሐ. በለጠች "የጉድ አቦል ፊልሞ ሲገነፍል ይታየኛል" ስትል ምን ለማለት ፈልጋ ነው?

መ. ብሀሩንና በለጠችን ያሳፈራቸው ማነው?

ሠ. ስለ ባህሩ መማንነት የበለጠ የሚገልፀው ሃሳብ የትኛው ነው?

ረ. የበለጠችና የባህሩ ግንኙነት የባልና ሚስት ወይስ የሰራተኛና የአሰሪ? ለምን ተወያዩበት።

**መልመጃ ሁለት**

1. የሚከተሉትን የምርጫ ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ።

ሀ. በለጠች በአክብሮት የምትጠራው ማንን ነው?

1. ቦጋለን 3. ባህሩን
2. የባህሩን አክስት 4. ሁለትና ሦስት

ለ. ባህሩን ከእንቅልፍ የቀሰቀሰው ምንድን ነው?

1. የቅዳሴ ድምፅ 3. የአብሽ ድምፅ
2. የመረዋ ድምፅ 4. የበለጠች ድምፅ

ሐ. የባህሩ ንግግር

1. ቁጣ የበዛበት ነው 3. ላቅ የበዛበት
2. ስድብ የበዛበት ነው 4. ትዕዘዝ የበዛበት ነው

መ. የበለጠችና የባህሩ ቃለምልልስ _____ ይመስላል።

1. የአባትና ልጅ 3. ሰራተኛና አሰሪ
2. የባልና ሚስት 4. የእህትና የወንድም

ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች

1. ለመሆኑ ጓደኛ ስለሚለው ቃል የምታውቁት ነገር አለ?
2. በፀኛ ክፍል ውስጥ አብራችሁ የምትማሩት አንድ የወንድ ወይም የሴት የጥናት ጓደኛ ካላችሁ ስሙን ወይም ስሟን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማላወቅ የጥናት ወይም የስራ ፕሮግራማችሁን በዝርዝር ግለፁ፡፡

## ሁለቱ ጓደኛሞች

ኡሞድ ለጥቂት ሰኮንድ በመስኮቱ ወደ ውጭ ያይና ተመልሶ ምላ መብላቱን ይቀጥላል፡፡ወዲያው በር ይንኳኳል፣ኡኬሎ ይገባል፡፡

ኡሞድ- እስካሁን ምን አዘገየህ? ወደዚህ ቅረብ፡፡ ምን የመሰለ የዶሮ አሮስቶ እንደሚጠብቅህ አታውቅም፡፡ ያውልህ ወንበር፡፡

ኡኬሎ፣ አልቀመጥም መብል አላሰኘኝም፡፡ ቢሮ ሳለሁ እርቦኝ ነበር፡፡ እዚህ ስደርስ ግን አንጀቴ ቁልፍ አለብኝ፡፡ በክፍሉ እየተዘዋወረ የግድግዳ ሥዕል ይመለከታል፡፡

ኡሞድ ፡ ተው ይሻልሃል! ሆድ ባዶ አይወድም

ኡኬሎ ፡ በጓዳዬ ጉዳይ ገባ አትበለኝና ዘበኛውን ተቆጣው፡፡ ምን የመሰሉትን ሀረጋዊያን ሲያንገላታ ደረስኩበት፡፡ ባልደርስላቸው---

ኡሞድ ፡ ተወው ባክህ! ደግ አደረገ፡፡ ለማኝ አስቸግሯል

ኡኬሎ ፡ "ልጄ ነው! ረ ልጄ ነው! ያው አንድዬ ያውቀዋል አንድ ነው" እያሉ ሲሮሹ ነበር፡፡

ኡሞድ ፡ ወድያው አይመልስም አጥንት ይግጣል፡፡ ስሙን ጠይቀኸዋል?

ኡኬሎ ፡ "አቶ ኡባንግ እባላለሁ" አሉኝ፡፡

ኡሞድ ፡ አአውቀዋለሁ፣ ድሮ የአባቴ ጓደኛ ነበር፡፡ አሁን ግን ይኸው እንደሚታየው፤

አልም ያለ ሰካራም ሆኗል፣ አልኮሊስት ለመጠጫ ገንዘብ ካልወሰድኩ ነው የሚለው፡፡ ነጋ ገንዘብ አምጣ፣ እሰጠው ነበር፣ የድሮውን እያስታወስኩኝ አሁን ግን ገና ደጃፌን ሲረግጥ በዘበኛ አስባርረዋለሁ ይህ ፄካኔ አይምሰልህ ለራሱ ብዬ ነው ለነፍሴ በሰማይ ቤት መጠየቅ አለ፣ ፍርድ አለ ለአልኮሊስት ገንዘብ መለገስ ለታመመ ሰው መርዝ ማቅመስ ነው አፍን በጠረጴዛ መሀረብ ጠራርጎ ከመሶቡ ይነሳል "ሆድ ለባሰው ማፄድ አታውሰው" የሚለው የአባቶቻችን ምሳሌ ትልቅ ቁም ነገር ያዘለ መሆኑን መረዳት አለብህ፡፡

ኡኬሎ ፡ በምፀት ጥርሱን ብልፄ በማድረግ ታዲያ መልካችሁን ምን እንዲህ አመሳሰለው?

ኡሞድ ፡ ምን ማለትህ ነው? የሚማሰል ወጥ ነው፡፡

ኡኬሎ ፡ መልካችሁን ምን አመሳሰለው ማለቴ ነው፡፡ ሸማግሌው ቁርጥ አንተን ነው፡፡ አንተን ልብ አድርጎ ላየህ ሰው የሳቸው ፎቶ ነህ፡፡

ኡሞድ ፡ ይህ ምኑ ያስገርማል? አንድ ቀን ከጋምቤላ ከተማ ልከ አንተን የሚመስል ሰው አይኑ ነው ጥርሱ፣ አፍንጫው፣ጀሮውላይቀር ከነ አሳሳቁ፣ ከነ አረማመዱ ቁርጥ አንተን የሚመስል አፍሪካዊ አጋጥሞኝ ነበር፡፡ ልዩነቱ በቆዳ በርዝመት በቀለም ብቻ ነው፡፡ እንዳንተ አጭር

ረጅም ወንበር ላይ ይተመጥና የጠገበ ሆዱን እየደባበሰ ቀበቶውን ፈታ ያደርጋል። ጥርሱን በስንጥር ይነቃቅላል መልክ አታላይ ነው መመሳሰል መላመድን አያስከትልም።

## መልመጃ አንድ

1. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ።
   ሀ. ለጥቂት ሰኮንድ፣ ወደ ውጭ ሲመለከት ከቆየ በኋላ ተመልሶ ምላ መብላት የጀመረው ማነው?
   ለ. እልም ያለ ሰካርምና አልኮሊስት በመሆን ነጋ ጠባ ገንዘብ ስጡኝ የሚለው ማነው?
   ሐ. "ለአልካሊስት ገንዘብ መስጠት ለታመመ ሰው መርዝ ማቅመስ ነው" ሲል ምን ማለት ነው?
   መ. ኡመድ "የሚማሰለው ወጥ ነው" ያለው ኡኬሎ ምን ለማለት የፈለገውን ሃሳብ ነው?
2. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ አመልክቱ።
   ሀ. ምንባቡ የቀረበው በምን አይነት ዘዴ ነው?
      1. በትረካ
      2. በገለፃ
      3. በሁለት ጓደኛሞች ቃለ ምልልስ
      4. በስዕላዊ መግለጫ
   ለ. በክፍል ውስጥ እየተዘዋወረ የግድግዳ ስዕል የመለከት የነበረው ማነው?
      1. ኡኬሎ
      2. ኡባንግ
      3. ኡመድ
      4. ኡኬሎና ኡመድ
   ሐ. በምንባቡ ውስጥ ያለው ምልልስ በማንና በማን መካከል የተካሄደ ነው
      1. በኡኬሎና ኡባንግ
      2. በኡመድና በኡኬሎ
      3. ኡባንግና ኡሞድ
      4. መልስ የለውም
   መ. አቶ ኡባንግ ለኡመድ _____ነው?
      1. አባቱ
      2. ወንድሙ
      3. ጓደኛ
      4. የአባቱ ጓደኛ
   ሠ. "አልኮሊስት ነው" ሲል _____።
      1. አልኮል የሚጠጣ
      2. አልኮል የሚሸጥ
      3. አልኮል የሚገዛ
      4. የአልኮል ነጋዴ
   ረ. "ሆድ ለባሰው ማፏጨድ አታውሰው" ሲል _____።
      1. ለተቸገረ እርዳ
      2. ሆድ የባሰውን አዕናናው
      3. የበማያገባው መግባው
      4. ያዘነውን አታስከፋው
   ሰ. በምንባቡ መሠረት ሽማግሌው የሚመስሉት ማንን ነው?
      1. አቶ ኡባንግን
      2. ኡሞድን
      3. ኡኬሎን
      4. ማንንም አይመስሉም

## መልመጃ ሁለት

1. ቀጥሎ በቀረቡት ዐ.ነገሮች መካከል ያለውን የትርጉም ልዩነት ግለፁ።
   ሀ. ኡሞድ ይመጣል።
   ለ. ኡሞድ ይመጣል?
   ሐ. ዳሱ ተጣለ።
   መ. ዳሱ ተጣለ?

ቅድመ ንባብ የመወያያ ጥያቄዎች

1. ልብ ወለድ የሚለውን ቃል ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
2. ቃሉ ምን ማለት እንደሆነ እሰኪ በቡድን ተወያዩበት፡፡
3. እስካሁን ካነበባችሁት የልብ ወለድ መፅሐፍ አንዱን ወደ ክፍል በማምጣት ታሪኩን ለክፍል ጓደኞቻችሁና ለመምህራችሁ አሰረዱ፡፡

## ሽልንጌን /ልብ ወለድ/

ባቡሩ መንቀሳቀስ ሲጀምር በቀጭን ለስላሳ ድምጽ ሽልንጌን ሽልንጌን እያለች ትጮህ ጀመር፡፡ በባቡሩ ሞተርና ግምግምታ ከተሳፋሪዎችና ከሻጮች ጫጫታ በላይ ለመስማት የሚጣጣር ኡኡታ ነበር፡፡ ሽልንጌን ሽልንጌን በቡሩ ሀይለኛ ፍሽካውን በሞተሩ ጃስ ጃስ ላይ አከለበት፡፡ የተንጠለጠሉት ሻጮች ጠብ ጠብ እያሉ ወረዱ፡፡ ፍጥነቱ ሲቀጥል ግስገሳው ሲጨምር በዚያው መጠን የአሚና አቤቱታ እየቀነሰ ወደ ኋላ እየቀረ ሄደ፡፡ ፓፓያ የያዘችበትን እንቅብ በራሷ ላይ እንዳስቀመጠች እየሮጠች ብትጮህም አልደረሰችበትም፡፡ ባቡሩ ፊኛውን እያነፈሰ መሳተቱን ቀጠለ፡፡ የኑሪያን መኖ የያዘውን የብረት ዘንግ እየተምዘገዘገ ሲፈተልክ እጆቿን ወደ ሰማይ እያርገበገበች ተንበርክካ እንባ በተቀላቀለበት ድምፅ ሽልንጌን ወይ ሽልንጌን ብላ ጮኸች፡፡ ሳታውቀው በሐዘኑ ፈንታ ራሽን ስትደፋ የፍሬው እንቅብ ተንሸራቶ ከእቅፏ ወደቀ፡፡ ፓፓያዎቹም እንደ እምቧይ እየተንከባለሉ በሐዲዱ ላይ ወደቁ፡፡

አሚና ጠና ያለች የአርባ ስምንት አመት ሴት ነበረች፡፡ የራር ጣቢያ አጠገብ ተወልዳ ለአቅመ ሄዋን እስክትደርስ ድረስ ከቤተ ሰቦቿ ጋር ከብቶች እያገደች ስትኖር ከተዳረች ወዲህ ባለቤቷ ከተማ ሄዶ የቀን ስራ እየሰራ መኖርን ስለመረጠ ያላቸውን ከብቶች ሸጠው የረር በፈሾሽኝነት አንዲት ዳስ ሰርተው ተቀመጡ፡፡ ከጥቂት አመታት በኋላ ለጥቂት ጊዜ ስታሰቃየው የነበረችው ወባ ባለቤቷን ነጥቃ ወሰደችው፡፡ በባህላቸው መሠረት የባሏ ወንድም መጥቶ አግብቼ ልውሰድሽ ቢላት ከዘላንነቷ የከተማ ኑሮ መርጣ ብቻዋንነ ቀረች፡፡ ከዚያ በኋላ ታናሽ እህቷ ፋጡማ ከበሏ ሸሽታ መጥታ ጥቂት ጊዜ አብረው ከኖሩ በኋላ እዚህ መጥቶ ካገኘኝ ይገድለኛል ብላ ጥላት ወደ ድሬዳዋ ወረደች፡፡

ከዚያን ጊዜ በኋላ አሚና ብቻዋን ትኖራለች፡፡ ዳሊ ሳይሟሽሽ የደረቷ ፍሬ ሳይጠወልግ በፊት አብር አዳሪ ነበራት፡፡ በመጠኑም ጥቅም ታገኝ ነበር፡፡ ገን በመጨረሻ ካንድ የባቡር ዘበኛ ወንድ ልጅ ካገኘች በኋላ ባሏ፡ ልጇ እና ኣብሮሽ ብቻ ቀሩ፡፡ አብሮሽ አምስት አመት ሲሞላው አክስቱ መጥታ ወሰደችው፡፡ ፋጡማ በድሬዳዋ የጥጥ ፋብሪካ ሰራተኛ ናት፡፡ በወር የምታገኘው ሠላሳ ብር ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ውስጥ በየሳምንቱ አንዳንድ ብር ደመዝ ውስጥ አስቀርታ ባጠራቀመችው ገንዘብ ጨርቃ ጨርቅና ምግብ ለአሚናና ለልጇ ይዛ መጣች፡፡

አሚና ኑሮዋ ከእጅ ወደ አፍ ቢሆንም ልጅ እንዲኖራት ትፈልግ ነበር፡፡ ግንነ እንደ እህቷ አልታደለችም ስለዚህ አሚናን ከነ ልጇ ወደ ድሬደዋ ይዛት ሄዳ ስራ ፈልጋላት አብረው እንዲኖሩ ብትላትም ለአሚና የረርን ለቆ መሄድ አልታይሽ አላት፡፡ በመጨረሻም "እንቺ እንኳ ባትሄጂም ልጅሽን ወስጂ ላስተምረው፡ እኔ እንደሚታየኝ ልጅ የለኝም" ብላ ብትለለምናት "እሱ እሺ ካለሽ ውሰጂው" አለቻት፡፡ አሚና ምንም ቢሆን እኔን እናቱን ጥሎኝ አይሄድም፡ እንቢ ብሎ ይቀራል ብላ ተማምና ነበር የተናገረችው ፋጡማ ገና አብሮሽን ለሆዱ ባቀረበችለት ምግብ ለገላው ባለበሰችው ቆንጆ ልብስ እንዲሁም በዓይነ ህሊናው ባሳለችለት የድሬዳዋ ከተማ ብልጭልጭ አባብላ "ከፋጤ ጋር እሄዳለሁ" ብሎ እናቱን ወጥር አድርጎ እንዲይዛት አፋጦ ያዛት፡፡

"ፋጤ ወጂን ዴማ!" እያለ አላስገባት አላስወጣት አላት፡፡ መለየቱ የእናቱ አንቷን የሚቆርጠው ቢሆን ከሷ ጋር ተቆራምዶ ከመኖር ከአክስቱ ጋር ድሬዳዋ ቢወርድ ቀን ይወጣለት ይሆናል ብላ በማመን ጨክና ወሰነች፡፡ አንድ ቀን አቅፋው ካደረች በኋላ ማለዳ ጥዋት የአዲስ አበባ የሌሊት ባቡር ሲገሰግስ ደረሰ፡፡ ሦስት ቀን ብቻ እንድታርፍ የተፈቀደላት ፋጡማ ለእረፍቷ ማለቅ አንድ ቀን ሲቀራት ማታውኑ ዕቃዋን አደራጅታ ገና ባቡሩ ሳይደርስ ነቅት ልብሶቿን ለብሳ አሚናንም ቀስቅሳትትጠባበቅ ጀመር፡፡ እናቱም ወደ ፍርጎው ውስፅ ሺገባ በፋጡማ እጆች ውስጥ እንዳለ ሲያዛጋና አይኖቹን ሲያሻሽ ተንጠላጥላ አቀፈችውና ሳመችው፡፡

"ልቀቂው፡ ባሩ ተነሳ፡፡" ብላ መንጭቃው ወደ ውስጥ ገባች፡፡ በእናቱ ዓይን እንባ ሞላ፡፡ የባሩ ፈሽካ ከሩቅ የሚሥህ መሰላት፡፡ ከፊት ለፊቷ ተብረት ቤት እየተምዘገዘገ፡ አንዱ አንዱን እየተከተለ ሲያልፍ ህልም እንጂ እውን አልመሰላትም፡፡ ወዲያው ከፊቷ ባዶ ሲሆን ባነነች፡፡ ጭርታና ባዶ ነብሷን ስትዘራ ዕንባዋን በሸሟ ከፊቷ ላይ ጠረጋ ሐዲዱ ላይ ተራምዳ ባቡሩ ወደ ወረደበት አቅጣጫ ተመለከተች፡፡ ግን ሁለት እየጠበቡ የሚገጥሙ የብረት በስመሮች በስተቀር ሌላ ሊታይ አልቻለም፡፡ ከዛን ወዲህ ስለልጇም አልሰማችም፡፡ እህቷም መጥታ አታውቅም፡፡ ሦስት አመት አለፈ፡፡

"ልጂ ሞቶም እንደሆን ጉዴን አያለሁ" ብላ ከሆዷና ከልበሷ ቆጥባ ሃያ ብር እስኪሞላት ድረስ ፓፓያውን ከሽልማት ድርጅት እየገዛች ለማትረፍ ስትጥር ነው እንዱ መንገደኛ እገዛሻለሁ ብሎ አንድ ብር ሰጥቷል መልሱን ሽልንግ ከሰጠችው በኋላ ፓፓያውን መልሶ ሽልንጓን ሳይመልስ፡ እጇን ስትዘረጋ ረግጧት ከባቡሩ ጋር የነጎደ፡፡ ፓፓያውስ በእርግጥ መበስበስ ይዟል፡፡ ገገር ከሌለው የአትክልት አገር ይኧው ነው፡፡ ሳይሸጥላት ብዙ ጊዜ ስለቆየ ነበር ዋናውን እንኳን ሳይመልስ ብላ አሚና በሃምሳ ሣንቲም የተስማማችው እንጂ ዋጋውስ አልነበረም፡፡

ምን ነካው ሰውየውን የለውም እንዳይባል ያለው ነው፡፡ አለባበሱ የጨዋ፡ መልኩ የዋህ፡ ቁመናው የአዋቂ የሚመስል፡፡ የስሙኒ ቅርጫት በሽልንግ ሲገዛና የሃምሳውን ሳንቲም ሙዝ በብር ገዝቶ ሲጨምር በአንድ ዓይኗ አሚና ራሷ አይታለች፡፡ እንደኔ ልጅ ኖሮት ለሱ ይሆናል የሚገዛው ብላ ገምታ ነው "መልስ አለሽ ወይ" ብሎ ይሄዳል ብላ ጨርሳ የማትገምተው ነው፡፡ ብቻ --- ጫጫታ ነበር፡ ጋጋታ ነበር፡፡ ከሰውየው ዙሪያ የነበረው ትፍግፍግ ግፊያ የተዘረጉ እጆች ብዙ የሚያካልቡ ነበሩ፡፡ እንዲህ ቁጢጥ እንዳለ ከኋላው አንዱ ሲገፋው ባፍጢሙ ሊደፋ ምንም አላቀረውም፡፡ ጭቅጭቁ፡ ግልምጫው፡ ከአጭበርባሪው ኪስ መጠበቁ ከዚያም በላይ ባቡሩ ተነሳ ብሎ ስጋቱ፡ ከሻጪውም ከገዢውም የሚወጣ "ፍራንኬን! ሳህኔን! ሲንዩን! ቅራቅንቦዩን! --- - ቀልብ የሚሰልብ ነበር፡፡" የአሚና ፓፓያ መበስበሱን ያወቀ ባቡሩ "ሄድኩ" የሚለውን መጨረሻ ፈሽካ ሲያሰማ ነው፡፡

"አልፈልግም ይህ በስብሷል፡፡" እንቅቡ ወደሷ ገፋለት፡፡ የለም ጥሩ ነው፡ ወላሂ አልበሰበሰም፡፡"

ተናደደ፡፡ "ቅጥፈት በአሮጊት አያምርም፡፡ ቃሪያው በስብሷል፡፡" በግራ እጇ የያዘችውን ብር መርጭቆ ወሰደ፡፡ ባቡሩ ለአመል ያህል ተወዛወዘ እንቅቧን ቶሎ ሯሷ ላይ አደረገችና አንድ እጇን ደረጃ ላይ እግሩ አጠገብ አድርጋ በተራ ድምጽ "ሽልንጌን አለችው፡፡ የምን ሽልንጌን?" ንዴት ሪሱን አዞረው፡፡ ዳግመኛ ውሸት? መጀመሪያ የበሰበሰ ፓፓያ ልትሸጥለት፡ አሁን ደግሞ ያልተቀበለውን መለስ ልትወስድበት? በጣም ተናደደ፡አረረ፡፡ ሊያናግራት አልቻለም፡፡ ዓይኑን አጉረጥርጦ ጥርሱን ነክሶ ብቻ

ገላመጣት፡፡ "ሽልንጌን" አለች ከባቡሩ ጋር እየተራመደች በጣም ጮክ ብላ፡፡ በጣም ባሽቀ ፍርጎው ላይ የነበሩት ሻጮች እየገፉት አወረዱትስ፡፡

"ሽልንጌን" ከባሩ ጋር ራመድ እያለች ጮኧች፡፡ ከደረጃው ላይ የተዘረጋው ክንዷ ለእግሩ አላማረውም፡፡ ቆዳው በእድሜና በፀሐይ ተኮማትሯል፡፡ አንድ ወፍራም የደም ስር ተጋድሞበታል፡፡ ባቡሩ እየፈጠነ ቢሄድም ከዝግሩ አልተነሳም፡፡ በመጫሚያው ጠንካራ ተረከዝ በጭካኔ ረገጠው፡፡ አሚና ግን ጥቂት ከመኮማተር በስተቀር የተሰማትም አልመሰለችም፡፡ የተመታው ክንዷ አንቀረፋ ጨኧቷን ቀጠለች፡፡

"ሽልንጌን"! ሽልንጌን!" የባቡሩ ፍጥነት ከአሚና እስኪለየው ድረስ የነደዱ ዓይኖቹ ከፊቷ ላይ ከተጨማደደ ከከሳውና ከጠወለገው የአሮጊት ፊት ላይ አልነቀለም፡፡ ባቡሩ ከተማውን አልፎ የቤቶች ትዕይንት በተፈጥሮ የጢሽኛ የዕፅዋት ትዕይንት እስከተተካ ድረስ ንዴቱ አልበረደላትም፡፡ ወደ መቀመጫው ሲመለስ እንደተናደደ ነበር፡፡

መቼስ የሚለክፍ አይጠፋም፡፡ ደህና እንዲያውም በድሬዳዋ ከተማ የልቡን አድርሶ የሙቀት ጉጉቱን፡--- አርክቶ ለዝናቡ፡ለብርዳሙ አዲስ አበባ ተዘጋጅቶ ሲመለስ ነውየረበሸችው፡፡ ሰላሙን በተነችበት፡፡ ደህና የልብ ልብ እየተሰማው የዐይኑ መነፅር፡ የእግሩ መጫሚያ፡ የሁለንተናው መስተካከል እየታወቀው ከእረፍት ሲመለስ ነው የጨነገፈችው፡፡ ጥርሱን ነክሶ በሰውነቱ የሚሰማው ስሜት እንዲያሳይ ደብቆ፡ ዙሪያውን የተቀመጡትን ተሳፋሪዎች ቃኛቸው፡፡ ከፊት ለፊት ያለችውን አሮጊት የሚንጫጩ የሶማሌ ጎረምሶች፡ ከበስተጀርባው ካለው ባለ ሪዛም ዐረብና ሁሉም ምንም አልተቀየሩም፡፡ አንዳንዶቹ የገዙትን ፍራፍሬ እየላጡ መብላት ጀምረዋል፡፡ አሮጊቷ አደሬ የአረግ ሬሳ የተሸለሙ ጣቶችን ከፊቷ ላይ አድርጋ ታንቀላፋለች፡፡ ባሱ አንጀት ውስጥ ብቻ ነው፡፡ የንዴትና የብሽቀት ትኩሳት ይፈላ የነበረው፤ የአሚና የተሰቃየ መልክ፡ የአሚና የተረገጠ ክንድ ከአይነ ህሊናው ፊት ለፊት ተደቅኖ ዕረፍት ሊሰጠው አልቻለም፡፡ ለምን እንዲህ አደረገ? ለምን ዋሸች? "እርሳው" አለ እራሱን፡፡ በመስኮት እየተንደረደረ የሚያልፈውን የገጠር ትዕይንትና ሺቦውን በራሱ እያከከ የሚያልፈውን የስልክ ብረት ይመለከት ጀመር፡፡ ግን በአሚና ነገር ይተካል፡፡ "ለምን ዋሸች?" "ይናደዳል ለምን እኔስ ያደረግሁትን አደረግኩ? ድንገት ፀፀት ንዴቱን ያቀዘቀዘለት ይመስል በአእምሮው መጣች፡፡ አዎ ሽልንግ? ምን ይጎዳው ኖሯል? ዋሽታ ሽልንግ ብትወስድበት የራሷ ጉዳይ ነው፡፡ ከጠቀማት---- ግን ጠረጠረ፡፡ የሚያታልል መልክ አልነበራትም፡፡ ማሰብ ጀመረ፡፡

ቅርጫቱን በሃምሳ ሳንቲም ገዛሁ፡፡ ኪሴ ውስጥ የነበሩትን ሁለት ሳንቲሞች አውጥቼ ከፈልኩ፡፡ ሙዝ በብር ገዛሁ፡፡ ሌላ ምንዛሪ አልነበረኝም፡፡ ፓፓያ ስገዛ ብሬን ሰጠኋትና መልስ ስጠባበቅ ተፋረስን፡፡ ብሬን ነጠቅሁና ኪሴ ሳደርግ "ሽልንጌን" ብላ ትጮኧ ጀመር፡፡ መልስ ከሰጠችኝ ኪሴ ውስጥ መኖር አለበት፡፡ እንደዋዛ ኮቱ ኪስ እጁን ሲሰድ ሁለት ስሙኒዎች ይዞ ወጣ፡፡ ክውታ፡ ድንዛዜ፡፡ ራሱን በእጆቹ ቀብሮ አቀርቅሮ ቀረ፡፡

## መልመጃ አንድ

1. በምንባቡ መሠረት ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ፡፡

ሀ. ታሪኩ የተፈፀመበት ቦታ የት ይመድላችኋል?

ለ. የታሪኩ ዋና ገፀ ባህሪ ማን ነው?

ሐ. በባቡሩና በመኪናው መካከል ያለው አንድነትና ልየነት ምንድን ነው?

መ. ምንባቡን ስታነቡ የተሰማችሁ ስሜት ነበር? ለምን እንደተስማማችሁ ምክኒያቱን ግለፁ፡፡

ሠ. የልቦለድ ድርሰቱ ፍሬ ሃሳብ ወይም መልዕክት ምንድን ነው?

2. ምንባቡን መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ ምረጡ፡፡

ሀ. አሚና በራሷ ላይ የተሸከመችሁ እንቅብ የወደቀበትና ፓፓያዎቹም የተዘረገፉበት ---------- ነበር፡፡

1. [illegible] ረስታ አንገቷን ዝቅ ስታደርግ
2. ከራሷ ላይ አውርዳ ለማስቀመጥ ስትሞክር
3. ተናዳ ወርውራ
4. ሰው ገፍቷት

ለ. የአሚና ፓፓያዎችና እንቅቧ በመንከባለላቸው

1. ተለያይቷል
2. ተመሳስ[illegible]ዋል
3. ተቃርነዋል
4. ተረዳድተዋል

ሐ. አሚና ወደ ከተማ የወጣችው _____ ነበር

1. ልጅ እንደወለደች
3. በልጅነቷ

# ምዕራፍ አራት

### የመነሻ መወያያ ነጥቦች

1. የሰው ልጅ እንዴት በፍቅር መኖር ይችላል?
2. በቤተሰብ ወይም አብሮ በሚኖሩ ሰዎች መካከል መፈቃቀር አለመኖር ምን ያስከትላል?

## ብርቱ ፍቅር

በዛብህና ሰብለ በአበባቸው ያዘንና የብስጭት፣ የጭቆናና የባርነት፣ የሽሙጥና ያሚት አለም ውስጥ ከዚህ ሁሉ ነፃ የሆነ ይህ ሁሉ የሌለበት ልዩ አለም፣ የፍቅር አለም ፣የደስታ አለም፣ የነፃነት አለም ፈጥረው አንድ ወር ያክል ደስ ብሎዋቸው ነፃ ሆነው ኖሩ::

ብርቱ ፍቅር ባለበት ክፉ ነገር የለም:: ብርቱ ፍቅር ካለ የሚቆጣ፣ የሚቀጣ፣ የሚሰቅ፣ የሚሳለቅ፣ የሚያማ፣ የሚያሸሚጥጥ ይኖራል ብሎ መፍራት፣ መጠርጠር እንኳን የለም::

ብርቱ ፍቅር ክፉውን ደህና፣ አስቸጋሪውን ቀና፣ ሩቁን ቅርብ፣ ጨለማውን ብርሃን፣ ዱሩን ሜዳ፣ አቀበቱን ደልዳላ አድርጎ ማሳየት አለበት:: አለዚያ ብርቱ ፍቅር አይባልም:: አዕምሮን ከመልካም በቀር ክፉ ሊያርስ ይችላል ብሎ እንዳያስብ የሚያሰውር፣ ጆሮን ከመልካም በቀር ክፉ እንዳያሰማ የሚያደነቁር ፍቅር፣ ብርቱ ፍቅር አይባልም::

የነሱ ፍቅር ግን በብዙ ሰው ደርሶ የሚያውቅ እጅግ ብርቱ ስለነበር ክፉ ነገር ሊያርስ ይቻል ይሆናል ብሎ ማሰብ፣ መፍራትን፣ መጠርጠርን እንኳ ካሳባቸው አጠፋ:: በሌላ ወገን ድፍረትን፣ ነፃነትን፣ ተስፋን፣ ደስታን ሰጥቶ ተባብረው በፈጠሩት የፍቅር አለም ውስጥ ደስ ብሏቸው ነፃ ሆነው አንድ ወር ያክል እንዲኖሩ አደረጋቸው::

*ምንጭ:- ሀዲስ አለማየሁ፣ ፍቅር እስከ መቃብር፣ ገጽ 323፣ ለንባብ እንዲመች ተሻሽሎ የተወሰደ::*

### ክፍል አንድ:- አንብቦ መረዳት

1. ከዚህ በታች የቀረቡትን ሀሳቦች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት በፅሁፍ መልሱ::

   ሀ. ከምንባቡ ለመረዳት እንደሚቻለው በዛብህና ሰብለ ህዘንና ብስጭት በሞራሽ ደርሶባቸው አያውቅም:::

   ለ. ብርቱ ፍቅር ሲያገ የሚያሳየውም ሆነ የሚያሰማው ክፉ ክፉ ነገርን ነው::

# ምዕራፍ ዘጠኝ

**የመነሻ መወያያ ነጥቦች**

ሙስና ምንድነው?

2. ሙስናን እንዴት መዋጋት ይቻላል?

## ደፋሩ አሸብር

አሸብር በተቀጠረበት መሥሪያ ቤት ውስጥ በህጋዊ ጨረታ ስም የሚካሄደው ህገ-ወጥ ዘረፋ፣ ጉቦና ምልጃ አስመርሮት ሙስናን በአደባባይ ሊዋጋ ቆርጦ የተነሳ ወጣት ነበር።

መጀመሪያ የተጣላው ከዕቃ ሽያጭና ግዥ ኃላፊዎች ጋር ሲሆን መስሪያ ቤቱን እየቦጠቦጡት መሆኑን በማስረጃ ሊያረጋግጥ ሲሞክር ዘበኛው ሳይቀር ብዙ ሠራተኞች ጠመዱት። ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ ሲያጣራ የዕቃ ግዥና ሽያጭ ኋላፊዎቹ የቻሉትን ያህል ሰርቀው እንዲያካፍሉት በስራ አስኪያጁ የተሰየሙ መሆናቸውንና ሥራ አስኪያጁም የሚኒስትሩን ድርሻ በሚስጢር እንደሚልክላቸው በሰፊው ሲወራ ሰማ።

እስከ ዘበኛው ድረስ ያሉ አንዳንድ የበታች ሠራተኞች ደግሞ ርክፍካፊው በገንዘብ፣ በዓይነት ወይም በግብዣና በጉርሻ እንደሚደርሳቸው አረጋገጠ። በዚህም ሆነ በዚያ "ማኖ" የነኩት ብዙ ነበሩ። በተቻለ መጠን ሁሉም ሰራተኛ "ማኖ" ነክቶ አፉን እንዲይዝ ይፈለጋል። ምንም ያልተነካኩ አንዳንድ ንፁሃን ቢኖሩም ከሥራ እንዳይባረሩ በመፍራት ማንንም አያጋልጡም። አንጀታቸው እያረረ "ሆድ ይፍጀው!" በማለት በዝምታ ለማቀርቀር ተገደዋል።

ደፋሩ አሸብር የ"ማኖ"ን ነገር ሲያወራ በመሰማቱ "አሸብር ማኖ" ተባለ። ዘራፊዎቹንና ጉበኞቹን ለማጋለጥ የሚፈሩትን ወይም የሚሸሹትን ሁሉ "አሃ! ማኖ ነክተሻል ማለት ነው?" ይላቸው ነበር።

*ምንጭ፡- ሲሳይ ንጉሡ፣ ረቂቅ አሻራ፣ ገጽ 205-206 መጠነኛ መሻሻል ተደርጎ የተወሰደ*

# ምዕራፍ አስራ አንድ

## የመነሻ መወያያ ነጥቦች

1. ጭውውት ምንድነው?
2. ጭውውት ከውይይት በምን ይለያል?

## ተከስተና ወይዘሮ ፅጌ

"ና አንተ ወደል፡ ድራሽህን ያጥፋውና!" ይሉታል ወይዘሮ ፅጌ ደናቱን ፍለጋ ወይም የልጅ እግር አያርፍምና ወዲያ ወዲህ ሲሮጥ እሳቸው ወዳለበት የገባ እንደሆነ::

"እንቢ" ብሏቸው ሊሮጥ ሲል ቅርብ ከሆነ ራሳቸው ለቀም አድርገው ሩቅ ከሆነ አስይዘው አስመጥተው ይይዙና

"ለምን ስጠራህ እንቢ አልክ?"

"እንዲያው"

"ንገረኝ ሳልመታህ"

"እንዲያው"

"መቼም አትወደኝ ከግንድ ጋር ያዋድህና!"

"አልወድዎትም"

"የኔ ልጅ ብትሆን አትወደኝም? የኔ ልጅ ብትሆን እንዲህ ያልተደረተ ልብስ አለብስሃለሁ እኮ!"

"አልፈልግም፡ አልወድዎትም!"

"ለምንድን ነው የማትወደኝ?"

"ክፉ ነዎት፡ ይቆጣሉ፡ ይቆነጥጣሉ::"

"የኔ ልጅ ከሆንክ አልቆነጥጥህም::"

"እምቢ ! የርሶ ልጅ አልሆንም፡ አልወድዎትም::"

"ደጃዝማችንስ ትወዳቸዋለህ?"

"አዎ! እሳቸውን እወዳቸዋለሁ::"

"ለምን?"

"እርሳቸው እንደ እርስዎ አይቆነጥጡኝም፡ ደግሞ መጫወቻ ይገዙልኛል::"

"ያች ክፉ እናትህ ትሆናለች እኔን እንድትጠላ የመከረችህ::"

"እሷ አልነገረችኝም፡ እንዲያው እኔ ነኝ የማልወድዎ::"

"እ! አልወድዎትም፡ አንተ ወደድከኝና መንግስተ ሰማያት ቀረበኝ!"

"ልቀቁኝ ልሂድ!"

"እኮ ለምን እንደማትወጂኝ ንገረኝና እለትሃለሁ?"

"ሁል ጊዜ ምንም ሳልልዎት ይቆነጥጡኛል፣ ደሞ ... ደሞ ውሸትዎን ሳልበላብዎ እንጀራዬን በላህ፣ ማሬን በላህ፣ ይላሉ::"

"ታዲያ የማንን እንጀራ እየበላህ ነው እንዲህ ወደል የሆንክ?"

"እማዬ ናት የምታበላኝ::"

"አዎ! እማዬ የምታበላህ የእኔን እንጀራ አይደለም? ከሰማይ እያወረደች ነው? ሂድ ወግድ፣ ገደል ይስደድህና፣ አንተ አ... ህያ" ይላሉ በመጨረሻ በቁንጥጫ ጭኑ እስኪበልዝ ልምዝማ ያደርጉት እና::

እሱም "የታባትዎ! አንቺ ውሻ! በዳ!" ብሏቸው ጭኑን እያሻሸ እያለቀሰ ይሮጣል:: እስኪረሳው ለሁለትና ለሶስት ቀናት ወደ ወይዘሮ ዕጌ እልፍኝ አይሄድም::

*ምንጭ፡- ሀዲስ አለማየሁ፣ የልምጥ ፣ ገጽ 102-104 እንደሚመች ተሻሽሎ የተመነደ*

## ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

1. ምንባቡን መሠረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ::

   ሀ. ምልልሱ ወይም ጭውውቱ የተካሄደው በስንት ሰዎች መካከል ነው?

   ለ. በምልልሱ የመጀመሪያ ተናጋሪ ማን ነው?

   ሐ. ከምልልሱ ለመረዳት እንደሚቻለው ወይዘሮ ዕጌ እንዴት ያሉ ሰው ናቸው?

   መ. ወይዘሮ ዕጌ ለተከሰተ እናት ምኗ ናቸው? በምን አወቃችሁ?

   ሠ. ተከሰተ ወይዘሮ ዕጌን የማይወዳቸው ለምንድነው?

2. **የሚከተሉትን ቃላትና ሀረጋት ፍቺያቸውን ሊያሳዩ የሚችሉ ዐረፍተ ነገሮችን ሥሩ::**

   ሀ. ያልተደረተ
   መ. እስኪበልዝ
   ለ. መንግስተ ሰማያት
   ሠ. ልምዝማ
   ሐ. ወደል
   ረ. እልፍኝ

## ክፍል ሁለት፡- ማዳመጥና መናገር

ተጥሎ የተረበውን የጭውውት መመሪያ መሠረት በማድረግ ጥንድ ጥንድ እየሆናችሁ በሚከተሉት መነሻ ነጥቦች ወይም መምህራችሁ በሚሰጣችሁ ርዕሶች ላይ ተመርኩዛችሁ ጭውውት አድርጉ::

ሀ. ለሥራ ሲባል በሀገሩዋ መንገድ ወደ ውጭ ሀገር መሄድ፣

ለ. ትምህርታቸውን ስለሚያቋርጡ ተማሪዎች፣

ሐ. ከትምህርት ቤት ስለሚያረፍዱ ተማሪዎች

# ምዕራፍ አስራ አምስት

**የመነሻ መወያያ ነጥቦች**

1. አንዳንድ ልጆች ቤተሰባቸውን የመርዳት አቅም እያላቸው የማይረዱ ለምን ይመስላችኋል?
2. እናንተስ ቤተሰባችሁን በምን አይነት መንገድ ትረዳላችሁ?

## የከፋው አባት ደብዳቤ

ልጄ . . . ለመሆኑ እናትህ መታሰቢያ እንዲሆን ሀውልት ለማሰራት ያስብክ መሆኑን ሰው ነግሮኻል። እንዴት ሞኝ ነህ! ከአሁን ወዲ ለእናትህ ከወርቅ፣ ከአልማዝ የተሰራ የመቃብር ሀውልት ብታቆምላት ምንም አይጠቅማትም። ለአሁን እናትህ ያረፈችበት የእንጨት ሳጥን፣ የለበሰችው አፈር ይቆረቁራት መሰለህ? ለምዳዋለች። ህይወቷን ሙሉ የተኛችው በአጠና አልጋ ላይ ነው። የኖረችው ወለሉ አፈር በሆነ ቤት ውስጥ ነው። ዛሬ ታዲያ በድኗ ያረፈበት የድሃ መቃብር ይጠላው መሰለህ?

አስራት እናትህ በድንገተኛ ህመም አልሞተችም። የዕድሜዋን አጋማሽ የጨረሰችው በማቃሰት ነው።ብዙ ጊዜ ታማ፣ ብዙ ጊዜ ተሳሳቁላ ነው ያለፈችው። እናትህን እንድታሳክማት ደጋግሜ ገልጬልህ ነበር። ዞር ብለህ ሳታያት፣ አንድ ቀንም ሳትጠይቃት ህይወቷ አለፈ።

አስራት የድንጋይ ሀውልት በስቃይ ለሞተች እናትህ ህይወት አይዘራባትም። ሰውን መርዳት በህይወቱ ነው። እናትህ "ልጄ ደረሰልኝ" ብላ ለብዙ አስባህ ነበር። አንተ ግን አልደረስክላትም። ልትረዳት ስትችል አልረዳሃትም። ስለዚህ እናትህ ያንተን የድንጋይ ክምር አትፈልግም። እኔም ያንተን ልጅነት አልሻም።

*ምንጭ፦ ከሙላቱ ገብሩ፣ የከፋው አባት ደብዳቤ*

### ክፍል አንድ፦ አንብቦ መረዳት

1. **የሚከተሉትን ሀሳቦች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ።**

ሀ. ደብዳቤው የተጻፈው ከልጅ ለአባት ነው።
ለ. ሀውልት ማሰራት በህይወት ለሚኖር ሰው ወጪው ከባድ ቢሆንም ለሚኽ ይጠቅማል።
ሐ. ለአስራት የእናቱ መታመም ከመሞታቸው በፊት ተደጋግሞ ተነግሮት ነበር።
መ. አስራት እናቱን መርዳት ሲችል ሳይረዳቸው ቀርቷል።

# ምዕራፍ አስራ ሰባት

**የመነሻ መወያያ ነጥቦች**

1. "ወርቅ ላደረበት..." የሚለውን ምሳሌያዊ አነጋገር አሚልታችሁ የያዘውን ሀሳብ አብራሩ።
2. አስተዋፅኦ ምንድነው? ለምን ያስፈልጋል?

## "ወርቅ ላበደረ..."

ከዕለታት አንድ ቀን ሁለት አዳኞች ነብር ለመያዝ ወደ ጫካ መሣሪያ ይዘው ይሄዳሉ። አንድን ነብር ያገኙና ያባርሩታል፣ ነብሩም ነብሱን ለማትረፍ ይሮጣል። አንድ ገበሬ በሬ ጠምዶ ሲያርስ ተባራሪው ነብር ይደርሳል። ነብሩም ገበሬውን "እባክህ ስለ እግዚአብሔር ብለህ አዳኞች እያባረሩኝ ነውና አድነኝ!" ይለዋል። ገበሬውም "እሺ!" ይልና ነብሩን ባዶ ስልቻ ውስጥ ከቶ ይቋጥርና ሥራውን ይቀጥላል። አዳኞቹም ገበሬው ጋር ይደርሳሉ፣ ከዚያም "አንተ አንድ ነብር በዚህ ሲያልፍ አላየህም?" ይሉታል፣ ገበሬውም "በዚህ በጫካው እየሮጠ ሄደ" ይላቸዋል። አዳኞቹ ወደ ተመሩበት ጫካ ፍለጋ ገቡ። ሲመሽ ገበሬው ስልቻውን ይፈታና "በል አዳኞቹ ከሄዱ ቆይተዋል፣ አሁን መሄድ ትችላለህ" ይለዋል። ነብሩ ግን "እኔን ቶሎ ሳትለቅ በስልቻህ ውስጥ አፍነህ ስለ አስጨነቅሽኝ አንዱን በሬህን ካልሰጠሽኝ እበላሃለሁ" ይለዋል። "አረ እግዚአብሄርን ፍራ ህይወትህን ባዳንኩህ ነው እበላሃለሁ የምትለኝ?" ይለዋል ገበሬው። ነብሩም "ህይወቴን ማዳንህን አልክድም፣ ግን በስልቻህ ውስጥ አፍነህ ስለአስመሸህብኝ ሳልበላ ማደር አልችልም፣ በጊዜ ለቀኸኝ ቢሆን እስካሁን የምበላው አላጣም ነበር" ይለዋል። "በሬህንም ከከለከልከኝ አንተን ነው የምበላው" ብሎ ያስፈራራዋል።

ገበሬውም "በል እንግዲህ ዳኛ ጋ እንሂድና በእኔ ከፈረዱ እንኳን አንዱን ሁለቱንም እሰጥሃለሁ" ይለዋል። ነብሩም "እንዲህ ቀኑን ሙሉ አፍነህ አውለህ ላይፈርዱብህ ነው?" ይለዋል። ሁለቱም ይስማሙና እንበሳ እንዲፈርድላቸው አንበሳ ጋር ይሄዳሉ። አንበሳም ነገሩን ከሰማ በኋላ "ለፍርድ አስቸጋሪ ነው፣ በገበሬው ላይ እንዳልፈርድ ህይወትህን አድኖታል፣ በነብር ላይ እንዳልፈርድ ቀኑን ሙሉ በስልቻ ውስጥ አውሎህ የሚበላ አላገኘህም፣ ለማንኛውም ዮተሻለ ዳኛ ብታገኙ ወደ ሌላ ሂዱ" ብሎ ያሰናብታቸዋል። በየአራዊቱ ቤት እየሄዱ ቢጠይቁ አንበሳው ያላቸውን ዓይነት አስተያየት እየሰጡ ሸኙአቸው። በመጨረሻም ጦጣ እንድትፈርድ ይስማሙና ይሄዳሉ። ለጦጣ ሁሉንም ይነግሯታል። ጦጣዋም "የናንተን ጉዳይ ሰምቶ ለመፍረድ አስቸጋሪ ነው፣ እስቲ ገበሬ እንዴት አድርገህ እንዳዳንከው አሣየኝ" አለችው። ገበሬውም ነብሩን ስልቻው ውስጥ ከቶ "ይኸውልሽ! እህል አስመስየ፣ በስልቻዬ ውስጥ አድርጌ ያዳንኩት፣ እንዲህ አድርጌ ነው" አላት። ጦጣዋም "አሁን ነብሩ በጅህ ነው" አለችው። ገሬውም ገባውና ነብሩን በዱላ ቀጥቅጦ ገደለው ይባላል።

*ምንጭ፡- ዘሪሁን አስፋው፣ የሥነ-ጽሑፍ መሰረታውያን*

የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ፣ 7ኛ ክፍል

# ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

### የመነሻ መወያያ ነጥቦች

1. ድርሰት ምን ማለት ነው?
2. ድርሰት ዕፍኾሁ ታውቃላችሁ? ከዚህ በፊት የፃፉችሁት ድርሰት ካለ ስለ ፃፉችሁት ነገር አጭር መግለጫ ስጡ::
3. ስንት የድርሰት ዓይነቶችን ታውቃላችሁ? ስማቸውን ዘርዝሩ::

## ገዳምነሽ

ከሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ከወጣች በኋላ እንኳን ብዙ ነገሮች እፊቷ ላይ ድቅን ይሉባታል:: ያገላገለቻቸው እናቶች፣ የተወለዱ ህፃናት፣ እውጪ የሚጠብቀው የቤተ-ዘመድ ሁኔታ፣ የሌሎችም የተለያዩ ሰዎች ገፅታ እየተፈራረቀ ትውስ ይላታል:: ነፍሰ ጡሯ ስትጨነትና ስታምጥ ከሷ ጋር ያሉት ሁሉ አብረው ይጨነቃሉ፤ አብረው ያምጣሉ:: ስትገላገል አብረው ይገላገላሉ:: ዕልልታቸውን ያቀልጡታል:: ሲስተር ገዳምነሽም እንዲሁ አብራ ተጨንቃ፣ አብራ ወልዳ፣ አብራ እልል ትላለች:: ታዲያ በሙያው ስትቆይ "መውለድ እንደምን ከባድና እንዲህንስ መልካም ዐጋ ነው? መውለድን፣ ከሞትነት መገላገልን የመሰለ ምን ጥሩ ነገር ይገኛል? ከሞትነት ማገላገልንስ የመሰለ ምን ክቡር ሙያ ይኖራል?" እያለች በሀሳብ ትሰምጣለች::

በዚህ ሙያ ከተሰማራች ሁለት ዓመት ሆኗታል:: ጥንት በእንዲህ ዓይነት የሥራ ገበታ ላይ እሰማራለሁ ብላ ገምታ፣ አልማም አታውቅ:: የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች ነበር ወደ ነርሶች ማሰልጠኛ ማዕከል የገባችው:: ያኔ የሙያው ባህርይ ይህን የዛሬውን ይመስላል የሚል ግምት አልነበራትም:: ስለ ህፃናትና ስለ ሌሎችም ቢሆን ደንታ ቢስ ነበረች:: ኮርሱን በመከታተል ላይ እያለች ግን ዝንባሌዋ ከፍ እያለ፣ ፍላጐቷም እየጨመረ መጣ:: ተመርቃ አገልግሎት መስጠት ከጀመረች ወዲህ ለሙያው ከፍተኛ ግምት እየሰጠችው በመሄዷ በተለይ አዋላጅነትን አለቅጥ ወደደችው:: የልጅ ፍቅር አሳደረባት:: ህፃናት አካባቢዋ እንዲቀርቡ የማትሻው ገዳምነሽ ከጊዜ በኋላ በመንገድ ያየቻቸውን፣ በየደረሰችበት የሚገጥሟትንና የጎረቤት ህፃናትን ሁሉ እያቀፈች መሳምና ማጫወት ስትጀምር በልጅነት ጠባይዋ መቀየር የማይደነቅ አልነበረም::

*ምንጭ፦ ከአብዱ አህመዶ፣ <u>ሙሽራው እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች</u>*

# ምዕራፍ ሃያ አንድ

## የመነሻ መወያያ ነጥቦች

1. ሥነ-ቃል ምንድነው?
2. የሥነ-ቃል ክፍሎች ምን ምን ናቸው?
3. በቃል የሚነገሩ የሥራና የልጆች የጨዋታ ዘፈኖችን ታውቃላችሁ? የምታውቁ ከሆነ እስከ የተወሰኑትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዝፈኑላቸው::

## ሥነ-ቃልና ገበሬ

በግብርና ልዩ ልዩ ሥራዎች ላይ የሚዘመሙ ግጥሞች ሲጨኑ አያለ ጉዳዮችን እንደሚያንፀባርቁ እንገነዘባለን:: ከሁሉም በፊት ገበሬው የሙያውን ታላቅነትና ህልውና አስፈላጊነት በመግለፅ ለግብርና ያለውን ፍቅርና አክብሮት በጠነከረ ሁኔታ የሚያሳይባቸውን ግጥሞች እናገኛለን::

ኧረ ደግ ሚዜ ደግ ባልንጀራ፣
እርሻ ረስ አያለ ያበላል እንጀራ::
ከሁሉም ከሁለም እርሻ ደግ ናት፣
አፈር መስሎ ሰርቶ ጌታ መስሎ መብላት::

የግብር ሥራ ዋናነት /አስፈላጊነት/ ያለ በሬ አጋዥነት ሊታሰብ አይችልም:: የሀገራችን ገበሬም የሚያርሰው በበሬ ነው:: በሬ ለግብርና ሥራ ከፍተኛ አገልግሎት የሚሰጥ የቤት እንስሳ መሆኑ ግልፅ ነው:: በአጠቃላይ የገበሬው ሕይወት ከበሬው ጋር በጠለቀ ሁኔታ የተቆራኘ መሆኑ ይታወቃል:: ይህም በሥነ-ቃል ግጥሞች ይታወሳል:: ይህም በገበሬ አወዳሽነትና በበሬ ተወዳሽነት እንደዚህ ይቀርባል::

ብሬ ካላንተማ አያ ካላንተማ፣
አይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሰማ::
በሬ ያለህ ማነው ስምህን አሳንሶ፣
መንግሥት ሰማያት ሳይልህ ጨርሶ::

የግብርና ሥራውን በወቅቱ ያላጠናቀቀ ወይም የሥራውን አድካሚነት እያስታመሰ ግሽሽ የሚልና ሥራውን የሚጠየፍ ባላገር በሌሎች ገበሬዎችና በአካባቢው ሰዎች ዝቅ ያለ ግምት ይሰጠዋል::

በስንፍናው ይወቀሳል፣ ይሰደባል:: በወቅቱ ጠንክሮ ባለመሥራቱ በቤተሰቡ ላይ የሚያመጣው ችግር እየተሰላ የማይረባ ሰው መሆኑ በያጋጣሚው ይነገርበታል::

የግብርና ሥነ-ቃላዊ ግጥሞች ይዘት ሌላው ገፅታ እንዲህ ያሉትን ባላገሮች ለመውቀሻና ለማንቋሰሻ ማገልገላቸው ነው። ቀጥሉ የቀረበው ምሳሌ ይህንኑ ይመለከታል።

በበጋ እረስ ቢሉት ፀሐይ እየፈራ፣
በሐምሌ እረስ ቢሉት ዝናብ እየፈራ፣
ልጁ እንጀራ ቢለው በጅቡ አስፈራራ።

ግብርናን ገሸሽ የሚለው ገበሬ በዚህ ዓይነት ሲወቀስ ታታሪውና በሙያው የተመሰገነው ደግሞ በአካባቢውና በመንደሩ ሲሞገስና ሲወደስ ይታያል። በአስተራረሱ፣ በሰብል አጠባበቁ፣ በሚያገኘው ምርትና በጊዜ አጠቃቀሙ ከፍ ያለ ከበሬታ ይቸረዋል። ጉብዝናውም እንደሚከተለው ይመሰከራል።

በሬ ገራፊ እስከ ቅንድቡ፣
ነጭ ጤፍ አብቃይ እስከ ድንበሩ።
የግራሩን ሥር መንጥሮ ቢያርሰው፣
ነጭ ጤፍ አብቃይ ጅብ የማይጥሰው።

በሥነ-ቃል ዜማዎች ግብርናን፣ ገበሬንና በሬን ማንሳት ብቻ አይደለም የተለመደው። የሚወዱትንና የሚያደንቁትን ማነሳሳትም ዘወትራዊ ነው። ገበሬው ስለሚወዳት ወይም ልቡን ስለሰረቀችው ጉብል ያንጎራጉራል። የፍቅር ስሜቱን የሚገልፅባቸው ግጥሞች ገበሬው በሚያከናውናቸው የተለያዩ ሥራዎች ላይ ሲዜሙ ይሰማሉ። እንደሚከተለው፡-

በሬ ሲያሰቃየኝ አልጠመድ ብሉ፣
አጣማጅ ልትሆነኝ መጣችልኝ ቶሉ።
አራሽ ኑኝ ገበሬ እኔ ወዳጅሽ፣
ጅራፍ ሳጮህልሽ አጫውችኝ መጥተሽ።

ከነዚህ በተጨማሪ ገበሬው በሥራ ላይ በሚያሰማቸው ዘፈኖች፣ እንጉርጉሮዎች፣ ብሶቱን ጥላቻውን፣ ተቃውሞውን፣ እንዲሁም በዘመኑ የሚያያቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ክንዋኔዎች ላይ ያለውን አስተያየት ያንፀባርቃል። በአደባባይ የሚያወጣውንና በሆዱ ያመቀውን ሁሉ በሥራ ወቅት ይዘረግፈዋል። የበደለውን ሹም ያማርራል፣ የክፉውንና የጨካኙን ግፍ፣ ጉቦን፣ ምልጃን ሁሉ በዚሁ አጋጣሚ ያወሳል። ሁኔታው ዘወትር ሲያስጨንቀውና ሲያንገላታው ደግሞ እንዲህ ይገልፃል።

የሀብታሙ ቤት ዛሬስ መች ቸገረ፣
የደሀው ነው እንጂ ገመዱ ያጠረ።
ነጭ ማር ቢኖረኝ ወይም ሃያ ብር፣
ከባህር ገብቼ አልቀልጥም ነበር።



እስካሁን በግብርና ሥራ ላይ የሚሰሙ ግጥሞችን በምሳሌዎች እያጣቀስን አይተናል። የሥራ ግጥሞች በተዘፈኑበት ማህበራዊ አጋጣሚ ላይ ብቻ እንደሚያተኩሩም አውተናል። በይዘታቸው ስለሚሠራው ሥራ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ጉዳዮችንም እንደሚያነሱና ከግብርና ሥራ ውጭም ይህንን የመሰሉ ግጥሞች እንዳሉ ለመገንዘብ ያስችለናል።

## ክፍል አንድ፡- አንብቦ መረዳት

1. ቀጥሉ ለቀረቡት ቃላት በምንባቡ መሠረት ተመሳሳይ ፍችያቸውን በዐረፍተ ነገር ውስጥ አሳዩ።

ሀ. ሲጤኑ ሐ. አጋዥነት ሠ. ተወዳሽነት
ለ. ህልውና መ. የተቆራኝ

2. ቀጥሉ ለቀረቡት ቃላት ደግሞ ተቃራኒ ፍችያቸውን በዐረፍተ ነገር ውስጥ አሳዩ።

ሀ. አያሌ ሐ. ፍቅር ሠ. ከበሬው
ለ. አወደሰ መ. ስንፍና

3. በምንባቡ መሠረት ለሚከተሉት ጥያቄዎች ምላሽ በፅሁፍ ስጡ።

ሀ. በግብርና ሥራ ላይ የሚነገሩ ግጥሞች ምን ምን ጉዳዮችን ያነሳሉ?
ለ. በግብርና ሥራ ላይ ድክመት ወይም ስንፍና የሚታይበት ገበሬ በአካባቢው ሰዎች እንዴት ይታያል?
ሐ. ለግብርና ሥራ ዋና ወይም አስፈላጊ የተባለው ምንድነው?
መ. በምንባቡ ውስጥ የግብርና ሥራ እንዴት ተደርጎ ነው የቀረበው?
ሠ. የግብርና ሥራ በወቅቱ ጠንክሮ ካልተሰራ ምን ዓይነት ችግር ያመጣል?

## ክፍል ሁለት፡- መፃፍ

1. ቀጥሉ የቀረቡት የሥነ-ቃል ግጥሞች በምንባቡ መሠረት የያዙትን ሀሳብ በፅሑፍ ግለፁ።

ሀ. በሬ ካላንተማ አያ ካላንተማ፣
ዓይኔም አያይልኝ ጆሮዬም አይሰማ።

ለ. የግራሩን ሥር መንጥሮ ቢያርሰው፣
ነጭ ጤፍ አብቃይ ጅብ የማይጥሰው።

## ክፍል ሶስት፡- መናገር

1. በአካባቢያችሁ የግብርና ሥራ ጋር በተያያዘ የሚነገሩ ሥነ-ቃሎችን ዕፋችሁ አምጡና ለጓደኞቻችሁ አንብቡ።
2. በአካባቢያችሁ ከተለያዩ በዓላት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ሥነ-ቃሎችን ዕፋችሁ አምጡና በቡድን በቡድን በመሆን በሚያነሷቸው ነገሮች ላይ ተወያዩባቸው።



216

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

### የመነሻ መወያያ ነጥቦች

1. ለዛ ያላቸው ንግግሮች ከተራ ወይም ዘወትራዊ አነጋገሮች በምን ይለ
2. በፈጠራዊ አነጋገሮችና በዘይቤ ዊ አነጋገሮች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
3. ንግግርን ለዛ ባለው ሁኔታ ለማቅረብ ምሳሌያዊ አነጋገሮች አስፈላጊ ናቸው ትላላችሁ? የተወሰኑ ምሳሌዎችን ስጡ::

## ከባሌ መልስ

የባሌን ምድር ንዳር እስከ እንደማቅ ያለበሰው ጭጋግ እየለቀቀ ሄደና ረፋዱ ላይ ወሐይ ብልጭ አለች:: የጥጥ ባ የሚመስል ጉም በንፋስ እየተባረረ ወደ አርሲ ምድር ይሮጣል::

ዲንሾ ግን ያው እንደወትሮዋ አኩርፋለች:: ዲንሾ ላይ ሳያካፋ መድረስ ዘበት ነው:: ከረምት ከበጋ ታዲያ ዩዲንሾ ውበት ከነዝናቧ ነው:: ያለዝናብ ዲንሾ አትሆንም ነበር:: በጋርኳ ውስጥ በነፃነት የሚኳልሉት ብርቅዬ አራዊት፣ እንደመስታወት በጠሩት ወንዞች ውስጥ የሚርመሰመሱት ዓሣዎች፣ ዘወትር አረንጓዴ ምንጣፍ የደረቡ የሚመስሉት ጉብታዎች፣ ያለዝናብ የሚታሰቡ አይደሉም::

አውቶብሱ ለቁርስ ዲንሾ ሲቆም ተሳፋሪው በሙሉ ይወርዳል:: ቁርስ የሚያደርገውም የማያደርገውም ዝናብም ሆነ ብራ ሁሉም ሰው ከመኪናው ወርዶ እግሩን ማፍታታት ወይም የዲንሾን ነፋስ መቀበል ይፈልጋል::

መኪናው ዲን ደርሶ ሲቆም መንገደኞቹ መውረድ ጀመሩ:: ኢየሩሳሌም ከመጠችበት አልተነ ችም:: ዓይኖቿ ቀልተዋል:: ተከናንባው የነበረውን ጋቢ ከእራሷ ላይ ስታነሳው ፀጉሯ እንደ ፈረሰ የእህል ነዶ እየተዝለፈለፈ ወርዶ ፊቷን አለበሰው:: ሁለት ወፍራም ጉንጉኖች ሠሩና ወደ ኋላዋ ወረወረቻቸው:: ከዚያም እንደጋለ ምጣድ የሚፋጁትን ጉንጮቿን አባበሰችና ፣ ነይኖቿን ዳርና ዳር በአመልካች ጣቷ ጠረግ አድርጋ ቀና ስትል አጠገቧ የነበሩት ሰዎች ሁሉ ከመኪናው ላይ ወርደዋል::

*ምንጭ:- መሉጌታ ጉደታ፣ የእንባ ጠብታዎች፣ ገጽ 23-24 መጠነኛ መሻሻል ተደርጎ የተወሰደ*

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት

## የመነሻ መወያያ ነጥቦች

1. ልብ-ወለድ ምንድነው?
2. ልብ-ወለድ ከይዘትና ከአቀራረብ አኳያ በስንት ይከፈላል?
3. ልብ-ወለድ ዕሁፎችን አንብባችሁ ታውቃላችሁ? እስኪ ያነበባችኋቸውን የመጽሐፎች ርዕስና የደራሲዎቻቸውን ስም ግለጹ::
4. የልብ-ወለድ አላባውያንን /ፍሬ ነገሮች/ ታውቋቸዋላችሁ? የምታውቋቸውን ያህል ዘርዝሩ::

## ውለታ

"የልብ ወዳጅህ ከሆነ የልብ ወዳጅ ውለታ ይከብዳል እንዴ?" አለ ጉዱ ካሳ::

መውደድስ...ለኔ የሚያደርገውን ሁሉ ስመለከት እንዲያውም ከራሱ አብልጠ የሚወደኝ ይመስለኛል፣ እኔም በጣም እወደዋለሁ:: ነገር ግን ውለታው በ ም በዛና ለመክፈል የሚልችለው መስሎ ስለታየኝ ከበደኝ::"

"ለምን ይከብድሃል? ወዳጅ እኮ ውለታውን እንዲሁ ይወላል፣ እንዲሁ ይሰጣል እንጂ አያበድርም::"

"አዎ! እንዳለት ወዳጅ ውለታውን እንዲሁ ይሰጣል እንጂ አያበድርም፣ ብቻ ከወዳጅች እንዱ ሁልጊዜ ውለታ ሰጪ፣ ሁለተኛው ሁልጊዜ ውለታ ተቀባይ ሲሆን፣ ውለታ ሰጪው አይሰለችውም? ውለታ ተቀባዩስ ይለኝታ ካለው አይከብደውም? "

"አያመስለኝም! ይልቅ ቅድም እንዳልከው እንኳን ከራሱ አብልጠ የራሱን ያህልም የሚወድህ ከሆነ አንተም ያንኑ ያህል ከወደድከው ሰው ለራሱ የሚያደርገውን ውለታ እንደማይቆጥር፣ እንዲሁም እንደራሱ ለሚወደው ወዳጁ የሚያደርገውን ውለታ አይቆጥርም:: እንዲያውም ሰው እንደራሱ የሚወደው ወዳጅ እንኳን የለውም፣ ከልቡ ለሚወደው ወዳጁ ውለታ ባደረገ መጠን ደስታው እየበዛ ይሄዳል እንጂ አይሰለችም:: የእውነተኛ ፍቅር ባለቤት ለመስለቻቸት ቦታ የለውም!"

"የሚለት ሁሉ እውነት ነው:: ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ እሱ ለእኔ ያደረገው ብዙ ሆኖ እኔ ለእሱ አደረኩት የምለው ነገር ስላጣሁ ትንሽ ቅር ይለኛል::"

"እርዳታ በሚፈልግበት ጊዜ እያወቅህ እርዳታህን ነፍገኸዋል?"

"ቀለሙ ተቸግሮ! የአኔን እርዳታ ፈልጎ እኔ ልነፍገው ? ኧረ አሱስ የለም!"

"እሺ እንግዲያው አንተ እርዳታ ለመርዳት ወይም ውለታ ለመዋል እንዲመችህ ተቸግሮ እንድታየው ትፈልጋለህ? "

"ኧረ በስመ አብ! ኧረ ደህና ይሁንና የእኔ ውለታ ይቅርበት ጌታዬ!" አለ በዛብህ ትንሽ ፍርሞም ብሎ::

"ይሽውልህ! እንግዲያውስ ቅድም አንተ ያልከው ሞሞቀኛ አስተያየት፣ የሞቀኛ ስሜት እንጂ የልብ ወዳጅ አስተያየትና የልብ ወዳጅ ስሜት አያደለም::"

"እንዴት? ምነው?"

"ለምን እኔ እርዳታ በምፈልግበት ጊዜ ወዳጄ እርዳታ በሚሰጥበት ሁኔታ ሆነ ብሎ የሚያዝን፣ በወዳጁ መልካም ዕድል የተመቀኘ መስሎ ሊታይ ይችላል::"

"እንደሱ አድርጎ ከተረዳሙት ሊተረጎም ይችላል፣ ብቻ እኔ በትርጉም ሳይሆን በቀጥታው በቀለሙና በእኔ መካከል ያለውን ፍቅርና የውለታውን ብዛት ስመለከት ምናልባት ይህ ከእንድ ወገን ብቻ የሆነ የውለታ ብዛት የጋራ ፍቅራችንን እንዳይቀንሰው፣ እንዳያበላሸው ፈርቼ ነው:: የቀለሙን ፍቅር እንደ ብዙ ሃብት አለኝ ብዬ ስለምመካበት፣ እሱን የሚቀንስብኝ ምክንያት እንዳያፈጠር እጠነቀቃለሁ:: ምንም ከእርሶ ባላውቅ ከወዳጅህ ጋር በፍቅርና በመከባበር ለመቆየት ብትፈልግ ውለታው አይለፍብህ:: የሚባለው ተረት ጥሩ ትምህርት የሚሰጥ ይመስለኛል::"

"አም በወዳጅነት ስም ለሚነግዱ ገበያተኞች ጥሩ ትምህርት የሚሰጥ ተረት ነው! በእኔ አስተያየት ግን ውለታ እንዲዋልላቸው ውለታ የሚውሉ ነጋዴዎች እንጂ የልብ ወዳጆች አይደሉም! ውለታውን ቆጥሮ ሰጥቶ፣ ቆጥሮ የሚቀበል የልብ ወዳጅ አይደለም! በእኔ አስተያየት የልብ ወዳጅ ማለት ለወዳጁ የሚያደርገውን ለራሱ እንደሚያደርገው ሁሉ ሳይከብደው ደስ ብሎ የሚቀበል ነው! በል አሁን ወደ እራትህ ሂድ:: ክርክራችን ዛሬ የሚያልቅ አይመስለኝም ::"

*ምንጭ:- ሀዲስ አለማየሁ፣ ፍቅር እስከ መቃብር፣ ገፅ 380-382፣ መጠነኛ መሻሻል ተደርጎ የተወሰደ::*

# ምዕራፍ ሃያ ሰባት

## የአንድ ቀን ውሎ

የኩርኩር ዘመን አልፎ ሰይቼንቶ በአዲሳ አበባ አበባ ሥራ ሲጀምር የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ ነበርኩ። ትምህርት ቢታችን ክትልቅ መንገድ ዳር ነበር እና አንዱ የትምህርት ቢታችን ጓደኛ እየቆመ አላፊ አገዳሚውን ሲመለከት ሰዎች እጃቸውን እያወዛወዙ አውቶሞቢሎች እያቆሙ "የት ነው?" እያሉ ለመጠየቅ እያሳፈሩ ሲወስዱ አይቷል። በፊልም እንዳየውና አሜሪካዊው አስተማሪያችን እንደነገረን ሠልጥኖ "ሲፍት" መዘውተሩ መሰለውና አንድ ቀን እሁድ እሱን ላቆመለት ሲይቼንቶ "እበባከም ፒያሳ" ብሎ ተሳፈረ። ክዚያም በቃኝ እግዜር ይስጥልኝ፣ ያሰንብትልኝ" ሲል መንገዱን መቀጠል ነዋ።

"ምነው ሰውዩ ክፈሰ እንጂ! " ሲል ሾፌሩ ሥንዝቶኝ።

ቀራው ፡ማሪ ነው አለና አመዱ ቡን ብሎ ፣ "ምኑን ሲል የሊባ ጣቱን በቀርሱ ነክሶ ጠየቀ። ባለማወቅ እንጂ ለማሮበርበር አለመሆኑን የተረዳው /ወይም ገና አዲስ ኑጋዲ በመሆኑ ነገር ጠልቶ/ ሾፌሩ እምብዛም ሳይጠናወተዉ፣ በማመናጨቅ አኳኋን "በል ሂድ" ብሎት አውቶሞቢሉን እሽክረክረ። ያን ጊዜ የሲቼንቶዎች አገልግሎት ገና መለመዱ ነበር።

ክዚያ ወዲህ በአዲስ አበባ ጎብረተሰብ መካከል የሲይቼንቶ አገልግሎት ይዞታ እጅግ እረጅም ጎዳና ሠዋድል። ክአዲስ አበባ ተንቀሳቃሽ ሕይወት ወይም የሕይወት እንቅስቃሴ ትልቅ ክፍል የያዘ ነው። ሲይቼንቶዎች በይዞታቸው መጠን ደግሞ ተጠቂነታቸው በዝቷል።

ብልግናቸውና ድፍረታቸው እይጣል ነው። ሲቶችን ሚሚገፏ ይሻል። ወንዶችን ይጠልፋሉ። ተሳፋሪን ከውለታ ውጭ የትም ይጥላሉ። ሠሸት ሲልም ይዘርፋለ። ክዚህም ሁለ በላይ ለአዲስ አበባ ክተማ የትራፊክ አደጋ በአብዛኛው ምክንያቶቹ እነርሱ ናቸዉ ይባላል። አም እውነትም ይሁን ውሸት፡ በከተማው ነሮ በሰባራ ስንጥሩ ይወተላለ። የትም ሠብተ ቤት ያመሸው ወንድ ሲይቼንቶ አጥቼ ሲል ለሚሰጉ ሊያሳብብ ይችላል። ቦርሳው የትም ያረሳ ባለሰይቼንቶ ዘረፊኝ ይላል። ጠንብዘ የኢሊትሪክ ምሶሶ የለተመውም በድንገት ሲይቼንቶ ከፊቱ ቶሶና ተጋጨቡ፡ የሚለውን ምክንያት ይሰማል። በአዲስ አበባ ጥራሶች ነጋ ጠባ መሳት ከሚወርድባቸው ክሳሎች እንደኛቼ ሲይቼንቶዎች ኖቸው። ምን ያህሉ እውነት ነው? ምን ያህሉ ኮብኳር ዮቲጋንን ሲሰን ይችላል? አንድ

የሲይቼንቶው ባለቤት በወር 120 /አንድ መቶ ሃያ ብር/ ይከፍለኛል። እኔ ደግሞ ቤንዚኑን ችዬ በቀን ቢያንስ አሥሪ አምስት ብር ማስጉት አለብኝ። አውቶሞቢሏ ተበላሽታ ወይም በትራፊክ ተይዛ ውላ እንደሆነ በቂ ምክንያት ማቅረብ አለብኝ። አለበለዚያ መታማት፣ መጨቃጨት፣ ቆይቶም ከሥራ መባረር አለ። እንደገና "ሆ" ብሎ ሥራ መጀመር ነው።

የሲይቼንቶ ሾፌር በተሳፋሪና በጋዜጣ ዐይን ተደጋግሞ ተተርኳል። ተሳፋሪስ በሲይቼንቶ ዓይን እንዲት ነው? የሲይቼንቶ ሾፌር የራሱ ሮር እንዳለውስ ? ለዚህ የእንዱን ቀን ውሉዱን ብቻ እተርካለሁ። የማርያም ዕለት ነው።

ክመኝታዬ በአሥራ አንድ ሰዓት እንታለሁ። እስክለባብስ፣ እስክታጠብ፣ እስራ አንድ ተኩል ይሆናል። ክቤቴ የምወጣው ለክቱም ለደቱም ምናምን ላልቀምስ ነው። ያች መክረኛ ሚስት ዘወትር በአሥራ አንድ ሰዓት እየተነሳች፣ ቁርስ ማዘጋጀት የት ትችልና? የሲይቼንቶ ሾፌር ቁርስና ምሳ ክደረስበት ነው።

ጥቂት እንደ ሂድኩ ክአጠገቡ ሻንጣ ሞልቶ፣ በካፖርት የተጠቀለለ ሰው እጁን እርገበገበልኝ። ባያርገበገብም ማቆሜ አልቀረም ነበር። ተሳፋሪ በአቋሙ፣ በአስተያየቱ ክሩት ያስታውቃል።
"አውቶቡስ ተራ"

"ሰባ አምስት ሳንቲም" አልኩት። እርቀቱ ዘጠኝ ኪሎ ሜትር ያህል ነበር። ሌላ ተሳፋሪ ካላገኘሁ ቢያንስ ቢያንስ የአርባ ሳንቲም ቤንዚን አቃጥላለሁ። ራሱን ነቀነቀ። "እሺ ሃምሳ ሳንቲም ይግቡ፡" ሰውየው ግን ፍንክች አላለም። መቼም የተዋት ገጅ ነውና በስሙኒው አላፈርኩት።
ጥቂት እንደተጓዝን ክአጠገባቸው ሻንጣ የደረደሩ ሰዎች ክምችት ብለው አገኘን፡ ቆምኩ።
"ሁለ ሣዚያ ሶስት ሰው"
"ሁለ ሣዚያ ሶስት ሰው" ደገመልኝ፡ አቅማማሁ
"ሃምሳ ሃምሳ እንከፍላለን" አሉ። የፊተኛውን ተሳፋሪ በአስተያየት አቆላመጥኩት። ወየ ፍንክች
"ሁለት ብር" በስሙኒ ሁለት ብር መለወጥ ቀላል ምርጫ አይደለም። በጥዋቱ መኒታረኩ ደግሞ አስጠላኝ። አጉል ጊዜ ክመጥፋቱ እርቡኑ አድርሶ ሌላ ገበያ ማጣደፉ ይሻላል።

አውቶቡስ ተራ እንደ ደረስን የአሥር ብር ኖት አውጥቶ ዘረጋልኝ። "ዝርዝር የሉትም" "የለኝም" አለ በንረንን ድምፅ። የተገላቢጦሽ ተቆጥቷል። "እሺ መንዝሬ ላምጣ" ሰል ወየትሁት

አልያዝኩም። ተዘድሬ ማምጣት ነበረብኝ ግልት ነው? የኔም ንዲት ኸፈለ። "ዘል ውረድ ቶሱ!" አልያግ በኢታው እንድ ባለ ሲይቼንቶ ሰደሀኝ ብሱ ዪጋዚማ ያመግል።

ደንኑቱ የዝያ እምላክ አከተትሱ ለንሠልኝ። "ቤተ ክርስቲያን" ይሉኛል፡ አንድ ደንስንስ ያሱ ወይዘር፣ የሚሳለሙትን ቤተ ክርስቲያን አብሬያቸው የማዘወትር ይመስል፣ "ማርያም ነዋ!" ባለግወቱ ተደንቶዋል። ክትድስት ማርያም መርካቶ፣ ክመርካቶ ቅድስት ማርያም፣ ሚዝስኩ አደባባይ ተዋት ገቢ ሠራተኞችና ተሳላሚ ሳሥላስ ሰዓት ሰዓት ሞላ። ከመጀመሪያው ንዲቴ በእሁኑኛው ገበያ ጋር፡ እናብ ጉዳይ የምሄደላትን የሠር ኮንትራተኛ እረስቻታለሁ። እርሷም ነገ በጋዚማ ልትጽፍብኝ ነው?

ከሦስት ሰዓት በኋላ የሚያጋጮኝ የቢሮ ሠራተኛ ተግፋሪዎች የሠረ ድምር ያልለተቃቸው ፡ ሥራቸውንና አለቃቸውን የሚያማርሩ ነቸው።

"ትናንትም ለስት እንሳለች ነው። ግላለፈ ነው። የራስ ጉዳዩ ነው ያንሳ እንጂ። እባክህን ተመው የኔ አለቃ ራስ የመጣሁ በእምስት ሰዓት ነው። ታሪያ ለላውን ፈርሙ ይላል። ይቅግኝና እንተያያለን፡ ሌላው ይመልሳል። የኔታክብቸው አይመስላቸውም።

በዚሁ ጊዜ ድግሞ ሌሉች ደንበኞች መበቆችና ነገርተኞች ናቸው። ፍርድ ቤት ሲሉኝ ክፍተኛ ወይም እውራጃ ሠሆን አስበት። ወረዳውስ በሲይቼንቶ ሾፈሮች ከስና ቅጣት ተሞልተ የስ፡ አንዳንዶቹ በኔ ሙግት ለመሣር ይክጅላሉ። አራራ አምስት ሳንቲም ሆኖ የለ" ይላል ከተሳፈሩ፡ ጉዞ ከጀመርን በኋላ፡ የፈለጉ ቢንተሳተሱ የራሳቸው ጉዳይ ነው። እንድ ሁለት ነበሩ እንርሱም ትተውታል። ስል በለዘብታ እመልስላቸዋለሁ። ቢጋዚማ ወደኑ ጋውጅ ካልፈለጉ መውረድ ይችላሉ። በውለታዬ ሠሠረት ከሥፍራው ስደርስ ነዋ፡ ያኔ ፍርድ ቤቱ ሀ"ኳስኗል።" መልስ አልሰማቸውም። መነፋላቸው ላይትር ሳምባዉን ያመልቱታል።

አንዳንድ ሲይቼንቱ ነጂዎች "ሲት ተሳፋሪዎች ለመዳፈር ይከጅላሉ" የሚለው ሐ"ሄት ምናልባት በከፈል እውነት አለው። ሠንደኛ ሰዓት ... አንዳንድ ሲቶች ወጣትና ጉረምሳ ነበን ከሽ ... ነን መቀመጥ ደስ ይላቸዋል ... ለምሳሌ ጠዋት ያረፈደባቸው የመ ... ቦኛዉ በአኗት ሺ ጊዜ ይትርታ ብዙ ፈተን ስለሳ ... ነን ወስላታ፣ ቆይማ" ስትል በመሽን ... ጭመጠች። ደሀና ለባዘለ ከሮዓት ያመሩ ... ሾፈሩ የሚጠረጥሩት ተሳፋሪዎች ብዙ ናቸው። በአጋርቶ ሸሚዝ ላይ ደንስ ሹራብ በጅንትላት ላዩ ያዘ"ው ... የብ ባደረገ ሹፈር ግን ይዝናናል። ... ሠሠመ ሩርዬ መምሰልም አለ።

ግራ ሊስንቱቱ ይደርሳሉ። ብዙዎቹ ቢነጋገሩ ፈጽሞ አይደግሙም። እንዲያውም መንሣሣት ... ነው። ስንዳንዴ ሽሬ ላይ ሥንቱን ያመርጹታል።

እቱ እቴ ፡ ምን ያቆምሃል ? ሂድ እንጂ ፡ ሴላ ሰው ለማፈር የታጣሁ እንደሆነ ... ትገሽ ፈቶት በል፡ የምንወርደው እዝያ ጋ ነው።" "ያላችሁኝ ከዚህ ድረስ ነው" እላቸዋለሁ። "ታዲያ ምን ያመለስ ?" አግ በቢንዚን እላለሁ። በሆዴ ከሁሉም የሚያስጨንቀኝ የጠላው ሽታ ነው። እናን አድርጎ ያደዘኛል። ሞትታውም በማም የባሰባቸው አንድም "ሲማላኝ ነው" ብለው ሳይጨርሱና አውቶሞቢሏን አቁሚ ለማውረድ ፋታ ሳይሰጡኝ "ቢ" አድርገው ወንበሩን አጥለቀለቁት። እኔም እየተናንቀኝ እንደምንም ችዬ አደረስኳቸውና በኩሊ አላጥብኩ። ሽታው ግን ሊጠፋ አልቻለም። የጠማ መንገደኛ ማሣፈር ችግር ነው። አባክመን ቀስር ልደታ፣ ጉለሌ፣ መርካቶ፣ ጎላ ሠፈር ጨርቆስ፣ ቦሌ... ... ... ጎፋም ሠፈር ስንከልክል ቆየኩና ... ... በዛር እንደሚወጣ ሁሉ፣ ራሴን ሊያሳምመኝ የተቃረበውን የመጠጥ ሽታ በመጠጥ ለመሸሽ ሞ... ... መጅ ቤት ጎራ ማለት ነዋ፣ ሳይታወቅ ሁለት ሶስት ጠርሙሶ ይገባል። በዋቅታ ጊዜ ሳይታወቅ ... ሁለት ልጅ ሳይ ጎልጅ ቤት በውጣ ሞቅ ብሎኝ ደሀ ብዬ ነበር። ... ... ...

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ

## ሙሉ ልብስ

### ክፍል አንድ ሥኑጹሁፍ

### መልመጃ አንድ

በምድብ 'ሀ' ሥር ለተዘረዘሩት የልብ ወለድ አላባውያን ከ'ለ' ምድብ ስር መገለጫዎቹን በመምረጥ አዛምዱ

| "ሀ" | "ለ" |
|---|---|
| _____ 1. ገፀ ባህርይ | ሀ. ከልቦለዱ ታሪክ ተጨምቆ ወይም ተፈልቅቆ የሚወጣ መልዕክት |
| _____ 2. መቼት | ለ. በምክንያትና በውጤት የተሳሰረ የድርጊቶች ቅደም ተከተል |
| _____ 3. ግጭት | ሐ. ባለ ታሪክ |
| _____ 4. ጭብጥ | መ. ገፀ ባህሪያት እርስ በርስ የሚፈጥሩት ንትርክ ወይም ከራሳቸው ሀሳብ ጋር የሚፈጥሩት ቅራኔ ነው። |
| _____ 5. ታሪክ | ሠ. ሰፋ ያለ ታሪክና ብዙ ገፀ ባህሪያት ያሉት |
| _____ 6. ትልም/ሴራ | ረ.በጊዜ ቅደም ተከተል የተደረደሩ የሁነቶች ትረካ ነው። |
| | ሰ. 'መች' ና 'የት' ከሚሰኙት ቃላት የተመሰረተ |
| | ሸ. ደራሲው ታሪኩን የሚያቀርብበት ትረካ |

### ሙሉ ልብስ

እማይዩ ! ነው የምላት። ተልኬ ሄጀ ስቆይ ወይም ከልጆች ጋር ተጣልቼ ስትቆጣኝ ወይም ሳትመታኝ ግን አኮርፋትና "አንቺ እማ" ብዬ አጠራታለሁ።

እሷም "አንተ አንዱ !... አንዴ... አንድዬ" ካለችኝ ደስ ያላት መሆኑን አውቃለሁ። እኔም እንኳን ስሜን ጠርታ ሠፈራችን ስትደርስ እቤት አስከትደርስ አርፌ መቀመጥ ያቅተኛል። እሷ እንደሆነች ለሠፈሩ ሰዎች የምታወራው ነገር ስለማታጣ ገና በሩቅ ድምጿን እሰማዋለሁ።

በተለይ እማማ ደፈርሻን ሳታናግር በበራፋቸው ያለፈችበት ቀን ትዝ አይለኝም። ዛሬም "እትዬ ደፈርሻ ደህና ዋሉ? ልጄ ከሰል ሲያመጣልኝ እካፍልሻለሁ ብለውኝ አልነበር? ምነው ዝም አሉኝ ታዲያ?" " በይ እንድርያስን ላኪና አንድ ዛምቢል ውሰጂ። ረስቼው ነው እናቴ። አሁንም ደርሰ ታል።

ይኸኔ ነው " አንዴ ! አንዱ ! አንድዬ" እያለች መጣራቷን የቀጠለችው። ድምጿን ሰምቼ ዝም ማለት አይሆንልኝም። እሷ ጠርታኝ ይቅርና ከሰው ጋርም ቆማ ስታወራም ቢሆን ካጠገቧ ቆሜ ቀሚሷን ይዤ ብታከኮት ደስ ይለኛል። ጥሪዋን እንደሰማሁ ብር ብዬ አጠገቧ ደርሼ አንገቴን ወደ ላይ አንጋጥጬ እየተመለከትኳት "ወይ! እማዬ" አልኳት።

"እርጌውን ዘምቢል አምጣና ከትዩ ደፈርሻ ቤት የሚሰጡህን ዕቃ ይዘህ ና" አለችኝ።

ባመጣሁት ከሰል ውሃ አሙቃ፣ ሰውነቷን ታጠበችና አዲስ ያሠራችውን ቀሚስና ኩታ ለብሳ፣ "እናትህ አላማረብኝም ታዲያ ?" አለችኝ፣ "እማዬ ቆንጆ ነሽ እኮ! እንዴት ያምርብሻል! ጫማም ገዛሽ እንዴ? ዘንጠሻል" አልኳት።

ይኸን ጊዜ ድንግጥ አለችና እኔን በማየት ፋንታ ጫማዋን አየች። እገዛልሃለሁ ብላኝ ነበር። ለኔ የገባችውን ቃል ሳትፈጽም ዛሬ ስራሷ ሽራ ጫማ ገዝታ ማድረጓ አሳፍሯታል።

"ዛሬ ቀኑ ስንት ነው?" አለች። "ዛሬ ቀኑ እኮ መድኃኒያ አለም ነው። የነማማ ዙሪያሽ ማህባር ዛሬ ነው። ረስቼው ነው። ጠበል ቅመሽ ብለዋል" አልኳት፣ ችኩል ችኩል እያልኩ።

"እህ ፡ ሐያ ሰባት ለካ ዛሬ ነው?" አለች።

ድሮ ቀን የምትቁጥረው በአላት እየጠራች ነበር። ዛሬ ፈደል አውቃ ቀን መቁጠር፣ ስም መጻፍ፣ ያገኘችውን በአማርኛ የተጻፈውን ነገር ሁሉ ማንበብ ሆኗል፣ የሷ ነገር።

እማይዩ አዲስ ልብሷን ለባብሳለች። አዲስ ጫማ አድርጋለች። ሌላ ጓደኛ የላት። ጓደኛዋ እኔ ነኝ። ወደ ሰው ቤትም ስትሄድ ታስከትለኛለች። ግን ድሮ ልትወጣ ስትል የምትሰጠኝን ትዕዛዞች ሁሉ አልተናገረችም።

እኔ ግን አፍ አፏን አጠብቃለሁ። ዝም አለችኝ ብዬ መናገር ጀመርኩ።

"እማዬ ልብስሽ በጣም ያምራል።"

"ወደድከው ?"

"አዎን በጣም ቆንጆ ነው። እነማማ ዙሪያሽ ቤት ልትሄጂ ነው?"

"አሁን አልሄድም" አለች ሌላ ምንም ሳትል።

"የምትሔጅበት አለሽ ?

"አዎን" አሁንም ዝም።

"እኔም ካንቺ ጋር እሔዳለሁ ? እግሬን ልታጠብ ? ፊቴን ልታጠብ ? ፀጉሬን ሳበጥር?" አልኳት ስፈራ ስቸር ልቤ እየመታ።

አሁንም መልሷ፡ ' አይ' ብቻ ሆነ። ልታደርገው የማትፈልገው ወይም የማትችለው ነገር ሲያጋጥማት ብዙ አትናገርም። ዝም ትላለች ወይም 'አዎን' ወይም 'አይ' የሚል መልስ ትሰጣለች።

ብዙ አሳብ ገባኝ። የልጅነት ታሪኳን፡ በሕይወትዋ ላይ የገጠማትን ችግር፣ ከአባቴ ጋር የነበራቸውን አኗኗር ሁሉ ታወራልኛለች። እኔም ዝም ብዬ አሰማታለሁ። ታሳዝነኛለች፣ አንዳንዴም ታስቀኛለች። 'አይ ልጅነት' ትለኛለች። እኔም የማይሆን ተያቴ መጠየቄ ይሰማኛል።

እግይዬ እናቴ ብቻ አይደለችም። እኔም ልጅዋ ብቻ አይደለሁም። ጓደኛዋም ነኝ። ሁሉንም ታወራልኝ ነበር።

ዛሬ ግን አላወራችልኝም። ዛሬ ከሁሉም ቀናት በላይ በጣም የምታከብረው ቀን ነው። ታጂያ ምንድነው ያ የምታከብረው በአል ? ግሀበሩ እንደሆነ ሁልጊዜ በየወሩ የምንሄድበት ነው። እዚያም ቢሆን 'አሁን አልሄድም' ብላለች። ታጂያ 'የት ልትሄድ ነው የደበቀችኝ' እያልኩ ሳሰላስል፡ ከሩቁ የሰማሁት የድምፅ ግጉያ አሳቤን አቋረጠኝ።

' ሀሎ ሀሎ ! የቀበሌያችን ኗሪዎች የሆናችሁ ሁሉ !

በተበሌያችን መሠረተ ትምህርት ያጠናቀቁ ዛሬ ስለሚመረቁ በምረቃው ሥነ ሥርዐት ላይ እንድትገኙ ተጋብዛችኋል' አለ በድምፅ ማጉያው የተሳለፈው ድምፅ።

ትዝ አለኝ። እግይዬ መሠረተ ትምህርት አጠናቃለች። ግታ ስትፈትል ታመሽ ነበር። 'ነይ እንተኛ መሽቷል ስላት፡ ስመረቅ የምለብሰው ስለሆነ ቶሎ ቶሎ መፍተል አለብኝ' እያለች ያወራችልኝ በአዕምሮዬ ውስጥ መጣ። 'ለካ እዚያ ልትሄድ ነው እንዲህ ያመረችው ! ለራስዋ አዲስ ልብስ ብትለብስ እኔን ባርጌ ልብሴም ቢሆን ብትወስደኝ ምናለበት ? ልጅዋ ነኝ' ብዬ በሆዴ እግይዬን ተቆጣኋት።

"በል ቤቱን ጠብት፣ ቶሎ እመጣለሁ" ብላኝ በፈት በር ወጣች። ወጣ እንዳለችም፣ የፈት በሩን ከውስጥ ተረቀርቅሩና ብዙ ጊዜ እሷ ስታደርግ እንዳየሁት፣ በኋላ በኩል በሩን ልቆልፍ ፈለግሁ። ያቺን እኔ ነፍስ ከገወቁ በፈት የነበረች እርጌ ቁልፍ ድሮ ከምትቀመጥበት ቦታ ብፈልግ አጣኋት። እግይዬን ከሩት ሆኜ ልከተላት ስላሰብኩ ቶሎ ቆልፈ ለመሄድ በጣም ቸኮልሁ። ቁልፏ የዛገች ስለ ነበረች፣ ዐፈር መስላ አንድ ቦታ ተደብቃ ይሆናል ብዬ ብፈልግ፣ ብፈልግ ላገኛት አልቻልኩም። 'እኔ ግን ምንም ቢሆን አልቀራት። እንደምንም ብዬ እሄዳታለሁ!' ድንጋይ አመጣሁና በውስጥ በኩል በሩን ደገፍ አደረግሁት። እንዳሰብኩት ተዘጋ። 'ኋላ እንዲት ሊከፍት ይሆን ?' ብዬ ስመለስ የግደርገውን እንዲ ሞከርኩ። እጀን በታችኛው ክፍን በኩል ሾለከ አድርጌ ስንፋው ተከፈተ። የኋላውን በር ከዘጋሁ በኋላ ተቂት ርተ ብዬ ሄድሁ። እግይዬን ራቅ ብላ አየኋት። ወደ ቀበሌያችን አዳራሽ እየሄደች ነው። አንድ አሳብ ስለ መጣልኝ፣ እሷን መከተሌን ትቼ ወደ አንድ አብሬው ከምጫወተው ልጅ ቤት ሄድኩ። ወደ ልጁ ጠጋ ብዬ፣ "ያንተን ዐይነት ልብስ ልታስፋልኝ ነው እናቴ። መስጀ ለልብስ ሰፊው እንዳሳየው ታውሰኛለህ ልብስህን" አልኩት።

ልጁ እሺ ብሉ ወደ ቤታቸው ይዞኝ ሲጋበ፣ "እናቴ እንዳትቆጣ የምጫወት መስለን መኝታ ቤት እንገባና የፈለግኸውን ልብስ ቀስ ብለን እናወጣለን" ብሉ አስጠነቀቀን።

በዚህ ዘዴ የፈለግሁትን ልብስ ይዘን ወጣን። የኔን እርጌ ልብስ ጓርአችን ደብቄ የሱን ልብስ ስለብሰው ልኪ ሆነ። አሁን እንዲህ ቁምጣና ሸሚዝ ለብሻለሁ። በዚያው ሳልኖ የግዘጋቻ ቤቱን አትልከተኛ አባባ መንፈቁን ስለግዉቃቸው፣ አበባ ለመንኳቸው። ከየወይነቱ ቆርጠው ሰጡኝ። ብር ብዙ ወደ ቀበሌያችን አዳራሽ አመራሁ።

የቀበሌው አዳራሽ በሰዎች ተሞልቷል። የቀበሌያችን ሊቀመንበርና የመሠረተ ትምህርት ኃላፊው ከፊት ቆመዋል። የመሠረተ ትምህርት ተመራቂዎችና ተመልካቾች ፊታቸውን ወደ ሊቀመንበሩ አዙረዋል። የተመራቂዎች ስም መጠራት ተጀምሯል። የእግይዬ ተራ ዐልፎ እንደሆነ እበሽቃለሁ፣' ያለችበትን ቦታ ቆሜ ስፈልግ ጥቁር ጓኗን ከሩቀ አየሁት። ተንጠራርቼ ስመለከት በእጅዋ ሳየ ወረቀት አልያዘችም። የምስክር ወረቀቷን አለመቀበሏን ስላረጋገጠሁ ደስ አለኝ። ወዲያው ስሟ ተጠራ። የመሠረተ ትምህርት ኃላፊዉም ስለ እሷ እንዲህ ብለው ተናገሩ።

"ጓጂ ትምህርታቸውን ከጀመሩ አንስቶ እንድም ቀን ቀርተው አያውቁም። በተሰጠው ፈተናም አስደሳች ውጤት አግኝተዋል። ስለዚህ የቀበሌያችን የትምህርት ኮሚቴ ይህን ሽልማትም አዘጋጅቶላቸዋል።"

ይህን ጊዜ አዳራሹን የሞላው ሰው አጨበጨበ። እኔም ከፊቴ ከቆሙት ሰዎች መኻል ተሹለክልኬ ወጣሁና ወደ እሷ ሰሔድ፣ ሰጪ ሁሉ በአድናቆት ተመለከታኝ። እግይዬ የምስክር ወረቀቷንና ሽልማቷን ተቀብላ መለስ ስትል ድንገት ከፊቷ ድቅን ብዬ፣ "እንኳን ደስ አለሽ እግይዬ!" አልኳት።

"ዉይ ! አንተ ጉደኛ" አለችኝ። የያዝኩትን አበባ ዘሉለት እጀ ሰጠኋት። አበባ የደስታ መገለጫ ስጦታ መሆኑን ከአሁን ቀደም ሰዎች ሲያደርጉ አይቻለሁ።

ያበረከትሁላትን አበባ ስትቀበለኝ፣ በአደራሹ የሞላው ሰው ሁሉ በአድናቆት ተመለከተኝ። ያን የሰው ልብስ ለብሼ አምሬ ታየኋት። ጎንበስ ብላ ሳመችኝ። አዳራሹን የሞላው ሰው ሁሉ ጭብጨባውን አቀለጠው።

የንግዱ ምረቃ ሲያበቃ ተያይዘን ወጣን። የምረቃው በአል በደስታ ዐሰፈ። ወደ ዒታችን ስንመለስ ግን አንድ አሳብ ገባኝ። 'ልብሱን እንዲያውሰኝ ብዬ የሞሸሁት ልጅ ምን ይለኝ ይሆን?"

ልብሱን ተለካህ ወይ?' ሲለኝ ምን እለዋለሁ። ይህን ሳስላስል እግዙ፣

"አንተ አንዱ!" ስትለኝ ተሰማኝ::

"አቤት! እማይዩ! አልኳት::

"እነዚህ ሰዎች ዛሬ ይሰው ይሆን?" አለችኝ::

"ምኑን እማይዩ?" አልኳት::

"አይ ተወው ! አንድ ቦታ ደርሰን እንምጣ እስቲ" ብለኝ፣ ወደ አንድ፣ ብዙ ክፍሎች ያሉት ትልቅ ቤት ይዛኝ ገባች::

አንድ የገንዘብ ቤት የሚል የተጻፈበት ክፍል ውስጥ ልትገባ ስትል፣ "አንዱ፣ እዚህ ቆየኝ መጣሁ" አለችኝና ውጭ አስቀምጣኝ ገባች:: እዚያው ቁጭ እንዳልኩ አሁንም ያ ነገር ትዝ አለኝ::

" ልጁ ልብስህን ተለካህ ወይ" ብሎ ሲጠይቀኝ አዎን ተለካሁ' ብዬ ብመልስለት: ሌላ ቀን ደግሞ "ልብስህ አልወጣም እንዴ?" ቢለኝ ምን ብዬ እመልስለታለሁ? ልቤ ተጨነቀች:: እንግዲህ ይኸ ልጅ ሲያላግጥብኝ ሊኖር ነው:: ለምን ዋሸሁ:: ለምን ዝም ብዬ ልብስህን አውሰኝ አላልኩም እያልኩ እቆጭ ጀመር::

በዚህ ሁኔታ በመሸበር ላይ እያለሁ፣ እማይዩ ከገባችበት ክፍል ወጣችና "በል ና እንሂድ" አለችኝ:: ተስትያት ቤቱን ለቀን ስንወጣ፣

" አንተ አንዱ" አለችኝ::

" አቤት! እማይዩ!"

" የማንን ልብስ ነው ለብስህ የመጣኸው?" ብላ ጠየቀችኝ:: ታሪኩን ነገርኳት:: ከዚህ በኋላ ምንም ጥያቄ አላነሣችብኝም:: እኔ ግን አሁንም የሰው ልብስ ስዋስ የዋሸሁት እያሳሰበኝ ነው:: ከፊታችን የሚመጣ አንድ ልጅ አየሁ:: ልጁ እንደኔው አዲስ ቁምጣና ሸሚዝ ለብሶ ወደ እኛ አቅጣጫ እየመጣ ነው::

"እንዴት ደስ ይላል ይኸ ልብስ!" ስል በልቤ እማይዩ ወደኔ ዞር አለችና፣

"ይኸ ልብስ ደስ ይልሃል?" ብላ ጠየቀችኝ::

እናቴ ልታደርግልኝ የማትችለውን ነገር ሳላስበው ተናግሬ ለምን አሳሰብኳት ብዬ ድንግጥ አልኩ:: እንዲህ ያለ ልብስ ገዝታ ለኔ የምታለብስበት ገንዘብ እንደሌላት ስለማውቅ፣ ከንቱ ምኞት መሆኑን አላጣሁትም:: ግን ለጥያቄዋ መልስ መስጠት አለብኝ:: ምኞት አይከለከል::

" አዎን እማይዩ" ብዬ ከመለስኩላት በኋላ፣ ሁለታችንም ዝም አልን:: እኔም በሐሳቤ ማውራቴን ቀጠልኩ:: ጥቂት እንደ ተጓዝን እማይዩ የቤታችንን መንገድ ትታ ሌላ መንገድ ያዘችና፣

" ና በዚህ በኩል" አለችኝ:: እንዳለችም ተከተልኳት:: እሷም እጥፍ አለችና ወደ ነጋዴዎች ሠፈር ገባች:: እኔ ግን ጎራ ማለታችን ትዝም አላለኝ:: በመዋሸቴ የልጆች መቀለጃ ስለምሆን፣ ሥጋቱ ከልቤ አልጠፋ አለኝ:: እማይዩ በማህበር ልብስ ወደሚሰፋበት ሱቅ ጎራ አለች::



አዳራሹ ውስጥ እንደ ገባን ወደ አንድ ልብስ ሰፊ ጠጋ ብላ " ለዚህ ልጅ ሙሉ ልብስ . ለኩት፣

[illegible]

" አይ ምኞት ! ዛሬ ይቺ እማይዩ ጤናም የላት' አልኩ በሆዴ::

" ሦስት ሜተር ተኩል ይበቃዋል::"

" ስንት ነው የጨርቁና የጁ ዋጋ ?"

" ሐያ ስምንት ብር ይሆናል" አላት::

ይኸን ጊዜ አይኔን ጨፈንኩ በድንጋጤ፣ ይህን የሚያክል ገንዘብ እማይዩ ይዛም አታውቅም:: 'አሁን ምን ሊያደርግላት ጠየቀች' ብዬ ተናደድኩ::

" እሺ እንግዲያው ይስፋለት" ብላ ለልብስ ሰፊው ስትነግረው ሰማሁ::

" ቀብድ ገማሽ ዋጋ ይክፈሉ" ብሎ መለሰላት:: ይኸን ጊዜ የቀረውን ፊቴን በአረፍት ሸፍኜ ወደ መሬት ጎንበስ አልኩ::

" እንካ መልስ አምጣ" ስተል ድመጿ ተሰማኝ:: ቀና አልኩና ቀስ ብዬ በሁለት እጆቼ ሸፍኛቸው የነበሩትን ዐይኖቼን ከፈት ሳደርግ፣ እዉነትም መሐረቧን ፈትታ የሃምሳ ብር ኖት ስትስጠው አየሁ:: በፈንጠዚያ ሁለቴ ዘለልኩና ዐይኗን፣ አፍንጫዋን፣ ጉንጭን፣ አፏን ሳምኳት:: እማይዩ እወዳታለሁ:: እማይዩ ትጠብቀኛለች:: ዛሬም ልጅዋ ውሽታም እንዳልባልላት ቀልቧ ነግሯት አድናኛለች..... እማይዩ አሁን ደመወዝተኛ ነች፣ ያውም ባለ ሃምሳ ብር ደመወዝ:: የሚቀጥለውን ወር ደመወዟን ደግሞ ምን እናደርግበት ይሆን?

ምንጭ: ወጋየሁ ተበጀ፣ ሙሉ ልብስ (የአጭር ልብወለድ ስብስብ)፣ 1980 አ.ም

## ክፍል ሁለት- አንብቦ መረዳት

### መልመጃ ሁለት

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሀሰት" በማለት መልሱ::
   - 1.1. ምንባቡ ረጅም ልብወለድ ነው::
   - 1.2. የልቦለዱ ዋንኛ ገፀባህርያት አራት ናቸው::
   - 1.3. የምንባቡ አቀራረብ ደራሲው እንደተረት የአንድን ልጅና እናት ታሪክ በመተረክ ነው::
   - 1.4. በልቦለዱ ውስጥ ከልብወለድ አላባውያን አንዱ የሆነው ግጭት የለበትም::
   - 1.5. በልቦለዱ ታሪክ ውስጥ ምልሰት አለ::
   - 1.6. የባለታሪኩ ስም አንዷለም ነው::
   - 1.7. ባለታሪኮቹ የተደላደለ ሀብት ያላቸዉና ጥሩ ኑሮ የሚኖሩ ናቸው::
   - 1.8. የባለታሪኩ አባት በልቦለዱ ታሪክ እንደ ንኡስ ገፀባህሪ እንጂ ዋና ገፀባህሪ አይባሉም::



224

[illegible]

[illegible]

[illegible]

1. የሚከተለውን [illegible] በሚል [illegible] የቀረበውን [illegible]

[illegible]

[illegible]

ተማሪ ሙሉነሽ [illegible] ወይ አክሊሉ [illegible]

ተማሪ አክሊሉ፡ "እባክሽ ተይኝ? ደህና ሆንኩ አልሆንኩ ምን ያገባሻል

ሙሉነሽ፡- " እንዴት እባክህ? የእግዜርም ሰላምታ ካስጠላህ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ?

ሚስጥረ፡- " አንተንም እንደኛው ዱርዬዎች አስቸገሩህ እንዴ! ?"

አክሊሉ፡- "እነሱስ ከኛ ምን ይፈልጋሉ ብለሽ ነው? አሉ እንጂ ከዱርዬዎች የባሱ"

ሚስጥረ፡- " እነማን ናቸው ደግሞ እውነት በት/ቤታችን አካባቢ ከነገሱት ዱርዬዎች ብሰዉ የተገኙት?"

ሙሉነሽ፡- " አባትህ ፎራፊነትህን ነቁብህ እንዴ! ?"

አክሊሉ፡- "እሱ እኔን ስለሚያምነኝ በቀላሉ ይሸወዳል!" አሉ እንጂ እዚህ ግግምያሉ ገገማዎች!"

ሙሉነሽና ሚስጥረ፡- "በአክሊሉ ምላሽ ከት ብለው ይስቁበታል።

አክሊሉ፡- "ምን ያስቃችኋል? እውነቴን ነው፤ ፋዘር በቀላሉ ነው የሚሸወደው?"

ምስጥረ፡- "ሰው በራሱ ላይ እየቀለደ ራሱን ለመሸወድ መከራውን ሲያይ አያስቅም ትላለህ?"

አክሊሉ፡- "ማን አንቺ ? ማን አባቱ ነው ደግሞ አክሊሉ በራሱ ላይ ይቀልዳል፤ ራሱን ለመሸወድ መከራውን ያያል ብሎ የሚያወራብኝ?"

ሙሉነሽ፡ " አንተው ነሃ !"

አክሊሉ፡ "መቼ ? ለማንስ ነው ደግሞ እያበድኩ ነው ብዬ ያወራሁት?"

ሙሉነሽ፡- "ለሁላችንም "

አክሊሉ፡ "እናንተ ሰዎች ይኼ ቀለም አጠባው በዝቶባችሁ ጭንቅላታችሁን [illegible] አደረገው ልበል!"

ሚስጥረ፡ "ትምህርትን በእግባቡ መማርና ከአላማችን ለመድረስ ትጉቶ ውጪታማ መሆንም እብደት ሆነ ደግሞ !"

አክሊሉ፡ "ታዲያ ለእንድ ሰው እንኳን ፡እንዲት ቃል ያልተነፈስኩትን በእደባባይ ለፍርሃል ትሉኛላችሁ እንዴ!"

ሙሉነሽ፡ "መልዕክት ለማስተላለፍ የግድ ሁሉ ነገር መነገር ላይኖርበት እኮ ይቻላል!"

አክሊሉ፡ "ካልተናገርኩ ሆዴ ውስጥ ያለውን ጠንቋለሽ ነዋ ያወቅሽው? ወይስ በምልክት ቋንቋ ነገርከኝ ልትይኝ ይሆን?"

ሙሉነሽ፡ "ድርጊት ከንግግር በላይ እይናገርም ብለህ ታምናለህ?"

አክሊሉ፡ "ፋሮች ! እናንተም እኮ ከዛ ሞዛዛ አጉል ሁቀኛ ነኝ ባይ አትሻሉም።"

ሚስጥረ፡ " ማንን ነው ዛሬ እንደዚህ የዘመትክበት ?"

(ተማሪ አዳነች ክፍላቸው መጥታ ትተላተላለች)

አዳነች፡ " Good morning every body"

ሙሉነሽና ሚስጥረ፡ "እግዝአብሔር ይመስገን ! አንች ደህና ነሽ !"

አዳነች፡ "Thank you! I am well! What a bout you? "

አክሊሉ፡ "ቀፋፊ ይሽንን ወልጋዳ እንግሊዘኛሽን እዛው ያጉረኛ አስተማሪሽ ላይ ተወላገጂበት።"

አዳነች ፡ " ተወላገደም፡ ተሰባበረም ዋናው የተማሩትን ደፍሮ መጠቀሙ ነው

ሚስጥረ፡ " ሽረ ዝም በይው ! መወላገዱንና መሰባበሩንም ለመለየት እኮ ግውቅን ይጠይቃል።

ሙሉነሽ፡ " በጣም ታሳዝናለህ !"

አክሊሉ፡ "በፈተና መውደቅ በእኔ አልተጀመረም ምኑ ነው የሚያሳዝነው?"

ምስጥረ እና አዳነች (በአንድ ድምፅ)፡ " ወደክ እንዴ ! ?"

አክሊሉ፡ "ድሮስ!በእጃቸው ከሚሄዱ፡ አሊያም በአይናቸው ጥራት ተጠቅመው ከሚያልፉ በስተቀር እንደኔ አይነቱ ምስኪን እንዴት ሆኖ ያልፋል ብላችሁ ነው! ?"

አዳነች፡ "እንተስ በአይን ጥራቱ መች ስንፈህ ታውቃለህ ? ጀግና ፡ አልነበርክ እንዴ?"

አክሊሉ፡ "አላስበላ ሲለኝስ? እንዳባቱ ገዳይ ጥምድ አድርጎ ይዞኝ አላላውስ ሲለኝስ? ያፋራ! መናጢ ! "

አዳነች፡ " ማንን ነው ዛሬ እንዲህ በቃላት ሾተል የዘመትክበት?"

አክልሉ፡ " አሁን እውነት አጥተሽው ነው ? አፍርጠው ካላልሽ በስተቀር።"



ሙሉነሽ፡ " ተውት ! እኳሄዱ የበለጠ ስህተት ውስጥ እያስገባው ነው?"

አክሊሉ፡ "ምንድነው ስህተቱ ! ልክ ነዋ! እንደሱ ደግሞ ገፀግ ፋራ አለ እንዴ! ምናልባት ለእናንተ ጀለስ ስለሆነ አልታያችሁ ይሆናል እንጂ።"

ሙሉነሽ፡ " ይቅር ይበልህ ! በተግሪንታችን ከተነሳንበት ግብ እንድንደርስ እንደ ወንድም ሆኖ የሚደግፈንና የሚያበረታታን ሁላችንንም ነው። የእናንተ ጀለስ ከምትል የመማር አላማና ጥረት ያለው ተማሪ ሁሉ አለኝታ ብትለው ይሻላል።"

አዳነች፡ "ውይ ! አክሊሉ ቲቸር ላይ ነው ይሽ ሁሉ ውርጅብኝህ?"

ሚስጥረ፡ " እስቲ እንዲት ነገር ይሽን በደለች የምትለውን ተናገር?"

አክሊሉ፡ "ምን የማታውቁት ነገር አለና ነው የምነግራችሁ? አመቱን በሙሉ ዘምተብኝ አይደል እንዴ የከረመው። ቲስትም ሆነ ፈተና በተሰጠ ቲጠር ከአንዳችሁ እንኳን እንዳልኮርጅ እንደ ፈላ ዝንጅሮ ከተማረው አርቆ እያስተመጠ በአንዲት ቲስት እንኳን ሳላልፍ አሙቱ ያሰተው። እሺ በራሱስ ትምህርት መብቱ ነው ይባል፡ የገንማንቱ ብዛት አይደል፣ ለሁሉም አስተማሪዎች ተንደኛ ኮራጅ ነው ብሎ አስተባብሮብኝ፣ ሁሉም በፈተኑ ቁጥር ብቻዩን አርቶው እያስተመጡ ከሃያ የሚመስል ውጪት ከመቶ የተሞላልኝ።"

ሙሉነሽ፡ " መኮረጅ እኮ በራሱ ወንጀልም ሃጢያትም ነው።"

አክሊሉ፡ " ለእናንተ ይሆን ይሆናል፣ ለእኛ መብትም ነፃነትም ነው።"

አዳነች፡ " ቆይ እስቲ አንድ ምሳሌ ልስጥህ"

ሚስጥረ፡ " ሽረ እናንተ ቆመን ስንነዛንዝ ሰዓቱ እንዳይልፍ ?"

ሙሉነሽ፡ " አይሆሽ ገና ነው፡ ብዙ ደቂቃ አለን"

አዳነች፡ " አንድ በጣም የምትወደው ጓደኛህ"

አክሊሉ፡ " እሺ በጣም የምወደው ጓደኛዬ ምን ይሁንልሽ ?"

አዳነች፡ " ቆይ አስፈሩርስኝ ! " ራሴን ካላጠፋሁ ብሎ ራሱን ለመስቀል ታጣቂ ሰብስቦ ሲገምድ ብታየው፡ ጎሽ የኔ ወንድም በርታልኝ ብለህ ገመዱን መግመድ ታግዘዋለህ ወይስ ምን ታደጋለህ?"

አክሊሉ፡ "ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህ ነው ተረቱ፡ አሁን የእኔ ነገርና የአንቺ ምሳሌ ስጋዊ አይደለም አፅማዊ ግንኙነትም የላቸው።"

ሙሉነሽ፡ " የእናትና ልጅ ያህል ግንኙነት አላቸው።"

አዳነች፦ " ላለፈው ደግሞ የፀፀት እስረኛ መሆን የለብህም፤ ያለፈው ባለማውቅ አልፏል። ከሚመጣው አመት ጀምሮ ትምህርትህን በስነ ስርዓት ብትከታተል ቲቸርም ምርጥ ጀለስህ ይሆናል፤ አንተም በደረጃ ነቅንቀህ ታልፋለህ።"

ሙሉነሽ፦ "ይኸውልህ አንተ ጓደኛህ ራሱን እንዳይገድል ለመታደግ እንደሄድክበት ድንቅ አካሄድ ነው ቲቸርም ያደረጉት። ችሎታውና ሞንቅላቱ እንዳለህ ስለሚያውቁ የትም የማያደርሰውን የጥገኝነት እስረኛነትህን ገመድ ለመበጠስ አሙቱን ሙሉ የተረባረቡብህ።"

አዳነች፦ "ይህን የአሁኑን ውሳኔህን ተግብረህ በሚመጣው አመት ጠንካራ ተማሪ ከሆንክ ቲቸር እንድን ሰው እንዳዳኑ ቁጠረውና ሞኖን ጥላቻህን አራግፈህ ወደ ግቢ የሚያደርስኝን መንገድ እየጠረጉልኝ ያሉ ታታሪ መሆንድስ ብለህ ውደኛቸው።

ሚስጥረ፦ ለንተ ጥሩ ተማሪ ሁን ለንጂ እኛ ያገኘነውን አባታዊ ፍቅር ፤ ለሌላ አይወስድባቸውም።

አክሊሉ፦ "አሁን ሳስበው ቀናና በብርሃን የተሞላውን መንገድ ንቁ፤ ብርሃኑን ላለማየት አይኔን ጨፍኜ እየተወሳገድኩ በመንገዝ ላይ ነበርኩ። እናንተን ግን በማም ነው ያደነኳችሁ፤ ዱርዬ ነው በማለት፤ እንደተናነሳሽ ውሻ በሩቁ ሳትሸሹኝ፤ ቀርባችሁ ከጨለማው ወደ ብርሃን እንድመለስ ምርኩዝ የሚሆን ምክር ነው የሰጣችሁኝ። ራሱን በመስተዋት እንደሚያይ ሰው የህይወት ጉዞዬን ምን እንደሚጨልል መስተዋት ሆናችሁ ነው ያሳያችሁኝ። እጅግ በጣም ነው የማመሰግናችሁ። የሚመጣው አመት እንደናንተ የደረጃ ተማሪ ሆኜ እንደምሸለም ነው ታል የምገባላችሁ።

ሙሉነሽ፦ " እኛም እናመሰግንሃለን። አይዞህ ከጎንህ አንለይም። በምንችለው ሁሉ እናግዝሃለን።

(አክሊሉ ተራ በተራ ይሰግቸውና ተያይዘው ከመድረክ ይወጣሉ)

(በአክሊሉ ውሳኔ ተደስተው እየተፍናለተለቱ ደስሙታል። አክሊሉም ውስጠ ሆነበረው ሞንትት ተራንፎ ደስታና ብሩህ ተስፋ ታየው።)

አክሊሉ፦ " ሊበሏት የከጀሏትን አሞራ ጅግራ ናት ይሏታል' ነው ተረቱ፤ ጥፋት ሊበላንና ሊቆጣጠረን አራዳ ይለናል። ድንቄም አራዳ! ሞልጥ ያለው ፋራው እኔው እንደነበርኩ ቁልጭ ብሎ የታየኝ አሁን ነው። እና እናንተም ሁላችሁ እንደኔ አራዳ እያለ አባብሎ ወደ ገደል ከሚመራችሁ ተወንቲቱ እየጠራችሁ

ያላችሁም ካላችሁ ቆም ብላችሁ አስተውሉና ኑ! አብረን እንመለስ ! መንገዱ የተሳሳተ፡ ሞልቶ ወዳለው የተፋት ግዋ የሚያደርስ ነውና እዚች ጋ እተና ግሉቱ ነው አራድኑቱ ! ከግንም በላይ ለራስ ግውቱና አሸናፊ መሆን ነው አራድኑቱ !"

(ብሎ እጅ ነስቶ ከመድረክ ይወርዳል።)

- ተፈፀመ -

## ክፍል ሁለት፦ አንብቦ መረዳት

1. ለሚከተሉት ተያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛ መልሳቸውን ከቀረቡት አማራጮች ምረጡ።

ሀ. የአክሊሉ የቋንቋ አጠቃቀም

1. ደካማ ሆኖ ይታያል።
2. የተለያዩ ሐሳቦችን የሚያንብና ያወቀውንም በንግግሩ የሚጠቀም ሆኖ ይታያል።
3. ሥርዓት የለለው መረን መሆኑን ይናገራል።
4. ብዙም ስለላልተናገረ ግወቅ ያዳግታል።

ለ. " ሰው ራሱ ላይ እየቀለደ ራሱን ለመሸወድ መክራውን ሲያይ አያስትም . . ."
የሚለው የማን ንግግር ነው?

1. የመምህራችው
2. የአክሊሉ
3. የሙሉነሽ
4. የሚስጥረ

ሐ. ሙሉነሽ "ድርጊትህ ከንግግር በላይ አይናገርም..." ስትል ምን ግለቷ ነው?

1. የተግባር ሰው ነህ ልትለው ፈልጋ ነው።
2. ቃል ባትገባም ታደርገዋለህ ግለቷ ነው።
3. ባፍህ ባትናገርም በድርጊቶችህ እየተናገርክ ነው ለግለት ነው።
4. ሞዴውሙት ከንግግር በላይ ነገሮችን ይገልፃል ለግለት ነው።

መ. አዳነች በእንግሊዝኛ ቋንቋ መናገር መሞከሯ

1. ጉረኛነቷን ይገልፃል።
2. የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታዋን ከክፍል ውጭ በልምምድ ለግዳበር ቆርጣ መነሳቷን ያሰላያል።
3. ችሎታ እንዳለው ሰው ለግሰመሰል እንጂ ምንም የግታውቅ መሆኗን ያሳያል።
4. በችሎታዋ ንበዝ ብትሆንም ለጓደኞቿ ያላትን ንቀት ለመግለፅ የተጠቀመችበት መሆኑን ያሳያል።



ሠ. "ይቅር ይበልህ !" የሚለው አባባል የሚያመለክተው

1. እርግግንን ነው።
2. ስድብን ነው።
3. የሴጣን ጆሮ እይስግህ ለግለት ነው።
4. ስታውቀው ሀጢያት እየሠራህ ነውና ይቅርታ ጠይቅ ለግለት ነው።

ረ. በአክሊሉ ንግግር ውስጥ " እንደ ፈሳ ዝንጅሮ" የሚለው አነጋገር በንጠቁማብ በመጠቀም ቢፃፍ እንዴት ይፃፋል?

1. " እንደ . . . ዝንጅሮ አርቀው"
2. " እንደ ፈሳ . . . አርቀው"
3. " እንደ ፈሳ ዝንጅሮ . . ."
4. " እንደ. . . ዝንጅሮ አርቀው"

2. ለሚከተሉት ተያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክለኛውን መልስ በቃል ተናገሩ።

ሀ. በምንባቡ ውስጥ ያሉት ገፀባህርያት ስንት ናቸው?

ለ. አክሊሉ ምን አይነት ተማሪ ነበር?

ሐ. አክሊሉ መምህሩን የጠላቸው ለምን ነበር?

መ. አክሊሉ በአዳነች ለቀረበለት የምሳሌ ታሪክ ከሰጠው ምላሽ ስለ አክሊሉ ምን እንድናውቅ ያደርጋል?

ሠ. በምንባቡ ውስጥ የአክሊሉ ድርጊትን ከሚጠላቸው መምህር ድርጊት ጋር በመመሳሰል የቀረበው ምንድነው?

ረ. ሚስጥረ ምን አይነት ተማሪ ትመስላችኋለች ?

ሰ. ሙሉነሽ አክሊሉን "ንበዝ !" ብላ እንድትጨብጠው ያደረጋት ምንድ ነው ?

ሸ. ሙሉነሽ "አካሄዱ ይበልጥ ስሁትት ውስጥ እየከተተው ነው" ስትል ምን ለግለት ፈልጋ ነው ?

## ክፍል ሶስት፦ ፅህፈት

1. በሞዴውሙቱ ውስጥ ከቀረቡት ገፀ-ባህርያት ማንን በይበልጥ እንደወደዳችሁ ከነምክንያታችሁ ሃፉ።
2. "ከሞዴውሙቱ የተማርኩት ነገር ቢኖር" በሚል ርዕስ ድርሰት ሃፉና አንብቡ።
3. እንደ ተማሪ ሙሉነሽ፡ ሚስጥር፡ አክሊሉና አዳነች በመሆን ሞዴውሙቱን በቃል አዋንታችሁና ተለግምዳችሁ በክፍል ውስጥ ለጓደኞቻችሁ ካተረባችሁ በኋላ ለትቤቱ ግህበረሰብ ለግሳየት ከመምህራችሁ ጋር በመነጋገር ሁኔታዎችን ያመቻቹላችሁ።

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት

## ሱጴ

**መልመጃ አንድ**

1. ሱጴ በደቡብ ክልል በየትኛው ዞን ይገኛል?
2. ሱጴ የምትታወቅበት ምርት ምንድነው?

የጥር ወር የሱጴ ከተማን ከረጅም እንቅልፍ ለመቀስቀስ ተጉዞ መጥቷል። ህይወት እግሯን በጋዲ የታሰረች ይመስል፣ በአንድ ቦታ ረግታ ማዛጋቷን ከጥር ወር ዋዜማ ጋር አቁማለች።

የአብዛኛው የሱጴ ቦሩ ህዝብ ኑሮ ከቡና ንግድ ኡደት ጋር የተያያዘ እንደመሆኑ ደን መመንጠር፣ የቡና ችግኝ ማፍላት፣ መትከል፣ መኮትኮት ቡና ሲደርስ ደግሞ መልቀም፣ ማድረቅ፣ መፈልፈል፣ ማጠብና መጫን ሲሆን ቡና ተለቅሞ ከገባ በኋላ ግን ስልቱ ይለወጣል። በጥር ወር እግር ሳቢያ የጠጅ ነጋዴዎች ገበያ ይደራል። አዝማሪ የማስንቆውን ጭራ በባህር እጣን ማሟሸት ይጀምራል። በአዲስ አበባና በሌሎች ርዕሰ ከተሞች ተቀማጭ የሆኑ ቀፈታቸው ወደ ፊት የገፋ ባለእርስቶች ፣ አትራፊ ነጋዴዎች እና አራጣ አበዳሪዎች እንደመስቀል ወፍ ቀጠሮ ጠብቀው ሱጴ ላይ ከወይዘሮ ዝናሽ ቤት ይናገኛሉ። ከወሎ፣ ከሰባት ቤት ጉራጌ፣ ከጎጃም፣ ከትግሬና ከሌላም ስፍራ ለቡና ለቀማ የሚመጡ የቀን ሠራተኞች በቡድን በቡድን ሆነው ሱጴን ማጣበብ ይጀምራሉ። ሴተኛ አዳሪዎችም የአዲስ መጤዎችን ዱካ ተከትለው መጥተው እንደ የደረጃቸው ሠፈር ያበጃሉ። የሻማ፣የኩራዝ፣ የፋኖስ፣ የማሾ ቤቶች፣ እንደ አሸን በየቦታው ይፈላሉ። አዝማሪዎች በየሰፈሩ ያቅራራሉ። ጠላው፣ ካቲካላው፣ ጠጁ፣ አረቄው፣ በያይነቱ፣ ኮኛክና ውስኪው-ይንቆረቆራል። ያለማቋረጥ እንደገባ የወንዝ ፏፏቴ የወንጀሉም ብዛት በዚያው መጠን ይጨምራል። በየቀኑ ከቡና ዛፍ ሥር በጨቤ ወይም በማጭድ ወይም በቆንጨራ ተዘንጥሎ የወደቀ እሬሳ አይጠፋም። የፖሊስ ጣቢያው በእስረኞች ተሞልቶ፣ ቤቱ ቀርቶ ደጁም ይጨናነቃል። ለሴተኛ አዳሪ ገንዘብ ያልከፈለው፣ ከቀን ሠራተኞች ገንዘብ የሠረቀችው፣ በስካር ጓደኛውን የገደለው፣ ልጃገረዷን የደፈረው፣ ከአባወራ ሚስት ጋራ የተያዘው፣ በስርቆት፣ በነፍስ መግደል ሙከራ፣ በማጭበርበር የተወነጀለው ሁሉ በአንድነት ይታጎራሉ።

ተፈጥሮም የደረሰው የቡና ፍሬ እንጆሪ መስሎ ወደ ጥቁር አረንጓዴነት ቀለም ከሚያደሉት ወዛም ቅጠላ ቅጠሎች ጋር እያነፃፀረች፣ ምንጮችና ጅረቶችን በጥራታቸው ኩል መስሎ ከሚንጣለለው ሰማይ ጋራ እያወዳደረች፣ የንብ መንጋዎችን ካንዱ ቀፎ ወደ ሌላው እያዘመተች፣ በየሜዳው አበባዎችን እያፈነዳች፣ ትስቃለች --- ትስቃለች --- ታሾፋለች... ላንዳፍታ ቆሞ የሚያደንቃት የለም።

በክረምቱ ወራት የእሱንና የቤተሰቦቹን ችግር ለመወጣት ገና ያላረ ' ዉ ) ቡና ዛፍ ላይ እንዳለ በርካሽ ዋጋ የሸጠው ገበሬ፣ ቡናው ደርሶ አበዳሪዉ በግፍ ሲሸመጥጥ ይመለከትና ባዶ እጁን ወደ ቤቱ ተመልሶ ከእሳት ዳር ተቀምጦ ይተክዛል። ባሏ የኮበለለባት ሚስት ከልጆቿ ጋር በእሳት ዳር ተቀምጣ እንባዋን ታፈሳለች። በሴትና በሴተኛ አዳሪዎች ምክር የደረሰች ልጃቸው የኮበለለችባቸው ወላጆች፣ ሚስት ቡሃቃውን ሳትከድን ህፃን ልጅ ጥላበት የኮበለለችበት ባል፣ ከቡና ሺያጭ ከተገኘው ትንሽ ትርፍ ባሏ በየመጠጥ ቤት እየሰከረ የሚያስቸግራት ሚስት፣ ሁሉም በየቤቱ ከንፈሩን ይመጣል። ቤተሰቦች ይበታተናሉ።

እንግዲህ ህዝቡ ቡናው የሚያከትምበት አዲስ ወግ ይሻል። እንደ መሻቱም ወግ የሚያጣበት ጊዜ እንብዛም ነው። እንደ ሀዲስ አይነት ጥቁር እንግዳ እንደ አይናለምና ዳኛቸው ሠርግ አይነቱን ይጥልለታል።

ሀዲስ ቀን በስራ የደከመውን ሰውነቱን ለማዝናናት በአስር ብር ከተከራያት ደሳሳ ጎጆው ታ ስር እግሮቹን አጣምሮ ተቀምጧል:: ግን ለመዝናናት አልቻለም:: በአ ቡ "መዝናናት የሚችሉ የተባረከ ናቸው ይላል ደጋግሞ:: መማር እኮ በአንድ በኩል ጭንቀትን ማብዛት ሳይሆን አይቀርም እያለ ያስባል: አሳቡ ግን አንድ አቅጣጫን ይዞ አይጓዝም::

ከቤት ውስጥ ከሚነደው ፋኖስ እየተነነ የሚወጣው ጋዝ ከቀዝቃዛው የምሽት አየር ጋ እየተዋሀደ፣ አንዳንዴ መጥቶ አፍንጫውን ይወጋዋል። ስለተላመደ ው አያስጨንቀውም። እንደፈር በሚንቦገቦጉ ከዋክብት የታጀበች ብርማ ግማሽ ጨረቃ በቀዝቃዛው ብርሃኗ ሜዳውን፣ ቤቱን፣ ዛፉን ቁጥቋጦውን ጥቁር ግራጫ ቀለም እየቀባች ታዥጎረጉረዋለች። ቁጥቋጦውን ያደባ ነብር፣ ጉቶው ያደፈጠ ወንበዴ ፣ አንዱን ዛፍ አሳብ የተጫነው ጎሊያድ ፣ ሌላውን አንገቷን እንደ ባህር ማሽ የዘለሰች ልጃገረድ ታስመልሰዋለች። ፌንጣዎች ጭርር ጭርር እያሉ ከእልቁ ወንዝ እንቁራሪቶ ቁርርታና እልልታ ጋራ በመቀባበል የተወሳሰበ ህብረ ሙዚቃ ይፈጥራሉ።»

ምንጭ (ከበአሉ ግርማ፣ የህሊና ደውል ገፅ 15-16 የተወሰደ)

## ክፍል አንድ አንብቦ መረዳት

### መልመጃ ሁለት

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት እውነት ወይም ሀሰት በማለት በቃል መልሱ::

1.1. የሱጴን ከተማ ከረዥም እንቅልፏ ለመቀስቀስ የመጣው ህዝቡ ነው።

1.2. የሱጴ ቦሮ ህዝብ ኑሮ ከቡና ንግድ ጋር የተያያዘ ነው::

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የእኔ መሆኑን በጥናቱ የተጠቀምኩባቸውን ድርሳናት ዋቢነታቸውን በትክክል ማመልከቴን (መሰነዴን) አረጋግጣለሁ።

ስም፡- ዳዊት ፍሬሕይወት

ፊርማ፡- _____

ቦታ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ድኅረ ምረቃ መርኃ ግብር

ቀን፡- ሰኔ 2000 ዓ.ም